# የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ትንተና በጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሒውማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ሥነፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በፎክሎር የፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ሰዋገኝ አስራት
አማካሪ ጉዳይ እምሬ (ዶ/ር)

ህዳር፣ 2009 ዓ.ም
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፤

የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ- ምረቃ መርሃ-ግብር

# የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ትንተና በጎንጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ

በ

ሰዋገኝ አሰራት

2009 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
| ዶ/ር ጉዳይ እምሬ | ______________ |
| የውጭ ፈታኝ ስም | ፊርማ |
| ዶ/ር አንተነህ አወቀ | ______________ |
| የውስጥ ፈታኝ ስም | ፊርማ |
| ዶ/ር ጌታቸው ስንሻው | ______________ |

# ማረጋገጫ

የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ትንተና በጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፤ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ- ምረቃ መርሃ-ግብር በፎክሎር ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብሁት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምሁባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- ሰዋገኝ አስራት አድማሱ

ፊርማ

# ምስጋና

ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ለመስራት ከጀመርሁበት ጊዜ ጀምሮ አሁን እስከደረስኩበት ድረስ በማማከር፣ የተጣመመውን በማቃናት፣ የጎደለውን በማሟላት፣ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ምንጮችን በመጠቆምና የተለያዩ መጽሐፍትን በማዋስ፣ በፍጥነት አንብበው ገንቢ አስተያየት በመስጠትና ውድ ጊዜዎትን መስዋእት በማድረግ፣ ምክርዎን በመለገስ ከጎኔ ያልተለዩት፣ ዶ/ር ጉዳይ እምሬ በእጅጉ አመሰግናለሁ፡፡ አምላክ በጤና ይጠብቅዎት እላለሁ፡፡

ዶ/ር ጌታቸው ስንሻው እና ዶ/ር አለሙ ካሣዬ የደረጃ ማበልፀጊያ ላይ የቀረቡትን ስድስት ምዕራፎች በሚገባ አንብባችሁ ገንቢ የሆነ ሙያዊ አስተያየት ስለሰጣችሁኝ ምስጋናዬ ከልብ ይድረሳችሁ፡፡

በዩኒቨርስቲ ቆይታዬ አስፈላጊውን ምክር በመለገስ ብርታት ለሆናችሁኝ መምህራኖቼ ለዶ/ር ሙሉሰው አስራቴ፣ ለአቶ ወንድወሰን አዳነ፣ ለአቶ ደረጀ ገብሬ፣ ለዶ/ር ባይለየኝ ጣሳው እና ለዶ/ር ጌታሁን አማረ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ እንዲሁም ስማችሁን ያልጠቀስኳችሁ የክፍለ ትምህርቱ መምህራንና ሰራተኞች እስካሁን ላደረጋችሁልኝ ድጋፍና ላሳያችሁኝ መልካም ትብብር ምስጋናዬ የላቀ ነው እግዚአብሔር ይስጥልኝ፡፡

አቶ ሞላ ጀምበሬ ከምዝገባ ጊዜ ጀምሮ ላደረግህልኝ ድጋፍና በየጊዜው ለሰጠኸኝ አስተያየት ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ እግዚአብሄር ውለታህን ይክፈልህ፡፡ ዶ/ር ዋልተንጉስ መኰንን ጽሑፉን በማንበብና ሙያዊ አስተያየት በመስጠት ለዚህ ስላበቃኸኝ ምስጋናዬ ይድረስህ፡፡ ከአምስት ዓመት በላይ አብረን ለቆየነው የክፍል ጓደኞቼ ለለገሳችሁኝ ሃሳብ ሁሉ አመሰግናለሁ፡፡ዶ/ር አበበ መርዕድ፣ ዶ/ር ጌታዋ ሞላ፣ ዘላለም አበበ ላደረጋችሁልኝ ሁሉ አመሰግናለሁ፡፡ መሰሉ መንግስቱ ለሰጠሽኝ ምሁራዊ አስተያየትና ሙያዊ ምክር ከልብ አመሰግንሻለሁ፡፡ የ "IES" ቤተመጽሐፍት ሰራተኞች በሙሉ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ አቶ ይሳቅ አድነው ላደረግህልኝ ቀና ትብብር ሁሉ ከልብ አመሰግንሃለሁ፡፡ በጠቅላላው በዚህች ትንሽ ወረቀት ስማችሁን ለመዘርዘር ባለመቻሌ ትልቅ ይቅርታ እየጠየቅሁ ድጋፍ ላደረጋችሁልኝ፣ ሙያዊ አስተያየትና ምክር ለለገሳችሁኝ በሙሉ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

እንደኔው ሆናችሁ በማሰብ በየጊዜው ውድ የስራ ሰዓታችሁንና የእረፍት ቀናችሁን መስዋዕት በማድረግ በአካል ተገኝታችሁ አስፈላጊውን መረጃ ሁሉ ስታቀብሉኝ ለነበራችሁ መረጃ አቀባዮቼ፣ ያለናንተ ቀና ትብብር ጥናቱ እዚህ አይደርስም ነበርና ምስጋናዬ ከልብ

ይድረሳችሁ፡፡ የመስክ ስራዬን ጀምሬ እስክጨርስ ድረስ ከጎኔ ያልተለየኸው ዳኜ ይሁን ብዙ ውጣ ውረዶችን አብረን አይተናል፣ ለዚህ ጥናት ከፍተኛውን አስተዋጽኦ አድርገሃልና እግዚያብሄር ይሥጥህ፡፡ አመሰግንሃለሁ፡፡

ወ/ሮ ገነቴ ደምለውና አቶ የትዋለ ከበደ በመስክ ስራ ወቅት በእንግድነት ተቀብላችሁ በቤታችሁ ከማስተናገድ በተጨማሪ የጎደለውን መረጃ እያሟላችሁ ለዚህ አብቅታችሁኛል፣ እግዚአብሄር ዕድሜና ጤና ይስጥልኝ፡፡ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ ጓደኞቼ ሰውነት ጌታሁን፣ ሐረጎ ዋለና ጥሩ ቤዛ ላደረጋችሁልኝ ሁሉ አመሰግናለሁ፡፡ ብድር መላሽ ያድርገኝ፡፡

ለስራዬ መቃናት ለተባበራችሁኝ ጓደኞቼ እና ተማሪዎቼ ሁሉ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ የነበረብህ የስራ መደራረብ እንኳን ሳያግድህ አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ሁሉ ለተባበርከኝ ለአቶ ሀብታሙ ቸኮል ብድር መላሽ ያድርገኝ፡፡ ወ/ሮ ሚዛን ገብረየስ ከሁለተኛ ዲግሪዬ ጀምሮ አይዞሽ ባዬና መካሪ፣ ብርታቴ ነሽ፣ አምላክ እድሜና ጤናውን ይስጥሽ እላለሁ፡፡

በሞራል ላበረታታችሁኝ፣ በማቴሪያል አስፈላጊውን ሁሉ እገዛ ላደረጋችሁልኝና ከጎኔ ላልተለያችሁኝ ቤተሰቦቼ፣ እህቶቼና ወንድሞቼ ሁሉ ውለታችሁን መቼም አልረሳውም፡፡ ሚሚ ታናሽ እህቴ እግዚአብሔር ውለታሽን ይክፈልሽ፡፡ እየሩሳሌም አስራት፣ ትዕግስት እንዳወቀ፣ ሳሙኤል ተስፋዬ ላደረጋችሁልኝ ነገር ሁሉ እግዚአብሄር ውለታችሁን ይክፈላችሁ፡፡ ከምን ደረስሽ? አይዞሽ! እያልሽ ላተጋሽኝ እናቴ ወ/ሮ አመለወርቅ መኮንን ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረስሽ፣ እድሜና ጤናውን ይስጥሽ፡፡

በመጨረሻም ለቤተሰቦቼ፣ የቤቱን ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ በመሸከም፣ ያለ መታከት በተከታታይ ለአስራ አምስት አመታት ከጎኔ ሆነህ አይዞሽ እያልህ በማበረታታት፣ ጽሁፌን በማረም፣ በማስተካከል ለዚህ ላበቃኸኝ ውድ ባለቤቴ አቶ ጥላዬ የትዋለ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፣ ሁልግዜም ብርታቴ ነህ፡፡ ውድ ልጆቼ ሰለሞንና ኤደን ጥላዬ፣ ፋንታነሽ ይሁን፣ በላቸው የትዋለ ውለታችሁን ምንግዜም አልረሳውም፡፡ ብድር መላሽ ያድርገኝ፡፡ አመሰግናለሁ፡፡

ሰዋገኝ አስራት

መስከረም 2009

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ምስጋና v

ማውጫ vii

አጠቃሎ xiv

ምዕራፍ አንድ 1

መግቢያ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 3

1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት 5

1.4. የጥናቱ ፋይዳ 6

1.5. የጥናቱ ዓላማዎች 7

*1.5.1. የጥናቱ አብይ ዓላማ 7*

*1.5.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች 7*

1.6. የጥናቱ ወሰን 8

1.7. የጥናቱ ውሱንነት 8

1.8. የጥናቱ ሥነ-ምግባር፣ የመስክ ተሞክሮ፣ተግዳሮቶችና መፍትሂዎቻቸው 9

*1.8.1. የጥናቱ ሥነ-ምግባር 9*

*1.8.2. የመስክ ተሞክሮ 10*

*1.8.3. ተግዳሮቶች 16*

*1.8.4. የተወሰዱ መፍትሂዎች 17*

1.9. የጥናቱ አደረጃጀት ____ 18

ምዕራፍ ሁለት ____ 20

የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳና ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ____ 20

2.1. የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ ____ 20

*2.1.1. የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ከእርሻ አኳያ ____ 20*

*2.1.2. የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ከሀብት አያያዝ ____ 29*

*2.1.3. ፎክሎር እና የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ____ 33*

2.2. ጽንሰ-ሃሳባዊ ማዕቀፍ ____ 35

*2.2.1. የፎክሎር ጽንሰ-ሃሳብ ____ 36*

*2.2.1.1. "ፎክ" ____ 37*

*2.2.1.2. "ሎር" ____ 37*

*2.2.1.3. ልማድ ____ 38*

*2.2.1.4. ለውጥ ____ 39*

*2.2.1.5. ቀጣይነት ____ 40*

*2.2.2. የባህላዊ ዕውቀት ስያሜና ምንነት ____ 40*

*2.2.3. የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ምንድን ነው? ____ 42*

*2.2.4. የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ባህሪያትና አይነት ____ 44*

*2.2.5. የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን መጠቀም ለምን አስፈለገ? ____ 45*

*2.2.6. ወቅቶች ____ 46*

ምዕራፍ ሶስት ____ 50

የአጠናን ስልትና ዘዴዎች ____ 50

3.1. የጥናቱ አይነት ____ 50

3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ____ 52

*3.2.1. ካልዓይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ____ 52*

3.2.2. ቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች 54
3.2.2.1. ተሳትፏዊ ምልከታ 54
3.2.2.2. ቃለ-መጠይቅ 61
3.2.2.3. ተተኳሪ የቡድን ውይይት 64
3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች 66
3.4. የመረጃ አቀባይ አመራረጥ 67
3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ አንፃሮች 70
3.6. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ 71
3.6.1. የማህበራዊ ሥነ-ዕውቀት ንድፈ-ሃሳብ 73
3.6.2. የማህበረሰብ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ 74
3.6.3. ሥነ-ፋይዳ 76
3.6.4. ተምሳሌታዊ ትንተና 77
3.6.5. አውዳዊ ትንተና 78
ምዕራፍ አራት 82
አካባቢያዊ ዳራ 82
4.1. የአዊ ብሔረሰብ ታሪክ፣ መልካምድራዊ ሁኔታ፣ የዞኑ የህዝብ አሰፋፈር፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ 82
4.1.1. የአዊ ብሔረሰብ ታሪክ 82
4.1.2. የአዊ ብሔረሰብ ዞን መልካ ምድራዊ ሁኔታ 83
4.1.3. የአዊ ብሔረሰብ ዞን ህዝብ አሰፋፈር 86
4.1.4. የአዊ ብሔረሰብ ዞን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ 86
4.2. የጓጉሳ ሽኩዳድ/ የተጠኚ ወረዳ አካባቢያዊ ዳራ 88
4.2.1. የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ የህዝብ አሰፋፈርና መልካምድራዊ ሁኔታ 88
4.2.2. የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ ህዝብ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ 90

*4.2.3. የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ ህዝብ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታ ____ 91*

*4.2.4. ባህላዊ አደረጃጀትና ማህበራዊ ግንኙነቶች ____ 92*

**ምዕራፍ አምስት ____ 97**

**የባህላዊ ግብርና ዕውቀት የመረጃ ትንተና ____ 97**

5.1. የእርሻ መሳሪያዎች ____ 97

5.2. ግቢ /በልግ (ከመጋቢት እስከ ግንቦት) ____ 106

5.3. ክረምት (ከሰኔ እስከ ነሃሴ) ____ 128

5.4. ጥቢ (ከመስከረም እስከ ህዳር) ____ 141

5.5. መኸር (ከህዳር እስከ የካቲት) ____ 147

5.6. ከግብርናው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ልማዶችና እምነቶች ____ 158

**ምዕራፍ ስድስት ____ 171**

**የባህላዊ ግብርና ዕውቀት አይነቶችና የዕውቀት ተስተላልፎ ____ 171**

6.1. የባህላዊ ግብርና ዕውቀት አይነቶች ____ 171

*6.1.1. የማህበረሰብ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ____ 172*

*6.1.2. የቡድን ዕውቀት ____ 173*

*6.1.3. የግለሰብ ዕውቀት ____ 174*

6.2. የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ተስተላልፎ ____ 177

**ምዕራፍ ሰባት ____ 188**

**ለውጥና ቀጣይነት ____ 188**

7.1. ለውጥ ____ 188

7.2. ቀጣይነት ______ 203

ምዕራፍ ስምንት ______ 206

ማጠቃለያና ይሁንታ ______ 206

8.1. ማጠቃለያ ______ 206

8.2. ይሁንታ ______ 215

ዋቢ መጻህፍት ______ 216

አማርኛ ______ 216

English ______ 218

አባሪ አንድ፡- የመስክ ጥናት ጥያቄዎች ______ 229

አባሪ ሁለት፡- የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር ______ 233

አባሪ ሶስት፡- ልዩ ልዩ ፎቶግራፎች ______ 235

አባሪ አራት፡- ናሙና ቃለ-መጠይቆች ______ 238

# የፎቶግራፍ ማውጫ


ፎቶ 1፡-ውኃ እያርከፈከፉ ሲያበራዩ ____ 60

ፎቶ 2፡- በምልከታ ዘዴዎች መረጃ ከመስክ ሲሰበሰብ የሚያሳይ ናሙና ፎቶ ____ 61

ፎቶ 3፡- ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች በቃለ-መጠይቅ መረጃ ሲሰበሰብ ናሙና ____ 63

ፎቶ 4፡- ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች በቃለ-መጠይቅ መረጃ ሲሰበሰብ ናሙና ____ 64

ፎቶ 5፡- ከቡድን ውይይት መረጃ ሲሰበሰብ____ 66

ፎቶ 6፡-ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ናሙና በከፊል ____ 69

ፎቶ 7፡- የበሬ ዕቃ፣ ፎቶ 8፡-የፈረስ ዕቃ፣____ 99

ፎቶ 9፡- በፈረስ ሲታረስ____ 102

ፎቶ 10፡- በበሬና በፈረስ ሲታረስ፣ ____ 103

ፎቶ 11፡- በበሬ ብቻ ሲታረስ፣____ 103

ፎቶ 12፡- ባህላዊ ማዳበሪያ/ ኮምፖስት የተደፋበት የእርሻ መሬት፣ ____ 119

ፎቶ 13፡-ቄስ ወርቁ ባህላዊ ማዳበሪያውን ከአፈሩ ጋር ሲያዋህዱ____ 119

ፎቶ 14፡- ድንች ዘር ሲጣል (ሲዘራ) ____ 123

ፎቶ 15፡- ድንች ሲኮተኮት ፎቶ 16፡- ድንች ሲደገር/አፈር ሲታቀፍ ____ 124

ፎቶ 17፡- አምሳያ የተደረገበት የቦቆሎ ማሳ ____ 125

ፎቶ 19፡-የጤፍ እርሻ ጭቃ በራይ ሲበራይና ለዘር ሲዘጋጅ፣ ____ 132

ፎቶ 18፡-የጤፍ እርሻ ሲጎለጎል፣ ____ 132

ፎቶ 20፡- የጤፍ ዘር በብተና ሲዘራ____ 133

ፎቶ 21 ፡- የጤፍ ዘር ሲጠራ/ ሲበጠር ____ 133

ፎቶ 22፡- አቶ ልመንህ ዳኛው በመንሽ ውቻሬ ሲያወጡ ____ 149

ፎቶ 23፡-አውድማ ላይ ምሳ እየበሉ ጠላ ሲጠጡ፣____ 151

ፎቶ 24፡- ሴቶችና ወንዶች ባንድነት የጤፍ አረም ሲያርሙ፣ ____ 156

ፎቶ 25፡- ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰች ሴት አውደማ ውስጥ ከብት ስታዞር/ ስትነዳ፣_ 164

ፎቶ 26፡- ጤፍ በመስመር በእጅ ሲዘራ____ 198

ፎቶ 27፡- ጤፍ በአንድ በውኃ መያገር ፕላስቲክ ሲዘራ፣ ______ 198
ፎቶ 28፡- በአንድ ጊዜ 13 መስመር ጤፍና 13 መስመር ማዳበሪያ የሚዘራ በገበሬው የተፈጠረ እና የተሸሻለው ዘዴ ______ 199

## የካርታዎች ማውጫ

ካርታ 2:- የአዊ መስተዳድር ዞን ካርታ ______ 84
ካርታ 3፡- የጓጉሳ ሽኩዳድ ካርታ ______ 89

## የምስል ማውጫ

ምስል 1፡-የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ተስተላልፎ ሞዴል ______ 177
ምስል 2፡- ማጠቃለያ ምስል ______ 212

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የባህላዊ ግብርና ዕውቀት በጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ ምን እንደሆነ፣ እንዴት እንደሚተገበር፣ እንዴት እንደተወረሰና በምን መንገድ እንደሚተላለፍ ተንትኖ አሳይቷል፡፡ ዋና ዓላማውም የጓጉሳ ሽኩዳድ ገበሬዎች የሚተገበሯቸው የባህላዊ ግብርና ዕውቀቶችና ተያያዥ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ለተተኪው ትውልድ ማቆየት ነው፡፡

ጥናቱ አውድን መሰረት በማድረግ በአይነታዊ የጥናት ዘዴ የኢትኖግራፊክን የአጠናን ስልትን የተከተለ ነው፡፡ መረጃዎቹ ከካላይና ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ ሲሆን ከካላይ የተገኘው መረጃ ከቤተ-መጻሕፍት፣ እንዲሁም ቀዳማይ መረጃዎች ከቁልፍ መረጃ አቀባዮችና ከሌሎች መረጃ አቀባዮች ከመስክ ላይ ከተፈጥሯዊ አውዱ በቃለ-መጠይቅ፣ በተለያዩ የምልከታ ዘዴዎችና በቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተሰብስቧል፡፡ እነዚህን መረጃዎች ለመሰብሰብም ከግንቦት 2006 እስከ ሚያዚያ 2008ዓ.ም ባሉት ጊዚያቶች ለጥናቱ አስፈላጊ ሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ።

እነዚህ የተሰበሰቡት መረጃዎችም በማህበራዊ ግንባታ፣ በሥነ-ዕውቀት እና በሥነ-ፋይዳ ንድፈ ሀሳቦች መሰረትነት በአውዳዊና በተምሳሌታዊ የመተንተኛ ዘዴዎች ተተንተነዋል፡፡ መረጃዎቹ ተደራጅተውና ተተንትነው በተገኘው ውጤት መሰረትም ገበሬው በሕይወት ተሞክሮውና በልምዱ ያካበታቸው የበርካታ ዕውቀት ባለቤት መሆኑና ችግሮቹን ለመፍታትም የሚጠቀምበት መንገድ የኖረበትን ባህልና ማህበራዊ አውድ መሰረት አድርጎ እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ገበሬው የዓመቱን ወራቶች አራት ቦታ እኩል በመከፈል የሚሰራ ሲሆን በነዚህ ወራቶችም የሚከውናቸው ተለያዩ ስራዎች አሉት፡፡ እነዚህ ተግባራትም እርሻ፣ ዘር፣ አረም ኩትኳቶ፣ ሰብል ጥበቃ አጨዳ፣ ዘር፣ ውቂያና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እንዲሁም ባህላዊ ማዳበሪያን በማዘጋጀት እንደ ሰብሉ አይነት በመለየት የሚጠቀም ከመሆኑ በተጨማሪ በአንድ ማሳ ላይ ባህላዊውን ማዳበሪያ ለመሬቱ ለምነት ሳይሳዊውን ደግሞ ለፍሬው በማለት እንደሚጠቀም በጥናቱ ታይቷል፡፡

ሥነ-ቃሎችን በመጠቀም ለተተኪው ትውልድ የስራን ጥቅም እንደሚያሳውቁ ታይቷል፡፡ ከአያት ከቅድመ አያቶቹ በውርስ ያገኘውን ዕውቀት መሰረት አድርጎ ከሚያየውና ከሚደርስበት በመነሳት የተለያዩ ዕውቀቶችን ለመፍጠር ጥረት ሲያደርግ ይስተዋላል፡፡ ያገኘውን ዕውቀትም ወደሌላ ያሸጋግራል፤ ማሸጋገሪያ መንገዶችም ቃልና ተግባር ሲሆኑ ለዚህም ዋና መሳሪያዎች ቃላዊ ግጥሞች (ስነቃሎች) ልማዶችና እምነቶች ናቸው፡፡ ይህንን ያገኘውን ዕውቀትም ከባህሉ ከቦታውና ከራሱ ጋር አጣምሮ ፈትሾ ሳያረጋግጥ በተግባር እንደማያውለው በጥናቱ ታይቷል፡፡

በአጠቃላይ ይህ የባህላዊ ግብርና እውቀት ረጅም ጊዜ ልምድ ዳበረ በመሆኑ ትኩረት ባይነፈገውና ከዘመናዊው ግብርና ጋር ተሳስሮ የሚሄድበት መንገድ ቢመቻች፣ ግብርና ፖሊሲ አውጪዎች ከገበሬው በመነሳት የገበሬውን እውቀት መሰረቱን የመመርመርና ተነጋግሮ የመስራት ልምዱ ቢያዳብሩ የተሻለ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ አጠቃላይ የጥናቱ ማስተዋወቂያ ሲሆን በውስጡም ስምንት ንኡሳን ክፍሎችን አሉት፡፡ 1. የጥናቱ ዳራ፣ 2. የጥናቱ መነሻ ጉዳይ፣ 3. የጥናቱ አስፈላጊነትና ፋይዳ፣ 4. የጥናቱ ዓላማዎች፣ 5. የጥናቱ ወሰን፣ 6. የጥናቱ ሥነ-ምግባር፣ 7.የመስክ ተሞክሮዎች፣ ተግዳሮቶች፣ መፍትሂዎቻቸው፣ 8.የጥናቱ አደረጃጀትና በመጨረሻውም የምእራፉ ማጠቃለያ በዝርዝር የቀረበበት ክፍል ነው፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የግብርና ሥራ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ ቢሆንም በእርግጠኝነት በዚህ ግዜ ነው የተጀመረው ለማለት የሚያስችል መረጃ ማግኘት አልቻልሁም፡፡ ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ"... አቤልም በግ ጠባቂ ነበር፤ ቃየንም ምድርን የሚያርስ ነበር" (ዘፍ. 4÷3) በማለት ይገልጻል፡፡ ይህም ከአዳም ልጆች አንዱ ገበሬ እንደነበር ያመላክታል፡፡ "It was only in the Neolithic era, less than 10,000 years ago, that humans began to cultivate plants and breed animals that they themselves had domesticated..." (Marcel and Laurance, 2006፡28)፡፡ በአዲሱ የድንጋይ ዘመን 10000 ዓመት በፊት ሰዎች ተክሎችን ማልማት፣ እንስሳትን ማለማመድና ማርባት እንደጀመሩ ይገልጻሉ፡፡ ይህ የድንጋይ ዘመን ሰዎች ተረጋግተው አንድ ቦታ መቀመጥ የጀመሩበት ጊዜ በመሆኑ እርሻ የጀመሩበት ዘመን እንደነበር ይገልጻሉ፡፡ እነ Marcel and Laurance (2006፡28) አያይዘው ሲገልጹ ጥንታውያኑ ሰዎች በዚህ ወቅት ለእርሻ የሚሆኗቸውን መሳሪያዎች ከድንጋይ አዘጋጅተው መጠቀም ችለዋል ይላሉ፡፡

ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሆነው ግብርና ዕድሜ ጠገብ ከሆኑ ሙያዎች አንዱ ነው:: እንዲያውም ከብት የማርባትና እህል የማምረትን ብልሃት ፈጥረው ለሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ያስተዋወቁት የኢትዮጵያ አካል የሆኑት ጥንታውያን

የኩሽ ህዝቦች ናቸው (Houston, 1926: 54-58)[1]:: ይህንንም ሃሳብ ሲያጠናክሩ "Early evidence of the plow in Ethiopia appears bound up with, and confused by the interaction of Cushitic-speaking residents of the highlands" (McCann, 1995:39):: በሀገራችን የግብርና እርሻ በሰሜን ደጋማ አካባቢዎች የተጀመረ ሲሆን የጀመሩትም የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው:: ይህም ሃገራችን ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ የመጡ የአያሌ ግብርና ነክ እውቀቶችና ልምዶች ባለቤት መሆኗን ያሳያል (McCann, 1995:)::

በ Houston ገለጻ መሰረት ከኩሽ ህዝቦች አንዱ የሆነው የአገው ብሔረሰብ የግብርናን ስራ በቀዳሚነት የጀመረ ነው (1926:54-58):: የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው የአዊ ብሔረሰብ ደግሞ የዚሁ አካል ሲሆን የብሔረሰቡ አብዛኛው ክፍል ማለትም (86.24%) የሚሆነው በገጠር የሚኖርና በዚሁ በባህላዊ ግብርና ስራ የሚተዳደር ነው (የአዊ ዞን ገ.ኢ.ት.ል.መምሪያ[2]፣ 2007):: ገበሬው ክረምቱን ጠብቆ የተለያዩ የእህል አይነቶችን፣ በበጋ በመስኖ ውኃ በመጠቀም ድንች፣ ሽንኩርትና ቅመማ ቅመምን ያመርታል፣ ያመረተውንም ለገበያ ያቀርባል:: ይህ ለህልውና መሰረት የሆነው ባህላዊ የግብርና ዕውቀት ግን ትኩረት ተሰጥቶት ሲጠና አይስተዋልም::

የተለያዩ አጥኚዎችም[3] በሀገራችን በባህላዊ ዕውቀት ስር የሚገኙት የባህላዊ ግብርና፣ የባህላዊ የቤተሰብ እቅድ፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት፣ የእደ ጥበብ ሙያዎች፣ የባህላዊና ማህበራዊ አስተዳደር፣ በአጠቃላይ ባህላዊ እውቀቶች ቀጣይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል የተሰነደ መረጃ እንደሌለ ይገልጻሉ:: በመሆኑም ይህ በሀገራችን ቀደምትነት ያለውና ዕድሜ ጠገብ የሆነው የባህላዊ ግብርና ዕውቀት በአግባቡ ተሰብስቦና ተሰንዶ አይገኝም:: "በአፍሪካ ግብርና በራሱ ትኩረት ሲሰጠው አይስተዋልም:: ግብርናውን በተለያየ ርዕስ ስር በማካተት በማህበራዊው፣ በኢኮኖሚው፣

[1] ከእንግሊዘኛ ስም በኋላ የሚገኘው ዓመተ-ምህረት እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ሲሆን ከአማርኛ (ከኢትዮጵያዊያን) ስም በኋላ ያለው ዓመተ-ምህረት በኢትዮጵያ አቆጣጠር ነው::
[2] ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር መምሪያ
[3] Woldeselasie, 2005; Alemu, 2008; Alemayehu, 2012, and others.

በፖለቲካው ታሪክ ውስጥ ገበሬውን የማጥናት ሁኔታ ታይቷል (Marcel and Laurance, 2006፡5)፡፡ በአጠቃላይ ባህላዊው ዕውቀት በተለይ ደግሞ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት በሳይንሳዊና በተገቢው መንገድ ተጠንቶና ተሰንዶ አይገኝም በማለት ይገልጻሉ (Atteh, 1992:25)፡፡ ይህ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት መሰብሰብና መተንተን ይኖርበታል፡፡

ስለዚህ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ሲታሰብ ዕውቀቱን ለመተግበር የሚጠቀማቸው መሳሪያዎች፣ በስራው ውስጥ የሚተገብራቸው ልማዶች፣ እምነቶች፣ ለማወደስ ወይም ለማንኳሰስ የሚጠቀምባቸው ሥነ-ቃሎች… ባጠቃላይ ከባህላዊ ግብርና ዕውቀት ጋር የተያያዙ የፎክሎር ክፍሎች በጥናቱ ውስጥ ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ለዚህ ጥናት አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች በርካታ ናቸው፡፡ በትምህርት ቤት፣ ከሰዎች በመስማትና በንባብ ወቅት ያገኘኋቸው በቅደም ተከተል ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ በነበርሁበት ዘመን የእርሻ ትምህርት እንደ አንድ የትምህርት አይነት ይሰጥ ነበር፡፡ በዚያ ወቅት ገበሬው የተለያዩ የሰብል አይነቶችን ዘር የሚመርጥበትን፣ የሚያስቀምጥበትን፣ የሚዘራበትን፣ የሚያርምበትን፣ የሚኮተኩትበትን፣ ሰብሉን የሚሰበስብበትን ሁኔታና ጊዜያት እና የሚያስቀምጥበትን ዘዴ ስማር ሁልጊዜ በልጅነት አእምሮዬ ይመጣ የነበረው ገበሬው ሳይማር ይህን ሁሉ እንዴት ሊያውቅ ቻለ? ከየት ተማረው? የሚለው ነበር፡፡ ታዲያ ይህ ጥያቄ ዛሬ ጊዜውን ጠብቆ ምላሽ ለማግኘት ለጥናት አነሳስቶኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሚከተሉት ገጠመኞችም ተጨማሪ አነሳሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

ገጠመኝ አንድ[4]፡- ይህ ታሪክ ጎጃም ውስጥ በአካባቢና አፈር ጥበቃ የእርከን ስራ ወቅት የተፈጸመ ነው፡፡ አንድ በጎርፍ የተቦረቦረ ቦይ ላይ እርከን በሚሰራበት ወቅት የግብርና ኤክስቴንሽን ሰራተኛው በዩ ላይ የሚሰራው እርከን በድንጋይ ይሰራ ብሎ ድንጋይ

[4] አቶ ተፈራ ተመስገን የነገሩኝ ታሪክ

ማሽከም ይጀምራል፡፡ ነገር ግን በአካባቢው ከታውቁ አንድ ሽማግሌ ጋር ሊግባቡ አልቻሉም፡፡ ሽማግሌው በድንጋይ መሰራት የለበትም በማለት ይከራከራሉ፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ በክረምት ድንጋዩ ይናድና መሬቱን የበለጠ ይሸረሽረዋል የሚል ነበር፡፡ ኤክስቴንሽን ሰራተኛው በበኩሉ አንተ ምን ታውቃለህ፤ እኔ በምልህ መንገድ ስራ ይላቸዋል፡፡ በዚህም መንገድ መግባባት ሳይችሉ ቀሩ፡፡ በመጨረሻም ሽማግሌው ልማቱን አደናቀፉ ተብለው ለአንድ ቀን ታሰረው ዋሉ፡፡ ቦዩም ኤክስቴንሽን ሰራተኛው በሚፈልገው መንገድ በድንጋይ ተሰራ፡፡ ነገር ግን ቦዩ ላይ የተሰራው እርከን የክረምቱን ጎርፍ መቋቋም ባለመቻሉ በጎርፍ ተጠራርጎ ተወሰደ፡፡ ሽማግሌው እንደ ተናገሩትም መሬቱ የባሰ ተሸረሸረ። ሽማግሌው ግን ያንን ቦይ ዝም ብለው አላዩትም፡፡ ከራሳቸው ዛፍ ቆርጠው በቦዩ ላይ እንደ አጥር በማጠር በእርጥብ ቅጠል ሸምጠው በመስራት ቦዩ በአፈር እንዲሞላ አደረገት፡፡

ገጠመኝ ሁለት[5]፡- ይሄኛው ታሪክ የተፈጸመው እራሴ እሰራበት በነበረው ትምህርት ቤት ውስጥ ነው። በትምህርት ቤቱ ክልል ውስጥ የሚገኘው መሬት በየአመቱ ለገበሬዎች በኪራይ እየተሰጠ ለሰብል ምርት ይውላል፡፡ ከኪራይ የሚገኘውም ገንዘብ የትምህርት ቤቱን የውስጥ ገቢ ያዳብራል፡፡ በመሬቱ የሚበቅለው የእህል አይነት ኑግና ጤፍ ነው፡፡ በአንድ ወቅት ግን መሬቱን የተከራዩት ገበሬዎች የስንዴ ምርጥ ዘር መዝራት አለባችሁ ተብለው ተገደዱ፡፡ ነገር ግን ገበሬዎቹ መሬቱና የአየር ንብረቱ ለስንዴ አይሆንም በማለት ቢከራከሩም ሰሚ ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ ሰለዚህ በግዳጅ በብድር ማዳበሪያና የስንዴ ምርጥ ዘር ወስደው እንዲዘሩ ተገደዱ፡፡ ገበሬዎቹም የታዘዙትን አደረጉ፡፡ ይሁን እንጂ በሚያሳዝን ሁኔታ በማሳው ላይ ለምልክት ያህል እንኳን አንድም የስንዴ ዘር ሳይበቅል ቀረ፡፡ ገበሬዎችም ባለዕዳ ሆነው ቀሩ፡፡

ለዚህ የጥናት ርዕስ መመረጥ ሌላኛው ምክንያት የተጠኘው አካባቢ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት በስፋት አለመጠናቱ ነው፡፡ ለጥናት በመረጥሁት የአዊ ብሄረሰብ ዞን የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን በተመለከተ እኔ ያገኘሁት ሁለት ጥናቶችን ብቻ ነው፡፡ እነዚህም

[5] ጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ ቲሊሊ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት (በ1990)

Alemu (2008) በአንከሻ ባንጃ ወረዳ በሶሻል አንትሮፖሎጂ፣ Bekallu (1994) በአንከሻ ጓጉሳ ወረዳ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም የተጠኑ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ናቸው፡፡ የነዚህ ጥናቶች ዝርዝርም በምዕራፍ ሦስት በተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ውስጥ ቀርቧል፡፡ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ገጠመኞች የገበሬዎችን ባህላዊ የግብርና ዕውቀት እንዳጠና አነሳስተውኛል፡፡

ጥናቱ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት በመሆኑ የግብርና ዕውቀት በፆታ የሚገደብ ዕውቀት አይደለም፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት የሴቶችን የባህላዊ ግብርና ዕውቀትንም ይጨምራል፡፡ እንዲሁም የዕውቀት ተስተላልፎና ከባህላዊ ግብርና ዕውቀት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ይዳስሳል፡፡

## 1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት

ለጥናቱ አስፈላጊ ግብአቶችን ለመሰብሰብ በቀጥታ ግንኙነት ይኖራቸዋል ባልኳቸው መስሪያ ቤቶች ማለትም የግብርና ሚኒስቴር፣ የግብርና ምርምር ተቋምና ብዝሓ ሕይወት ቅኝት አድርጌ ነበር፡፡ በዚህ ወቅትም መረጃው በግብርና ሚንስቴር ባለመገኘቱ ወደ ግብርና ምርምር ተቋም ላኩኝ፡፡ እዚያም ያለው የምርጥ ዘር (የእንስሳትና የአዝርእት) ብቻ እንጂ የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን በተመለከተ ምንም መረጃ አልነበራቸውም፡፡ በዚህም ምናልባት ወደ ብዝሓ ሕይወት ብሄድ የምፈልገውን መረጃ ላገኝ እንደምችል ጥቆማ ሰጡኝ፡፡ ነገር ግን ብዝሓ ሕይወት መስሪያ ቤትም ከሌሎቹ የተለየ ነገር አላጋጠመኝም፡፡ ብዝሓ ሕይወት መስሪያ ቤት ውስጥ የሚገኙ መረጃዎች አንዳንድ ነባር ዝርያዎች መቼ እንደተሰበሰቡ፣ በማንና ከማን፣ ከየት እንደተሰበሰቡ የሚገልጽ መረጃዎች ብቻ ናቸው፡፡ የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን በተመለከተ ግን በአግባቡ ተሰንዶና ተዘጋጅቶ የተቀመጠ አላገኘሁም፡፡[6] ይህም የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ትኩረት የተነፈገው መሆኑን ያሳያል፡፡ ይኸውም በእኛ ሀገር ብቻ ሳይሆን በሌሎችም አገሮች ተመሳሳይ ነው፡፡ Warren (1993) ይህንን ሃሳብ ሲያጠናክሩ፣ የግብርና ዕውቀት ትግበራ በጽሑፍ መልክ የለም፣ ዕውቀት ከትውልድ

[6] በ30/03/2006 በተደረገ ቅኝት ፡፡

ትውልድ የሚተላለፈው በቃል ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ የዚህ ጥናት መጠናት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ጥናት የሚከተሉት ፋይዳዎች ይኖሩታል ተብሎም ይታሰባል፡፡

## 1.4. የጥናቱ ፋይዳ

ይህ ጥናት ለዞኑም ሆነ ለአካባቢው ማህበረሰብ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

- ❖ ፎክሎር ከብዙ የጥናት መስኮች ጋርም ይገናኛል፡፡ ፎክሎር ከአንትሮፖሎጂ፣ ከሥነጽሁፍ፣ ከታሪክ፣ ከፍልስፍና፣ ከቋንቋ... ጋር ይገናኛል (Clifored, 1988; Hymes, 1972)፡፡ በዚህም ከተለያዩ የማህበራዊ ሳይንስ ዘርፎች ጋር የሚጋራው ብዙ ስለሆነ ከሌሎች የትምህርት መሰኮች የሚደጋገፍ በመሆኑ ለሌሎች አጥኚዎች አዳዲስ የጥናት ዘዴዎችን እንዲያፈልቁ መነሻ ሊሆን ይችላል፡፡
- ❖ በተለያዩ ምክንያቶች ሊለውጡ የሚችሉ የባህላዊ ግብርና ዕውቀቶች አሁን ባሉበት ሁኔታ ለመጪው ትውልድ በሰነድነት ለማበርከት ያስችላል፤
- ❖ በክልልና በዞን ያሉ አመራሮችና የግብርና ሰራተኞች ለብሔረሰቡ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ትኩረት እንዲሰጡ ለማድረግ ያስችላል፤
- ❖ የግብርና ፖሊሲ የሚቀርጹ አካላት የልማት ዕቅዶች ሲያቅዱ ከገበሬው መነሳት እንዳለባቸውና ለማህበረሰቡ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ጠቋሚ ማስረጃ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡
- ❖ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ከዘመናዊው ግብርና ጋር እንዲደጋገፍ ለማድረግ ያስችላል፤
- ❖ ሌሎች አጥኚዎች ባህላዊ እውቀቶች በፎክሎር ስር ሊጠኑ እንደሚችሉና ቀርነቶችን ለመሙላት እንዲችሉ ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡
- ❖ በግብርናው ዙሪያ ለሚሰሩ ሀገር በቀልና ሀገር በቀል ላልሆኑ ድርጅቶች፣ የሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ መስሪያ ቤቶችና ተቋማት፣ እንደግብአት ሊያገለግል ይችላል፡፡

ጥናቱ ግቡን ይመታ ዘንድ የሚከተሉት ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

## 1.5. የጥናቱ ዓላማዎች

ይህ ጥናት አንድ አብይ ዓላማና ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡ ጥናቱ ከአብይ ዓላማ የሚነሱ ዝርዝር ዓላማዎችን ይዟል፡፡ እነዚህ ዓላማዎች ጥናቱ ግቡን ይመታ ዘንድ አቅጣጫን ጠቋሚዎች ናቸው፡፡

### 1.5.1. የጥናቱ አብይ ዓላማ

ይህ ጥናት በአዊ ብሔረሰብ ዞን ውስጥ የሚገኙት የጓጉሳ ሽኩዳድ ገበሬዎች የሚተገብሯቸውን የባህላዊ ግብርና እውቀቶችና ተያያዥ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በመሰብሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፉ ማድረግ ነው፡፡

### 1.5.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

ጥናቱ ከአብይ ዓላማው የሚነሱ ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡ እነዚህም፡-

1. የጓጉሳ ሽኩዳድ ገበሬዎች[7] ከማሳ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ሰብል ስብሰባ ድረስ እየተገበሩት ያለው የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን መመርመር፤
2. የጓጉሳ ሽኩዳድ ገበሬዎች የባህላዊ ግብርና ዕውቀታቸውን የሚያስተላልፉባቸው አውዶችና መንገዶች ምን ምን እንደሆኑ ጠይቆ መመዝገብና መመርመር፤
3. በባህላዊ የግብርና ዕውቀት ትግበራና ሽግግር ዙሪያ በጊዜ ሂደት እየታዩ ያሉ ለውጦች መነሻ ምክንያት መፈተሽ፣ የለውጡን አይነት መመርመርና፤
4. የጓጉሳ ሽኩዳድ ገበሬዎች ከባህላዊ ግብርና ስራቸው ጋር በተያያዘ የሚናገሯቸውን፣ የሚያበጇቸውን፣ የሚከውኗቸውን እና የሚፈጽሟቸውን ፎክሎራዊ ጉዳዮች መለየትና ፋይዳቸውን ተንትኖ መግለጽ የሚሉት ናቸው፡፡

---

[7] ሴቶችንም ያጠቃልላል

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚካሄደው በአማራ ክልል በአዊ መስተዳድር ዞን በሚገኘው የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ ሶስት የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ነው፡፡ የሚጠኑት የማህበረሰብ ክፍሎችም በሶስቱ የገጠር ቀበሌዎች የሚገኙ ገበሬዎች ናቸው፡፡ በወረዳው ውስጥ የሚገኘው ሞቃታማ ቀበሌ አንድ ወይናደጋ አንድ ቀበሌና ከደጋው አንድ ቀበሌ በጠቅላላው ሶስት የጥናት ቀበሌዎችን መረጥሁ፡፡ በዚህም ከወረዳው ቀበሌዎች ውስጥ ሁለት ዳር የወጡ ደጋና ሞቃታማ ቀበሌዎች የተመረጡ ሲሆን ከደጋው አግዛ ጋርዳ ኤሊያስ ቀበሌን ቆላ ተብሎ ከሚታሰበው ደግሞ አደጋ ጓሽታ ቀበሌን እንዲሁም ከወይና ደጋው አብስላ ሳሙኤል ቀበሌን ለጥናት ቦታ መርጫለሁ፡፡ አብስላን ከወይና ደጋነቱ በተጨማሪ በመምህርነት የሰራሁበት ቦታ ስለነበርና አካባቢውን ስለማውቀው ምርጫዬ አድርጌዋለሁ፡፡

ጥናቱ የፎክሎር ጥናት ሆኖ ትኩረቱን በባህላዊ የግብርና ዕውቀት ላይ ያደረገ ነው፡፡ የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይም ከማሳ ዝግጅት እስከ ሰብል ስብሰባ ድረስ ያለው የገበሬው የባህላዊ ግብርና እውቀትና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥነ-ቃሎች፣ ልማዶችና እምነቶችና ክዋኔዎች ናቸው፡፡

ከቦታ አንጻር በዞኑ ካሉ ወረዳዎች የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ ተመርጧል፡፡ በዚህም በወረዳው ከሚገኙት አስራ ሶስት የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ሶስት ቀበሌዎች ተመርጠዋል፡፡ የናሙና አወሳሰድ ዘዴው የአካባቢውን የአየር ጠባይ መሰረት በማድረግ አደጋ ጓሽታ፣ አብስላ ሳሙኤልና አግዛ ጋርዳ ኤሊያስ ቀበሌን ያካተተ ነው፡፡ ይህም የሆነው እንደ አየር ጠባዩ ሁኔታ የእርሻ መሳሪያዎችና አዝርእት ልዩነት ስለሚታይባቸው ነው፡፡

## 1.7. የጥናቱ ውሱንነት

ይህን ጥናት ምልዑ ለማድረግ ጥረት ቢደረግም ቀርነቶች የሉትም ለማለት ግን አይቻልም፡፡ ይህም የሆነው የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ በጣም ሰፊ በመሆኑ ሁሉንም የባህላዊ

ግብርና ዕውቀቶች መዳሰስ በለመቻሉ ውሱንነቶች እንደሚኖሩ ይገመታል፡፡ ከጊዜና ከገንዘብ ማነስ ጋር ተያይዞ ሌሎች የባህላዊ ግብርና እውቀቶችን በዚህ ማየት አልተቻለም፡፡ እንዲሁም ጥናቱ የሚሰራው በአማርኛ ቋንቋ በመሆኑና ለመረጃነት የሚያገለግሉት ጥናታዊ ጽሑፎችም ሆኑ አጋዥ መጻሕፍት በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተሰሩ በመሆናቸው ወደ አማርኛ ቋንቋ በመመለሱ ሂደት ላይ ውሱንነቶች ይፈጠራሉ፡፡ ሌሎቹ ውሱንነቶች በአጋጣሙ ችግሮች ላይ የተጠቀሱት ናቸው፡፡

ከቦታ አንጻር በዞኑ ካሉ ወረዳዎች የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ ተመርጧል፡፡ በዚህም በወረዳው ከሚገኙት አስራ ሶስት የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ሶስት ቀበሌዎች ተመርጠዋል፡፡ የናሙና አወሳሰድ ዘዴው የአካባቢውን የአየር ጠባይ መሰረት በማድረግ አደጋ ጓሽታ፣ አብስላ ሳሙኤልና አግዛ ጋርዳ ኤሊያስ ቀበሌን ያካተተ ነው፡፡ ይህም የሆነው እንደ አየር ጠባዩ ሁኔታ የእርሻ መሳሪያዎችና አዝርእት ልዩነት ስለሚታይባቸው ነው፡፡

## 1.8. የጥናቱ ሥነ-ምግባር፣ የመስክ ተሞክሮ፣ተግዳሮቶችና መፍትሄዎቻቸው

የጥናቱ ሥነ-ምግባር፣ የመስክ ተሞክሮዎች፣ ተግዳሮቶችና የተሰጡ መፍትሂዎች በቅደም ተከተል በዝርዝር የሚቀርቡበት ክፍል ነው፡፡

### 1.8.1. የጥናቱ ሥነ-ምግባር

የጥናቱ ሥነ-ምግባር አንድ የፎክሎር አጥኚ ትክክለኛ የሆነ ጥናትና ምርምር ለመስራት ይችል ዘንድ የተጠኚውን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግና ደንብ ማክበርና መጠበቅ፣ የጥናቱን ዓላማ በግልጽ ማስተዋወቅ ተገቢውን ከበሬታ መስጠት የሚሉትን የምርምር ሥነ-ምግባሮች መጠበቅ ከተመራማሪዋ/ው የሚጠበቁ ዋነኛ ተግባራት ናቸው ይላሉ (Chatherina 2007)፡፡

በዚህም መሰረት ለጥናት ወደ መረጥኳቸው ቀበሌዎች ከመንቀሳቀሴ በፊት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት፣ ለተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የጥናቱን ዓላማ

በማሳወቅ አስፈላጊውን የትብብር ደብዳቤ በማጻፍ ወደ ተጠኚዎቹ ማህበረሰቦች ገብቻለሁ፡፡ ወደ ቦታው በመሄድም በቅድሚያ በቦታው ለሚገኙ የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፣ ለቀበሌ አመራሮችና ለአካባቢው ሽማግሌዎች የጥናቱን ዓላማ በማስረዳት መረጃ አቀባዮችን ለማግኘት ችያለሁ፡፡ ከመረጃ አቀባዮቹ ጋር በመገናኘትም መረጃዎችን ሰብስቢያለሁ፡፡ በዚህ ወቅትም የሚሠጡት መረጃ ለማንም ተላልፎ የማይሰጥ መሆኑን በመግለጽ ፈቃደኝነታቸውን አግኝቻለሁ፡፡ ስማቸው እንዲጠቀስ የማይፈልጉትን፣ ፎቶ መነሳት የማይፈልጉትን ሰዎች ፍላጎታቸውን አክብሪያለሁ፡፡ በሚስጢር እንዲያዝላቸው የሚፈልጉትን ሚስጥራዊነቱን ጠብቄ መረጃውን ብቻ ተጠቅሚያለሁ፡፡

ባህሉን በጠበቀ መልኩ እነሱ የማይፈልጉትን የሴት ልጅ አለባበስ በማስወገድ እና አለባበሴን በሚፈልጉት መንገድ በማስተካከል በመረጃ አቀባዮቼ ዘንድ አመኔታን ለማግኘት ችያለሁ፡፡

ለጥናት የሚሆኑኝን መረጃዎች ለመሰብሰብ በተለያዩ ወቅቶች ወደ መስክ ሂጃለሁ፡፡ በዚህ ወቅትም የገጠሙኝ የመስክ ተሞክሮዎች እና ተግዳሮቶች ነበሩ፡፡

### 1.8.2. የመስክ ተሞክሮ

የመስክ ተሞክሮው በሁለት ክፍል የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ቅድመ መስክ ዝግጅት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የተከናወኑ ተግባራት ለመስክ ሥራ የሚሆኑኝን እቃዎች (የፎቶ ካሜራ፣ የቪዲዮ ካሜራ፣ መቅረጸ ድምጽ፣ ማስታወሻ ወረቀት፣ እስክርቢቶ) ማዘጋጀት፣ ከዩኒቨርሲቲው የትብብር ደብዳቤ ማጻፍና አስፈላጊውን የጉዞ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ናቸው፡፡

ሁለተኛው ክፍል ወደ መስክ መሄድ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ቀዳማይ መረጃ የተሰበሰበው ከመስክ ነው፡፡ ይህንን መረጃ ለመሰብሰብ በመጀመሪያ 2006ዓ.ም ግንቦትና ሰኔ፣ ለሁለተኛ ጊዜ በ2007ዓ.ም ከየካቲት እስከ ሚያዚያ እንዲሁም ለሶስተኛ ጊዜ ሐምሌ

እና ነሐሴ ለአራተኛ ጊዜ 2008 ዓ.ም. ህዳርና እና ከደረጃ ማበልጸጊያ በኋላ ደግሞ ለአምስተኛ ጊዜ በ2008ዓ.ም ሚያዚያና ግንቦት ባሉት ጊዚያቶች ከመስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አምስት ጊዜ ወደ ቦታው ሂጃለሁ፡፡

በዚህ ሂደት በአካባቢው ከ10 ዓመት በላይ በመምህርነት የሰራሁ በመሆኔ በማህረሰቡ ዘንድ በተለይም በሴት አለባበስ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ስላላቸው አለባበሴን በተመለከተ እነሱ የሚፈልጉትን አለባበስ ቀሚስ በመልበስ የነሱን ትኩረት ለማግኘት ችያለሁ፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የሴት ሱሪ መልበስ እንደ ነውር ይቆጠራል፡፡ ይህም ተቀባይነትን ያሳጣል፡፡ እኔ ግን በዚህ በኩል የሚመጣውን ችግር አስቀድሜ ለመከላከል ችያለሁ፡፡

በቅድሚያ ለዚህ ስራ መረጃ ሊሰጡኝ ወደ ሚችሉ የዞኑ ገንዘብና ኢኮኖሚ ጽ/ቤት በመሄድ ትብብር ደብዳቤዬን በማሳየት የሚመለከታቸውን አካላትና በቅርበት የማውቃቸውን የቢሮው ሰራተኞች አነጋግሪያለሁ፡፡ መረጃውን ሊሰጠኝ የሚችለው አካል ለጊዜው ስለሌለ የምፍልገውን የዞኑን መረጃ አዘጋጅተው በሁለት ቀን ውስጥ ሊሰጡኝ በቀጠሮ ተለያየን፡፡ በቀጠሮው መሰረት ከሁለት ቀን በኋላ በቦታው ተገኘሁ፡፡ እነሱም ቀና ትብብራቸው ሳይለየኝ አስፈላጊውን መረጃ ሁሉ የዞኑንና የተጠኚ ወረዳውን ካርታ ጨምረው ሰጡኝ፡፡ ሌላም የምፈልገው መረጃ ካለ ለመስጠት ዝግጁ መሆናቸውን በመግለጽ የቢሮና የግል ስልካቸውን ሰጡኝ፡፡

በመቀጠልም ወደ ጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ መስተዳድር በመሂድ ጉዳዩን ሳናግራቸው ወደ ወረዳው ግብርና ጽ/ቤት ላኩኝ፡፡ የወረዳው ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊም የቀድሞ ተማሪዬ ሆኖ አገኘሁት፡፡ እሱም ለሚመለከተው አካል ጉዳዬን ገልጾ የሚያስፈልገኝን መረጃ እንዲሰጠኝ ነገረልኝ፡፡ በሶስት ቀናት ውስጥ ምንም መጉላላት ሳያጋጥመኝ በቢሮ በኩል ያለውን መረጃ በዚህ መንገድ አሰባሰብሁ፡፡

በዚህ መሰረት ለጥናት የሚሆኑኝን ቀበሌዎች ለመምረጥ ከወረዳ ግብርና ኃላፊ ከአቶ ዘመን ጥላዬ ጋር ተገናኝቼ በጉዳዩ ከተወያየን በኋላቀጣዩ ስራዬ አብሮኝ የሚንቀሳቀስና መንገድ የሚመራኝ ሰው ማፈላለግ ነበር፡፡ ይህንም ለማግኘት በቅድሚያ ተማሪዎቼ የነበሩ ልጆችን ማፈላለግ ጀመርሁ፡፡ በነሱ ረዳትነትም አንድ የማውቀውን ዳኜ ይሁን የተባለ አስረኛ ክፍል ያጠናቀቀ ተማሪ በመንገድ መሪነት አገኘሁ፡፡ ከዳኜ ጋር ተነጋግረን ቀጠሮ ይዘን ተለያየን፤ ገበሬዎችን ለማግኘትና ተረጋግቶ ለመነጋገር የሃይማኖት በዓላት ቀናት ተመራጭነት እንዳላቸው ቀደም ብዬም አውቅ ስለነበር የካቲት 21/የማሪያም በዓል/ ለመሄድ ቀጠሮ ያዝን፡፡

አንደኛውን የጥናት ቀበሌ አደጋ ጓሽታ ውባጅ ቀበሌን ከስም በስተቀር ስለማላውቀው በቅድሚያ ግንቦት 8 አካባቢውን ለመቃኘት ከረዳቴ ጋር ለመሄድ ስንነሳ የግብርና መኪና ወደ መስክ ስለምትወጣ ከእነሱ ጋር ሂጂ በማለት የወረዳው ግብርና ኃላፊ ነገሩኝ፡፡ አደጋ ጓሽታ ውባጅ ቀበሌ ከዋናው መንገድ የራቀና አስቸጋሪ ስለነበር የመስተዳድሩ ምክትል አስተዳዳሪ ከግብርና፣ ከጤና፣ ከወረዳ መስተዳድር ለመስክ ስራ መኪና ይዘው ሲወጡ ከእነርሱ ጋር እየሄድሁ መረጃ እንድሰበስብ ሁኔታዎችን አመቻቹልኝ፡፡ መንገዱ እጅግ አስቸጋሪና ፈታኝ ነበር፡፡ ሆኖም በቦታው ተገኝተን ለቀበሌ ሊቀመንበሩ የትብብር ደብዳቤውን ሰጠን፡፡ ከዚያም አካባቢውን ቃኝተን በቀጠሮአችን ልንገናኝ ተለያየን፡፡

ቀጣዩ ስራዬ መረጃ አቀባዮችን ማግኘት ስለነበር አሁን በቦታው የሌለውንና ቀድሞ የጽ/ቤት ኃላፊ ከነበረው (ከአቶ ቴዎድሮስ ደሴ) ጋር ወደ ቦታው በመሄድ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉና ሌሎች መረጃ አቀባዮችን ሊጠቁሙኝ የሚችሉ ሰዎችን ነገረኝ፡፡ በዚህም ግንቦት 12 ወደ ቦታው በመሄድ ሰዎችን አገኘሁ፡፡ በአካባቢው ለረጅም ዓመት የኖሩ ዕድሜያቸው ከ80 ዓመት በላይ የሆኑ አዛውንት አገኘሁ፤ እሳቸውም በዚህ ጉዳይ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ ሰዎችን ከተለያየ ጎጦች ጠቆሙኝ፡፡ በእለቱም ያገኘኋቸውን ሁለት ሴትና ሁለት ወንድ መረጃ አቀባዮች ጋር እራሴን በማስተዋወቅና የጥናቱን ዓላማ በግልጽ በመንገር የሚያውቁትን፣ የኖሩበትንና እየኖሩበት ያለውን ሕይወት

በተመለከተ ስለባህላዊ ግብርና እንዲያወጉኝና ሲሰሩም እንድመለከት ፈቃደኝነታቸውን ሰጥተውኝ በቀጠሮ ተለያየን፡፡

ቀጣይ ጉዞ ወደ አብስላ ሳሙኤል ቀበሌ በመሆኑ ቀን አመቻችተን በማግስቱ ግንቦት13 ሄድን፡፡ በዚሁ ዕለት የአካባቢው ታቦት መስቀላ ክርስቶስ በዓል ስለሆነ በ13 ስራ አይሰሩም፡፡ በእለቱም በቦታው በመገኘት ደብዳቤዬን ከሰጠሁ በኋላ ቄስ አወቀ የሚባሉ ቀድሞ የማውቃቸውን የተማሪዎቼ ወላጅ አጠያይቄ አገኘሁ፡፡ በእሳቸውም አማካይነት ለመረጃው የበለጠ ቅርበት ያላቸውን ሰዎች ለማግኘት ቻልሁ፡፡ በዚህ ቀበሌ ብዙም የጎላ ችግር አላጋጠመኝም፡፡

የሚቀጥለው ጉዞ ወደ አግዛ ጋርዳ ኤሊያስ ቀበሌ ሆነ፡፡ ይህ ቀበሌ የረዳቴ ቤተሰቦች ቀበሌ በመሆኑ ከአብስላ በተሻለ መልኩ መረጃ አቀባዮችን ለማግኘት አልተቸገርሁም፡፡ በአካባቢው ለስራ በቆየሁባቸው አመታት በተለያዩ ወቅቶች በለቅሶ፣ በአውዳመት ዝክር፣ የሁለተኛ ዲግሪዬን የመመረቂያ ጽሑፍ በሰራሁበት ወቅት አካባቢውን የመመልከት አጋጣሚ ነበረኝ፡፡ በዚህም ምክንያት መረጃ አቀባዮችን ለማግኘት አልተቸገርሁም፡፡

ጥናቱ ወቅትን ጠብቆ የሚከናወን ቢሆንም ከምልከታ ውጪ ያሉትን መረጃዎች በቃለ-መጠይቅ ዘዴ በመቅረጸ ድምጽ አማካኝነት ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ወቅት የሚፈልጉትን ደግሞ በእርሻ፣ በጉልጓሎ፣ በጭቃ በራይ፣ በዘር በአረም፣ በአጨዳና በውቂያ ወቅቶች በቦታው በመገኘት ከተፈጥሯዊ አውዱ በፎቶግራፍ፣ በምስልና በድምጽ መቅረጫ መረጃ ሰብስቤአለሁ፡፡

በቃለ መጠይቅ የሚሰበሰቡትን መረጃዎች ለመሰብሰብ ቀጠሮ በመያዝና በቦታው በመገኘት በተለያየ ምክንያት የማላገኛቸውን ደግሞ ቀጠሮ በመያዝና በተደጋጋሚ በመሄድ መረጃዎችን ሰብስቤአለሁ፡፡ በፎክሎር ጥናት መስከኛ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ የሚያገኘውን መረጃ መያዝ ስላለበት በተለያየ አጋጣሚ የማገኛቸውን መረጃዎች ሳልንቅ በፎቶ ካሜራ ለማስቀረት ችያለሁ፡፡

በመስክ ስራ ላይ የተለያዩ ገጠመኞች ይኖራሉ፡፡ ለሶስተኛ ጊዜ ወደ መስክ (ከየካቲት-ሚያዚያ 2007ዓ.ም) የሄድሁበት ወቅት በደጋው አካባቢ የውቂያ ወቅት ነበር፡፡ ከመረጃ አቀባዮቼ መካከል የረዳቴ ቤተሰቦች ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ሰዎች ጤፍ እንደሚወቁ ተነግሮኝ መረጃውን ለመሰብሰብ ከሌሊቱ 11፡00 ሰዓት በቦታው ተገኘሁ፡፡ አካባቢው ጨለማ ስለነበር በፎቶግራፍም ሆነ በምስል መቅረጫ ማስቀረት ባልችልም ከዳር ሆኜ መመልከቴን ቀጠልሁ፡፡ ስራው የሚከናወነው በባትሪ ብርሃን በመታገዝ ነበር፡፡

ክምሩ ከመናዱና ከመነስነሱ በፊት በሶስት ሰዎች በዕድሜ ተዋረድ ከትንሽ ወደ ትልቅ የምርቃት ስርዓት ተከናወነና ክምሩ እየተናደ በተለቀለቀው አውድማ ላይ መነሥነስ ተጀመረ፡፡ ከዚያም ከብቶች አፋቸውን ተለጉመው በተነሰነሰው እህል ላይ ይነዱ ጀመር፡፡ በዚህ መንገድ ስራው ቀጠለና እረፋዱ ላይ (4፡00 ሰዓት ገደማ) ጠላና ጥሬ ተዘጋጅቶ መጣ፡፡ በዚው አካባቢ ያለው ሁሉ መብላት ጀመረ፡፡ እኔም እንድቀምስ ተጠየቅሁ፡፡ ትንሽ ልቆይ ሰዓት ገናነው ስላቸው "ስለማውቅሽ ነው እንጂ እምቢ ብትይም በግድ አፍሽን መንግጌ ነበር የማቀምስሽ" አሉኝ፡፡ ለምን ስላቸው "አጉማስ ቢደቃሽ በማን ልታላክኪ? በአውድማ አካባቢ የሚያልፍ ሳይቀምስ አይሄድም ነውር ነው" አሉኝ፡፡

በመስክ ስራ ወቅት አልፎ አልፎ እቤታቸው ሲጋብዙኝ በመገኘት ያቀረቡልኝን በመጋበዝ አስፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ችያለሁ፡፡ አድካሚ የሆነውን የገጠር መንገድ ከእነሱ ጋር እየተጫወትሁ ስለምጓዝ ብዙም ድካም ሳይሰማኝ ተወጥቼዋለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በሶስተኛው ዙር መስክ ስራ ወቅት ገበሬው እርሻ የሚጀምርበት ወቅት በመሆኑ ከመስክ በምልከታ የሚሰበሰበውን መረጃ መሰብሰቢያ ወቅት ነበር፡፡ ሆኖም በዚያ ወቅት በተለይም በአደጋ ጓሽታ ውባጅ ቀበሌ የምፈልገውን መረጃ ለማግኘት አስቸጋሪ ወቅት ነበር፡፡ አምስተኛው ዙር አገራዊ ምርጫ የሚካሄድበት ጊዜ በመሆኑ ለእያንዳንዱ እንቅስቃስዬ የሚያነሱት ጥያቄ አስደንጋጭ ነበር፡፡ በእኛ ፎቶ እንጂራ

ልትበይ ነው? የየትኛው ፓርቲ አባል ነሽ? እባክሽን ልጆቻችንን እናሳድግበት?... የሚሉ ነገሮች ይሰነዘሩ ነበር፡፡ ነገር ግን በተረጋጋ መንፈስ ከነሱ በተጎራባች ባለው ቀበሌ አስተማሪ እንደነበርሁና ባካባቢውም ሆነ በከተማ የማውቃቸውን ሰዎች እየጠቀስሁ ሁኔታዎችን በማርገብ የምፈልገውን መረጃ ለማግኘት ችያለሁ፡፡

በተለያየ ወቅት ወደ መስክ በመሄድ የምፈልጋቸውን መረጃዎች ለማግኘት ጥረት አድርጊያለሁ፡፡ በመረጃ ስብሰባ ወቅት ከአንድ ቀበሌ በስተቀር በሌሎቹ ቀበሌዎች መረጃን ለመሰብሰብ በመረጃ አቀባዮቹ በኩል የተቸገርሁበት አጋጣሚ የለም፡፡ ይሁን እንጂ በዚያ ወቅት የተከሰተው የዝናብ እጥረት በገበሬው ዘር መዝሪያ ጊዜ ላይ ተጽእኖ ነበረው፡፡

በወቅቱ በመጠኑም ቢሆን ሌሊት ዝናብ ማካፋት በመጀመሩ የጭቃ በራይ ወደ ሚያከናወኑበት ቦታ በመሄድ የሰውየውን ፈቃድ በመጠየቅ የምልከታ ሂደቱን በፎቶ እና በምስል መቅረጫ መረጃዎችን ሰበሰብሁ፡፡ አበራይቶ ከጨረሰ በኋላ ከአሁን አሁን ይዘራል ብለን ስንጠብቀው አሁን አልዘራም ትንሽ “ዳ”[8] ብላችሁ ኑ አለን፡፡ ከዚያ ስንወጣ አብሮኝ ያለውን ረዳቴን አይደርቅበትም? ብዬ ስጠይቀው አንቺን ፈርቶ እኮ ነው አለኝ፡፡ ለምንድን ነው እኔን የፈራኝ? ያውቀኛል እንዲሁም ነግሬዋለሁ ስለው “በመስመር ዝሩ ስለሚባሉ ከግብርናዎች እየተደበቁ ነው የሚዘሩት አለኝ፡፡” ለምን የሚል ጥያቄን ሳስከትል “ባለፈው የምርት ዘመን ለቆላ የሚሆን ምርጥ ዘር አምጥተው ለዚህ አይሆንም ቢሏቸው በግድ አዘሯቸውና ጠፍቶ ቀረ፡፡” አለኝ እና ግብርናዎች ዝም ይሏቸዋል ስለው ያው 100 ብር ይቀ»ዕቸዋል ቢቀጡ ይመርጣሉ” አለኝ፡፡

እኛም ይህን እያወራን ወደ ሌላ ጭቃ በራይ ወደ ሚከናወንበት ቦታ ሄድን፡፡ ጭቃ በራዩን ለጤፍ ዘር የሚከናወነውን ሂደት ለመመልከትና ለመቅረጽ ግን የዝናብ እጥረቱ እንቅፋት ነበር፡፡ በጤፍ ዘር ወቅት መጠነኛም ዝናብ ባለበት ጭቃ በራይ ይከናወናል፡፡ በዚህ ወቅት አንድ አባት ዝናቡ ማካፋት ሲጀምር ጭቃ በራይ

[8] ዳ- ማለት በአካባቢው ዘግየት ቆየት ማለት ነው፡፡ ዳ ብላችሁ ኑ ሲል ቆይታችሁ ተመለሱ ማለት ነው፡፡

ይጀምራሉ፡፡ ነገር ግን የዝናቡ ሁኔታ ለበራይ አጥጋቢ አልነበረም፡፡ በመሆኑም መሬቱ እየደረቀ መሄድ ሲጀምር ውኃ ከጉድጓድ እየተቀዳ በጀሪካን እያመላለሱ እርሻውን በማርከፍከፍ አበራይተው ጤፉን ለመዝራት ችለዋል፡፡ በእነዚህና የመሳሰሉትን ተግባራት በመስክ ምልከታ ወቅት ያየኋቸው ተግባራት ናቸው፡፡ ይህን ምልከታ አጠናቅቄ ስሰናበታቸው አቶ ፈንቴ የነበረባቸውን ስጋት ሳይደብቁ እንዲህ አሉኝ "ግብርናዎችን መስለሽኝ በመስመር ዝራ ትይኛለሽ ብዬ ፈርቼ፡፡ ያልሽኝን አላመንሁም፡፡ ኋላ ዳኜ (በመረጃ ስብሰባ ወቅት ረዳት ሆኖ ሲያግዘኝ የነበረና የዚያው አካባቢ ልጅ) ቢነግረኝ ነው ያመንሁ አሉኝ፡፡" ከዚህ ልምድ የተረዳሁት ነገር ቢኖር የመስክ ስራ አልጋ ባልጋ አለመሆኑን ነው፡፡

### 1.8.3. ተግዳሮቶች

ከላይ እንደተገለጸው የመስክ ስራ ምንም ችግር የሌለበት አልጋ ባልጋ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም፡፡ የተለያዩ ችግሮች ያጋጥማሉ፡፡ እኔም መስከኛ ነኝና በዚህ ችግር ውስጥ ማለፌ አልቀረም፡፡ በተለይም ወቅቱ የአምስተኛ ዙር አገራዊ ምርጫ የሚካሄድበት ስለነበር የሚከተሉት ችግሮች አጋጥመውኛል፡፡

- በየቢሮው የሚገኙ ሰራተኞች ለስብሰባና ለቅስቀሳ ወደ ተለያዩ ቀበሌዎች በመውጣታቸው ምክንያት መረጃ የሚሰጡ ሰራተኞችን በቢሯቸው ማግኘት እጅግ አስቸጋሪና ጊዜን የሚወስድ መሆኑ፣
- ቁልፍ መረጃ አቀባዮችም በስብሰባ ምክንያት፣ እንዲሁም መረጃውን በመስጠታቸው ምክንያት ችግር የሚፈጠርባቸው እየመሰላቸው በቀጠሮ ያለመገኘት፡፡ ቢገኙም የተለያየ ምክንያት በመፍጠር እንዳልተመቻቸው መግለጽ፣ መረጃ የሚሰጡትም ቢሆኑ የተሟላ መረጃ ለመስጠት አለመቻል፣
- ከወቅቱ የፖለቲካ ሁኔታ ጋር በማያያዝ ልክ እንደ ተቀዋሚ ፓርቲ አባል በመቁጠር ምን ልታደርጊው ነው? ለምን ፈለግሽው? ወዘተ. በማለት መረጃውን ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆን፣

- መረጃውን በመስጠታቸው ምክንያት ከመንግስት የሚያገኙትን ጥቅማ ጥቅም እናጣለን ብሎ ማሰብ፣
- ገበሬውን ለቃለ-መጠይቅ በወቅቱ ለማግኘት አለመቻል፤
- በዘር ወቅት በብተና የሚዘሩት ገበሬዎች እንዳይከሰሱ/እንዳይቀጡ በመፍራት ለምልከታው ፈቃደኛ ያለመሆን፣
- ስማቸውን ለመናገር ፈቃደኛ ያለመሆን፣
- በመቅረጸ ድምጽም ሆነ በካሜራ ለመቀረጽ ፈቃደኛ ያለመሆን፣

እነዚህ በመረጃ አሰባሰብ ወቅት በመረጃ አቀባዮች ያጋጠሙኝ ፈታኝና አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲሆኑ፤ ሌላው ደግሞ በክፍለ ትምህርቱ በፎክሎር መርሃ ግብር በሶስተኛ ዲግሪ የተሰሩ ሚሚያ የጥናት ወረቀቶች ቤተመጻህፍት ውስጥ በወቅቱ ያለመግባት/ ያለመኖር ናቸው፡፡

### 1.8.4. የተወሰዱ መፍትሄዎች

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች በሚከተሉት መንገዶች ለመፍታት ተሞክሯል፤

- በተደጋጋሚ ወደ ቢሮ በመሄድ በምሳ ሰአታቸውና ከስራ ሰአት ውጪ ትብብራቸውን በመጠየቅ፣
- የጥናቱን ዓላማ በተደጋጋሚ በማስረዳት፣
- ጥናቱ ከምርጫና ከፖለቲካ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የሌለው መሆኑን በመግለጽና በማግባባት፣
- በቀጠሮ ያልተገኙትን ያለመሰልቸት በተደጋጋሚ ሙከራ ማድረግ፤
- ስማቸውን ለመናገር ፈቃደኛ ያልሆኑትን መረጃውን ብቻ በመውሰድ፤
- ከጥናት ቀበሌዎች አንዱ በመምህርነት የሰራሁበት በመሆኑ እንዲሁም በወረዳ ከተማውም የሰራሁ በመሆኔ ያንን በመግለጽና አመኔታቸውን በማግኘት፣
- በአብዛኛው የእረፍት (የበአላት) ቀናትን በመጠቀምና በሚገኙበት ቦታ ለምሳሌ ቤተክርስቲያን፣ በቁጠባ መሰብሰቢያቸው ቀን እና ብድር በሚመልሱበት፣ ለቅስቀሳ በሚሰበሰቡበት ቦታ እና ቀን በመገኘት፣

- መረጃ በመስጠታቸው ምክንያት ምንም ዓይነት ችግር ነገር እንደማይደርስባቸው በመንገር፣ ችግሩን ለመቅረፍ ችያለሁ፡፡

## 1.9. የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ በስምንት ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን በምዕራፍ አንድ በመግቢያው ክፍል የጥናቱን ዳራ ስለጥናቱ ምንነት መጠነኛ ማብራሪያ የተሰጠበት ሲሆን ይህንን ጥናት ለማጥናት አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች፣ ጥናቱ ቢጠና አስፈላጊነቱ እስከምን ድረስ እንደሆነ፣ የጥናቱ አብይና ዝርዝር ዓላማ፣ ፋይዳው፣ ውሱንነቱ እና የጥናቱ ሥነ ምግባር፣ ምቹ ሁኔታ፣ ተግዳሮቶችና መፍትሄዎቻቸው የሚሉትን ንኡሳን ክፍሎች አካቶ ይዟል፡፡

በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝትና ጽንሰ ሀሳባዊ ዳራ በሚለው ምዕራፍ ስር በተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት ስር በአገር ውስጥና በውጭ አገር አጥኚዎች በባህላዊ የግብርና ዕውቀት ላይ የተሰሩ ጥናቶች የተካተቱ ሲሆን በጽንሰ ሀሳባዊ ዳራ ስር ደግሞ የፎክሎር ጽንሰ ሃሳብ፣ የባህላዊ ዕውቀት ስያሜና ምንነት፣ የባህላዊ ዕውቀት የሚያካትታቸው ነገሮች፣ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ምንነት፣ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ባህሪያትና ዓይነት፣ የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን መጠቀም ለምን አስፈለገ እና ወቅቶች የሚሉት የጽንሰ ሀሳባዊ ብያኔ ቀርቦበታል፡፡

በምዕራፍ ሶስት የአጠናን ስልትና ዘዴዎች፣ በሚለው ስር የጥናቱ አይነት፣ ለጥናቱ ግብአት የሚሆኑ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ የመረጃ አቀባይ አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ እይታዎች፤ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች፣ የማህበራዊ ሥነ-ዕውቀት፣ የማህበረሰብ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ፣ ሥነ-ፋይዳ ንድፈ-ሃሳብ፣ ተምሳሌታዊ ትንተናና አውዳዊ ትንተና የሚሉትን ይዟል፡፡

በምዕራፍ አራት የቀረበው አካባቢያዊ ዳራ ሲሆን ጥናቱ የሚከናወንበት ዞን መልክዓ ምድራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ሁኔታ፣ እንዲሁም የተጠኚው የጓጉሳ ሽኩዳድ

ወረዳ ዳራ መልካምድራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበረሰባዊ ሁኔታና ባህላዊ አደረጃጀቶች የሚሉት ርዕሶች ተካተዋል፡፡

በምዕራፍ አምስት የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ትንተና በሚለው ስር የእርሻ መሳሪያዎች፣ በልግ፣ ክረምት፣ ጥቢ፣ መኸር እና ልማዶችና እምነቶች በሚሉት ክፍሎች ከመስክ በተገኘው መረጃ መሰረትነት መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

በምዕራፍ ስድስት የባህላዊ ግብርና ዕውቀትና ተስተላልፎ ትንተና በሚለው ስር የባህላዊ ግብርና ዕውቀት አይነት የማህበረሰብ፣ የቡድን እና የግለሰብ ዕውቀትና የዕውቀት ተስተላልፎ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

በምዕራፍ ሰባት ደግሞ ቀጣይነት፣ ለውጥ፣ የለውጡ መንስኤዎች፣ (ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ የሚሉት) ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በምዕራፍ ስምንት ማጠቃለያና ይሁንታን በመጨረሻም የዋቢ መጻህፍት ዝርዝርና ልዩ ልዩ አባሪዎች ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ የሆነው የጓጉሳ ሽኩዳድ ገበሬዎች የባህላዊ ግብርና ዕውቀት መነሻ ሃሳብ የቀረበበት፣ ጥናቱን ለማጥናት አነሳሽ የሆኑ ጉዳዮች፣ የዚህ ጥናት መጠናት አስፈላጊነትና ፋይዳ፣ ጥናቱን ወደ ግብ ሊያደርሱት የሚችሉ ዓላማዎች፣ ጥናቱ የሚጠናበት የይዘት፣ የቦታና የጊዜ ወሰን፣ እንዲሁም በጥናቱ ወቅት አጥኚው የሚከተላቸው ሥነ-ምግባሮች፣ የመስክ ልምድ፣ ተግዳሮቶችና የተወሰዱ መፍትሂዎች፣ ጥናቱ የተዋቀረበት አጠቃላይ ክፍሎች በዝርዝር የቀረቡበት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳና ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ

ይህ ምዕራፍ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎችን የያዘ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ የቀረበበት ነው፡፡ በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ቀርቧል፡፡ በጽንሰ-ሃሳብ ማዕቀፍ የፎክሎር ጽንሰ-ሃሳብ፣ የባህላዊ ዕውቀት ስያሜና ምንነት፣ የባህላዊ ዕውቀት የሚያካትታቸው ጉዳች፣ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ምንነት፣ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ባህሪያትና አይነት፣ የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን መጠቀም አስፈላጊነት የእርሻ መሳሪያዎችና ወቅቶች የሚሉት ጽንሰ ሀሳቦች እና የምዕራፉ ማጠቃለያ በቅደም ተከተል የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡

## 2.1. የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ

በዚህ ንዑስ ርዕስ የቀረቡት ጥናቶች በባህላዊ ግብርና ዕውቀት ላይ የተሰሩና ከዚሁ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ስራዎች ናቸው፡፡ እነዚህም በሶስት ተከፍለው ተመርምረዋል፡፡ ምደባቸው በሚያነሱት ይዘት ተቀራራቢነት ያላቸውን ወደ አንድ በማምጣት የተደረገ ነው፡፡ ምደባውም የመጀመሪያው ክፍል ባህላዊ ዕውቀት ከእርሻ፣ ባህላዊ ዕውቀት ከሀብት አያያዝ፣ ፎክሎርና ግብርና የሚሉት ናቸው፡፡ ጥናቶችም በተመደቡበት ክፍል በሚከተለው መንገድ ተቃኝተው ቀርበዋል፡፡

### 2.1.1. የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ከእርሻ አኳያ

በዚህ ስር የተቃኙት ጥናቶች ስምንት ሲሆኑ፣ ባህላዊ የሥነ ምህዳር ዕውቀት፣ ባህላዊ የእርሻ ቦታዎች ምደባ፣ ባህላዊ የአፈር ጥበቃ፣ ባህላዊ የግብርና ዘዴ እና የመስኖ እርሻ ላይ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶች ናቸው፡፡ ጥናቶቹ በተለያዩ ሀገራትና የትምህርት መስኮች የተሰሩ ሲሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር ቀረቤታ ያላቸው በመሆናቸው የተቃኙ ናቸው፡፡

Henry (2012) "The Use and Role of Indigenous Knowledge in Small-Scale Agricultural Systems in Africa: the Case of Farmers in Northern Malawi"

የሚለው ስራቸው ዋና ዓላማ ባህላዊው፣ አካባቢያዊው ወይም የተለመደው የሥነ-ምህዳር ዕውቀት የትኛው ነው? የሚለውን ማሳወቅ ነው፡፡ ይህን በሚከተለው መንገድ አጥንተውታል፡፡ በአካባቢው የሚገኘው የእርሻ ቦታ ሶስት አይነት ሲሆን በቤት አጠገብ የሚገኝ፣ በቤት አካባቢ የሚገኝና ከቤት አካባቢ ከ100 ሜትር እስከ 20 ኪሎ ሜትር ራቅ ያለ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ እነዚህም ቦታዎች በአካባቢው ስያሜ በቅደም ተከተል "Dimba, Khonde, Munda Ukulu"[9] በመባል የሚታወቁ ሲሆን እያንዳንዱም ስያሜ የተለየ ትርጉም አለው በማለት ይገልጻሉ፡፡ አያይዘውም ገበሬው የአፈር አይነትን እንደለምነቱ ሁኔታ የሚገልጽበትን ባህላዊ ዕውቀት፣ (1) በተከታታይ በሚታረስበት የጊዜ ርዝመት፣ (2) ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ እና (3) አፈር በጣቶቹ መካከል በመያዝና በመዳሰስ በባህላዊ መንገድ መለየት ይችላል በማለት በሶስት ደረጃ መድበውታል፡፡

Henry (2012) ከዚህም በተጨማሪ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው ውስጥ የባህላዊ ዕውቀት ሚና በእርሻ ደረጃ፣ የእርሻ ወቅቶችን መለየት፣ አፈራርቆ መዝራት፣ በመስኖ መጠቀም፤ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የባህላዊ ዕውቀት ሚና በደን አጠባበቅ፣ ባህላዊ ዕውቀት በችግር ፈቺነት፣ ባህላዊና ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ባህሪያት፣ ባህላዊ የግብርና ዕውቀት ለእድገት ያለው አግባብነት፣ የሳይንሳዊ ዕውቀትና ባህላዊ የግብርና እውቅት ወሰንና ድንበር የሚሉትን ጉዳዮች በስፋት ዳሰዋል፡፡ በጥናቱ በስተመጨረሻም ባህላዊ ዕውቀት በተፈለገው መንገድ እየተላለፈ አይደለም፤ ለማረጋገጥ የተሞከረው ግን ባህላዊ የግብርና ዕውቀት ለእድገት ሙሉ በሙሉ ዋጋ አለው በማለት ጥናታቸውን አጠቃለዋል፡፡

የHenry ጥናት ከባህላዊ ዕውቀት በተጨማሪ ሳይንሳዊ ዕውቀትንም በጥናቱ የተመለከተ ሲሆን የጥናት ዘዴውም መጠናዊ ጥናት ዘዴን የተከተለ በመሆኑ እንለያያለን፡፡ Henry ጥናቱን ያጠናበት መንገድ መጠናዊ ከመሆኑ በተጨማሪ እኔ ጥናት ሳይንሳዊ ዕውቀትን አይመለከትም፡፡

[9] የቃሎችን ትክክለኛ ትርጉም ማግኘት ስላልቻልሁ ቃሉን በተገኘበት ቋንቋ ለማቀመጥ ተገድጃለሁ፡፡

Habtamu (2011) "Farmers: Indigenous Agricultural Knowledge Practice in South East Zone of Tigray" በሚለው ጥናታቸው በባህላዊ የግብርና ዕውቀት ስለ አፈርና ውኃ ጥበቃ፣ ሰለ ሰብል አይነቶች፣ በሰብል ላይ ተጽኖ የሚያሳድሩ ነገሮችንና መከላከያ መንገዶችንም አካተዋል፡፡ በዚህም መሰረት በባህላዊ የግብርና ዕውቀት ሰብልን በማፈራረቅ፣ ብስባሽንና የሰብሎችን ቅሬት በማሳ ላይ በመጨመር፣ ቶሎ የሚበሰብሱ የተክሎችን ቅጠል በማሳ ላይ በማልበስ፣ የአፈርን ለምነት የሚጠብቁ ሲሆን በውኃ መጠረግን ለመከላከልም የውኃ መውረጃ፣ የውኃ መንገድ፣ በማሳና በማሳ መካከል ባዶ ቦታ በመተውና በላዩ ላይ ሳር በማብቀል የአፈርን በውኃ መጠረግ ይከላከላሉ ይላሉ፡፡ የሰብልን አይነት ለመለየትም በቀለሙ፣ ለመድረስ በሚፈጀው ጊዜ፣ በሚበቅልበት የአፈር አይነት፣ በሽታን፣ አረምንና ድርቅን በመቋቋም አቅሙ፣ በገበያ ላይ ባለው ተፈላጊነት ይለዩታል በማለት ይገልጻሉ፡፡ እንዲሁም አፈራርቆ በመዝራት፣ የመዘሪያ ጊዜውን በመለየት፣ በአንድ ማሳ ሁለትና ከዚያ በላይ ሰብሎችን በመዝራት፣ የተለያዩ ባህላዊ ነገሮችን ዘሮቹ ላይ በመቀባት ሰብልን ከበሽታ ይከላከላሉ በማለት ገልጸዋል፡፡

የHabtamu ጥናት ትኩረት ደግሞ በአፈርና ውሀ ጥበቃ፣ በሰብል አይነቶች መለያ ዘዴ እና ከበሽታ መከላከያ ዘዴዎች ላይ ነው፡፡ በጥናታቸው ውስጥ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ለይተው አያሳዩ እንጂ የሰብል መለያ ዘዴዎች ብሎ ያስቀመጣቸው እውቀቶች ፎክሎራዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እንዲሁም በጥናት ዘዴያችንም ልዩነት አለን፤ የእሱ የጥናት ዘዴ መጠናዊ ሲሆን የእኔ የጥናት ዘዴ ደግሞ አይነታዊ ነው፡፡

Polthanee (2010) "Indigenous Agricultural Knowledge-A Sample Practice in North east Thailand" በሚለው ጥናታዊ ስራቸው ዋና ዓላማ የታይላንድ ገበሬዎችን ባህላዊ ዕውቀት አጥንተው አስተዋውቀዋል፡፡ በሰሜን ምስራቅ ታይላንድ ባህላዊ የግብርና ዕውቀትና ልምድን አስመልክቶ የመሬት ዝግጅት፣ ዘርን ማጎንቆል (ዘር ከመዘራቱ በፊት ከ1-2 ቀን በውኃ መዘፍዘፍ)፣ ባህላዊ ዘርን ማቆያ ዘዴ (ካሳቫ ከመተከሉ በፊት ለ2 ወር ያህል ጥላማ ቦታ ላይ ማቆየት)፣ ቅርንጫፎችን ማጥፋት

(ተክሉ እንዲወፍርና አጭር እንዲሆን)፣ አበባውን መለየት፣ የቅጠሎችን አካባቢ መቀነስ (ካሳቫ ቅጠሉ ሲበዛ ስሩ ይቀንሳል)፣ የአፈሩን ጥራት ማረጋገጥ፣ በተባይ መበላትን መቀነስ፣ በአንድ ማሳ ላይ የተለያዩ አዝርእትን መዝራት የታይላንድ ገበሬ ዕውቀት ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡

Polthanee ጥናት ጋር በመሬት ዝግጅት ብንመሳሰልም ዘር ከመዘራቱ በፊት በተለያየ ዘዴ በማገንቆል መዝራት በአፈር ውስጥ የሚቆይበትን ጊዜ እንደሚቀንስ በጥናታቸው አሳይተዋል፡፡ ይህን የእኔ ጥናት አይመለከትም፤ ከዚህም በተጨማሪ የጥናት ዘዴያቸው በሙከራዊ ላይ የተመሰረተና በዋናነት ዘር ከመዘራቱ በፊት በዘሩ ላይ በሚከናወኑ ድርጊቶች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የእኔ ጥናት ግን በአይነታዊ የጥናት ዘዴ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የማህበረሰቡን የባህላዊ ግብርና ዕውቀት በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በመጠቀም መሰብሰብና መተንተን ነው፡፡

Haimanot (2011) "An Ethno-botanical Study of Useful Plants of the Farming Site in Gozamen Woreda, East Gojjam Zone of Amhara Region, Ethiopia" በሚለው ጥናታቸው ባህላዊ የአፈር ምደባን፣ ባህላዊ የእርሻ ቦታ ስያሜን፣ ባህላዊ የተክሎችን ምደባና ባህላዊ የወቅቶች ምደባን አሳይተዋል፡፡ በዚህም መሰረት የአካባቢው አርሶ አደር በጓሮ እና በማሳ ቦታዎች ሰብልን በማምረት እንደሚተዳደር ገልጸው በአካባቢው የሚገኘውን የአፈር አይነት በባህላዊ ምደባ እንደሚከተለው በስድስት መድበዋቸዋል፡፡ (1) **ዋልካ**፡- የሚታረስበት ወቅት መስከረም ሲሆን በውስጡ በጣም ብዙ ውኃ የመያዝ አቅም ያለው ነው፡፡ (2) **ቦረንቅ**፡- ለእርሻ አገልግሎት የማይውል የአፈር አይነት ነው፡፡ (3) **ደባይ**፡- በነሐሴ የሚታረስ መሬት ሲሆን ውኃ የመያዝ አቅም ያለው የአፈር አይነት ነው፡፡ (4) **ቦረቦር**፡- ከሰኔ- ሐምሌ ባለው ወቅት ይታረሳል፤ ቀላል አፈር ሲሆን በንፋስና በዝናብ የመወሰድ ኃይሉ ከፍተኛ ነው፡፡ (5) **አሻልማ**፡- ሐምሌ ላይ ይታረሳል፤ አፈሩ ከባድና በአንጻሩም ለም መሬት ነው፡፡ (6) **ዳልቻ**- ሰኔ ላይ የሚታረስ ሲሆን ጥልቅነት የሌለውና ለምነቱም አነስተኛ ነው፡፡ በማለት በጥናታቸው አስፍረዋል፡፡

Haimanot (2011) የእርሻ ቦታዎችን በባህላዊ ምደባ (1) ጓሮ- በቤት አጠገብና አካባቢ የሚገኙ ቦታ ሲሆን በሚገባ የቀለዘ፣ የተለያዩ አይነት እጽዋቶችና ተክሎች፣ ሰብሎች በአንድ ላይ የሚይዝና በመጠን አነስተኛ ነው፡፡ አብዛኞቹ ለመድሃኒትነት የሚውሉ እጽዋትም በዚሁ ቦታ የሚበቅሉ ናቸው፡፡ (2) ማሳ- ከቤት በርቀት የሚገኝና ዋና የእርሻ መሬት ሲሆን ብዙም ለም ያልሆነ አንድ አይነት ሰብልን የሚይዝ በስፋቱ ከጓሮ የሚበልጥ መሬት ነው፤ በማለት ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ባህላዊ የተክሎች ምደባን ሲገልጹ ቁጥቋጦ፣ ዛፍ፣ ሐረግና አረማሞ ናቸው ይላሉ፡፡

ባህላዊ የወቅቶች ምደባ ክረምት፣ መኸር፣ በጋና በልግ ተብለው የሚከፈሉ ሲሆን (1) **ክረምት**፡- ከሰኔ እስከ መስከረም ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ሆኖ ለገበሬው ከፍተኛ የስራ ጫና ያለበትና የምግብ እጥረትም የሚከሰትበት ወቅት ነው፡፡ (2) **መኸር**፡- ከጥቅምት እስከ ታህሳስ ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ሆኖ ለገበሬው ሁለተኛው የስራ ጫና ወቅት ነው፤ ሰብል የሚሰበሰብበት ጊዜ ስለሆነ፣ (3) **በጋ**፡- ከታህሳስ መጨረሻ እስከ የካቲት አጋማሽ ያለውን ጊዜ ይሸፍናል፡ ደረቅ፣ የስራ ጫና የሚቀንስበትና የፈንጠዝያ ወቅት ነው፤ (4) **በልግ**[10]፡- ከየካቲት አጋማሽ እስከ ግንቦት ያለው ወቅት ሲሆን ለገበሬው ሶስተኛው የስራ ጫና ወቅት ሆኖ ማሳዎች ለዘር የሚዘጋጁበትና አንዳንድ ሰብሎችም የሚዘሩበት ወቅት ነው በማለት በጥናታቸው ገልጸዋል፡፡

የHaimanot ጥናት የእርሻ ቦታዎችና የአፈር አይነቶችን መዳሰሱ የሚያመሳስለን ሲሆን የእኔ ጥናት በቀጥታ የእሱን ስራ የሚመለከት ሳይሆን በተጓዳኝ የአፈር አይነቶችን ከአየር ጠባዩና ከሰብል ምርቱ ጋር በማያያዝ፣ እንዲሁም ወቅቶችን ከማሳ ዝግጅቱ፣ ከአዝርዕቱ ከገበሬው የስራ እንቅስቃሴ ጋር በማጣመር የገበሬውን ባህላዊ የግብርና ዕውቀት ከማሳ ዝግጅት እስከ ሰብል ስብሰባ ድረስ ያለውን፣ የዕውቀት ተስተላልፎ ያያል፣ ከባህላዊ የግብርና ዕውቀት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የቃኘ ነው፡፡

[10] አጽንኦቱ የኔ ነው፡፡

Desalegn (2006) "The Role of Indigenous Knowledge and Water Harvesting in Sustainable Agricultural System in Tigray" በሚለው ጥናታዊ ጽሁፋቸው ውስጥ ጥናቱን ባካሄዱበት አካባቢ ለግብርና ምርት መቀነሰና ለድርቅ መከሰት፣ እንዲሁም ለአፈር መከላት ምክንያት ተለዋዋጭ የሆነ የዝናብ መጠንና ፈጣን የሆነ የህዝብ ቁጥር እድገት ነው ይላሉ፡፡ በትግራይ የዝናቡ መጠን ተለዋዋጭና የእርጥበት መጠኑ በጣም አነስተኛ እንደሆነ ገልጸው የአፈሩ መከላትና የመሬቱ ተሰንጣቂ መሆን ለአነስተኛ የውኃ ማቆር እንኳን አመቺ አይደለም በማለት ይገልጻሉ፡፡ ይሁን እንጂ በባህላዊ ዕውቀት የአካባቢው ማህበረሰብ የአፈሩን ጠባይ የመለየት፣ የመስኖ ውኃ አያያዝና የመስኖ ብልሃት ከፍተኛ ዕውቀት አለው ይላሉ፡፡

ሥነ-ውኃዊ ሁደትን በመጠቀም አነስተኛ መስኖን ለቤተሰብ መተዳደሪያነት መገልገል ያለውንም አስተዋጽኦ ይገልጻሉ፡፡ ገበሬው ባጠቃላይ ስለአካባቢው ሰፊና የዳበረ ዕውቀት ያለው መሆኑን በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡ በመጨረሻም የባህላዊና የሳይንሳዊ ዕውቀትን ግንኙነት ወደ ፖሊሲ ድንጋጌ ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ እንደሆነ ገልጸው ጥናታቸውን አጠቃለዋል፡፡

ይህ ጥናት በባህላዊ የግብርና ዕውቀት ላይ የተሰራ መሆኑ ቢያመሳስለንም Desalegn ያደረገው ጥናት ትኩረቱ በአካባቢው ስላለው በግብርና ምርት መቀነስና ለድርቅ መከሰት፣ እንዲሁም ለአፈር መከላት ምክንያቶች ላይ ሲሆን ይህንን ለመከላከል መደረግ በሚገባው ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ገበሬው የአፈር አይነቱን የሚለይበት ባህላዊ ዕውቀት እንዳለው ይግለጹ እንጂ እንዴትና በምን ሁኔታ ለሚለው ግልጽ የሆነ ነገር በጥናታቸው ውስጥ አላስቀመጡም፡፡ እንዲሁም ዕውቀት እንዴት እንደሚተላለፍና እንደሚቀጥልም ያሳዩት ነገር የለም፡፡ የደሳለኝ ጥናት በማህበረሰቡ ውስጥ በመገኘት ባህሉን፣ የአሰራር ልምዱን እና ነባራዊ ሁኔታዎችን ያላማከለና በቁጥር ቀመር ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የእኔ ጥናት ይህንን ክፍተት ይደፍናል የሚል እምነት አለኝ፡፡

Negash (2005) "Indigenous Technical Knowledge of Farmers in North Shewa: Soil and Water Conservation and Pest Control" በሚለው ጥናታቸው እንደገለጹት የገበሬውን ባህላዊ የአፈርና ውኃ አጠባበቅ ልምድ በአስራአንድ ነጥቦች አስቀምጠዋል፡፡ እነርሱም (1) የውኃ አባት (ጎርፍ መቀልበሻ) (2) ዋገምት (በይ መቀልበሻ)፣ (3) በይ፣ (4) የድንጋይ እርከን (5) አፈር መጠበቂያ (6) ድንበር ሽለታ (ድንበር መተው)፣ (7) የተለያየ አዝርእትን መጠቀም (8) እርከን መሻር (9) ደገሌ (10) የድንጋይ እርከንና አትክልት እና (11) የድንጋይ ቅትር ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ገበሬው በእርሻ ቦታ ላይ የሚገኙ ሰብልን የሚያጠፉ ነፍሳትን በባህላዊ መንገድ በእጅ በማንሳት፣ በማታለያ ምግብ በመጠቀም፣ የተክሉን አገዳ በማጉበጥና በጭጋጋማ ጭስ በመጠቀም የተባይ ቁጥጥርን ያደርጋል፤ በማለት በጥናታቸው ውስጥ አስፍረዋል፡፡

የNegash ጥናት የተመለከተው ባህላዊ የአፈርና የውኃ አጠባበቅ መንገዶችንና የተባይ መከላከያ ዘዴን ነው፡፡ ይህ የእኔ ጥናት ትኩረት አይደለም፡፡ በጥናት አይነትም ቢሆን እንለያያለን፡፡ የጥናት ዘዴውም መጠናዊና ሙከራዊ ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ የኔ ጥናት ትኩረት ግን የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ከማሳ ዝግጅት እስከ ሰብል ስብሰባ ድረስ ያለውን ዕውቀት፣ የዕውቀትተስተላልፎና ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የሚመለከት ይሆናል፡፡

Shoko (2012) "Indigenous Weather Forcasting System: A Case Study of the Biotic Weather Forcasting Indicators for Wards 12 and 13 in Meringa District, Zimbabwe" በሚለው ጥናታዊ ጽሁፋቸው የአካባቢው ማህበረሰብ በሶስት መንገድ የአየር ትንበያ ተግባራትን እንደሚያከናውን አጥንተዋል፡፡ የአየር ትንበያው የሚደረገውም (1)በወፎች፣ (2)በፍጡራን ወይም በእንስሳት እና (3)በተክሎች በመጠቀም ነው ይላሉ፡፡

1. **በወፎች፡-** Lapwing[11] የምትባለው ወፍ እንቁላሏን በሚዳው የላይኛው ክፍል ከጣለች ወቅቱ የዝናብና የምርት ወቅት ነው ተብሎ ይታመናል፤ በተቃራኒው

[11] Lapwing , Cuckoo የወፍ አይነት (መጠሪያ ) ነው፡፡

እንቁላሏን በሚጻው ዝቅተኛ ስፍራ ከጣለች ደግሞ አነስተኛ ዝናብ ወይም ድርቅ ይሆናል ተብሎ በማህበረሰቡ ይታመናል በማለት በጥናታቸው ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም በጥናታቸው Cuckoo በህዳር መጀመሪያ ላይ ዝማሬ ካሰማች የዝናብ ወቅት ነው ይባላል በማለት ገልጸዋል፡፡

2. **በፍጡራን ወይም በእንስሳት**፡- የጉርጦችና የእንቁራሪቶች ጩኸት፣ የግመል የታችኛው የእግር ክፍል እብጠት መጨመር ለዝናብ መምጣት ምሳሌ ይደረጋሉ ብለዋል፡፡
3. **በተክሎች**፡- ቀድመው የሚበቅሉና የማይበቅሉ፣ ተክሎችን በመለየት የአየር ንብረትን እንደሚተነብዩ ይገልጻሉ፡፡ ለዚህም በትንበያው ወቅት ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ነገሮች ከላይ በቀረበው መንገድ ከ1-3 በቅደም ተከተል አስቀምጠዋቸዋል፡፡

በዚህ ባህላዊ የአየር ትንበያም ተመስርተው የእርሻ መሳሪያንና ዘርን ያዘጋጃሉ፤ የዘር ምርጫን፣ የዘርና የእርሻ ጊዜን፤ የአመራረት ዘዴንና የዘር አቀማመጥን እንዲወስኑ ያስችላቸዋል በማለት በጥናታቸው አስፍረዋል፡፡ በሌላም የአሳ ማስገሪያ ጊዜያቸውን፣ በየቀኑ ትኩረት የሚሰጧቸውን ነገሮች ይወስናሉ በማለት አስፍረዋል፡፡ በዚህም መሰረት ይህን ዕውቀት ሰንዶ ማስተላለፍና ከሳይንሳዊው ዘዴ ጋር ማዋሃድ ጠቃሚ ነው በማለት የሰብሎች የተባይ ማጥፊያ መድሃኒቶችና ዘዴዎች በአግባቡ ሊሰበሰቡና ሊሰነዱ ይገባል በማለት ጥናታቸውን አጠቃለዋል፡፡

የShoko ጥናት በባህላዊ የግብርና ዕውቀት ላይ የተመሰረተ መሆኑ የሚያመሳስለን ጉዳዮች አሉ፡፡ የሾኮ ጥናት ባህላዊ የአየር ትንበያ ላይ የተሰራ ቢሆንም ስለ ዕውቀት መንስኤ፣ መተላለፊያ መንገድ እና ስለ ባህሉ ያለው ነገር የለም፡፡ ምክንያቱም ከፎክሎር አንጻር ያልተጠና በመሆኑ ባህልን (አመራረት፣ የዕውቀት አስተላለፍ፣ የአኗኗር ዘይቤያቸውን) አልተመለከተም፡፡ ስለዚህ ከእኔ ጥናት ጋር እንለያያለን፡፡ የእኔ ጥናት የአየር ትንበያ ዘዴዎችን በቀጥታ አይመለከትም፡፡ ሆኖም ግን ከአስተራረስ

ዘዴያቸውና ከዘር ወቅታቸው እንዲሁም ከዝናብ አመጣጥ ጋርና ለዘርና ለጉልጓሎ ከሚሆን ጊዜ ጋር ተያይዞ የሚታይ ነገር ይኖራል፡፡

Mohapatra (2009) "Tribal Pest Control Practices of Tamil Nadu for Sustainable Agriculture" የሚለው ጥናታዊ ስራቸው ባህላዊ የተባይ መከላከያ ዘዴዎች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በዚህም የሩዝን፣ የቅባት እህልን፣ የክምችት እህልንና የአትክልት ተባይን ለማጥፋት የሚጠቀሙት የተለያዩ እጽዋቶችን ከእንስሳት ተዋጽኦ፣ ከብቶች ሽንትና እዳሪ ጋር እና ከጋዝ ጋር በመቀላቀል፣ በመቀመምና ባህላዊ መድሃኒት በማዘጋጀት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ የVatex[12] ቅጠልንና ቅቤው የወጣለትን ወተት በመቀላቀል፣ Jatorafa ቅጠልንና የላም ሽንትን በመቀላቀል፣ Adothoda ቅጠልንና የከብቶችን እዳሪ፣ Agave ቅጠልንና ነጭ ጋዝን በመቀላቀል ይጠቀማሉ፤ በማለት ይገልጻሉ፡፡ Mohapatra እንደሚሉት ይህን የሚያደርጉትም በቀላልና በቅርበት ስለሚያገኙትና እርካሽም ስለሆነ ነው ይላሉ፡፡ በጥናታቸው በስተመጨረሻም ሲያጠቃልሉ ሁሉም በባህላዊ ዕውቀት የሚዘጋጁ ባህላዊ የተባይ መከላከያ መድሃኒቶች ከሳይንሳዊው ጋር የሚዋሃዱበት መንገድ ቢመቻች በማለት ጥናታቸውን አጠቃለዋል፡፡

ይህ ጥናት በባህላዊ የግብርና ዕውቀት ላይ የተሰራ በመሆኑ ቢያመሳስለንም የMohapatra ጥናት የተክሎች ባህላዊ የተባይ መከላከያ መድሃኒት ላይ በማተኩሩ የምንለያይ ሲሆን የጥናት ዘዴውም ሙከራዊ ጥናት ነው፡፡ የእኔ ጥናት የሚያተኩረው ከማሳ ዝግጅት እስከ ሰብል ስብሰባ ድረስ ያለው የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ላይ ነው፡፡ ጥናቱ የፎክሎር ጥናት ዘርፍም በመሆኑ ከግብርናው ጋር አብረው የሚከወኑ ልማዶችን፣ እምነቶችን፣ ሥነ-ቃሎችን በመተንተን ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ የጥናት ዘዴዩም አይነታዊ በመሆኑ እንለያያለን፡፡

[12] Vatex, Jatorafa እና Adothoda ቀጥተኛ የአማርኛ ትርጉማቸውን ማግኘት ስላልቻልሁ በጥናቱ ውስጥ ያገኘሁትን የእንግሊዝኛ ቃል ተጠቅሚያለሁ፡፡

### 2.1.2. የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ከሀብት አያያዝ

በዚህ ስር የተቃኙት ጥናቶች ስድስት ሲሆኑ፣ ባህላዊ የሀብት አስተዳደር፣ ባህላዊ የመሬት አጠባበቅ፣ ባህላዊ የተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ፣ ባህላዊ የሥነ ምህዳር አጠባበቅ፣ ባህላዊ የንብ አያያዝ ላይ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ጥናቶች በተለያዩ ሀገራትና የትምህርት መስኮች የተሰሩ ጥናቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ጥናቶች ከኔ ጥናት ጋር ቀረቤታ ያላቸው በመሆኑ የተቃኙ ናቸው፡፡

Bekalu (1994) "Traditional Agricultural Practice and Resource Management among the Agew of Gojjam" በሚል ስራቸው፣ ባህላዊ የሃብት አስተዳደደር፣ የእርሻ መሬት አያያዝ፣ የውኃ አጠቃቀም፣ የመሬትን ለምነትን የሚጠብቅባቸውን ዘዴዎችና የከብት እርባታን፣ የእርሻ ስራ ሃብትን፣ ባህላዊ ማህበራትንና የባህላዊ ማህበራትን ተግባራት ገልጸዋል፡፡

የ Bekalu ጥናት ትኩረት ያደረገው ባህላዊ የገጠር ማህበራት በእርሻው ተግባር ላይ እና አጠቃላይ በተፈጥሮ ሃብት አጠባበቅ ላይ ያላቸው አስተዋጽኦ እና የማህበራት ተግባራት ላይ በመሆኑ በበቃሉ ጥናት የተዳሰሱትን የማህበራት ጉዳይ ይህ ጥናት አይመለከትም፡፡

Michal (2002) "Liking Indigenous with the 'Conventional' Measures for Sustainable Land Management in the Highlands of Ethiopia: A Case Study of Digil Watershed, East Gojjam" ባህላዊ የመሬት አጠባበቅ በአርሶ አደሩ የሚከወን መሆኑን ገልጸው የመሬት አጠባበቅ የድንጋይ የውኃ መቆጣጠሪያ ግንባታ፣ ፈሰስ፣ ባህላዊ ቦይ፣ ተከብከብና አግድመት ማረስ እንዲሁም ሁለት አይነት ሰብሎችን በመቀላቀል መዝራት (inter-cropping) (ባቄላን ከገብስ ወይም ከስንዴ ጋር ቀላቅሎ መዝራት)፣ መሬትን ሀረግ በማልበስ ከአፈር መሸርሸር ለመከላከል በተበላ መሬት ላይ

የከብት ጓያ[13] መዝራት (cover-cropping)፣ በምርምር የተሻሻለን ዝርያ መዝራት (improve-crop)፣ መሬትን ማሳደር፣ ግብጦን መዝራት፣ በእንስሳት እዳሪ መጠቀም፣ ሰብልን ማፈራረቅ፣ የመሳሰሉት የመሬትን ለምነት የሚጠብቁ ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡

Michal ጥናት የተመለከተው የመሬትን ለምነት መጠበቂያ መንገዶችን ነው፤ እነዚህ ጉዳዮች በእኔ ጥናትም በተጓዳኝ የሚዳሰሱ ቢሆንም የጥናቴ ዋና ትኩረት አይደሉም፡፡ የውኃ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን የእኔ ጥናት አይመለከተውም፡፡ የእኔ ጥናት የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ከማሳ ዝግጅት እስከ ሰብል ስብሰባ ድረስ ያለውን ዕውቀት፣ የዕውቀትተስተላልፎና ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የሚመለከት ነው፡፡

Woldeselasie (2005) "Indigenous Knowledge of Shifting Cultivators and Strategies of Natural Resource Management: The case of the Gumuze in Metekel, North Western Ethiopia" በሚለው ጥናታቸው ይህ የጉሙዝ ባህላዊ ዕውቀት በተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ መሰረት ልማድ፣ እሴት፣ ሥነ-ምግባር ሲጠበቁ የኖሩት በማህበረሰቡ የተከበሩ የሀገር ሽማግሌዎች ሲሆን እነሱም ይህን ያስከብራሉ፤ ያጠናክራሉ፤ ስለዚህ የዚህ ጥናት ዓላማ የጉሙዝን የባህላዊ ዕውቀትንና የማያልቅ ሀብትና የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም እቅድና ብቃት በመትከል ለማሳየትና ለመመርመር ነው ይላሉ፡፡ ጉምዞች የእለት ኑሮአቸው በዚህ ተፈጥሮ በቸረችው ቦታ ነው፤ ጉምዞች የማፈራረቅ እርሻ፣ ማሳ መረጣን፣ ምንጠራን፣ ማረስን፣ መሬትን ማሳደር፤ መዝራት፤ ማሳው ከተመረጠ በኋላ ይጀምራሉ በማለት ገልጸዋል፡፡ ማሳውን በሚመርጡበት ጊዜ ማሳው ላይ የተቆረጠ የዛፍ ቅርንጫፍ ወይም በዛፉ ቅርንጫፍ ላይ ሳር በማቀስመጥ ሌላ ማሳ የሚፈልግ ሰው ቢመጣ ቦታው የተያዘ መሆኑን ለማመላከት የሚጠቀሙበት ባህላዊ ዘዴ ነው ይላሉ፡፡ በአብዛኛው ለእርሻ የሚመረጠው ለምና ከሸለቆ አናት ላይ ያለ ቦታ ነው፤ ቦታው ከተመነጠረ በኋላ በቀላል የእጅ መሳሪያ ለዘር

[13] ለከብት መኖነት የሚያገለግል ተክል ነው፡፡ አብብቦ አበባው ካልፈካ በስተቀር ከብቶች ሲበሉት ሆዳቸውን በመንፋት የሚገድል ነው፡፡

ይዘጋጃል፣ በዚህ መሰረትም በማሳቸው ላይ ዳጉሳን ማሽላንና በቆሎን በማፈራረቅ ይዘራሉ በማለት ገልጸዋል፡፡

ጉምዞች ከማፈራረቅ እርሻ ጎን ለጎን የጫካ ምግቦችን በመሰብሰብ፣ እሳ በማስገር፣ ከብቶችን በማርባት (በዋናነት ፍየልና ዶሮ)፣ አደን፣ ማር በመቁረጥ፣ ወርቅን በባህላዊ መንገድ በማንጠር፣ የእጅ ስራና የሀገር ውስጥ ንግድን ያከናውናሉ፡፡ ይህ ሁሉ በሕይወት ለመቆየት የሚያደርጉት ነው፡፡ በጉምዝ ለተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ባህላዊ ዕውቀት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም የተፈጥሮ ሃብት የተባረከና ከ"ያምባ"[14] የተቸራቸው እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ለዚህም በእንክብካቤ በመያዝ ለሚቀጥለው ትውልድ ማሰተላለፍ አለብን ብለው ያምናሉ ይላሉ፡፡ በመጨረሻም ለነዚህ አካባቢዎች መንግስትም ትኩረት መስጠት አለበት በማለት ጥናታቸውን አጠቃለዋል፡፡ የWoldeselasie ጥናት ጉምዞች በሕይወት ለመቆየት በሚያደርጉት አጠቃላይ የኑሮ ዘይቤ ላይ ትኩረቱን ያደረገ ነው፡፡ ጉምዞች በማሳ መረጣ ወቅት የሚጠቀሙት ባህላዊ ህግ የፎክሎር ገጽታ ነው፡ ይህ ጥናት ባህላዊ የግብርና ዕውቀትን እንጂ የአኗኗር ዘይቤን አይመለከትም፡፡

Alemu (2008) "The Use of Indigenous Knowledge for the Management of Crop Production Constraints: The Case of Awi Community in Ankesha Guagusa Woreda" በሚል በሰሩት ጥናት ውስጥ እንደገለጹት የሰብል ምርት በበርካታ የስራ ሂደት ውስጥ ማለፍ አለበት፡፡ በምርት ማምረት ትግበራው ወቅትም በሰውና በሥነ-ምህዳር አማካኝነት የተለያዩ ተጽኖዎች ይደርሳሉ በማለት ገልጸዋል፡፡ በሰው ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ምክንያት የሚደርሰው ተጽእኖ በምርምር የተገኘ ዘር እጥረትና በወቅቱ አለመድረስ፣ የሰው ሰራሽ ማዳበሪያ እጥረት፣ ጸረ- አረም፣ የተባይ ማጥፊያ፣ የእርሻ መሬት እጥረት እና የስራ አቅም እጥረት ናቸው ይላሉ፡፡

በሥነ-ምህዳር ደግሞ የመሬት መሸርሸር፣ ለምነትን ማጣት፣ የዝናብ ዘግይቶ ወይም ቀድሞ መምጣት፣ ያለወቅቱ መዝነብ፣ የመስኖ ውኃ እጥረት፣ የተክሎች ተባይና በሽታ፣

[14] ያምባ፡- አምላክ ነው ብለው የሚያምኑት ነው፡፡

ያረም ወረራና የተፈጥሮ አደጋ ናቸው ይላሉ፡፡ እነዚህንም በሰብል ምርት ላይ ተጽእኖ የሚያደርሱትን በባህላዊ የግብርና ዕውቀት የአፈር ለምነትን ለመጠበቅ ሰብልን በማፈራረቅ፣ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በመጠቀም፣ በአፈርና ውኃ ጥበቃን ትናንሽ ቦይ በመቆፈር፣ የውኃ መውረጃዎችን በማዘጋጀት፣ አረምን በመቆጣጠር፤ የሰውን የስራ አቅም ደግሞ የህብረት ስራ ዘዴን በመጠቀም ለመከላከል ጥረት አድርጓል በማለት ይገልጻሉ፡፡

Alemu ጥናት በባህላዊ ግብርና ዕውቀት ላይ በአዊ ዞን መሰራቱ የሚያመሳስለን ቢሆንም የእሳቸው ጥናት በሰብል ምርትና ምርታማነት ላይ ተጽኖ የሚያደርሱትን በማመላከት ተጽእኖውን እና መከላከያ መንገዶችን ማሳየት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ከኔ ጥናት ጋር በእጅጉ ተቀራረቢ ቢሆንም የእኔ ጥናት ከማሳ ዝግጅት እስከ ሰበል ስብሰባ ድረስ ያለውን ሂደት የሚመለከት ነው፡፡ ስለዚህ ሳይንሳዊ ስለሆኑት ጉዳዮች፣ ስለ ህብረት ስራ ማህበራት አልመለከትም፡፡ ይህ የእኔ ጥናት ትኩረት አይደለም፡፡

Abera (2006) "Indigenous Common Grazing Land Management in Chencha Woreda, South Ethiopia" በሚለው ስራቸው የጋራ የግጦሽ መሬት ጠቀሜታ ሲገልጹ ተጠቃሚውን ቡድን የሚያስተሳስር፤ በባህላዊ ሃብት ጥበቃ ውስጥ ተቋማዊ መዋቅር ያለው፣ በሁሉም ማህበረሰብ ዘንድ ሊተገበር የሚችል መመሪያን ማስከበሪያ ዘዴ ያለው ነው ይላሉ፡፡ ማንኛውም የማህበረሰቡ አባል የጋራ የግጦሽ ቦታን ከውጭ ጣልቃ ገቦች ይጠብቃል በማለትም ይገልጻሉ፡፡ የጋራ የግጦሽ ቦታ ቀጣይነት እንዲኖረው የሚጠብቁበትን መንገድ፣ የጋራ የግጦሽ ቦታና የገጠሩ መተዳደሪያዎችን፣ የጋራ የከብት ግጦሽ መሬት ጥቅም፣ በቅይጥና በማፈራረቅ እርሻ ዘዴ ያለው ሚና፣ የጋራ የግጦሽ መሬት ለሌላ መተዳደሪያ ያለው አስተዋጽኦ፣ የግጦሽ መሬት አያያዝ ቀጣይነት ችግርና መልካም አጋጣሚዎች የሚሉትን በጥናታቸው ውስጥ አካተው አቅርበዋል፡፡

የ Abera ጥናት ትኩረት ያደረገው በጋራ የግጦሽ መሬት ላይ ነው፡፡ የእኔ ጥናት የግጦሽ መሬትን ትኩረት አያደርግም ነገር ግን መሬትን ለማሳደር /ለማከረም/ የሳር

መሬት ሆኖ የሚከርምበት ሁኔታን ከመሬት ለምነት አንጻር የምዳስስበት ሁኔት ሊኖር ይችላል፡፡

Workenehe (2011) "Identification and Documentation of Indigenous Knowledge of Bee keeping Practices in Selected Districts of Ethiopia" በሚል ጥናታቸው ባህላዊ የንብ አጠባበቅ ዕውቀት ከቦታ ቦታ ከአርሶ አደር አርሶ አደር የሚለያይ መሆኑና ይህም የተመሰረተው ከገበሬዎች ልምድና ከንቦች ጥበቃ ጋር ባላቸው ግንኙነት ነው በማለት አስፍረዋል፡፡

Workenehe ባህላዊ የቀፎ አይነቶችና የሚሰሩበት ቁስ፣ ባህላዊ የማር መቁረጫ ወቅት እንደአካባቢው ሁኔታና እንደልምዳቸው ከአካባቢ አካባቢ እንደሚለያይ አሳይተዋል፣ ከዚህም በተጨማሪ ባህላዊ የንብ አያያዝን፣ ባህላዊ የማር አቆራረጥ፣ ከንብ ንድፊያ መከላከያ ባህላዊ መንገዶችን፣ የንቦችን ጠላቶች ጠቅሰው እነዚህን ከጠላቶች የሚከላከሉበትን ባህላዊ ዘዴ፣ በንብ በመነደፍ የሚመጣ ህመምን መከላለከያ መንገዶችንና የማርን ጥቅም በጥናታቸው ውስጥ አካተው አቅርበዋል፡፡ ይህን ዕውቀትም በአግባቡ ሰንዶ ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍና ዕውቀት ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ይህ ጥናት በባህላዊ ግብርና ዕውቀት ላይ በማተኩሩ ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለን ቢሆንም ልዩነቶችም አሉን፡፡ የወርቅነህ ጥናት ትኩረት በባህላዊ የንብ አጠባበቅ ላይ ሲሆን የእኔ ጥናት ትኩርት ግን ከማሳ ዝግጅት እስከ ሰብል ስብሰባ ድረስ ያለው የባህላዊ ግብርና ዕውቀት በመሆኑ ሙሉ በሙሉ የተለያየ ነው፡፡

### 2.1.3. ፎክሎር እና የባህላዊ ግብርና ዕውቀት

በዚህ ስር የተቃኙት ጥናቶች ሁለት ሲሆኑ፣ ባህላዊ የግብርና ዕውቀት እና ፎክሎር ላይ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶች ናቸው፡፡ ጥናቶቹ የተሰሩት በግብርና የትምህርት መስክ ነው፡፡

Firew (2007) "Infra-specific folk taxonomy in sorghum (*Sorghum bicolor* (L.) Moench) in Ethiopia: folk nomenclature, classification, and criteria" በሚለው ጥናታዊ ስራቸው፤ የደቡብ ገበሬ ማሽላን ማምረት ከጀመረ 500 ዓመት ገደማ ይሆነዋል፡፡ ገበሬው 25 ቅርጻዊ፣ 16 ህይወታዊና ኢ-ህይወታዊ፣ 12 ከጥቅማቸው ጋር የተያያዘ የማሽላ ምደባ እንደሚጠቀም ገልጸዋል፡፡ የባህላዊ ዝርያዎች ስያሜም ከቅርጽ፣ ከቅርበትና ከመዝሪያ ወቅት አንጻር የተሰጠ ነው ይላሉ፡፡

Firew ከማሽላው አንጻር የተሰጠው ስያሜ ደግሞ በሥነ-እጹ- በአበባ፣ በዘር ቀለም፣ በተክሉ ቁመት፣ በምርቅ...፤ በግብርና አካባቢ ጥናቱ- ድርቅንና ቅዝቃዜን መቋቋም የሚችል፤ በቅርጸ ባህሪው- የቡቃያ ብርታት፣ የተክሉ የቅጠል ቁጥር፣ የተክሉ ቀለም፣ የቅጠሉ ቀለም፣ የተክሉ ውፍረት፣ የአንጓ ቁጥር፣ ምርቅ፣ የአበባው ቅጠል ብዛት፣ የገለፈት ቀለም፣ የዘሩ አይነት... ስያሜው እንደሚሰጥ ገልጸዋል፣ እንዲሁም በህይወታዊና ኢ-ህይወታዊ ምደባው- የቅጠሉ በሽታን መቋቋም፣ በአቀማመጥ የሚመጣን ሻጋታ (በሽታ) መቋቋም፣ ድርቅን መቋቋም፣ አነስተኛ ለምነት ያለውን መሬት መፈለግ፤ ከጥቅም ጋር የተያያዘው ምደባ፡- እንጀራ የመሆን፤ በገበያ ላይ ያለው ተፈላጊነት፣ ጣእም፣ የዱቄቱ ውኃ ማንሳት፣ ለከብቶች መኖነት፣ ለማገዶ ወዘተ. በሚል የተመደበ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

Firew (2009) "Folksong Based Appraisal of Bio-ecocultural Heritage of Sorghum" በሚለው ጥናታዊ ስራቸው እንደገለጹት ማሽላና ዘንጋዳ ከገበሬው ሕይወት ጋር በጣም የተቆራኘ ነው፡፡ ቁርኝቱ ከዘር መረጣ እስከ አጠቃቀም ያለው የሚገለጸው በህዝባዊ ዝማሬ ነው፡፡ ይህም በቃልና በዜማ (በትረካ፣ በግጥም) አይነት ያለውን ሁሉ ያጠቃልላል ይላሉ፡፡ Firew ገበሬው በቁጥር የበዙና የተለያዩ በእርሻ ላይ ያሉ በርካታ ሥነ-ህይወታዊ፣ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነ-ምህዳራዊ፣ ሥነ-ማህበረሰባዊና ባህላዊ ሁኔታዎችን በህዝባዊ ዝማሬው ይገልጻል በማለት በጥናታቸው አስፍረዋል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ገበሬዎች በተለያየ መንገድ ባህላዊ የእጽዋት ዕውቀት በዘፈን ይገልጸዋል በማለት ጽፈዋል፡፡

የFirew ሁለት ስራዎች በባህላዊ የግብርና ዕውቀት በፎክሎር ላይ የሚያተኩሩ ጥናቶች በመሆናቸው በእጅጉ እንቀራረባለን፡፡ የፍሬው የመጀመሪያው ስራ በባህላዊ የበቆሎ ምደባ ላይ የቀረበ ጥናት ሲሆን ገበሬው ባህላዊ ዕውቀት ተጠቅሞ የበቆሎ ዝርያዎችን እንዴት እንደሚመድብ ያሣየ ጥናት ነው፡፡ ይህ ምደባ ግን ከተክሎቹ ሁኔታ አንጻር የተሰጠ ነው፡፡ እንደሳቸው ጥናት ማየት የፈለጉት "folk taxonomy" ከተክሉ ውጫዊ ቅርጽ እንጂ ከማህበረሰቡ ባህል፣ እምነት፣ ልማድ አንጻር ያለውን ፎክሎራዊ ጉዳይ እና ለምን ስያሜው እንደተሰጠ ከባህሉ አንጻር አልተመለከቱም፡፡ የእኔ ስራ በፎክሎር ዘርፎች ላይ ያተኮረ ሲሆን የፍሬው ስራ በቆሎ ላይ ትኩረቱን አድርጎ የዘር ምደባ ላይ ያተኩራል እንጂ ለምን? እንዴት? መቼ? ለሚሉትን ጉዳዮች መልስ የሰጠ አይደለም፡፡

የሁለተኛው ስራ ደግሞ በበቆሎ ከዘር መረጣ እስከ አጠቃቀም ድረስ ባለው የማህበረሰቡ ቃላዊ ግጥም ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ የFirew ስራ የበቆሎን ቃላዊ ግጥም መሰብሰብ ላይ ያተኮረ እንጂ በግጥሞቹ ላይ ምንም አይነት ትንታኔን አልሰጠም፡፡ እንዲሁም ግጥሞቹ መቼና እንዴት እንደሚባሉም የሰጠው ማብራሪያ የለውም፡፡ የእኔ ጥናት ትኩረት ግን የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ከማሳ ዝግጅት እስከ ሰብል ስብሰባ ድረስ ያለውን ዕውቀት፣ የዕውቀት ተስተላልፎና ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የሚመለከት በመሆኑም ቃላዊ ግጥሞች መቼ? የት? እና እንዴት? ለምን? እንደሚባሉ ትንታኔ ይሰጣል፣ ይተረጉማል፡፡

## 2.2. ጽንሰ-ሃሳባዊ ማዕቀፍ

በዚህ ክፍል ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ቀርቧል፡፡ በዚህ የጽንሰ ሃሳብ ማዕቀፍ የፎክሎር ጽንሰ ሃሰብ፣ የባህላዊ ዕውቀት ስያሜና ምንነት፣ የባህላዊ ዕውቀት የሚያካትታቸው ጉዳች፣ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ምንነት፣ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ባህሪያትና አይነት፣ የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን መጠቀም አስፈላጊነት የእርሻ መሳሪያዎችና ወቅቶች የሚሉት ጽንሰ ሃሰባዊ ዳራዎች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### 2.2.1. የፎክሎር ጽንሰ-ሃሳብ

ፎክሎር የአንድን ማህበረሰብ አጠቃላይ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ ደንብ፣ ስርአት፣እሴት፣ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና፣ አኗኗር ወዘተ የሚያጠና ሰፊና ጥልቅ የሆነ የሰብአዊ ሳይንስ ዘርፍ ነው (Sims and Stephens, 2005፡138; Robert and Micaiel, 1995:1; Schoemaker, 1990:3; Oring, 1986፡ 86፡229; Dorson, 1972፡3-4; Ben-Amos, 1971፡13; Goldstein,1964፡I):: ይህን አስመልክተው የተለያዩ የመስኩ ተመራማሪዎች ፎክሎርን እንደየ ግንዛቤያቸውና እንደየተነሱበት የዘመን መንፈስ ከልዩ ልዩ ጉዳዮች አንጻር በይነውታል፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትና ሌሎችም ምሁራኖች ስለ ፎክሎር የተለያዩ ሀሳቦችን የሰነዘሩት አጥኚዎች ፎክሎር ጓዘ ከባድ እና ብዙ ከመሆኑ የተነሳ አንድ ቁርጥ ያለ ብያኔ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑን ይስማሙበታል:: ለፎክሎር ብያኔ ከመስጠት ይልቅ በስሩ የሚያካትታቸውን ጉዳዮች መዘርዘር ተመራጭ መሆኑን የዘርፉ ተመራማሪዎች ያስረዳሉ (Dundes, 1965; Michael, 1994)፡፡ ይህም ሆኖ ምሁራኑ ፎክሎርን በሶስት፣ በአራት፣ በአምስት፣ እና በሰባት፣ ሲመድቡት ይስተዋላል፡፡

ፎክሎርን "ቃላዊ፣ ቁሳዊ እና ልማዳዊ ፎክሎር" በሚል በሶስት ምድብ፣ Toelken, (1996፣9)፣ "ሰዎች የሚሏቸው (verbal lore)፣ የሚያበጁቸው (material lore) እና የሚያደርጓቸው (customary lore)" በማለት ፎክሎርን በሶስት ምድቦች ይከፍላሉ (Schoemaker, 1990፡3; William, 1986:229) "ቃላዊ፣ ልማዳዊ እና ቁሳዊ ፎክሎር" በሚል በሶስት ምድብ Brunvand, (1972፣8)፣ "የቃላዊ ሰነጽሁፍ (oral literature) ቁሳዊ ባህል (material culture) ማህበረሰባዊ ልማድ (social folk custom) ማህበረሰባዊ ትውን ጥበባት (performing folk arts)" በማለት ፎክሎርን በአራት ክፍል መድበውታል (Dorson,1972፡2-4):: ምሁራን "ፎክሎር"ን በተለያየ ምድብ ቢመድቡትም ቃሉ ግን ከሁለት "ፎክ" እና "ሎር" ከተሰኙ ቃላት ጥምረት የተመሰረተ ነው (Dundes, 1980:1)፡፡

### *2.2.1.1. "ፎክ"*

"ፎክ" ማለት ቡድን፣ ህዝብ (ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ስብስብ) ማለት ነው፡፡ ፎክ (ቡድን) ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የጋራ ልምድና ፍላጎት ያላቸው ሰዎች የፈጠሩት ስብስብ ማለት ነው (Dundes, 1965:2) ፡፡

"ፎክ" መገለጫው ባህልን መሰረት ያደረገ ተግባቦት ያላቸው ሰዎች ስብስብ ነው ብለዋል (Toelken, 1996፡56)፡፡ የToelken ገለጻ ከDundes ብዙም ያልተለየ ቢሆንም በገለጻቸው ውስጥ ለቡድኑ መሰባሰብ ምክንያቱ ባህላዊ መሰረት ነው ይላሉ፡፡ ይህም ባህላዊ መሰረት ያለውና ኢመደበኛ፣ ውስብስብነት የሌለው ልማዳዊነትን የሚያመላክት ነው (Sims and Stephens, 2005:34)፡፡

ፎክሎር በሰዎች ለሰዎች የተፈጠረና ሰዎች የሚኖሩትና የሚኖሩበት ነው፡፡ ፎክ "የጋራ ጉዳይ ያሰባሰባቸው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ስብስብ ፎክ ወይም ቡድን ይባላል" ይላሉ (Dundes, 1980፡6)፡፡ ይህም የቡድኑ አባላት ለመሰባሰብ አንዳች የጋራ የሆነ ጉዳይ ያለቸውና ያ ጉዳይም ለመሰባሰባቸው ምክንያት መሆኑን ያሳየናል፡፡ ይህ የጋራ ጉዳይም በጋራ የተገነባ ዕውቀት ሎር ነው፡፡

### 2.2.1.2. *"ሎር"*

የሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ህብረት ከሌላ ማህበረሰብ ጋር የሚጋሩት የጋራ ዕውቀት "ሎር" ነው፡፡ ይህ የጋራ ዕውቀትም ለረጅም ዘመናት ትውልድን አስተሳስሮ የቆየ ነው፡፡ ይህም የአኗኗር፣ የአስተዳደር፣ የአለባበስ፣ የአመራረት ህጎች፣ የአነጋገር፣ የአበላል ደንቦች... እምነት፣ አምልኮን የተመለከቱትን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ስለሆነም ይህ "ፎክ"ን አንድ አድርጎ የቆየው "ሎር" ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ እስካሁን ድረስ የዘለቀው ባህላዊ ዕውቀት ነው (Oring, 1986; Dorson, 1986; Bouman, 1992; Georges and Jones, 1995); ፡፡

ፎክሎር ስሜት በሚሰጥ ቋንቋ፣ በምልክት እና በእንቅስቃሴ ላይ የተመሰረተ የጋራ ዕውቀት እንደሆነ ይገልጻሉ (Robert, Gorge and Oring, 1995፡1)። ይህ የጋራ ዕውቀት ሎር ተብሎ የሚታወቀው ሲሆን ስያሜውም "የማህበረሰብ የጋራ ዕውቀት" የሚያመለክት ነው ይላሉ፡፡

የፎክሎሩ ጥናት የበለጠ ዕውነታ አዘል ትርጉም ሊኖረው የሚችለው ቡድኑ ቀድሞ በገነባዉ የዕውቀት ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ ከእነርሱ ጋር በቀዬው እያስተያየ ሲተረጎም ነው (Ben-Amos, 1979)። ይህ ጥናት በባህላዊ ግብርና ዕውቀት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ የተመረጠው ምደባ የSchoemaker (1990፡3) ምደባ ነው፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ ሰዎች በሚሉት፣ በሚያደርጉትና በሚያበጁት ላይ የሚያተኩር ስለሆነ ነው፡፡

- ሰዎች "የሚሉት"፡- ውበት ባለው ቋንቋ በሚናገሩት ነገር ይግባባሉ፡፡ ይህም "ሥነ ቃል" ነው፡፡
- ሰዎች "የሚያደርጉት"፡- ሰዎች በሚያደርጉት ነገር ሃሳብ በድርጊት ይለዋወጣሉ ይህ በድርጊት ሃሳብ መለዋወጥም "ልማዳዊ ባህል" ይባላል፡፡
- ሰዎች "የሚያበጁት" ደግሞ "ቁሳዊ ባህል" ነው፡፡

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት "በሚያደርጉት" ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

### *2.2.1.3. ልማድ*

ልማድ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ዋና ጉዳይ ነው፡፡ ይህን መሰረታዊ ጉዳይ በተመለከተ የፎክሎር ባለሙያዎች የተለያዩ ትርጉሞችን "ልማድ የአንድ ነገር በጥቂት ለውጥ ወይም ያለምንም ለውጥ ከትውልድ ትውልድ መደበኛ ባልሆነ መንገድ መተላለፍ ነው" (Green, 1997:800)፡፡[15] ከዚህ በተጨማሪም Green የሃያኛው ክፍለ ዘመን የፎክሎር ባለሙያዎች ልማድን ባለፈውና በአሁኑ ጊዜ መካከል ያለ ግንኙነት ነው ይላሉ፡፡

---

[15] "Tradition as something down from one generation to the next, generally by informal means, with little or no change in the transmition of that item or in the item that is transmited" (Green, 1997:800).

ያለፈው ለአሁኑ መነሻ ሲሆን የአሁኑ ደግሞ ያለፈው የሚታይበት ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

ይህም ልማድ ለፎክሎር ሙያ ዋና ጉዳይና ከጊዜ ጋር ተያያዥ የሆነና መደበኛ ባልሆነ መንገድ የሚገኝ በተከታታይ ከለውጥ ጋር የሚያያዝ አስተሳሰብ ነው፡፡ ይህም በቡድን ውስጥ የሚገኝን ዕውቀት ወይም ባህል መቀባበል ነው፤ ሊባል ይችላል፡፡ ልማድ "የምንቀባበለው ዕውቀትና ዕውቀትን የምንቀባበልበት ሂደት እና ማንነትን የሚፈጥርና የሚተክል ነገር ነው" (Sims and Stephens, 2005:65)፡፡

በአጠቃላይ ልማድ በተወሰነ ቡድን ውስጥ ያሉ እውቀቶችና አስተሳሰቦች ቀጣይነት ነው፤ ቀጣይነቱም በቅብብሎሽ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ልማድ የቡድን ዕውቀትና የዕውቀት ሽግግር መንገድ ሲሆን ይህም ዕውቀት በተከታታይነትና በለውጥ ሂደት የሚቀጥል መሆኑን ያሳያል፡፡ ቀጣይነትና ተለዋዋጭነት የፎክሎር ሂደት ነው (Toelken, 1996፡97)፡፡

በዚህ አመለካከት ማህበረሰብም ሆነ ባህል በውስጣዊም ይሁን ውጫዊ ጉዳዮች መነሻነት፣ በሰው ሰራሽም ሆነ ተፈጥሯዊ ለውጥ ምክንያት እየተለወጠ መሄዱ አይቀሬ ነው። ለለውጡ መፋጠን የበለጠ ጎልቶ የሚጠቀስና የሚቀርብ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ጉዳዮቹ ለውጡን ማስከተላቸው አይቀሬ ነው።

### 2.2.1.4. *ለውጥ*

ለወጠ፣ ቀየረ መነዘረ የሚል ትርጉም ይኖረዋል (Leslu, 1973፡292)፡፡ "አዲስ ሁኔታ፣ የተለየ ነገር፣ ልዩነት" በማለት ይገልጸዋል፡፡ ለውጥ በየትኛውም ጊዜ የነበረ ያለና የሚኖር ተፈጥሯዊ ሂደት ነው (የኢትዮጵያ ቋንቋና ጥናት ምርምር ማዕከል አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 1993፡21)፡፡ ይህም ባለፈው በነበረው ላይ ማሻሻያ ማድረግ መሆኑን ያሳያል፡፡ ምሁራኑ እንደሚናገሩት ለውጥ የፎክሎር አንዱና መሰረታዊ ባህሪ ነው (Toelken 1996; Dorson 1972; እና Sims and Stephens 2005፡74)፡፡ ልምድ

በተለያዩ ሁኔታዎች ምክንያት ይለወጣል፡፡ ይህም በፎክ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ውስጥ ለውጥ፣ ተገቢና የሚኖር ነው፡፡ ስለዚህ ተከታታይነትና ለውጥ በባህላዊ ግብርና ዕውቀት ይዳሰሳል፡፡

ዋናውን ሃሳብ የያዘውን የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን ምንነት ከመግለጼ በፊት በቅድሚያ የባህላዊ ዕውቀትን ስያሜና ምንነት መግለጽ አስፈላጊ ነው ብዬ በማሰቤ እንደሚከተለው አቅርቤያለሁ፡፡

### 2.2.1.5. *ቀጣይነት*

ቀጣይነት፣ ከቃሉ መረዳት እንደሚቻለው በተደጋጋሚ የሚከወን ድርጊት ነው፡፡ በተደጋጋሚነት የሚከወነውም ነገር ድግግሞሹ ሲበዛ ልምድ ይሆናል፡፡ በጊዜ ርዝመት የሚደረግ ድግግሞሽ ልምድን ይፈጠራል፤ የልምድ መደጋገም ደግሞ ተከታታይነትን ይፈጥራል፡፡ ይሁን እንጂ ተደጋጋሚነት ሲባል ተመሳሳይነት አይደለም፤ አንድ ነገር እየተደጋገመ በሄደ ቁጥር መለወጡ የማይቀር ነው፡፡ Sims and Stephens ተከታታይነት የሚለው ቃል የልምዱን ትርጉም የያዙ ክሮች ናቸው በማለት ይገልጹታል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ልምድ የሚቀየርበት ሁኔታ ይፈጠራል ይላሉ፤ ይህም የልምድን ተለዋጭነትን ያስከትላል (Sims and Stephens, 2005:65)፡፡

### 2.2.2. የባህላዊ ዕውቀት ስያሜና ምንነት

ባህላዊ ዕውቀትን የተለያዩ ምሁራን በተለያየ ሥያሜ ሲጠሩት ይስተዋላል፡- “ሀገር በቀል ዕውቀት”፣ “ባህላዊ ዕውቀት”፣ “የተወላጅ ዕውቀት”፣ “የፎክ ዕውቀት”፣ “የህዝብ ዕውቀት”...፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ግን የባህላዊ ዕውቀት የሚለውን ስያሜ ለመጠቀም መርጫለሁ፡፡ ባህላዊ ዕውቀት ዋነው የጥናቱ ርእስም በመሆኑ ነው፡፡

ባህላዊ ዕውቀት ጥንታዊነት ያለውና ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ ነው፡፡ “የባህላዊ ዕውቀት ጽንሰ ሃሳብ አዲስ ክስተት አይደለም፡፡ የሰው ልጅ አካባቢውን መላመድ

ከጀመረበትና መሰረታዊ ፍላጎቱን ማሟላት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ያለና ጥንታዊነት ያለው ነው" (Alemayehu, 2012:61)፡፡

እንደ Rajasekaran and Martin (1993:8) ባህላዊ ዕውቀት ትክክለኛ የዕውቀት ክፍል የሆነ በአካባቢው ማህበረሰብ በረጅም ጊዜ ልምድና ሙከራ የተጠራቀመና መደበኛ ባልሆነ መንገድ በአንድ ባህል የሚፈጠር የዕውቀት ክፍል ነው በማለት ሲገልጹ ባህላዊ ዕውቀት ባህላዊ በሆነ መንገድ የሚፈጠር በፈጣን ለውጥ ላይ ያለና አዳዲስ ነገሮችን የሚፈጥር ከባቢያዊና አለማቀፋዊ የዕውቀት ዘዴ ነው (Warren, 1990)፡፡ Rajasekaran and Martin ይህን ይበሉ እንጂ ባህላዊ እውቀት አለማቀፋዊ ሳይሆን እንደየአካባቢውና እንደየባህሉ የተለያየ ነው፡፡

ሀገር በቀል ዕውቀት ባህላዊ ዕውቀት ነው፤ ዕውቀት ለዚያ ማህበረሰብ ወይም ባህል የተለየ ነው፡፡ ባህላዊ ወይም ሀገር በቀል ዕውቀት የተወሰነ ማህበረሰብ ወይም ባህላዊ ቡድን በረጅም ጊዜ ሂደት ያዳበረውና አሁንም ድረስ እያሳደገው ያለ ንብረቱ ነው (Grolink, 2005)፡፡ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች በመነሳት ባህላዊ ዕውቀት የአንድ ማህበረሰብ ንብረት ነው፡፡ የባለቤትነት ማረጋገጫ የሌለው፣ ማህበረሰቡ በጋራ የሚጠቀምበትና አብሮት የኖረ እንዲሁም ከጊዜ ወደ ጊዜም እያዳበረው የመጣ አሁንም ድረስ የሚጠቀምበት ንብረቱ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ባህላዊ ዕውቀት የተለየ፣ በተለየ ቦታ በተመሳሳይ ባህልና ማህበራዊ ግንኙነት የሚፈጠር ነው (Owuer, 2007:23)፡፡ አያይዘውም ይህ ዕውቀት የሚያሳየው የትምህርት ሂደትና ማህበራዊ ህይወትን፣ ማንነትን፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተግባራትን የሚያስተምር እና በእያንዳንዱ ቡድን ተግባራዊ የሚሆን ነው ይላሉ (Owuer, p.23)፡፡

ባህላዊ ዕውቀት ዘርፈ ብዙ መሆኑን ጠቁመው ጥቂቶቹን "የተፈጥሮ ሀብት አያያዝና አጠቃቀም፣ የግብርና ዕውቀት፣ ባህላዊ የሰውና የከብት ጤና አጠባበቅ፣ የልጆች አስተዳደግ፣ መደበኛ ያልሆነ ትምህርት፣ ባህላዊ የግጭት ማስወገድ ዕውቀት፣ እደ

ጥበባትና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡" ይህም ባህላዊ ዕውቀት በውስጡ በርካታ ነገሮችን እንደሚያካትት ያሳያል (አለሳና ገብሬ፣ 2004፣77)፡፡

ደግሞ ባህላዊ ዕውቀት ለተፈጠረበት ማህበረሰብ ወይም ባህል የተለየ ትርጉም አለው፡፡ ይህም መሰረት የሚያደርገው በግብርና፣ በጤና አጠባበቅ፣ በምግብ ዝግጅት፣ በትምህርትና በተፈጥሮ ሃብት አጠባበቅ፣ እና ሌሎችንም የገጠሩ ማህበረሰብ ስራዎችን ያካተተ ነው ይላሉ (Boven and Morohashi, 2002:12) ፡፡

በጥናቱ የመግቢያ ክፍል ለመጠቆም እንደተሞከረው ባህላዊ ዕውቀት ከሚያካትታቸው በርካታ የዕውቀት ዘርፎች መካከል አንዱ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት ነው፡፡

### 2.2.3. የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ምንድን ነው?

የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ጽንሰ ሀሳቡ ከባህላዊ ዕውቀት የተለየ ትርጉም አይገኝለትም፡፡ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ያልተጻፈ የዕውቀት አካል ነው፡፡ በተለያዩ ሰዎች ቋንቋና ችሎታ፣ በብዙ ማህበረሰቦች ባህልና አካባቢያዊ ሁኔታ፣ ዛሬም ያለ ዕውቀት ነው፡፡ ባህላዊ ዕውቀት ሁሉንም የሰው ልምድ የሚሸፍን ነው፣ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት በባህላዊ የውሳኔ ሰጭነት ደረጃ የሚረጋገጥና በሕይወት ከመቆየት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው (Sundamari and Ranganathan, 2003)፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች ምሁራን ባህላዊ የግብርና ዕውቀት በውስጡ የሚያካትታቸውን እንደሚከተለው ይገልጿቸዋል፡-

- የሰው ጤና፡- አመጋገብ፣ የሰው በሽታዎች አይነት፣ የባህላዊ መድሃኒት አጠቃቀምና የህክምና ዘዴ፣ የመድሃኒት እጽዋት መገኛ፣ ጠቃሚው ክፍል የሚሰበሰብበት ጊዜ፣ የአዘገጃጀትና የአቀማመጥ ዘዴ… በማለት ገልጸዋል፡፡

- እንስሳትና የእንስሳት በሽታ፡- የእንስሳት ዝርያና ምርት፣ ባህላዊ የእንስሳት አመጋገብ፣ የእንስሳት የምግብ አይነቶችና የእንስሳት በሽታ ምድብ፣ ባህላዊ የእንስሳት ህክምና...፣
- ውኃና ባህላዊ የውኃ አስተዳደር፡- የውኃ አጠባበቅ ዘዴ፣ ባህላዊ የመስኖ አጠቃቀም ብልሃት፣ የዓሳና በውኃ ውስጥ የሚገኙ እጽዋት አያያዝና አጠቃቀም...በማለት ገልጸዋል፣
- አፈር፡- የአፈር አይነት፣ የአፈር አጠባበቅ ስልት፣ የአፈር ለምነትን የመጠበቂያ ዘዴ፣ ናቸው ይላሉ...፣
- ግብርና፡- የእርሻ ቦታን የዝግጅት ጊዜ ጠቋሚዎች፣ የማሳ ዝግጅት ልምድ፣ ሀገር በቀል ተክሎችን የማስተላለፊያ (የማቆያ ዘዴ)፣ ዘሮችን የማስቀመጥ (የማድረቅ፣ የመለየት፣ የማጽዳት)፣ የዘር ዝግጅትና ባህላዊ አዝርእትን የሚያዩበት መንገድ (የሚቀመጡበትና የሚያዋህዱበት)፣ የዘር ግጅትና ጥንቃቄ፣ የእርሻ መሳሪያዎች ዝግጅት፣ የበሽታ መከላከያ ዘዴና ገቢዩ፣... ናቸው በማለት ገልጸዋል (Warren, 1991; Emery, 1996)፡፡

ይህ ዕውቀት ማህበረሰቡ መደበኛ ትምህርት ሳይማር በሕይወት ተሞክሮው ያዳበረውና በተለያየ መልክ እየገለጸ ከትውልድ ትውልድ በቅብብሎሽ እያስተላለፈ ያቆየው ነው፡፡ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት በማህበረሰቡ አእምሮና በእንቀስቃሴው ውስጥ ያለና በትረካው፣ በዘፈኑ፣ በጭፈራው፣ በተረትና ምሳሌው፣ በአፈታሪኩ፣ በባህሉ፣ በእሴቱ፣ በእምነቱ፣ በቋንቋው፣ በዘር ግንዱ፣ በማህበረሰቡ ህግ፣ በግብርና ልምዱ፣ በቁሱ፣ በመሳሪያዎቹ፣ በእጽዋት ዝርያዎቹና በእንስሳት ዝርያዎቹ ወዘተ. የሚገለጽና ባህላዊ ዕውቀት በቃል፣ በተለየ ምሳሌና በባህል የሚተላለፍ ነው (Grenier, 1998:1)፡፡

ገበሬው አካባቢውን የሚረዳበት የዝናብ ኡደቱን፣ የምርት ጊዜውን የሚለይበት፣ የሰብል አይነቶችንና የመዝሪያ ጊዜአቸውን፣ የሚስማማቸውን የአፈር አይነትና ወቅት፣ የአየር ንብረት... የሚረዳበትና ህይወቱን የሚመራበት የራሱ የሆነ ባህላዊ ዕውቀት አለው፡፡ ገበሬዎች የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት ለውጡን፣ የሰብሉንና የመስኖ ኡደቱን

የሚረዱበት ዕውቀት አላቸው፤ ይህም ዕውቀት በረጅም ዓመት ልምድ የተገኘና ካለፈው ትውልድ የተወረሰ፣ ከከባቢያዊ ሁኔታና ፍላጎት ጋር የተላመደ ዕውቀት ነው በማለት (Grenier, 1998:1) ይገልጻሉ፡፡

ከላይ የተነሱትን ሀሳቦች መሰረት በማድረግ ለዚህ ጥናት የሚሆን ሃሳብ (ተግባራዊ ብያኔ (operational definition)) መያዝ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሰረት በዚህ ጥናት ውስጥ "የባህላዊ ግብርና ዕውቀት" ሲባል በገጠሩ ማህበረሰብ አእምሮና በእንቀስቃሴው ውስጥ ያለና በሕይወት የመቆየት ሁኔታ ጋር የተቆራኘ፣ ዕውቀት በረጅም ዓመት ልምድ የዳበረ፣ በቃልና በተግባር ከትውልድ ትውልድ በቅብብሎሽ ሲተላልፍ የኖረ፣ ከከባቢያዊ ሁኔታና ፍላጎት ጋር የተላመደ በሁኔታዎች አስገዳጅነት የሚለወጥ፣ ገበሬው አሁንም ድረስ እየተጠቀመበት ያለና የጋራ ሀብት የሆነ ዕውቀት ነው፤ የሚለውን እሳቤ የሚመለከት ነው፡፡

### 2.2.4. የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ባህሪያትና አይነት

በባህላዊ ዕውቀትና በሌሎች የዕውቀት ዘርፎች መካከል ያለውን ልዩነት በትክክል ለማስቀመጥ አስቸጋሪ ነው (Agrawal, 1995:416)፡፡ ባህላዊ የግብርና ዕውቀት በተመሳሳይ ሁኔታ የሚፈጠር ሳይሆን እንደ ግለሰቦች አመለካከት፣ አቀባበል፣ የዕውቀት አፈጣጠር የሚለያይና በተወሰነ አካባቢና ቦታ የሚገኙ የገጠር ማህበረሰቦች የሚመለከቱትን፣ በራሳቸው ስሜት የሚሰማቸውን፣ በራሳቸው ቋንቋ ተጠቅመው የሚገልጹት ነው (Grenier,1998:47)፡፡ አንትሮፖሎጅስቶችና ሌሎች የሚስማሙበት ደግሞ፣ አካባቢያዊ የሆኑ፤ አንድ የተወሰነ አካባቢና ባህልን መሰረት አድርገው የሚፈጠሩ፣ ዋናው መተላለፊያ መንገዳቸው ቃላዊ ተግባቦት፣ መፈጠሪያቸው ተግባራዊ ልምምድ፣ ትኩረታቸው ታሪካዊ ወይም ተግባራዊ የሆነ፣ ድግግሞሻዊና ተለዋዋጭ የሆኑ፣ በርካታ የማህበረሰቡ አባላትን ይሁንታ የሚፈልጉ፣ ወጥነት በሌለው መንገድ የሚሰራጩ፣ መገለጫቸው ተግባራዊ ክዋኔ የሆነና ሁለንተናዊ የሆኑ ናቸው (Ellen, et al. 2000: 4-6)፡፡

ከላይ በተጠቀሰው የምሁራኑ ገለጻ ዕውቀት በሁለት የሚከፈል ሲሆን አንደኛው ከትውልድ ትውልድ በውርስ የሚመጣው ዕውቀት በመነገር፣ በመመልከት፣ በባህላዊ መረጃ፣ የአንድ ቡድን ዕውቀት መጠበቂያና መተላለፊያ በሆነው ተረት፣ ከበራ የተለያዩ ሃይማኖታዊ ክበራዎች… የተወረሰና በአጠቃላይ አብዛኛው የማህበረሰቡ አባል የሚጋራው ዕውቀት ነው፡፡ ሁለተኛው ዕውቀት ደግሞ ከማህበረሰቡ የተገኘን ዕውቀት መሰረት አድርጎ በአውድ በመቀንበብ የግለሰብ ገበሬዎችን ልምድና ችሎታ የሚጠይቅ በጥልቅ ምልከታ፣ ትርጉምና ፍከራ ወደ እራስ ልምድና ተሞክሮ በማምጣት የተገኘ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ነው፡፡ በዚህ መሰረት ይህ ጥናት ከባህላዊ ግብርና ዕውቀት ጋር የተያያዙ የዕውቀት አይነቶች የሚዳስስ ይሆናል፡፡

## 2.2.5. የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን መጠቀም ለምን አስፈለገ?

ያገሬው ህዝብ የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን የሚጠቀሙት ዋጋው በጣም አነስተኛ በአብዛኛውም ነጻ በመሆኑ፣ በማህበረሰቡ አንድነትንና ትስስርን ስለሚፈጥር፣ ሀሳቡንና ተግባሩን በቀላሉ መረዳት ስለሚያስችል፡፡ ምክንያቱም ዕውቀት በራስ ቋንቋ በቃል ስለሚተላለፍ፣ በሰው ጤናና በሌሎች ላይ የሚያመጣው ችግር ባለመኖሩ፣ ምንም አይነት የልዩ ሙያን ባለቤትነትና ኤክስፐርትነትን… ስለማይጠይቅ ነው (Akullo and Kanzikwera, 2007፡10)[16]፡፡ እነሱ ይህን ይበሉ እንጂ ዋናው ጉዳይ በህይወት ከመቆየት (ከህልውና) ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ምክንያቱም ገበሬው ለመኖር ማምረት አለበት፤ ከጊዜ ወደ ጊዜም ከሚያየውና ከሚደርስበት ተነስቶ እያሻሻለ መሄድ የግድ ስለሆነ እስካሁን ጠብቆት ቆይቷል፡፡

ያገሬው ህዝብ የሚለው ገበሬዎችን፣ መሬት የሌላቸውንና በጉልበት ስራ በግብርናው ላይ የተሰማሩትን፣ ሴቶችን፣ የእደ ጥበብ ባለሙያዎችን፣ ከብት አርቢዎችን ሁሉ

[16] The practical resons of the use of indigenous knowledge practices, particularly for local people as follows:- They are cheap and in most cases cost free in monetary terms, They create social harmony and cohesion, they are to grasp to concepts and practice because knowledge can be passed on orally using the local language, they are available on demand and problems domestically, they donot have side effects to human health and others, their application never demands specialist like veterinary doctors or extention workers (Akullo and Kanzikwera, 2007፡10).

ያጠቃልላል፡፡ ይህ ህዝብ እንደ ከባቢው ሁኔታ ምን መስራት እንዳለበትና እንደሌለበት፣ ተጽእኖን እንዴት ወደሌላ መለወጥ እንዳለበት ያውቃል፡፡

### 2.2.6. **ወቅቶች**

ገበሬዎች ስራቸውን ሁሉ የሚያከናወኑት ወቅትን መሰረት አድርገው ነው፡፡ የወቅቶች ምደባ ሁለት አይነት ሲሆን አንደኛው በተለምዶ ከመስከረም ጀምሮ እስከ ሰኔ በጋ፣ እንዲሁም ሐምሌና ነሐሴ ደግሞ ክረምት ነው ሲሉ ሌላው ሁለተኛው ደግሞ የአመቱ ወራቶች በአራት ቦታ ተከፋፍለው የሚገኙበት ነው፡፡ ይኸውም ጥቢ፣ መኸር፣ በልግና ክረምት ናቸው፡፡ በግብርናው ስራ ውስጥ ደግሞ ወቅት ዋናው ጉዳይ ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ ቄስ ታዬ

> መቼም እኛ ገበሬዎች የምንሰራው በወቅቱ ነው፡፡ ተመስከረም አንድ ጀምሮ እስተ ህዳር ያለውን ጥቢ፣ ተታህሳስ እስተ የካቲት ያለው ያው በጋ ነው፡፡ እሱን መኸር እንለዋለን፡፡ ሰብሉ የሚሰበሰብበትና ተወቅቶ የሚገባበት ነው፡፡ የደስታና የፌሽታ ጊዜ ነው፡፡ ተመጋቢት አንድ ጀምሮ አፍላ የእርሻ መጀመሪያችን ነው፡፡ ይህ ጊዜ የክረምቱ መግቢያ ምልክት ነው፡፡ ስለዚህ ወቅቱ ግቢ ነው፡፡ ተሰኔ አንድ ጀምሮ ያለው ጊዜ ክረምት ነው፡፡ የእርሻ፣ የዘር፣ የአረም ወቅት ነው፡፤ እንግዲህ ይኸው ነው፡፡ በዚህ ነው የምንሰራው፡፡[17]

የወቅቶቹን አከፋፈል አስመልክቶ በተለያዩ መዝገበ ቃላት የተሰጣቸው ስያሜዎች ከገበሬው አከፋፈል ጋር በእጅጉ ተቀራራቢነት ያለው ነው፡፡

***መጸው፡-*** እንደ ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ምርምር የአማርኛ መዝገበ ቃላት አገላለጽ (1993፡67) "ከመስከረም 26 - ታህሳስ 25 ቀን ያለው ወቅት መጸው ይባላል፡፡ Leslau

[17] ቄስ ታዬ ታፈረ፣ አብስላ ዋርዳ ቀበሌ፣ ዋህሳ ደሽ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ 24/06/2007

(1973፡41) "season after the summer rains" ከክረምት ዝናብ በኋላ ያለው ጊዜ ሲሉ ደስታ (1962፡605) "...91 ቀን ከመስከረም 26 - ታህሳስ 27፣ ወርሃ ጽጌ ማለት ነው" ይላሉ፡፡ ኪዳነወልድ (1948፡744) ደግሞ ይህን ወቅት "ፀደይ፣ አጨዳ (ያጨዳ ወራት ዘመን) በልግ በወዲያ መኸር በወዲህ በልግ የሚደርስበት የሚታጨድበት፣ በሐጋይና በክምረት መካከል ያለ ክፍል" በማለት ይገልጹታል፡፡ ከዚህ መረዳት የምንችለው ከመስከረም መጨረሻ እስከ ታህሳስ መጨረሻ ያለው ጊዜ መጸው ተብሎ ይጠራል፡፡

***በጋ፡-*** ማለት በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፡231)እና ደስታ (1962፡151) አገላለጽ በመጸውና በጸደይ መካከል ያለ ከታህሳስ 26 - መጋቢት 25 ቀን ያለው ጸሐይና ድርቅ የበዛበት ወቅት ነው፣ ከመስከረም እስከ ግንቦት ያሉትም ዘጠኙ ወራት በተለምዶ በጋ እየተባሉ ይጠራሉ በማለት ሲገልጹ፡፡ Leslau (1973፡98) "dray season" ደረቅ ወቅት በማለት ይገልጹታል፡፡ ከዚህ ገለጻ መረዳት የሚቻለው በአራት ከተከፈሉት ወቅቶች አንዱ የሆነው በጋ የሚባለው ወቅት ከታህሳስ 25- መጋቢት 25 ያለውን ጊዜ የሚጠቃልል ነው፡፡

***መኸር፡-*** "Autumn harvest, crop in Ethiopia" Leslau (1973፡33). "የበጋ ዝናብ ጸደይ" ኪዳነወልድ (1962፡271) ይሉታል፤ ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ምርምር የአማርኛ መዝገበ ቃላት አገላለጽ በልግ በኢትዮጵያ የእርሻ ወቅት ነው፡፡ "በበልግ ወራት ለበልግ የሚበቃ ዝናም፣ ለአዝመራና ለግጦሽ የሚሆን በቂ ዝናም የሚገኝበት ወቅት (በአብዛኛው ከየካቲት እስከ ሚያዚያ ያሉት ወራት)" (1993፡231) እንዲሁም (ገጽ 581) "ጸደይ ከመጋቢት 26 እስከ ሰኔ 25 የበልግ ወቅት የዘር ወራት" ነው፡፡ "የበጋ መኸር፣ የበጋ ዝናም፣ የበጋ ቡቃያና መከር ይሉታል (ደስታ፣ 1962፡178)፡፡

***ክረምት፡-*** በኪዳነወልድ ገለጻ "በቁሙ ዝናም የዝናም ወራት በጸደይና በመጸው መካከል ያለ ክፍል ሲሉት Leslau (1973፡157) "Rainy season (from July to September)" ሐምሌ እስከ መስከረም ያለው የዝናብ ወቅት በማለት ይገልጹታል፡፡ የኢትዮጵያ

ቋንቋዎች ጥናት ምርምር የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፡389) "ከሰኔ 26 እስከ መስከረም 25 ድረስ ያለው የዝናም ወራት ጊዜ" ነው፡፡

ገበሬዎች በአመቱ ወስጥ የሚያከናውኑት ተግባር ከወቅቶች ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ተግባራቸውን ያለ ወቅቱ ካከናወኑ ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ውድቀት ያጋጥማቸዋል፡፡[18] ይህም በጥናት አካባቢዬ የተመለከትሁት ነው፡፡ ገበሬዎቹ ተግባራቸውን በወቅት ከፋፍለው ያከናውናሉ፡፡ እኔም ለዚህ ጥናት የተጠቀምሁት የገበሬውን የወቅት አከፋፈል ሲሆን ከመጋቢት/1 እስከ ግንቦት /30 ያለው ጊዜ ግቢ፣ ከሰኔ/1 እስከ ጳጉሜ/5 ያለው ክረምት፣ ከመስከረም/1 እስከ ህዳር/30 ጥቢና ከታህሳስ/1 እስከ የካቲት/30 ድረስ መኸር ናቸው፡፡ እነሱም ከዚህ በታች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

እነዚህ ወቅቶች ገበሬው ባህላዊ የግብርና ዕውቀት ተጠቅሞ የተለያዩ ተግባራትን የሚያከናውንባቸው ናቸው፡፡ ይህ ጥናትም የሚቃኘው እነዚህን ወቅቶች መሰረት በማድረግ የገበሬው የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ይዳሰሳል፡፡ አከፋፈላቸውም ገበሬው እራሱ በከፋፈለበት መንገድ ነው፡፡ ገበሬው ሲነሳ የግብርና መሳሪያዎችም አብረው ይቃኛሉ፡፡

በጠቅላላው በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት እና ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ የሚሉ ሁለት አንኳር ነጥቦች ቀርበዋል፡፡ በመጀመሪያው በተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ስር በባህላዊ ግብርና ዕውቀት ላይ በተለያዩ አጥኚዎች የተጠኑ አስራ ሰባት የሚሆኑ ጥናታዊ ስራዎች ተዳሰው ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉበትና የሚለያዩበት የቀረበ ሲሆን ይህም በአጠናን ዘዴ እና በይዘት ያላቸው አንድነትና ልዩነት ለማሳየት

[18] The recognition of seasonal rhythms and their critical relationship to the organization of agricultural activities is manifested in agricultural calendars. ...The peasant organizes his agricultural activities through out the year in relation to . . . the calendar's . . . seasons, and he believes that if he departs from traditional seasonal patterns, his work will fail either totally or partially (Brosius et.al., 1986:187).

ተሞክሯል፡፡ በሁለተኛው አንኳር ነጥብ ጽንሰ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ሲሆን በዚህ ስር ስለ ፎክሎር ምንነት ማለትም የፎክ፣ የሎር፣ የልምድ እና የፎክለር ቀጣይነትና ለውጥ ምንነት የቀረበ ሲሆን የባህላዊ ዕውቀት ምንነት በተለያዩ ምሁራን የተሰጡ ማብራሪያዎች ቀርበዋል፡፡ ባህላዊ ዕውቀት ምን ምንን እንደሚያካትትም ተገልጿል፡፡

የባህላዊ ዕውቀት አካል የሆነው ባህላዊ የግብርና ዕውቀት ምንነት በምሁራን አተያይ የተሰጡት ሀሳቦችን በማቅረብ ለዚህ ጥናት መነሻ የሚሆን "ተግባራዊ ብያኔ በመስጠት ለጥናቱ የሚሆን ትርጉምን ለመስጠት ተሞክሯል፡፡ ከዚሁም በተጨማሪ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ከሌሎች የዕውቀት ዘርፎች የሚለይበትን ባህሪ፣ ዕውቀትንም መጠቀም ስላስፈለገበት ምክንያት፣ የእርሻ መሳሪያዎችን በተመለከተ እና ገበሬው ከፋፍሎ የሚጠቀምባቸው ባህላዊ የወቅቶች ምድባ በዝርዝር የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ስልትና ዘዴዎች

ይህ ምዕራፍ የጥናቱን አይነት፣ ሥነ-ዘዴዎችና ጥናቱን የሚያጠናክሩ ንድፈ ሀሳቦች ገለጻ የተካሄደበት ክፍል ነው፡፡ ምዕራፉ ስድስት ንዑሳን ክፍሎችን ይዟል፡፡ እነሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 3.1. የጥናቱ አይነት

ይህ ጥናት ዋና ትኩረቱ ባህላዊ የግብርና ዕውቀት በመሆኑ በሰዎች ዕውቀት፣ ልምድ ላይ አተኩሯል፡፡ "ለፎክሎር አንድ ወጥ ብያኔ እንደሌለው ሁሉ አንድ ወጥ የሆነ የፎክሎር ጥናታዊ ዘዴም የለም…" (Goldstein, 1964፡2)፡፡ የGoldstein ገለጻ ፎክሎርን ለማጥናት አንድ ወጥ የሆነ የምርምር ዘዴ እንደሌለና የተለያዩ ዘዴዎች መጠቀም እንደሚቻል ያሳያል፡፡

በመሆኑም ተፈጥሯዊ አውድን መሰረት በማድረግ በዋናነት ጥናቱ አይነታዊ (qualitative) የጥናት ዘዴን የተከተለ ሆኖ በተንታኝ ዘዴ የተከናወነ ነው፡፡ ምክንያቱም አይነታዊ ዘዴ ቃለ-መጠይቅን፣ ምልከታን፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይትን እና የተለያዩ የጽሁፍ መዛግብትን ለመጠቀም የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡ አይነታዊ የጥናት ዘዴ አውድን መሰረት ያደርጋል (Catherine, 2007:16)፡፡ እንደ ምሁራኑ ገለጻ ይህ ደግሞ ተመራጩ የፎክሎር አጠናን ዘዴ ነው (Dundes, 1980; Ben-Amos, 1979; Goldstine, 1964)::

በአይነታዊ የጥናት ዘዴ መረጃ ለመሰብሰብ የተለያዩ አማራጮች (Creswell, 2014:14) ቢኖሩም ጥናቱ በሰዎች ዕውቀትና ልምድ ላይ ስለሚያተኩር ይህ ጥናት ተግባራዊ የሆነው በኢትኖግራፊክ የአጠናን ስልት ነው፡፡ በአይነታዊ ምርምር የጋራ ባህል ለመመርመር ኢትኖግራፊያዊ የጥናት ዘዴ ይሰራበታል (Kurger, 2008:18)፡፡ ይህ ዘዴ የባህል ትርጎማ ተመራማሪዎች ያዩትንና የሰሙትን የተጠኚውን ማህበረሰብ ማህበራዊ

አመለካከት የመግለጽ ችሎታን ያካትታል (Given, 2008:288)፡፡ ኢትኖግራፊያዊ የጥናት ዘዴ በተጠኚዎች መካከል ለረዥም ጊዜ ተገኝቶ የሚጠናውን ባህል በዕለት ከዕለት ሕይወት እየተከወነ ባለበት ተፈጥሯዊ አውድ በተሳታፊነት ተጠኚዎች የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን እየተመለከቱ በመቅረጽ እየሆነ ያለውን ለመግለጽ ያስችላል (Savage, 2006:385)፡፡

ፎክሎር የሰው ልጅን ልምድና ተግባራዊ ጥበባዊ ስራዎችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለማየት የሚያስችል ሙያ ነው፡፡ ፎክሎር ከብዙ የጥናት መስኮች ጋርም ይገናኛል፡፡ ፎክሎር ከአንትሮፖሎጂ፣ ከሥነ-ጽሁፍ፣ ከታሪክ፣ ከፍልስፍና፣ ከቋንቋ... ጋር ይገናኛል (Clifored, 1988; Hymes, 1972)፡፡ ለዚህ ጥናት ኢትኖግራፊክ የአጠናን ስልትን ተጠቅሚያለሁ፡፡

ኢትኖግራፊክ ጥናት ስለ ማህበረሰብ፣ ቡድኖች ሕይወት፣ ወይም የሕይወት አመራር ገፅታን ከራሱ ከቡድኑ ወይም ከህዝቡ አመለካከትና ከሚኖርበት የሕይወት ልምድ አንፃር የሚመረምር ነው (Fetterman,1998:32; O'Reilly, 2005:84)፡፡ ኢትኖግራፊያዊ ምርምር በባህሪው በተጠኚዎች ትርጉም ፈጣሪነት ዙሪያ ያጠነጥናል፤ ተጠኚዎቹ የሚኖሩበትን የራሳቸውን ዓለም እንዴት እንደሚተረጉሙት መረዳት ላይ ያተኩራል፤ ሰዎች ፈጥረው የሚጠቀሙበትን የባህል ዓለም መረዳትን ይጠይቃል (Goldbart & Hustler, 2005፡16)፡፡ ተጠኚው ማህበረሰብ ስለሚያከናውናቸው ተግባሮች እና ስላዳበሯቸው ልምዶች ምንነት ለመረዳት ያስችላል፡፡

ይህ ዘዴ ፎክሎሩን ከማህበረሰቡና አተገባበሩ ጋር የሚመለከት በመሆኑ ከፎክሎር ቅንጣቶች ጋር በማያያዝ የተሟላ መረጃ ለማግኘት ያስችላል። የዚህ ዓይነቱ ጥናት ዋና መሠረቱ የመስክ ሥራ ነው፡፡ የመስክ ሥራ ሦስት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት፤ (1) የሚጠናውን ማህበረሰብ ወግና ልማድ፣ ተቋማት፣ መዋቅርና የሚከውኗቸውን ድርጊቶች መግለፅ፣ (2) እንዴት እንደሚከውኑ መግለፅ እና (3) ከማህበረሰቡ ተቋማትና ባህል ጋር የተያያዙ አስተሳሰቦችንና ስሜቶችን መመዝገብ ናቸው (O'Reilly, 2005:8)፡፡ እነዚህ

በዚህ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ መረጃዎቹም ከማን፣ መቼና ከየት እንደተሰበሰቡ በመረጃ ትንተናው ክፍል ከመረጃዎቹ ጋር ሰፍሮ ይገኛል፡፡

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ጥናቱ ግቡን ይመታ ዘንድ የተነደፉ ዓላማዎችን ለማሳካት ካልዓይና ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ተግባር ላይ ውለዋል፡፡ ለጥናቱ ተገቢ የሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ለመምረጥ በጥናቱ አይነትና በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካከል ያለው ንድፈ ሀሳባዊ ትስስርና ዘዴው መረጃዎችን ለማስገኘት የሚኖረው ፋይዳ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ የዘርፉ ባለሙያዎች ያስገነዝባሉ:: የጋራ ባህል ያላቸውን ቡድኖች ዕውቀትና እምነት ለማጥናት ምልከታና ቃለ-መጠይቅ አግባብነት ያላቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ናቸው (Jaccard and Jacoby, 2010:463)፡፡ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መጠቀም፣ መረጃዎቹን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለመረዳት ከማስቻሉም በተጨማሪ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ጥንካሬ እና ድክመት ለመለየትና ክፍተቶችን ለመሸፈን ያስችላል (Denscombe, 2007:134) ፡፡

በዚህም መሠረት በመረጃ ስብሰባ ወቅት ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ከቤተ መጻህፍት፣ ከቤተ መዛግብት፣ ከዞንና ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ጽ/ቤች ከተገኙ ሰነዶች፣ ከወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ከተገኙ መረጃዎች የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ ከመስክ ከተፈጥሯዊ አውዱ፣ ከጉዳዩ ባለቤቶች በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት አማካኝነት የተሰበሰቡ ሲሆን ከካልዓይና ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡት መረጃዎች ተቀናጅተው፣ ተደራጅተውና ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### 3.2.1. ካልዓይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

አንድ ተመራማሪ ለጥናቱ የሚሆን መረጃ ለመሰብሰብ ወደ መስክ ከመሔዱ በፊት ሊያስብባቸው የሚገቡ በርካታ ጉዳዮች አሉ፡፡ ይህን አስመልክቶ ፊቃደ እንደሚገልጹት፡-

> እኔ እስከማውቀው ድረስ ማንኛውም መስከኛ (field worker) በተለይ ለስራ ወደ ገጠር የሚሰማራ... በባዶ ሆዱ መስክ አይወጣም፡፡ የሥነቃል ተመራማሪውም... በባዶ ሆዱ ወደ መስክ መውጣትን አያስብም፡፡ በዚህ ዓይነት በባዶ ራሱ መስክ መሰማራት የለበትም፡፡ እዚያ ሔጄ ምን እንደ ምጠይቅና ምን እንደምሰራ አስባለሁ ማለት አይፈቀድለትም (ፈቃደ፣ 1991፡124-125)፡፡

በፈቃደ ገለጻ መሰረት መስከኛው ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ወደ መስክ ከመሰማራቱ በፊት አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ማከናወን አለበት፡፡ Goldstein በበኩላቸው አንድ መስከኛ ጥናት በሚያካሔድበት ወቅት ስለ ጥናቱ ቦታና ማህበረሰቡ ጥልቀት ያለው ዕውቀት ሊኖረው ይገባል (1964:37)፡፡ ማንም ሰው በባህል ወደ በለጸገው አካባቢ በመሄድ የተወሰኑ ጠቃሚ ነገሮችን ለማግኘት ይችላል፡፡ ነገር ግን በስርዓት የተነደፈ የመስክ ምርምር የሚጀምረው በቤተ መጻህፍትና በቤተ መዛግብት ውስጥ ነው (MacDonald,1972፡408)፡፡ በዚህ መሰረት ስለሚጠናው አካባቢያዊ ዳራ ለማወቅና የጥናት አቅጣጫን ለመተለም ያመች ዘንድ ጥናቱን የጀመርሁት ከቤተ መጻሕፍትና ከቤተ መዛግብት ነው፡፡

ከላይ የተነሳውን የምሁራኑን ሃሳብ መነሻ በማድረግ የመስክ ጉዞ ከመጀመሬ በፊትም ስለጥናት ቦታው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና መልክዓ ምድራዊ ሁኔታዎች በሚመለከት ተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት አድርጌ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ፡፡ ይህም በGoldstein (1964:37) እና Robert and Junes (1995፡15) ሃሳብ መሰረትነት ስለ ጥናት ቦታውና ማህበረሰቡ በቂ ዕውቀት እንዲኖረኝ ረድቶኛል፡፡ እንዲሁም ከዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ጽ/ቤትና ከወረዳ ግብርና ጽ/ቤት፣ ከወረዳ መስተዳድር፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ጽ/ቤት የተገኙ ሰነዶችን በመመርመር ስለዞኑና ስለወረዳው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በቤተ-መጻህፍት ባደረግሁት ንባብ የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት አድርጊያለሁ፡፡ በዚህም ለንድፈ ሃሳብ መሰረት የሚሆነኝን ርዕሰ ጉዳይ ከንባብ አግኝቻለሁ፡፡ የጥናቱን አይነት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴንና የመረጃ መተንተኛ ዘዴን ለመተለም የሚያስችሉኝን መሰረታዊ ነጥቦች ለማግኘት ችያለሁ፡፡

### 3.2.2. ቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለጥናቱ ተገቢ የሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ለመምረጥ በጥናቱ ዘዴና በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካከል ያለውን ንድፈ ሀሳባዊ ትስስርና መረጃዎችን በማስገኘት በኩል የሚኖረው ፋይዳ ታይቷል፡፡ መስክ ከመሄዴ በፊት ቀዳማይ መረጃን ለመሰብሰብና ለማጠናቀር አመቺ የሆኑ ዘዴዎችን ማወቅ ነበረብኝ፡፡ በዚህም መሰረት ምልከታ፣ ቃለ-መጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይት ለጥናቴ ተገቢነት ያላቸው ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡

መረጃን ከመስክ ለመሰብሰብ በዋናነት ምልከታና ቃለ መጠይቅ በተፈጥሯዊ አውድ ያገለግሉ ሲሆን ተተኳሪ የቡድን ውይይት (focus group discussion) የመረጃዎችን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ሲባል በጥናቱ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው (Spradley, 1980: 58-62; Goldstein, 1964:77; Robert & Jones, 1995:15; ፈቃደ፣ 1991፡ 90)፡፡ በመስክ ተገኝቼ የምፈልገውን መረጃ ለማግኘት እችል ዘንድ በመጀመሪያ ለመረጃ አቀባዮቼ ስለማንነቴ እና ስለምሰራው ጥናት ዓላማ በግልጽ አሳውቄያሁ፡፡ ይህም ባካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ተዓማኒነት እንዲኖርና በቀላሉ ተግባብቶ የሚፈለገውን መረጃ ለመሰብሰብ ያስችላል፤ አጥኚዋም ሆነ መረጃ አቀባዮቿ ባይተዋርነት እንዳይሰማቸውም ያድርጋል (George and Jones, 1992:2; ፈቃደ፣ 1991፡92)፡፡

#### 3.2.2.1. ተሳትፏዊ ምልከታ

ምልከታው በተፈጥሯዊ አውዱ የሚከናወኑትን የባህላዊ ግብርና እውቀቶች እንዴት እንደሚተገበሩ ለመመልከት የሚደረግ ነው፡፡ ምልከታ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ዋናው

ጉዳይ ነው፡፡ ምልከታ መረጃ ሰብሳቢዋ መረጃ ልትሰበስብባቸው ከምትፈልጋቸው ተጠኚዎች ጋር ወይም አካባቢ በአካል በመገኘት መረጃ የምትሰበስብበት መንገድ ነው (Spradley, 1980:58-62; ያለው፡2004:182)፡፡ ለምልከታ ወደ መስክ ከመሄዳችን በፊት ልብ ልንላቸውና ልንከተላቸው የሚገቡን ነገሮች አሉ፡፡ እነሱም እንዴት መመልከት አለብን፣ ምልከታውን በምን ሁኔታ መቅረጽ አለብን፣ ማስታወሻ አያያዛችን ምን መምሰል አለበት፣ እና ምልከታችን በትክክለኛ መንገድ ማካሔዳችንን በምን አይነት ዘዴ ማረጋገጥ አለብን የሚሉትን ናቸው (Kothari, 2004፡96)፡፡ መረጃን በምልከታ ለመሰብሰብ ተፈጥሯዊ መቼት ወሳኝ ነው፡፡ ፎክሎር በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው አገልግሎት በትክክል የሚታወቀው ደግሞ በተፈጥሯዊ አውዱ ነው፡፡

በፎክሎር ጥናት ምልከታ ማለት የአንድን ጉዳይ ክዋኔ በአካል ተገኝቶ በሁሉም የስሜት ሕዋሳት አማካይነት ተረድቶ መረጃ መሰብሰብ ማለት ነው፣ በመሆኑም ምልከታ አንድን ድርጊት ማየት ብቻ ሳይሆን "መቅመስ፣ መዳሰስ፣ መስማትና ማሽተትን" ሁሉ ይጨምራል (Goldstein, 1964:77)[19] ፡፡ ምልከታ አጥኚው ለተወሰነ ጊዜ ከሚያጠናው ማህበረሰብ ጋር አብሮ በመኖር አጠቃላይ የማህበረሰቡን እሴቱን፣ ባህሉን፣ ወጉን፣ ደንቡን፣ ልምዱን፣ ስርአቱን፣ ቋንቋውን፣ አኗኗሩን፣ ወዘተ. በተመለከተ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው (Spradley, 1980: 58-62; O'Reill, 2005፡104)፡፡

ለምናጠናው ጥናት አስፈላጊውንና ትክክለኛውን መረጃ ለማግኘት የምናጠናውን ማህበረሰብ አጠቃላይ አኗኗር፣ እምነት እና እሴት ጠንቅቀን በማወቅ እና የሚበሉትን በመብላት የሚጠጡትን በመጠጣት የሚተገብሩትን በመተግበር በአጠቃላይ እነሱን መስሎ በመኖር ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት የሚያስችል ዘዴ ነው (Hammersley and Atkinson, 2007፡1)፡፡

---

[19] Observation used by field worker in obtaining data by direct observation, looking from the outside in and describing the situation as he sees it. "The term, "observation", ...is not limited only to visual aspects of the situation, but also involves a full range of sensual experience including hearing, feeling, smelling, and tasting, whenever these may be appropriate (Goldstein, 1964:77).

Spradley, ደግሞ ተሳትፏዊ ምልከታን በአምስት ክፍሎች ይከፈሉታል፡፡ እነሱም ሙሉ ታሳታፊ ተመልካች (complete pareticipant obeservation)፣ ንቁ ታሳታፊ ተመልካች (active participant observation)፣ ተሳታፊ ተመልካች (Moderate participant observation)፣ ፍዝ ተመልካች (Passive pareticipant observation) እና ተመልካች (none pareticipant observation) ናቸው (1980: 58-62;)፡፡[20]

በተሳትፏዊ ምልከታ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መረጃ ለመሰብሰብ ያለው ጠቀሜታ በስራው የሚሳተፉት አባላት የሚያደርጉትን እያንዳንዱን ሁኔታና የእርስ በእርስ መስተጋብር በቅርበት ለማየት ማስቻሉ ነው፡፡ ሙሉ ተሳትፏዊ ምልከታ ከኢትኖግራፊክ የምርምር ዘዴ ጋር የጠበቀ ንድፈ ሀሳባዊ ትስስር ያለው በመሆኑ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ያገለግላል (Murchison, 2010:100)፡፡ ተሳትፏዊ ምልከታ በስራ ወቅት የሚቀርቡትን የተለመዱ፣ ተደጋጋሚ ወይም አዲስና የተለዩ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተመራጩ ዘዴ ነው (Murchison, P:97)፡፡ ይሁን እንጂ እያንዳንዱን እንቅስቃሴ እየተመለከቱ ማስታወሻ ለመያዝ አስቸጋሪ ነው፡፡

---

[20] **non pareticipant observation፡-** the observer who has no involvement with the people or activities studied. It is entirely possible to collect data by observation alone. Sometimes this kind of research may be undertaken by an extremely shy individual who would like to conduct ethnographic fieldwork but wants to avoid involvement. **Passive pareticipant observation፡-** the ethnographer engaged in passive participation is present at the scene of action but does not participate or interact with other people to any great extent. About all you need to do is find an "observation post" from which to observe and record what goes on. If the passive participant occupies any role in the social situation, it will only be that of "bystander," "spectator," or "loiterer." **Moderate participation፡-** occurs when the ethnographer seeks to maintain a balance between being an insider and an outsider, between participation and observation. **Active participation፡-** begins with observations, but as knowledge of what others do grows, the ethnographer tries to learn the same behavior.... **complete pareticipant obeservation፡-** The highest level of involvement for ethnographers probably comes when they study a situation in which they are already ordinary participants.... (Spradley, 1980: 58-62;).

ተሳትፏዊ ምልከታ መረጃን ለመሰብሰብ የተጠቀምሁት በእርሻ፣ በጤፍና የበቆሎ ዘር መምረጥ ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም በተሳትፎ መረጃን ለመሰብሰብ ሴቶችን የሚያሳትፍ ስራ በመሆኑና እየተሳተፉ ለመመልከትም አመቺ ስለነበር ነው፡፡ ሙሉ ተሳትፏዊ ተመልካች ተመሳሳይ ሚና ያላቸውን ሰዎች መለየት ከማስቻሉም በላይ በስራው ውስጥ ያለውን መረጃ በቀላሉ መረዳት ያስችለዋል (Goldstein, 1964:78-80)፡፡ ይህንንም በአረም ወቅት የተመለከትሁ ሲሆን የሚያስፈልግ ተክል እኳን ቢሆን ያለ ቦታው የተገኘ በመሆኑ አረም ተብሎ ይነቀላል፡፡ ልጆች ከከብት ጥበቃ ጎን ለጎን የመጀመሪያ ስራቸውን የሚጀምሩት ጉልጓሎ የድንች ዘር እና በጎመን አረም፣ ላይ እንደሆነና እንዴትና ምኑን ማረም እንዳለባቸው የሚማሩት በተግባር እያዩ እንደሆነ ተመልክቻለሁ፡፡

ይሁን እንጂ በመረጃ አሰባሰብ ወቅት ምልከታም የራሱ ጠንካራ ጎኖች ያሉትን ያህል ክፍተቶችም አሉበት፡፡ በተሳትፏዊ ምልከታ ወቅት አጥኚው የባህሉ አካል ተደረጎ ስለሚቆጠር መረጃን በአስፈላጊው መንገድ ለማግኘት ቢያስችልም መረጃውን ቀርጾ ለማስቀረትና ማስታወሻ ለመያዝ ግን አያመቸውም፡፡ በከፊል ተሳትፏዊ ወቅትም ማስታወሻ ለመያዝና ለመቅረጽ ቢያመቸውም የሚያመልጡት መረጃዎች ይኖራሉ፡፡ በታዛቢ ምልከታ ወቅት ደግሞ እንደባይተዋር ስለሚቆጠር ተገቢውን መረጃ ለማግኘት ይቸገራል፡፡ ስለዚህም ሙሉ ለሙሉ ተሳታፊ መሆንንና ሙሉ ለሙሉ ታዛቢ መሆን ተገቢ ባለመሆኑ እንደ ሁኔታው መጠቀም ያስፈልጋል (Spradley, 1980:58-62; Hammersley and Atkinson, 2007፡1)፡፡

ጥናቱን ተግባራዊ ለማድረግም ከ2006 እስከ 2008 በተለያየ ጊዜ በቦታው በመገኘት ከተፈጥሯዊ አውዱ መረጃውን እንደወረደ ሰብስቢያለሁ፡፡ በዚህ መንገድ የተሰበሰበው መረጃ የማህበረሰቡ የአኗኗር ዘዴ፣ እምነትና ዕውቀት ተተንተኗል፡፡ አስፈላጊውን መረጃ በተፈለገው መንገድ ለማግኘት ያስችል ዘንድም የማህበረሰቡን የአኗኗር ዘዴ፣ እምነትና እሴት በሚገባ በማወቅ የሚበሉትን በመብላት፣ የሚጠጡትን በመጠጣት እነሱን መስዬና ተመሳስዬ የሚፈለገውን መረጃ ማግኘት ችያለሁ፡፡

በከፊል ተሳትፏዊ ምልከታ፡- ይህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተጠቀምሁት በጉልጓሎ፣ በኩትኳቶ፣ በአጨዳና በዘር ወቅት ሲሆን እነዚህ ተግባራት ሴቶች የሚሳተፉባቸው በመሆናቸው በቅርበት ለመመልከት እድሉን የፈጠሩልኝ ናቸው፡፡ በዚህ ወቅትም የስራ መሳሪያዎችን በማቀበል፣ ዘር በመያዝ፣ በማጨድና የታጨደውን በመዘርጋጋት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ በተለይም በአጨዳ ወቅት ባህላዊ የሆነውን የወንፊልና የደቦ የስራ መረዳጃን ለመመልከት ችያለሁ፡፡

በኩትኳቶ ወቅትም አብሬ በመሆን የሚሰሩትን አይቻለሁ፡፡ ድንች ሲዘራ በመስመር የሚዘራ በመሆኑ ለመኮትኮት አያስቸግርም፡፡ የድንች መኮትኮቻ መሳሪያው በጣም ሹልና ቀጠን ያለ ሲሆን እጀታው ደግሞ በጣም ቆልመም ያለ ነው፡፡ ይህም የድንቹን ስር እንዳይጎዳው ተደርጎ የተዘጋጀ ሲሆን ከውስጥ ዘልቆ አፈርን ለማነሳሳት የሚያገለግል ነው፡፡ በድንች ኩትኳቶ ላይ የሚሳተፉት "ነፍስ ያወቁ" ልጆችና አዋቂዎች ናቸው፡፡ በዚህ ወቅት የልጆች ተግባር በኩትኳቶ ወቅት አፈር የለበሰውን የድንች ቅጠል እየተከታተሉ አፈሩን በማንሳት ቅጠሉን ማቃናትና አፈር ማሳቀፍ ነው፡፡ የድንች ተክል በተደጋጋሚ እስከ ሶስት ጊዜ ከተኮተኮተ በኋላ በደንብ ማደግ ሲጀምር በፈረስ/በበሬ እያረሱ አፈር ያሳቅፉታል፡፡ በዚህ ወቅትም የድንቹን ቅጠል እንዳይበሉት ከልጥ በተሰራ መለጎሚያ አፋቸው ይለጎማል፤ እንዲሁም ከፈረሶቹ ፊት ፊታቸውን የሚሄድ ወይም የሚመራ ሰው አለ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ በከብቶቹ የተረገጠውን እያቃኑ፤ አፈር የተጫነው ካለም እየተከተሉ ያስተካክላሉ፡፡

በዚህ ወቅት ከፊል ተሳትፎ ተመልካችነቴ እያንዳንዱን እንቅስቃሴ ለመከታተል እድሉን ፈጥሮልኛል፡፡ የጤፍ እርሻ፣ ጉልጓሎ፣ የጭቃ በራይ፣ የጤፍ ዘር፣ የጤፍ አረም ስራዎችን በተሳታፊና በታዛቢ ምልከታ አይቻለሁ፤ በጉልጓሎ ወቅት ልክ እንደ ጎመን አረም ልጆቹን ጨምሮ ሁሉም ይሳተፋል፤ ጉልጓሎ የሚከናወነው ለጤፍ እና ለዳጉሳ ማሳ ነው፤ ታርሶና ደቆ የተዘጋጀው መሬት ከሰኔ ሃያ አንድ በኋላ ይጎለጎላል፤ ገበሬው በሬዎቹን ጠምዶ በተወሰነ እርቀት ቦይ እየተቀደደ ይተዋል፤ ጎልጓዮቹም ከእርሻው

መሀል የሚያነሱትን አረም ስሩን ወደ ላይ እያደረጉ በፈሰሱ ውስጥ ያስቀምጡታል እኔም አልፎ አልፎ ሳሩን በማንሳት እየተሳተፍሁ መረጃን ሰብስቤያለሁ፡፡

***ታዛቢ ተመልካች፡-*** በዚህ ጥናት ወቅት በባህሉ የተከለከሉና የሚጠበቁ ደንቦችን ማክበር ካጥኚዋ የሚጠበቅ ተግባር በመሆኑ ይህንን ተግባራዊ በማድረግ በተከለከሉ ቦታዎች እንደ ንቁ ተመልካች በመሆን መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ፡፡ በባህሉ በእህል ውቂያ ወቅት እህሉ ተጣርቶ እስኪያልቅ ድረስ ሴት አውድማ ውስጥ ስለማትገባ ባህሉን ጠብቄ ከዳር በመሆን ለመመልከት ችያለሁ፡፡ በዚህ ወቅትም ከክምሩ አካባቢ በተዘጋጀው አውድማ ላይ ሁለት ሰዎች ክምሩን እየናዱ ይነሰንሳሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ በተነሰነሰው እህል በርከት ያሉ ከብቶችና ፈረሶች ያዞራሉ (እህሉን ያስደቀድቃሉ)፡፡ በዚህ መንገድም እስከ እኩለ ቀን ድረስ ከቆዩ በኋላ ከብቶቹ ውኃ እንዲጠጡ ወደ ወንዝ ሲወርዱ ገበሬዎቹ በመንሽ በደንብ ያልደቀቀውን ገለባ (ውቻሬ) ከአውድማው ዳር ያስቀምጣሉ፡፡ ከዚያም በእግራቸው እየበረበሩ ከስር ያልደቀቀውን ወደ ላይ ያወጡትና ከብቶቹን መልሰው አፋቸውን እየለጎሙ ያስገቧቸዋል፣ በመቀጠልም በትንሽ በትንሹ ከዳር የነበረውን ገለባ ያስገባሉ፣ በድጋሜም በከብቶች ይደቀደቃል፡፡ በመቀጠልም ከብቶቹ ይወጡና በመንሽ ገለባ ማውጣት ይጀመራል፡፡ የመጀመሪያው ገለባ ሲወጣ የተቀመጠው በአውድማው ዳር ለዳር ሲሆን የሁለተኛው ገለባ ግን ከአውድማው ውጭ ይሆናል፡፡ በዚህ መንገድ ገለባው ከወጣ በኋላ በረጅም የቅርከሃ መጥረጊያ እየተንጣረበ የቀረው ገለባ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም ከምስራቅ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ እኩል ለሁለት ተከፍሎ ይዛራል (ይባነናል)፡፡ በአውድማ ላይ የሚከናወነውን እያንዳንዱን ድርጊት በትኩረት በማየት ንቁ ተመልካችነቴ ጠቅሞኛል፡፡

በዚህም መሰረት በገበሬዎች ማሳ በተደጋጋሚ በመገኘት የተሳትፎ ምልከታ ዘዴዎችን በመጠቀም ተሳታፊ ተመልካች በመሆን እና ንቁ ተመለካች እንዲሁም ታዛቢ ተመልካች በመሆን በእርሻ፣ በጉልጓሎ፣ በጭቃ በራይ፣ በዘር፣ በአረም፣ በውቂያ በአውድማ ቦታዎች በመገኘት መረጃዎችን ሰብስቢያለሁ፡፡



ፎቶ 1፡-ውኃ እያርከፈከፉ ሲበራዩ[21]

ሌላው በፍዝ ተመልካችነት የሰበሰብሁት የእህል ውቂያ ተግባራትን ሲሆን በዚህ ወቅት እህሉ ተወቅቶ ተጣርቶ ለመሰፈር እስኪዘጋጅ ድረስ የሴት ወደ አውድማው መግባትን[22] ባህሉ ስለማይፈቅድ ከዳር ሆኜ ታዛቢ ተመልካች በመሆን መረጃውን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

አጠቃላይ ምልከታ አንድን ድርጊት ከመመልከት ባለፈ የድርጊቱ ባለቤቶች የሚሰማቸውን ስሜት የመጋራት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በፎክሎር ጥናት በምልከታ መረጃ መሰብሰብ ማለት በማህበረሰቡና በባህሉ ውስጥ ዘልቆና ጠልቆ በመግባት የማህበረሰቡን የዕለት ተለት እንቅስቃሴ ለማወቅና የራስ ለማድረግ መሞከር ነው (Goldstein, 1964:77)፡፡

ይህም የባህሉ ባለቤቶች በቀያቸው በነፃነት የሚከውኑት ጉዳይ በመሆኑ በርካታ መረጃዎችን ለማግኘት አጋጣሚው ሰፊ ነበር፡፡ በዚህም ከተለያዩ አቅጣጫዎች

21 በ2007 ሐምሌ ላይ በነበረወው የዝናብ እጥረት ምክንያት መሬቱ በደንብ ባለመራሱ ምክንያት ጭቃ በራዩን ሳይጨርሱ መሬቱ መድረቅ በመጀመሩ ምክንያት አቶ ወርቁ ፈንቴ ከልጆቻቸው ጋር ውኃ ከጉድጓድ እየቀዱና በጀሪካን በማመላለስ እያርከፈከፉ ሲያበራዩ የሚያሳይ ፎቶ ሹምታ 24/112007፡፡

22 የሴት አውድማ ያለመግባት በምእራፍ አምስት ልማዶችና እምነቶች በተተነተኑበት ክፍል ቀርቧል፡፡

ቃለ-መጠይቅ በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ የፊት ለፊት/የገጽ ለገጽ/ የሃሳብ ልውውጥ ነው፡፡ ቃለ-መጠይቅ የተጠያቂውን ሀሳቦችና ልምዶች የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችል የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው (Murchison, 2010:100; Goldstein, 1964፡140)፡፡

የቃለ-መጠይቅ አይነቶች የተደራጀ ቃለ-መጠየቅ (structured interview)፣ ያልተደራጀ ቃለ-መጠይቅ (unstructured interview) እና በከፊል የተደራጀ ቃለ-መጠይቅ (semi-structured interview) ናቸው (Davis, 1999:94-5; O'Reilly, 2005:116; Hammersley & Atkinson, 2007:99; ፈቃደ፣ 1991፣95;)፡፡ በዚህ ጥናት ግን በከፊል የተደራጀና ያልተደራጀ ቃለ-መጠይቅ ተግባራዊ አድርጊያለሁ፡፡ ለቁልፍ መረጃ አቀባዮችም ሆነ ለሌሎች የመረጃ አቀባዮች መነሻ የሚሆን በከፊል የተደራጀ ቃለ-መጠይቅ ያቀረብኩ ሲሆን ከሚሰጡት ምላሽ በመነሳት ያልተደራጁ ጥያቄዎች አቅርቤ ምላሽ ሰጥተውባቸዋል፡፡ ይህን መረጃ ለመሰብሰብ በመኖሪያ ቤታቸው፣ በስራ ቦታቸው፣ በቤተክርስቲያን፣ በገጠር ብድር መክፈያ ቦታ፣ በገጠር ቀበሌ ጽ/ቤቶች በመገኘት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

ቃለ-መጠይቁ የተከናወነው ከምልከታ በፊትና በኋላ ነው፡፡ ምክንያቱም ከምልከታ በፊት የተደረጉት በ2006 ግንቦት ላይ ሲሆን ምልከታውን እንዴትና መቼ መቼ ማካሄድ እንደለብኝ የጠቆሙኝ ሲሆኑ ከምልከታ በኋላ በ2007 እና 2008 የተደረጉ ናቸው፡፡ ይህም የሆነው መረጃውን ሙሉ በሙሉ በምልከታ ብቻ መሰብሰብ የመረጃውን ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ ስለሚያስገባው ነው፡፡ ቃለ-መጠይቅ በምልከታ ወቅት ግልጽ ላልሆኑ መረጃዎች፣ ለታሪኮች፣ ለልማዶችና እምነቶች፣ ወዘተ. ለሥነ-ቃሎች ማብራሪያዎችን ለማግኘት ስለሚረዳ ነው፡፡ በቃለ መጠይቅ መረጃን በመሰብሰብ ሂደት የራሱ የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት፡፡ ይሁን እንጂ ጠንካራ ጎኑን በመውሰድና ድክመቱን በሌሎች ዘዴዎች በመሸፈን ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ከጠንካራ ጎኖቹ ዋነኛው በምልከታ ወቅት ሊገኙ የማይችሉ መረጃዎችን ማስገኘት መቻሉ ነው (Hammersley & Atkinson, 2007; Creswell, 2014)፡፡

ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሚፈለገውን መረጃ ለማግኘት የሚያስችል፣ ለመረጃ አቀባዩም ነጻነት የሚሰጥ እና በመረጃ አቀባዩ እና በመረጃ ሰብሳቢው መካከል መልካም የሚባል ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስችል እንደሆነ Goldstein (1964፡108) ያስረዳሉ፡፡ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ፊት ለፊት የሚቀርብ በመሆኑ የመላሹን የፊት ገጽታና የአካል እንቅስቃሴ እየተመለከትሁ ተጨማሪ ጥያቄዎችን በማንሳት ተፈላጊውን መረጃ ለማግኘት አስችሎኛል፡፡

በቃለ-መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ እንደወረደ የተቀዳ ነው፡፡ መረጃ አቀባዮቹ መረጃውን ሲሰጡ የተናገሩበት ዘያቸው፣ ቃላቶቻቸው፣ ስሜቶቻቸው … በተናገሩበት መንገድ እንዳለ የተወሰደ ነው፡፡ የHammersley & Atkinson (2007:1)ንን ገለጻ መሰረት በማድረግ በጥናት ወቅትም ትኩረት ሰጥቼ በየትኛውም ቦታ የተገኘውን መረጃ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የሰዎችን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ምን አሉ፣ ምን አደረጉ የሚለውን በመከታተልና በመደበኛና መደበኛ ባልሆነ መንገድ በመጠየቅ መረጃን ለመሰብሰብ አስችሎኛል፡፡ (የቃለ መጠይቁን በአባሪ አንድ፣ የመስክ ፎቶ በአባሪ ሶስት ይመልከቱ)



**ፎቶ 3፡- ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች በቃለ-መጠይቅ መረጃ ሲሰበሰብ ናሙና[23]**

[23] ከግራ ወደ ቀኝ ፤ ወ/ሮ አዳኔ ተክሌ፣ አብስላ ሳሙኤል ቤተክርስቲያን 29/11/2007 እና አቶ አየለ አንተነህ፣ አዲጋ ውባጅ የገጠር ብድር በሚመልሱበት ቦታ፣ በ27/07/2007፡፡



ፎቶ 4፡- ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች በቃለ-መጠይቅ መረጃ ሲሰበሰብ ናሙና[24]

Hammersley & Atkinson (2007:99)ን መነሻ በማድረግ በቃለ-መጠይቅ ወቅት በምልከታ ጊዜ ላየኋቸውና ግልጽ ላልሆኑልኝ ነገሮች በአውድማ ላይ ስለሚከናወኑ ነገሮች፣ ልማዶችና እምነቶች ለምን እንደሚከናወኑ ማብራሪያ ያገኘሁበትና በምልከታ ላላገኘኋቸው ለአውድማ ማዘጋጃ ይውላሉ የተባሉ ሸክላ የዕቃዎች መረጃዎችም መልስ ያገኘሁበት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ በመቀጠልም ሶስተኛውን ዘዴ ተተኳሪ የቡድን ውይይትን ተጠቀሚያለሁ፡፡

### *3.2.2.3. ተተኳሪ የቡድን ውይይት*

ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ተተኳሪ የቡድን ውይይት ነው፡፡ ይህ ዘዴ በቃለ መጠይቅና በምልከታ ወቅት ላልተመለሱ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ከማስቻሉም በላይ የመረጃውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥና አስችሎኛል፡፡ ተተኳሪ የቡድን ውይይት ጥልቅና ዝርዝር መረጃን ለማግኘት የሚረዳ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆን ለምርምሩ የውሳኔ ሃሳብ ለማፍለቅም ያግዛል (ያለው፡ 2004፡192)፡፡ ተተኳሪ የቡድን ውይይት የተጠኚውን የቡድን ባህሪያት፣ ልምዶችና መስተጋብሮችን ለመመርመር የሚያስችሉ

[24] ቄስ አወቀ ተፈራ ፣ አብስላ ሳሙኤል ቀበሌ ጽ/ቤት ውስጥ፣ 03/7/2007

መረጃዎችን ለማስገኘት የሚያስችል ነው (Lioyd-evans, 2006:154)፡፡ እንዲሁም የቡድኑ አመለካከቶችና የቡድን ሀሳቦች የሚንጸባረቁበት ነው፡፡ በቡድን ውይይት ላይ በተነሱት ሀሳቦች ተሳታፊዎች አንዱን ሃሳብ በመደገፍና በመቃወም እንዲሁም የማዳበሪያ ሃሳብ በመስጠት ሃሳቡን በማዳበራቸው የመረጃውን ትክክለኛነት ለማውቅ አስችሎኛል፡፡ የቡድን ውይይት ዋና ዓላማው የመረጃውን ተአማኒነት ማረጋገጥ ነው፡፡

በተተኳሪ የቡድን ውይይት ወቅት በምልከታና በቃለ መጠይቅ የተሳተፉና ያልተሳተፉ መረጃ አቀባዮች የተካተቱበት ነው፡፡ በቃለመጠይቅ ወቅት የተናገሩትን በቡድን ወይይትም ወቅት የተናገሩ ሲሆን አንዳንዶቹ ጋር ደግሞ የሃሳብ ልዩነት ታይቷል፡፡ በተለይ በዕድሜ የገፉ አዛውንቶች በሚናገሩት ነገር እርግጠኞች ሆነው ያለምንም ፍርሃት ሃሳባቸውን ሲያረጋግጡ በጎልማሶችና በወጣቶች ዘንድ ግን የስጋት ሁኔታ ይታይባቸዋል፡፡ በዚህም በቃለ መጠይቅ ወቅት ብቻቸውን የተናገሩትን ነገር በቡድኑ መሃል ለመናገር ሲፈሩ ተስተውለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ስለ ባህላዊ ማዳበሪያ አዘገጃጀትና አጠቃቀም የተነሳው ሃሳብ፣ ስለዘር መረጣ፣ አሁን እየተጠቀሙበት ያለውን የግብርና ዕውቀት የተማሩበትን መንገድ በተመለከተ በተነሱት ሀሳቦች ላይ የቀረበው ሁሉንም ያሳተፈ ነው፡፡ ለውጥና ቀጣይነትን አስመልክቶ በቀረቡት ሀሳቦች ላይ በተደረገው ውይይት ወጣቶቹ ሀሳባቸውን በግለጽ ለመናገር ሲቸገሩ አዛውንቶች ግን የሚሰማቸውን ስሜት በግልጽ ለማቅረብና ለመወያየት ችለዋል፡፡ በዚህም አመዛኙ በተደረገው ውይይት ላይ የተገኘው ሃሳብ የመረጃውን ተዓማኒነትና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አስችሎኛል፡፡

በተተኳሪ የቡድን ውይይት ወቅት በያንዳንዱ ቡድን ውስጥ የሚኖሩት አባላት ከአምስት ማነስ ከአስራ ሁለትም መብለጥ የለባቸውም ይላሉ፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት ያስቀመጡት የቡድኑ አባላት ከአምስት ካነሱ መረጃው ተዓማኒነትን ያጣል ሲሉ ከአስራ ሁለት ከበለጡ ደግሞ ለቁጥጥር አመቺ እንዳልሆነ ይገልጻሉ (Tester, 1997:6; Robson, et al., 2002:2; ያለው፣ 2004፡191)፡፡

በዚህ መሰረት በውይይት ወቅት የተሳተፉ አባላት ሶስት ቡድን ውስጥ እኩል የሆኑ አባላት የተሳተፉ ሲሆን በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥም ሰባት ሰባት አባላት ተሳትፈዋል፡፡ ቡድኑም ሲደራጅ አንድ የሴት አንድ የወንድና አንድ ሁለቱንም ጾታ ያካተተ ነው፡፡ በውይይቱም የባህላዊ ግብርና ዕውቀትንና አጠቃላይ የዕውቀት ተስተላልፏቸውን እንዲሁም ከግብርናው ጋር የተያያዙ እምነቶችና ልማዶችን... በተመለከተ ተወያይተዋል፡፡ በነዚህ ከላይ በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች በወግ በወጉ አደራጅቼ ተተንትኛለሁ፡፡ (የቡድን ውይይት መነሻ ጥያቄዎችን በአባሪ ሁለት ይመልከቱ)



ፎቶ 5፡- ከቡድን ውይይት መረጃ ሲሰበሰብ ሰባት አይና፣ 27/7/2007

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለአንድ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ የተለያዩ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አገልግሎት ላይ ይውላሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል መቅረጸ-ድምጽ፣ ቪድዮ ካሜራ፣ ፎቶ ካሜራ እና ማስታወሻ ደብተሮች ናቸው፡፡ የመስክ ሥራ መረጃ፣ በዘመናዊ ዲጂታል የምሥልና የድምፅ መቅረጫ መሣሪያዎች ቢሰበሰብ በርካታ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል (Mattews and Ross, 2010:197)፡፡ እንዲሁም በመስክ ላይ የፎክሎር የመረጃ

አሰባሰብ ወቅት የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን መጠቀም አስተማማኝ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንደሚያግዝ ያብራራሉ Tolelkene (1996:359)፡፡ በዚህም መሰረት መረጃን ከመስክ ለመሰብሰብ የተለያዩ መሳሪያዎች በአስፈላጊው ቦታ ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

**መቅረጸ ድምጽ፡-** በከፊል በተደራጀና ባልተደራጀ ቃለ-መጠይቅ መረጃ በሰበሰብሁበት ወቅት የመረጃ አቀባዮቼን መልካም ፈቃድ በመጠየቅ መረጃውን በመቅረጸ ድምጽ ሰብስቢያለሁ፡፡

***ቪዲዮ ካሜራ፡-*** በምልከታ ወቅት መረጃዎችን ሰብስቤአለሁ፡፡ በዚህ ወቅትም በተለይም የጤፍ ማሳ ዝግጅትን በተመለከተ የእርሻ፣ የጉልጓሎ፣ የጭቃ በራይ እና ዘር አዘራርን እንዲሁም የጤፍ በራይን የምስልና ድምጽ መቅረጫ መሳሪያን ተጠቅሜ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ይህም እንቅስቃሴዎች ጎልተው እንዲታዩ ከማድረጉም በላይ የእያንዳንዱን ተግባር በቅደም ተከተል ለማየት የሚያስችለኝን መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

**የፎቶግራፍ ካሜራ፡-** በቃለ-መጠይቅ ወቅት የመረጃ አቀባዮችን ማንነት ለመግለጽ የሚያስችል የፎቶ መረጃ ለመያዝ ችያለሁ፡፡ እንዲሁም የበሬ እቃዎችን፣ የእርሻ ተግባራትን፣ የውቂያ መሳሪያዎች፣ የአረም፣ የጉልጓሎና የእርሻ ተግባራት በፎቶግራፍ ተደግፈው እንዲቀርቡ የሚያስችሉ መረጃዎችን ሰብስቢያለሁ፡፡ ምስላቸው በፎቶግራፍ እንዲነሳ ፈቃደኛ ያልሆኑ የመረጃ ተባባሪዎች ሃሳብ ደግሞ በማስታወሻ በመያዝ መረጃው ተሰብስቧል፡፡ ስለዚህ መረጃዎችን በመቅረጸ ድምጽ፣ በምስልና ድምጽ መቅረጫ እና በፎቶግራፍ ሰብስቢያለሁ፡፡ (አባሪ ሶስትን ይመልከቱ)

## 3.4. የመረጃ አቀባይ አመራረጥ

ለዚህ ጥናት መረጃ ሊሠጡ የሚችሉ መረጃ አቀባዮች አመራረጥ ላይ ትኩረት ተደርጓል። በፎክሎር ጥናት ከመረጃ ሰብሳቢው በላይ ቁልፉ ሰው መረጃ አቀባዩ ነው

(Tolken, 1996:348-349)፡፡ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ለእኔ የባህል ተንቀሳቃሽ ቤተ-መጻሕፍት፣ መረዳት ለምፈልገው ሃሳብ ደግሞ የመጀመሪያ ደረጃ ምንጮቼ ናቸው፣ ምክንያቱም የተሟላና አስተማማኝ የሆነ የመረጃ ባለቤቶች ስለሆኑ ነው፡፡ መረጃ አቀባዩ የሚፈልገውን መረጃ በትክክል ካልሰጠ መረጃ ሰብሳቢውም ሆነ ተመራማሪው ምንም ያህል ጎበዞች ቢሆኑ ጥናቱን ከስህተት ሊታደጉት አይችሉም፡፡ አክለውም መረጃ አቀባዮች የተሟላና አስተማማኝ መረጃ ባለቤቶች ከመሆናቸውም በተጨማሪ የካበተ ዕውቀት ባለቤቶች ናቸው (Tolken 1996)፡፡ በዚህም መሰረት የታላሚ ናሙና (purposive sampling) አመራረጥ ዘዴን በመጠቀም ከተመረጡ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች መረጃውን የሰበሰብሁ ሲሆን መረጃ አቀባዮቹ የጥናቱ ዓላማ ሲገለጽላቸው በራሳቸው ለዚህ እከሌ ቢሆን፣ እንዲህ ያለውን መረጃማ እከሌ ያውቀዋል (እከሌ ይሻላል) በማለት በሚያቀርቡት ሃሳብ በስሚ ስሚ (snow-balling) እና በአጋጣሚ ካገኘኋቸው መረጃ አቀባዮች አስፈላጊ ያልሁትን መረጃ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡

"ዕውቀት ያካበተ ዕድሜ ጠገብ ሰው ሲሞት አንድ ቤተ መጻሕፍት እንደተቃጠለ ይቆጠራል" የቆየ የአፍሪካውያን አባባል (Grenier,1998:1)፡፡ ዕድሜ ጠገብ የሆኑና በግብርና ሙያ አንቱ የተባሉ ሰዎችና ባለሙያዎችን ከአካባቢው ማህበረሰብ፣ ከግብርና ባለሙያዎችና ከተለያዩ ሰዎች መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ዕድሜ የጠገቡ ሰዎች የበርካታ ዕውቀት ባለቤቶች ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት በአብዛኛው መረጃው የተሰበሰበው በዕድሜ ከገፉና ከ45-90 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ካሉ መረጃ አቀባዮች ነው፡፡ እነዚህ ከታች ያሉት ናሙና ፎቶዎች ይህን የሚያመላክቱ ናቸው፡፡



ፎቶ 6፡-ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ናሙና በከፊል

ይህም የሆነው በርካታ የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን መረጃ ከነሱ ማግኘት እንደሚቻል በማሰቤ ነው፡፡ ይህን ሃሳብ (Mullen, 1992:93) እንደሚከተለው ያጠናክራሉ፤ “ፎክሎር በማንኛውም የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም የተከማቸ ባህላዊ ዕውቀት የሚገኘው ግን በዕድሜ ከገፉ የማህበረሰቡ አዛውንቶች ዘንድ ነው”፡፡ ይሁን እንጂ የዕውቀት ተስተላልፎ ምን እንደሚመስል ለማየት ከ 45 ዓመት በታች ያሉትን በተለይም በ20ዎች የዕድሜ ክልል የሚገኙትም በዚህ ጥናት በመረጃ አቀባይነት

ተካተዋል፡፡ በዚህ መሰረትም መረጃው ከወጣት፣ ከጎልማሳ፣ ከአዛውንት ዕድሜያቸው ከ23-90 ዓመት ያሉ 12 ወንዶችና 6 ሴቶች በድምሩ 18 አውራ መረጃ አቀባዮች እና 22ቱ ደግሞ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎችና ሌሎች መረጃ አቀባዮች ሲሆኑ በጠቅላላው በዚህ ጥናት የተሳተፉት 40 ናቸው፡፡ የመረጃ አቀባዮቹ ስብጥር ዕድሜንና ጾታን ያካተተ ነው፡፡ (አባሪ ሶስትን ይመልከቱ)

## 3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ አንፃሮች

በተለያዩ የፎክሎር ዘርፎች ላይ ምርምር የሚያደርግ ባለሙያ በመስክ ሥራው አማካይነት በቅድሚያ ጥናቱን ወደሚያካሂድባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ይቀላቀላል፡፡ በዚህም ጊዜ ከላይ ከ3.2 እስከ 3.4 በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እና መረጃ አቀባዮች አማካኝነት መረጃዎችን በሁለት አንፃሮች፣ በውስጣዊ አንፃር (emic or insider perspective) እና በውጫዊ አንፃር (etic or outsider perspective) መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ በውስጣዊ አንፃር የሚጠናውን ማህበረሰብ አመለካከት ሲወክል ውጫዊ አንጻር ደግሞ ከማህበረሰቡ ውጭ የሆኑ ነገሮችን የሚወክል ነው (Jackson, 1987:86)፡፡ በዚህም መሰረት ከፎክሎር ንድፈ ሃሳብ አንጻር በመተንተን በውጫዊና በውስጣዊ እይታ ተቃኝቷል፡፡ የዚህ ጥናት አጥኚ የባህሉ ባለቤት ባለመሆኔ እያንዳንዱን ነገር በትኩረት የማየት እድሉ ሲገጥመኝ በስራ አጋጣሚ አካባቢውንና ባህሉን የማውቀው በመሆኔ የሚከለከሉና የማይከለከሉ (ነውር የሚባሉ) ነገሮችን የማወቅ ችግሩ አልገመጠኝም (Dundes, 1975፡132)፡፡ ለምሳሌ በአካባቢው የሴት ልጅ አለባበስ ምን መምሰል እንዳለበት በማወቄም ቅድመ ዝግጅትን ለማድረግ አግዞኛል፡፡

ሁለቱም አንጻሮች የራሳቸው የሆነ ችግር የላቸውም ማለት ግን አይደለም፡፡ ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ (emic/etic) አንጻሮች የየራሳቸው የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎን አላቸው (ፈቃደ፣1991፡58: እና Dundes, 1975፡124)፡፡ ትልቁ ጉዳይ አቻችሎ መስራት ላይ ነው፡፡ በውስጣዊ እይታ አጥኚዋ የምታጠናው የጥናት መረጃ የተሰበሰበው፣ የባህሉ ባለቤት የሆነው ማህበረሰብ፣ ባህሉንና እራሱን በሚገልፅበት መንገድ ነው፡፡ ይህ ጥናትም በውስጣዊ እይታ የተጠኚውን ማህበረሰብ ዕውቀት፣ እምነት፣ አስተሳሰብ፣

አመለካከት በቀጥታ የሚያጠና ነው፡፡ ይህም ከማህበረሰቡ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ፈጥሮ፣ የዝርዝር ጉዳዮችን መረጃ መሰብሰብና ለሌላው በግልፅ ማሳየት መቻል ነው፡፡ በዚህ ጊዜ አጥኚው የራሱን እምነትና አመለካከት በሚያጠናው ማህበረሰብ ባህል ላይ መጫን የለበትም (Fetterman, 1998:32) በማለት ይገልጻሉ፡፡

ውጫዊ እይታ የመረጃ መሰብሰቢያ አንፃር ለባህላዊ ጥናት አስፈላጊ ነው፤ ይኸውም፣ ከባህሉ ውጭ የሆነችን ተመራማሪ ብቻ የሚመለከት ሲሆን በምታጠናው ባህላዊ ጉዳይ ላይ ያላትን አመለካከት ከመረጃው ተነስታ የምትተነትንበት ነው፡፡ በውጫዊው እይታ እያንዳንዱን እንቅስቃሴና ሁነት በመተርጎመና በመተንተን፣ በውስጣዊ አመለካከት ለተሰበሰበው መረጃ ትርጓሜ መስጠትን ይመለከታል፡፡ የውስጣዊና የውጫዊ አመለካከት ተዛብቶ ለጥናቱ ኢ-ተአማኒነትን እንዳያስከትል ሚዛናዊ ማድረግ ይጠበቃል (Fetterman,1998:32)፡፡ በዚህ መንገድም እያንዳንዳቸው መረጃዎች በትኩረት ተሰብስበዋል፡፡

## 3.6. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

መረጃን መተንተን ከመስክ የተገኘን ጥሬ መረጃ ከተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች ጋር በማዋሀድ ጥሬ መረጃው ትርጉም እንዲኖረው ማድረግ ነው (Maykut and Morehouse 1994፡110):: በመረጃ አተናተን ስልት ላይ የመስኩ ተመራማሪዎች የተለያዩ ሀሳቦችን ይሰነዝራሉ:: እነዚህ ተመራማሪዎች እንደሚሉት ከመስክ የተገኘን መረጃ ለመመርመር አውዳዊ አገባቡን መመልከት ያስፈልጋል(Schoemaker,1990፡8):: እንደ Schoemaker ገለጻ ትንተና ማለት በተለያዩ አውዳዊ አጠቃቀም ላይ ያየነውን፣ ከመረጃ ሰጪዎች የተቀበልነውን፣ በተለያየ መንገድ ወዘተ. እየጠየቅን አካተን ያዳበርነው እንደሆነ ነው:: ፎክሎር በባህሪው ፈርጀ ብዙ በመሆኑ ከተለያዩ የማህበረሰብ የጥናት መስኮች ጋር ይገናኛል፡፡ ይህን አስመልክቶ እነ Sims የሚከተለውን ብለዋል፡-

> The study of folklore touches on every dimension of human experience and artistic expression. It has grown out of the study of literature, has roots in anthropology, and contains elements of psychology and sociology.

> In many ways, it is the study of culture, visual and performing arts, sculpture, architecture, music, theater, literature, linguistics, and history rolled into one (Sims and Stephens, 2005: 3).

የSims and Stephens (2005) ገለጻ እንደሚያመለክተው ፎክሎር የሰው ልጅን ልምዶች፣ ተግባራዊና ኪናዊ ስራዎች ጭምር ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለመመርመር የሚችል ሙያ መሆኑና በዚህም ማህበረሰብን ከሚያጠኑ እንደ ሥነ-ጽሁፍ፣ ሥነ-ሰብ፣ ሥነ-ልቦናና ሌሎችም የሚጋራው ድንበር በጣም ሰፊ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ይህ ጥናት በዋናነት የተከተለው ኢትኖግራፊ ያጠናን ዘዴ ነው፡፡ የኢትኖግራፊ ጥናት የማህበረሰቡን ዕውቀት፣ አመለካከት፣ ባህሉን፣ እሴቱን፣ ወጉን፣ ደንቡንና ልማዱን መሰረት አድርጎ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት መረጃን ከአውድ በመሰብሰብ፣ በመተንተንና በመፊከር የተከናወነ ነው፡፡ ይህም ትርጓሜ (ትንታኔ) ከዘዴዎቹ ጋር ተስማሚ ከሆኑ ንድፈ ሃሳብ አንጻር መሆን አለበት።

በተለያዩ መንገዶች የተሰበሰቡት መረጃዎች በየምድቡ ተመድበው ተስማሚ ከሆኑ ንድፈ-ሃሳቦች አኳያ መተንተን አለባቸው (Marshal & Rossman, 2006:156; Creswell, 2007:161)። ከዚህ በተጨማሪ ትንተና በዋናነት መሰረት የሚያደርገው ድርጊቱ የተገለፀበትን ሥልት፣ የድርጊቱን አይነት እና ድርጊቱ የተከናወነበትን አውድ ነው (Dundes,1980:22)፡፡ ትንተና ማለት ድርጊቱ የተከናወነበት ስልት ምን ነበር? እንዴት ተከናወነ? የሚሉትን ማየት፣ ድርጊቱ ምንድን ነው? የሚሉትን የሚመለከት በመሆኑ እርሻ፣ አጨዳ፣ ውቂያ፣ ጭቃ በራይ…፣ የመሳሰሉትን ድጊቶች መመርመር፣ መቼና የት ነው ድርጊቱ የሚከናወነው? የሚለውን መመርመር የትንተናው ሂደት ነው፡፡

የፎክሎር ትንተና ዋናው ጉዳዩ አውድ ነው፡፡ አውዱ ደግሞ ማህበራዊና ባህላዊ አውድ ነው (Bauman, 1986:363)፡፡ በዚህ መሰረት በማህበራዊ አውድ ትኩረቱ በማህበሩ መዋቅርና ግንኙነት ላይ ሆኖ የማህበር፣ የግለሰብ እና የተቋም፣ ልምድና ሁነቶችን

የሚመለከት ሲሆን፤ በባህላዊ አውድ ደግሞ የማህበሩን ወይም የቡድኑን የጋራ እሴቶች፣ እንዲሁም በእሴቶቹና በእሴቶቹ ባለቤቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ይመለከታል፡፡ እንደ ፈቃደ (2004፡3) ገለጻ ትንተና ማለት የተሰበሰቡትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ በየቅንጣቱ በመለየትና በመመደብ ዋና የሆኑትን የይዘትና ቅርጽ ባህሪ መለየትና መተንተን ሲሆን ሌላው ደግሞ የጋራ ጭብጦች ላይ ተመስርቶ ማጠቃለያ ላይ መድረስ ማለት ነው ፡፡

በዚሁ መሠረት ጥናቱ የማህበረሰብ ዕውቀት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ለጥናቱ መተንተኛነት የተመረጡት የማህበራዊ ሥነ-ዕውቀት(Social Epistemology)፣ የማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ (Social constructionist theory)፣ ሥነ- ፋይዳ (Axiology) ንድፈ ሃሳብ፣ ተምሳሌታዊ የትንተና ዘዴ (symbolic analysis) እና አውዳዊ የትንተና ዘዴዎች (contextual analysis) ናቸው፡፡

### 3.6.1. የማህበራዊ ሥነ-ዕውቀት ንድፈ-ሃሳብ

"ሥነ-ዕውቀት (epistemology) እንዴት እንደምናውቅና ምን እንደምናውቅ የምንረዳበት ወይም የምንገልጽበት መንገድ ነው" (Crotty,1998:3)፡፡ "ሥነ-ዕውቀት፣ የዕውቀትን አፈጣጠር/ ተፈጥሮ፣ የዕውቀትን መጠነ ርዕይና የዕውቀትን አጠቃላይ መርሆዎች የሚያጠና ነው" (Guba and Lincoln, 199:201; Hamyln,1995)፡፡ "ሥነ ዕውቀት በአዋቂው (knower) አስተሳሰብ እና በሚታወቀው /እውን በሆነው (known or being) ዕውቀት መካከል ያለውን ግንኙነት ይገልፃል" (Denzin and Lincoln, 2000) ይላሉ፡፡ በማርክዚዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት ደግሞ ሥነ- ዕውቀትን እንደሚከተለው ተበይኗል፡-

> ሥነ-ዕውቀት የዕውቀት ጥናት ምርምር ንድፈ ሃሳብ ማለት ሲሆን ጥናቱ የሚያተኩረው በዕውቀት ምንነትና መሰረቶቹ ላይ በተለይም የዕውቀት ወሰንና ትክክለኛነቱን የሚመዝኑ ነጥቦችን ይመረምራል፡፡ እውነታ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር ምን ግንኙነት አለው? የዕውቀት መነሻና መሰረቶች

ምንድን ናቸው? የዕውቀትስ አመጣጡ እንዴት ነው? የዕውቀትስ ዳር ድንበሩ እስከ የት ነው? እውነቱስ በምን ይለካል? የሚሉትን ጥያቄዎች የሚያጠና የፍልስፍና ዘርፍ ሥነ ዕውቀት ይባላል፡፡ ... ዕውቀት ተፈጥሮንና አካባቢን ለመቆጣጠር የሚረዳ ነው፡፡ ዕውቀት የሚገኘው በግለሰብ ጥረት ብቻ ሳይሆን ዋናው መሰረቱ የህብረተሰቡ ፍላጎት በመሆኑ ቀጥታ ማህበራዊ ይዘት ያለው ነው፡፡ የዕውቀት ወሰን ይህ ነው የማይባል ታዳጊና ታሪካዊ መሆኑን የሚያስረዳን የሰው ልጅ ፍላጎትና ቁሳዊ ሃይል እያደገ ሲሄድ ዕውቀትም አብሮ ስፋትና ጥልቀት ማግኘቱ ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው የእውነት መለኪያው ተግባር መሆኑን ነው፡፡ አንድ ሃሳብ ትክክለኛነቱ የሚረጋገጠው ለተግባር በሚሰጠው አገልግሎት ሲሆን ይህን አገልግሎት ሊሰጥ የሚችለው የነባራዊ እውነታ ትክክለኛ ግንዛቤ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ የሰው ልጅ አካባቢውን የማንጸባረቅ ችሎታው በተግባር ግፊት የተነሳ የመንቀሳቀሻ ሚዳው በሰፋ ቁጥር ረቂቅ ሀሳቦች በአጠቃላይ የነባራዊ ሁኔታ ነጸብራቅ ናቸው (የማርክዚዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት፣ 1978፡118-119) ፡፡

ስለዚህም ይህ ጥናት በባህላዊ ግብርና ዕውቀት ላይ የሚያተኩር በመሆኑና የዕውቀት አፈጣጠርን፣ አተገባበርንና ተስተላልፎን የሚፈትሽ በመሆኑ በዚህ ጥናት የማህበራዊ ሥነ-ዕውቀት ንድፈ ሃሳብ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ማህበረሰቡ አሁን እየተጠቀመበት ያለውን ባህላዊ የግብርና እውቀት እንዴት አገኘው? እንዴትስ እየተጠቀመበት ነው? እንዴትና በምን ዘዴ ያሻሽለዋል? እንዴትስ ያስተላልፈዋል? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት የሚፈትሽ ይሆናል፡፡

### 3.6.2. የማህበረሰብ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ

የማህበረሰብ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ የተመረጠበት ምክንያት ለጥናቱ የሚሰበሰቡት ባህላዊ መረጃዎች ትርጉም የሚገኘው ከባህሉ ባለቤቶች በመሆኑ ነው፡፡ ዕውቀትም ሆነ እውነት ከማህበረሰብ ተራክቦ የሚመነጭ፣ በግለሰቦች አመለካከት ላይ የተመሰረተና ሊለወጥም

የሚችል ነው (Given, 2008፡816)፡፡ በ Given ገለጻ ዕውቀት ማሕበረሰቡ በየዕለት ተዕለት ውሎው ከሚያከናውናቸው ተግባራት በሂደት ልማድ እየፈጠረ፣ በኋላም ተቋማትን እየገነባ ይሄዳል የሚል አስተሳሰብ አላቸው፡፡ የጋራ ዕውቀትም እያንዳንዱ ሰው በተናጠል ካለው ዕውቀት ተጠራቅሞ የተገነባ ነው፡፡

በማህበረሰቡ ዕውቀት ሽግግር እውን የሚሆነው ድርጊቱን በሚተገብርባቸው አውድ ውስጥ በሚንፀባረቅበት ወቅት እና በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ነው (Sims, and Stephens, 2005፡43)። ንድፈ ሀሳቡ ዕውቀቱ በሂደት ባዋቀሯቸው የጋራ ጉዳዮች ውስጥ በግለሰብ ደረጃና በማሕበረሰብ ደረጃ ትርጉም አዘል ሆኖ ሊሰራ እንደሚችል ያነሳል፡፡ ሆኖም በግለሰብ ደረጃ ያለው ዕውቀት ከግለሰብ ግለሰብ ይለያያል (በገጽ፡43) ይላል፡፡ የማህበራዊ ቡድኖች ተራክቦ መሰረታዊ የትርጉም መፍጠሪያ ተደርጎም ይወሰዳል፡፡ ይህም በጥናቱ ተዳሷል፡፡

ይህ ንድፈ ሃሳብ ማህበረሰቡ በዕለት ተዕለት ውሎው ከሚያከናውናቸው ተግባራት በሂደት ልማድ እየፈጠረ፣ በኋላም ተቋማትን እየገነባ የሚሄድ ሲሆን እያንዳንዱ ሰው በተናጠል ያለው ዕውቀት ተጠራቅሞ የተገነባ ነው። በግለሰብም ሆነ ማህበራዊ ተቋማት ውስጥ ያለው የዕውቀት ስርጭቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማሸጋገር ቋንቋ ያለው ድርሻ ከፍተኛ ነው (Berger and Luckmann, 1966)። የማህበረሰቡ ዕውቀት ሽግግር እውን የሚሆነው በሚያከብራቸው ልዩ ልዩ ከበራዎች በአውድ ውስጥ በሚንፀባረቅበት ወቅት ነው (Sims and Stephens, 2005)። Berger and Luckmannም እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡ "It is the sum total 'what everybody knows' about a social world, an assemblage of maxims, morals, proverbial nuggets of wisdom, values and beliefs, myth, and so forth (Berger and Luckmann: 1966:65)፡፡ ስለዚህ ዕውቀት ተፈጥሯዊ ሳይሆን ማሕበራዊ ውቅር ነው (Berger and Luckmann, 1966:1). ማህበራዊ ግንባታ ዕውቀት በአንድ በተወሰነ ማህበራዊ አውድ ላይ ተመስርቶ የሰው ልጅ አእምሮ የሚፈጥረውና በአውድ ምክንያት ሊለያይ የሚችል ነው (Jaccard and Jacob, 2010:19)፡፡ በዚህ ንድፈ ሃሳብ መሰረት መረጃ አቀባዩና

አጥኚው በትርጉም ሂደቱ በጋራ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠኚው ማህበረሰብ የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን አስመልክቶ የመረጃ ትርጓሜውን በራሱ ባህል መሰረትነት ለመተርጎምና ለመተንተን አስፈላጊ ንድፈ-ሃሳብ በመሆኑ በዚህ ጥናት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሰዎች በውስጣቸዉ የሚያስቡትንና የሚፈልጉትን ሁሉ በቀጥታ ስለማይናገሩ ሀሳባቸውንና አመለካከታቸውን በተዘዋዋሪ መንገድ ለመረዳት የሥነ-ቃል ሚና ከፍተኛ ነው። በመሆኑም የአንድ ሕዝብ እምነት፣ ፍልስፍና፣ ጭንቀት፣ ተስፋ፣ ምኞት፣ ሀዘንና ደስታ በአጠቃላይ ሥነ-ልቦናዊ አስተሳሰቡ በሥነ-ቃሉ ውስጥ ስለሚገኝ እነዚህን ምንጮች በማጥናት የማህበረሰቡን አመለካከት ማወቅ ይቻላል (ፈቃደ፣ 1991፡50)።

### 3.6.3. ሥነ-ፋይዳ

አንድ ባህል፣ ባህል ሆኖ ለመዝለቅ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው አንዳች የሆነ ፋይዳ መኖር እንዳለበት የሚያመለክት ሲሆን ባህል ለማህበረሰቡ ባህላዊ ዕውቀት መሰረት ለመጣል ያገለግላል። ስለሆነም ባህል ለማህበረሰቡ ከሚሰጠው ፋይዳ አንጻር ታይቶ መዳኘት አለበት (Sims and Stephens, 2005፡174; Bascom, 1954፡334; Okpewho, 1992፡10)፡፡ ሥነ-ፋይዳ፣ የፋይዳዎችን አመጣጥ፣ ይዘት፣ ፍቺ፣ ተፅዕኖ ወዘተ. የሚያጠና የፍልስፍና ክፍል ነው፡፡ …ፋይዳ የሚገኘው ከህሊና ብቻ ሳይሆን ከሰዎች ድካምና የስራ ውጤትም ነው፡፡ ፋይዳ ሰዎች በህብረት የሚያገኙትና በህብረት የሚቀበሉት ክስተት ነው (ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት፣ 1978፡122)፡፡

ሥነ-ፋይዳ የአንድን ቡድን ቃላዊ፣ ተለምዷዊ፣ ድርጊታዊና ጽሁፋዊ ሰነዶችን በመመርመር ሰዎች እነዚህን ጉዳዮች ለመጋራት ካላቸው ጥቅም አንጻር ለምንና እንዴት በሚሉ ጥያቄዎች አማካኝነት ፈትሾ ተግባራቸውን የሚያሳይ ንድፈ ሃሳብ ነው:: ለፎክሎር ፍች መስጠትም በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ተግባር መመርመር መሆኑ መታወቅ አለበት (ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ፡ ቃላት፣1978፡175)::

ፎክሎርና የፎክሎር ትርጉም ከሰው ጋር የተሳሰረ መሆኑንና ፎክሎር የማስተማር፣ የማዝናናት፣ የማስተላለፍ እና ባህላዊ ማንነትን የማስጠበቅ ተግባር እንዳለው ይገልጻል፡፡ ተግባር/ፋይዳ ማለት በቡድኖች መካከል ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት የሚመለከት ጽንሰ-ሃሳብ ነው (Fetterman, 1998፡25-26)፡፡

ሥነ-ፋይዳ ባህል ወይም ፎክሎር በማህበረሰብ ውስጥ ማህበራዊ ፋይዳ አለው ብሎ የሚነሳ ነው፡፡ ማንኛውም ፎክሎር ለሚተገብረው ማህበረሰብ ጥቅም አለው (Green, 1997፡386):: ምክንያቱም ይህ ማህበረሰብ ይህን ፎክሎር ያለ አንዳች ጥቅም ሊተገብረው አይችልም፡፡

ሥነ-ፋይዳ በአውድ የተሰበሰበ መረጃ ከመተንተን በተጨማሪ ትርጉም ያለው ፍቺ መስጠት አስፈላጊ መሆኑን የሚደግፍ ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡ በሥነ-ፋይዳ አማካኝነት ከአውድ የተሰበሰቡ መረጃዎች በአውዳዊ ትንተና እና በተምሳሌታዊ ትንተና ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ እነዚህ የትንተና ዘዴዎችም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 3.6.4. ተምሳሌታዊ ትንተና

በማህበረሰቡ ውስጥ ተምሳሌታዊነት በተለያዩ መንገዶች ይገለጻል፡፡ ተምሳሌታዊነት እንደየአካባቢውና ባህሉ ሊለያይ ይችላል፡፡ ተምሳሌት በወካይና ተወካይ መካከል ያለውን ዝምድና የሚያሳይ ሲሆን በአነጋገር፣ በእንቅስቃሴ፣ በቁስ፣ በተግባር ሁሉ የሚገለጽ ሆኖ በውስጡም በርካታ ትርጉሞችን የያዘ ነው (Dundes, 1989:112-114; Gulsfield and Jerz, 1984፡124)። በማህበረሰቡ ፎክሎራዊ ዕውቀት ውስጥ አብዛኞቹ ምሳሌያዊ ንግግሮች በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚወክሉት ነገር እንደሚኖር (Bayleyegn, 2009) ይገልጻል። "የአንድ ባህል ተምሳሌታዊነት የሚገለጸው ፎክሎሩ በተገለጸበት በዚያው ባህል ውስጥ ነው" (Bronner, 2007፡63):: "ተምሳሌት የሚባለው የአንድን ነገር ተጨባጭነት ወይም ተዛማጅነት ስዕላዊነትን በሚከስት ሁኔታ የሚያቀርብ ረቂቁን ሃሳብ የሚያብራራ የነገር ወይም የሁነት መግለጫ ነው" (Okpewho, 1992፡101)::

ተምሳሌታዊነት በቋንቋ፣ በቁሳቁስና በክዋኔዎች ይገለፃል፤ ዋና ጉዳዩ የቱ ተምሳሌት፣ የቱ ተራ እንደሆነ መለየቱ ላይ ነው፤ ምክንያቱም ለአንዱ ተምሳሌት የሆነው ለሌላው ተራ ነገር ሊሆን ይችላል፤ ተምሳሌት በውስጡ በርካታ መረጃዎችን የያዘ ነው (Berger and Luckmann, 1966:40; Gusfield and Jerz, 1984)፡፡ እምነቱ፣ ፍልስፍናው፣ እውቀቱ፣ በቁሱ፣ በአነጋገሩ፣ በእንቅስቃሴው፣... ይገለጻል፡፡

እንደ Berger and Luckmann, አገላለጽ፣ በቋንቋ ተምሳሌቶች ይፈጠራሉ፤ ይገልፃሉም፡፡ የተፈጠሩት ተምሳሌቶችም ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገሩ በቋንቋ ሲገለፁ ይኖራሉ፡፡ ተምሳሌታዊ ነው ማለትም ፍቺ አዘል ሆነ ማለት ነው (Berger and Luckmann, 1966:40)፡፡ ይህ ፍቺ የተባለው በተምሳሌታዊ ነገር ውስጥ የታቀፈውና ለግለሰብም ሆነ ለማሕበረሰብ አገልግሎት የሚሰጥ ዕውቀት ነው፡፡ ከዚህም በላይ በተምሳሌታዊነቱ እና በፍቺው ዝምድና ላይ አንዳች የሚቀርብ ምክንያት መኖሩ ስለማይቀር ያለውን ዕውቀት ተጨባጭ ያደርገዋል፡፡

ተምሳሌቶች የህዝቡን አንድነት ለማሳየት፣ ለመጠበቅና ለማቆየት ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ (Bell, 1997:61)፡፡ በዚህ ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎችም ባመዛኙ ከሚያሳዩት ቅርፅ ወይም ከአውድ፣ ከተግባርና ከሚኖራቸው ተምሳሌታዊ ፍች አንፃር ተተንትነዋል፡፡ ስለዚህም ይህ ጥናት በማህበረሰቡ ዕውቀት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ይህ የመተንተኛ ዘዴ ለጥናቱ ተስማሚ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### 3.6.5. *አውዳዊ ትንተና*

ፎክሎር ሲጠና በአውድ ውስጥ መጠናት አለበት (Dorson, 1972; Paredes and Bauman, 1972; Doundes, 1980; Bauman, 1992; Workman, 1993)፡፡ ከላይ በ 3.1. ስር ለመግለጽ እንደተሞከረው ለፎክሎር ጥናት ዋናውና መሰረታዊ ነገሩ አውድ ነው፡፡ በአውዳዊ ትንተና መሰረት ተመራማሪው የሚያጠናውን ማህበረሰብ አካባቢና ባህል በትክክል እንዲያውቅና እንዲረዳ ያደርገዋል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የፎክሎር ትርጉም በአውድ ውስጥ ምን ማለት እንደሆነ፣ እንዴት እንደሚጠቀምበት፣ እንዴት

እንደሚረዳው፣ እንዴት ፍቺ እንደሚሰጠው፣ ሊያውቅ አይችልም፡፡ በፎክሎር ላይም ጥልቀት ያለው ጥናትና የተሟላ ትንታኔ ማድረግ አይችልም (Dundes, 1980)::

አውዳዊ ትንተና፣ ከአውድ የተሰበሰቡ መረጃዎች የሚተነተኑበት ዘዴ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው የፎክሎር ጥናት ትንተና በተፈጠረበት አካባቢና ማህበረሰብ፣ በራሱ ዕውቀት ላይ ተመስርቶ፣ የማህበረሰቡን አመለካከት፣ አስተሳሰብ፣ ስሜት ከራሱ ከህበረተሰቡ ጋር አገናኝቶ መጠናት ስላለበት ነው (Bauman,1983; Jackson,1986፡4)፡፡ አውድ በሥነ-ሰብ ጥናት ውስጥ ላሉ ሁሉም ተመራማሪዎች ወሳኝ ጉዳይ ቢሆንም ለሁሉም የጥናት መስክ ግን ወሳኝ እና በተመሳሳይ መንገድ የሚያገለግል አይደለም። አውድ ፎክሎር የሚከወንበት ወሳኝ ማህበራዊ ሁነት እንደሆነ ተገልጿል (Sims and Stephens, 2005፡137)። ማንኛውም ድርጊት (ክዋኔ) ሲተነተን የድርጊቱ አውድ መገለጽ አለበት (Okpewho, 1992:10; Ben-Amos, 1993:1; ፈቃደ፣ 1991:37)፡፡

አውድ ሲባል ከዋኙ፣ ጊዜው፣ ቦታው፣ የአከዋወን ሁኔታውና ሂደት፣ የክዋኔው ታዳሚ፣ በከዋኙና በታዳሚው መካከል ያለው መስተጋብርና ለክዋኔው መነሻ የሆነውን ባህል ሁለንተናዊ ሁኔታን ሁሉ ያካትታል (Dorson,1972:46)፡፡ በአውዳዊ ትንተና መሰረትነት አጥኚው የሚያጠናውን ማህበረሰብ ማንነት፣ ባህል፣ እምነት፣ ልማድ፣... በአጠቃላይ ሁለንተናውን ለማወቅ አውድ ከፍተኛውን ሚና ይወጣል፡፡ አንድ አውዳዊ አጥኚ የሰበሰበውን መረጃ ከአውድ ውጭ ለመተንተን ቢሞክር ችግር ሊገጥመው ይችላል (Ben-Amos,1993፡210-211)፡፡ Ben-Amos, ኢያይዘውም ከመስክ የተሰበሰበው መረጃ በጥሬው ከመተንተን ይልቅ አውዳዊ ትንታኔ ወይም ትርጓሜ ቢሰጥ የተሻለ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

አውዳዊ አጥኚ ቃሉን ከአውዱ ለይቶ ማየት የለበትም፣ ያለበለዚያ ችግር ይገጥመዋል (Ben-Amos, 210-211)፡፡ ይህ እንዳይሆን ድርጊቱ ለተከወነበት አውድም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል (Dundes, 1980:20-32)፡፡ ይህንንም ዘዴ ከኢትኖግራፊ ጋር በማጣመር አስቸጋሪውን የመስክ ስራ ውጤታማ ለማድረግ ቁልፉ አውዳዊ ጥናት ነው፡፡

የዚህ ጥናት መሰረታዊ ነገሩ አውድ ነው፡፡ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት አካባቢውንና ባህሉን መሰረት የሚያደርግ በመሆኑን በአውድ ይጠናል፡፡ ስለዚህ አውዳዊ ትንተናን መሰረት በማድረግ ከባህላዊ አውዱ፣ ከማህበራዊ አውዱና ከአውዳዊው ሁኔታ በመነሳት ትርጉም ይሰጣል፡፡ አውድ የመረጃ መሰብሰቢያ መተንተኛና መተርጎሚያ መሰረት ነው፡፡

በዚህ ዘዴ አማካይነት የሚተነተን መረጃ ሁሉን አቀፍ ክዋኔዎች የሚታዩበት ነው፡፡ ስለዚህ የአውዳዊ ትንተና ትኩረት ክዋኔን ማዕከል ያደረጉ መረጃዎችን ከባህላዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች አኳያ የከዋኙን አከዋወን ሁኔታ ከጊዜና ቦታ አንጻር የሚገለጽበት መንገድ ነው (Dorson, 1972)። አውድ ማለት በሰፋት ሲታይ ስለ አንድ ድርጊት ክንውን የሚገልጽ ሲሆን በፎክሎር ጥናት ውስጥ ደግሞ ንድፈ ሀሳቦችንና ዘዴዎችን ይመለከታል (Ben-Amos, 2006; Goldstein, 2004)።

በፎክሎር ጥናት ውስጥ የአውድ ግንዛቤ ያለውንና የታየውን መረጃ መግለጽ ብቻ ሳይሆን ባህላዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን አካቶ መተርጎምንና መተንተንን መሆኑን ሲያስረዱ የፎክሎር ትርጉም ከማብራራት ይልቅ ወደ ትርጓሜ ማደግ አለበት፡፡ ይህንን ትርጓሜም ሊወስኑ የሚችሉ የማህበራዊ፣ የባህላዊና የሁኔታ አውድ ናቸው (Ben-Amos, 1993:210-211)፡፡

አውዳዊ አጥኚ የፎክሎርን ሃሳብ በቃሉ ላይ ብቻ ሳያተኩር በጊዜው ሁነቱን፣ ወቅቱን፣ የተከወነበትን ባህል ዕውቀት ተስተላልፎ ማየት ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ ሁሉንም ክዋኔ ወይም እንቅስቃሴ የቃሉን የተለየ ሁነት፣ ለሁሉም ፎክሎራዊ ሁነት አካባቢያዊ ሁኔታውን፣ ለክዋኔው (የቡድን/አረም፣ አጨዳ፣ ጉልጓሎ/ና የግል/ እርሻ፣ አረም፣..) መነሻ የሆነው ነገር ሁሉ ከአውዱ ጋር መመዝገብ አለበት፡፡ የአንድን ማህበረሰብ ያለፈና የአሁኑን ዕውቀት በፎክሎር አማካኝነት መመርመር የሚቻለው ጥናቱ በማህበራዊና ባህላዊ አውድ ላይ ማካሄድ ሲቻል ነው (Bauman, 1983)፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ የአጠናን ስልትና ዘዴዎች በሚለው ክፍል ውስጥ ለጥናቱ ተስማሚ የሆነው አይነታዊ የጥናት ዘዴ ሆኖ ለዚህ የጥናት ዘዴ የሚሆኑ መረጃዎች በቀዳማይና በካልዓይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችም በሙሉ በቀጥታ ከተፈጥሯዊ አውድ የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ እነዚህ መረጃዎችም በፎቶ ግራፍ፣ በቪዲዮ፣ በመቅረጸ ድምጽና በማስታዎሻ ደብተር ተሰብስበዋል፡፡ ይህ መረጃ ሲሰበሰብም መረጃ አቀባዮችን መምረጥ አስፈላጊ በመሆኑ ለጥናቱ የሚሆን መረጃ አቀባዮች ቁልፍና ሌሎች መረጃ አቀባዮች ተመርጠው መረጃውን ሰጥተዋል፡፡

ይህ የተሰበሰበው መረጃም የሚተነተንበት የመተንተኛ ንድፈ ሃሳብ የማህበራዊ ሥነ-ዕውቀት ንድፈ-ሃሳብ፣ የማህበረሰብ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ፣ ሥነ-ፋይዳዊ ንድፈ-ሃሳብ፣ ሲሆኑ በእነዚህ ንድፈ ሀሳቦች መሰረትነት የተሰበሰበው መረጃ በተምሳሌታዊና በአውዳዊ መተንተኛ ዘዴዎች መረጃው ተተንትኖ እንደቀረበ የተገለጸበት ነው፡፡

# ምዕራፍ አራት

# አካባቢያዊ ዳራ

## 4.1. የአዊ ብሔረሰብ ታሪክ፣ መልካምድራዊ ሁኔታ፣ የዞኑ የህዝብ አሰፋፈር፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

በዚህ ርዕስ ስር የአዊ ብሄረሰብ ታሪክ፣ መልክዓ ምድራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ገጽታ፣ የዞኑ የትምህርትና የጤና ሽፋን በቅደም ተከተል በዝርዝር ቀርቧል፡፡

### 4.1.1. የአዊ ብሔረሰብ ታሪክ

በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት አራት የቋንቋ ነገዶች አንዱ የኩሽ ህዝብ ነው፡፡ የኩሽ ተናጋሪዎች በኢትዮጵያ ቀደምት ነዋሪዎች በመሆናቸው ኢትዮጵያንም የኩሽ ሀገር ብሎ መጥራት ይቻላል (Tadsse, 1972፡5፣ ባህሩ፣ 1992፡5)፡፡ አዊ ደግሞ ከኩሽ ቋንቋ ተናጋሪዎች አንዱ ነው፡፡ በቀድሞው ጊዜ አገው በመባል የሚታወቀው ህዝብ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በተለያዩ ቦታዎች ሰፍሮ የሚገኝ ነው፡፡ ከአክሱም ስልጣኔ ጋር ከተቀላቀሉት ውጪ የአገው ህዝቦች እንደሆኑ "በተለያዩ ታሪክ ጸሐፍት"[25] የሚገለጹት የተለያዩ አሃዞች ያሏቸው ቢሆኑም፣ አንደኛ "ቅማንት"፣ ሁለተኛ "ፈላሻ"፣ ሶስተኛ "አዊ" አራተኛ "ወይጦ" አምስተኛ "ኩምፈል"፣ ስድስተኛ "ሀሚር"፣ ሰባተኛ "ቢለን"፣ ስምንተኛ "በዋግ ላስታ የሚኖሩ" አገው ናቸው (አያሌው፣1997፡32-33)፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ጸሐፊው ከስምንቱ የአገው ቡድኖች ውጪ "ከሌላ ምንጭ አገኘሁት"[26] በማለት የላስታ ዋግ አገው ህዝቦች የቋንቋቸው ሥር አንድ ቢሆንም በሶስት እንደሚከፈሉና እነሱም የላስታ አገው፣ የዳሞት አገውና የሀልሀል በገስ አገው ናቸው ይላሉ (አያሌው፣1997፡32-33)፡፡ ይህን በተለያየ መንገድ የተገለጸውን ሃሳብ ስንመለከተው የአዊ ህዝብ በቀድሞው ጊዜ አገው በመባል የሚታወቀው ህዝብ በሰሜኑ

[25] ዶ/ር አያሌው በተለያየ ታሪክ ጸሐፍት ቢሉም ጸሐፍቱን ሲጠቅሱ አይስተዋሉም፡፡
[26] ምንጩ ግን አይጠቀስም

የኢትዮጵያ ክፍል በተለያዩ ቦታዎች ሰፍሮ የሚገኝ ነው፡፡ ከነዚህ ቦታዎች አንዱ በምዕራብ ጎጃም የሚገኘው የዳሞት አገው የአገው ምድር አውራጃ የአሁኑ አዊ ዞን ነው፡፡ የአገው መገኛ ቦታዎችም ከረን፣ ዋግ ሰቆጣና ላስታ ላሊበላ፣ ሰሜን ምስራቅ ጎንደርና ምዕራብ ጎጃም ናቸው (Melakneh, 1990፡8; ኢያሴው፣ 2007[27]፡32-33)፡፡


የአዊ ዞን አገዎች አሁን ወደሚገኙበት አካባቢ ከላስታ ላሊበላ የመጡ እንደሆኑ በአፈ ታሪክ ይነገራል፡፡ የአገው ሰባት ወንድማማቾች ከላስታ ላሊበላ ተነስተው ለጎሽና አንበሳ አደን ወደዚሁ ቦታ መጡ፡፡ አካባቢውን ሲያዩት በደን የተሸፈነ፣ ለምና ሰው ያልሰፈረበት ሆኖ በማግኘታቸው በጫካ ውስጥ የሚገኙቱን ማርና የዱር እንስሳት እያደኑ በመመገብ ከ6-7 ወር ያህል እየዞሩ አካባቢውን ተመለከቱት፤ መረመሩ፡፡ ከዚያም ሰፋፊ ቦታዎችን በመያዝ ወደ አገራቸው ተመልሰው ሚስቶቻቸውን፣ ልጆቻቸውንና ጓዛቸውን በማምጣት በተራራቀ ቦታ ማለትም አንከሻ፣ ባንጃ፣ ኳኩሪ፣ መተከሊ፣ ቻሪ፣ አዜኒ፣ እና ዘጋሚ[28] በሚባሉ አካባቢዎች ሰፈሩ፡፡ ቦታዎችም በሰባቱ ወንድማማቾች ሲጠሩ አሁንም በስማቸው ከወረዳ እስከ ቀበሌ የተሰየሙት ሁሉ መጠሪያ ሆኖ ቀረ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ "የአገው አዊ ህብረተሰብ ከወሎ ላስታ ላሊበላ በ16ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ ወደ አገው ምድርና መተከል አካባቢ ሰፈሩ" በማለት አቶ የትዋለ[29] ይገልጻሉ፡፡ ሌሎች ጸሐፍትና አጥኚዎችም በዚህ ሃሳብ ይስማማሉ (ዋለ፣ 2001፡5፣ ኢያሴው፣ 2007፡33-34፣ ዝክረ አዊ፣ 1998፡21፣ Melakneh,1990፡12)፡፡

### 4.1.2. የአዊ ብሔረሰብ ዞን መልካ ምድራዊ ሁኔታ

የአዊ ዞን በአማራ ክልል ከሚገኙት አስራአንድ ዞኖች አንዱ ነው፡፡ የአዊ ዞን በብሔረሰብ ዞንነት የተዋቀረው በ1986 ዓ.ም ሲሆን የዞኑ ዋና ከተማ እንጅባራ ከመዲናችን አዲስ አበባ ባህርዳር መስመር ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በ444 ኪሎ ሜትር፣ ከክልል ከተማው ከባህርዳር ደቡብ ምዕራብ በ132 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ

[27] የአውሮፓውያን አቆጣጠር ነው
[28] በአገውኛ ቋንቋ የተሰጡ ስያሜዎች
[29] አቶ የትዋለ ቃለ መጠይቅ፣ ቲሊሊ፣ ከመስክ መልስ ማታ ላይ ስለውሎዬ ስናወራ የነገሩኝ፡፡

ይገኛል፡፡




ካርታ 2:- የአዊ መስተዳድር ዞን ካርታ
ምንጭ፡- የአዊ ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር መምሪያ ግንቦት 2006

የአዊ ብሔረሰብ ዞን የቆዳ ስፋት 857,886 ሄክታር ወይም 8,588 ካሬ ኪሎ ሜትር ሲሆን ከክልሉ የቆዳ ስፋትም 5.2% ያህል ይሸፍናል፡፡ ዞኑ በአሁኑ ሰዓት በስምንት የገጠር ወረዳና በሶስት የከተማ አስተዳደሮች በድምሩ በ11 ወረዳዎች እንዲሁም በ29 የከተማና በ179 የገጠር በጠቅላላው በ208 የቀበሌ አስተዳደሮች የተዋቀረ ነው፡፡ ዞኑ በሰሜን ከሰሜን ጐንደር ዞን አስተዳደር፣ በምዕራብ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልል፣ በደቡብ ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል፣ በምስራቅ ከምዕራብ ጎጃም ዞን አስተዳደር ይዋሰናል (የአዊ ዞን ገ.ኢ.ል.ት.መምሪያ፣ 2004፡3)[30]፡፡

የዞኑ ጠቅላላ ስፋት 857,886 ሄክታር ወይም 8,588 ስኴየር ካሬ ኪሎሜትር ውስጥ 288,300 ሄክታር (33.6%) ለመኸር እርሻ የዋለ ነው፡፡ 23,072 ሄክታር መሬት ደግሞ በሰው ሰራሽ ደን የተሸፈነ ሲሆን 228,135 ሄ/ር በተፈጥሮ ደን ተሸፍኗል፡፡ በዚህ መሰረት 251,207 ሄክታር (29.28%) መሬት በደን የተሸፈነ፣ 217138 ሄክታር (25.33%) ለግጦሽ የዋለ ሲሆን ቀሪው 102187 ሄክታር (12.39%) ለሌሎች ተግባራት የሚወል ነው (የአዊ ዞን ገ.ኢ.ል.ጽ/ቤት፣ 2004፡3)፡፡

በዞኑ ለመስኖ፣ ለመጠጥና ለሀይል ማመንጫ አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉና ዓመቱን ሙሉ ያለማቋረጥ የሚፈሱ 20 ትላልቅና ከ200 በላይ ትናንሽ ወንዞችና ምንጮች ይገኛሉ፡፡ ተፈጥሮአዊ የሆኑ የመስህብ ሀብቶችም በዞኑ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እነዚህም ሃይቆች፣ ፏፏቴዎች፣ ዋሻዎች፣ ተራራዎች፣ የማዕድን ውሀ፣ ማዕድናት (ወርቅ፣ እብነበረድ፣ የኖራ ድንጋይ፣ ቀይ የሸክላ አፈር እና የግንባታ አሸዋ ሲገኙ በስፋት የሚበቅለው የቀርከሀ ተክል ደግሞ ሌላው የተፈጥሮ ሀብት ነው (የአዊ ዞን ገ.ኢ.ል፣ 2004፡3) ፡፡

የአዊ ዞን መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ከባህር ጠለል በላይ ከ700-2920 ሜትር ከፍታ አለው፡፡ የአየር ንብረቱ 17% ደጋ፣ 72% ወይናደጋ እና 11% ቆላ ነው፡፡ የዝናብ

[30] የአዊ ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር መምሪያ

መጠኑ በዓመት በአማካይ ከ800-2700 ሚሊ ሜትር፣ የሙቀት መጠኑም ከ15-24 ዲግሪ ሴልሽየስ ይደርሳል (የአዊ ዞን ገ.ኢ.ል.ጽ/ቤት፣ 2004፡3)፡፡

### 4.1.3. የአዊ ብሔረሰብ ዞን ህዝብ አሰፋፈር

በኢትዮጵያ ሕዝብና ቤት ቆጠራ እ.አ.አ. 2007 መረጃ መሰረት በዞኑ ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ብዛት ወንድ፣ 491,865 ሴት፣ 491,077 በጠቅላላው 982,942 ነው፡፡ ከዚህ ውስጥ የከተማ ነዋሪ ወንድ 61,089 ሴት 61,925 ድምር 123,014፤ በገጠር የሚኖረው ደግሞ ወንድ 430,776 ሴት 429,152 ድምር 859,928 ነው(2010፡10)፡፡ ይህም ከአጠቃላይ የዞኑ ህዝብ አብዛኛው በግብርና የሚተዳደርና የገጠር ኗሪ መሆኑን ያሳያል (የአዊ ዞን ገ.ኢ.ት. ል.መምሪያ፣ 2007)፡፡

### 4.1.4. የአዊ ብሔረሰብ ዞን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ

አብዛኛው የአዊ ብሔረሰብ የሚተዳደረው በግብርና ነው፡፡ ከአዊ ብሔረሰብ ዞን ውስጥ አብዛኛው ህዝብ የሚኖረው በዞኑ ገጠራማ ክፍል በመሆኑ መተዳደሪያው ግብርና ነው፡፡ ይህንን የግብርና ስራም ከቀደሙት እናትና አባቶቹ የወረሰው ዕውቀት መሆኑን የተለያዩ ጸሐፍት ይገልጻሉ፡፡[31] አገዎች የእህል ዘሮችን በማላመድና በማስተዋወቅ ረገድ የመጀመሪያዎቹ የኢትዮጵያ ህዝቦች ናቸው፡፡ ይህን ሃሳብ Gamst እንደሚከተለው ያጠናክራሉ፡ ቀደምቶቹ የአገው ህዝቦች በደቡብ አረቢያ የሚታወቁትን የእህል ዘሮች እንደ ስንዴና ገብስ ያሉትን የእህል ዘሮች ያመርቱ ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አገር በቀል የሆኑትን ጤፍ፣ ዳጉሳ፣ ሰሊጥ፣ ኑግ የመሳሰሉትንም አላምደዋል፡፡ በዚህም ለኢትዮጵያ አስፈላጊ የሆኑ እህሎችን በማላመድና በማምረት በኩል የቀዳሚነቱን ድርሻ አገዎች ይወስዳሉ (Gamst, 1968:8)፡፡

በግብርናው ቀዳሚ የሆነው ይህ ህዝብ የመስኖና የዝናብ ውኃን በመጠቀም የተለያዩ አዝርዕትን፤ የደጋ ፍራፍሬዎችንና አትክልትን በማምረት ለገበያ ያቀርባል፤ በምግብነትም ይጠቀማል፡፡ እነዚህንም ምግቦች በተለያየ ጊዜ ያመርታል፡፡ በዞኑ

[31] McCann, 1995; Houston 1926

በዓመት ሶስት ጊዜ ምርት ይመረታል፡፡ ይህም በበጋው ወራት ሁለት ጊዜ በጥቅምትና በመጋቢት በመስኖ ውኃና በክረምት ወራት በዝናብ ውኃ ነው፡፡ በዞኑ ሁለት አይነት ድንች ይመረታል፡፡ አንደኛው በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ የሚታወቀው አገሬ ድንች ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በብሔረሰቡ ብቻ የሚመረተውና ለምግብነት የሚውለው የአገው ድንች በመባል የሚታወቀው ነው (Desalgen, 2001፡10)፡፡ እንዲሁም ጤፍ፣ አጃ፣ ገብስ፣ በቆሎ፣ ሽንኩርት፣ ኑግ፣ ተልባና ቅመማ ቅመም የመሳሰሉት በስፋት ይመረታሉ (ብርሃኑ፣ 1999፡12)፡፡

ከግብርናው ጎን ለጎን እንስሳትን በማርባት ለግብርና ሥራ፣ ለንግድ፣ ለምግብነትና ለትራንስፖርት ይጠቀሙባቸዋል፡፡ በዞኑ ውስጥ የሚገኙት እንስሳትም 1,016,698 የዳልጋ ከብት፣ 304,346 በጎች፣ 129,208 ፍየሎች፣ 4275 አህያ፣ 9208 በቅሎ፣ 81175 ፈረስ፣ በድምሩ 138658 የጋማ ከብቶች፣ እንዲሁም 488,513 ዶሮ ናቸው (ባህልና ቱሪዝም፡ 2006፡ 14)፡፡

የዞኑ ማህበረሰብ ከዚህ ጎን ለጎን የዕደ ጥበብ ሥራዎችንም በስፋት ይሠራል፡፡ የሸክላ፣ የሽመና፣ የብረታብረት፣ የቀንድ፣ የቀርከሃ ሥራዎችና የጭራ ሥራ በዞኑ በስፋት የሚከናወኑ ናቸው፡፡ ከሸክላ ሥራ ማድጋ (እንስራ)፣ ዋዲያት፣ ድስት፣ ምጣድ፣... ከብረታ ብረት ማረሻ፣ ቢላዋ (ካራ)፣ መጥረቢያ፣ መኮትኮቻ...፣ ከቀንድ ዋንጫ፣ መለኪያ፣ የቢለዋ እጀታ፣ ዋገምት፣ መንጠቂያ፣ ቆርሸ[32]...፣ ከቀርከሃ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ጐተራ፣ ቅርጫት፣ ዘንቢል...፣ ጭራ ይሠራሉ፤ የተወሰነ ህብረተሰብ እነዚህን በመስራትና በመሸጥ ብቻ ሲተዳደር አብዛኛው ደግም ከእርሻ ጎን ለጎን የተለያዩ የእደጥበብ ውጤቶችን በመስራትና በመሸጥ ገቢውን ያዳብራል (ብርሃኑ፣ 1999፣14-15)፡፡

በዞኑ ውስጥ የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚኖሩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ብዛት ያላቸው የአማርኛና የአዊኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው፡፡ አማርኛ

---

[32] የእንዝርት ራስ

ተናጋሪዎች 38%፣ አዊኝ ተናጋሪዎች 60%፣ ኦሮሞኛ 0.1%፣ ጉምዝ ተናጋሪዎች 0.7% እንዲሁም ሌሎች 1.2% ናቸው (የአዊ ዞን ገ.ኢ.ት. ል.መምሪያ[33]፣ 2007)፡፡

ከዚህም ሌላ በዞኑ ውስጥ ከሚኖረው ህዝብ 94.4% የሚሆነው የኦርቶዶክስ እምነትን፣ 4.5% የእስልምናን፣ 1.1% የሚሆነው ደግሞ ሌሎች ሃይማኖቶችን ይከተላል (ባህልና ቱሪዝም፡ 2006፡14)፡፡

## 4.2. የጓጉሳ ሽኩዳድ/ የተጠኚ ወረዳ አካባቢያዊ ዳራ

በዚህ ርዕስ ስር የተጠኚ ወረዳው የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ የህዝብ አሰፋፈር፣ የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ ህዝብ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ ህዝብ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታ፣ ባህላዊ አደረጃጀትና ማህበራዊ ግንኙነቶች በዝርዝር የቀረበበት ክፍል ነው፡፡


### 4.2.1. የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ የህዝብ አሰፋፈርና መልካምድራዊ ሁኔታ

የወረዳ ከተማው ቲሊሊ ከአዲስ አበባ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ 427 ኪ.ሜ.፣ ከክልል ከተማው ከባህርዳር ደቡብ ምዕራብ በ149 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ፣ ከዞን ከተማ እንጅባራ ደግሞ በደቡብ ምዕራብ በ17 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ በሰሜን ከባንጃ ወረዳ፣ በምዕራብ ከአንከሻ ወረዳ፣ በምስራቅ ሰከላ ወረዳ፣ በደቡብና ደቡብ ምስራቅ ከቡሬ ወረዳ፣ በደብብ ምዕራብ ከወንበርማ ወረዳ ጋር ይዋሰናል፡፡

የወረዳው የቆዳ ስፋት 285,764 ካሬ ኪሎሜትር ወይም 2,857.6 ሄክታር ነው፡፡ ወረዳው በአንድ የከተማና በ13 የገጠር ቀበሌዎች የተዋቀረ ነው፡፡ ከጠቅላላ የቆዳ ስፋቱ በመታረስ ላይ ያለው የመሬት መጠን 18429.29፣ ወደፊት ሊታረስ የሚችል

[33] ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር መምሪያ

393.5፣ ሊታረስ የማይችል 1489.45፣ በደንና ቁጥቋጦ የተሸፈነ 3333.725፣ በቤቶች ግንባታ ላይ የዋለ 1735.975 ነው፡፡[34]




ካርታ 3፡- የጓጉሳ ሽኩዳድ ካርታ

ምንጭ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጂ.አይ.ኤስ

---

[34] እ.አ.አ. በ2007 ሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ላይ ወረዳው አዲስ በመሆኑ እንደወረዳ ተይዞ አልተቆጠረም፡፡ በወቅቱ ወረዳው ከባንጃ ሽኩዳድ ጋር የተካተተ ነበር፡፤ በዚህም ምክንያት የወረዳውን መረጃ የወሰድሁት ከወረዳው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ጽሕፈት ቤት ነው፡፡

የወረዳው የመሬት አቀማመጥ 24% ሜዳማ፣ 68% ወጣ ገባ፣ 2% ረግረጋማ፣ 6% በውኃ የተሸፈነ ነው፡፡ የወረዳው የአፈር አይነትም ጥቁር አፈር 2%፣ ቀይ አፈር 43%፣ ቡናማ አፈር 55% ነው (የጓ/ ሽ/ ወረዳ ገ/ ኢ/ ል/ት/ ጽ/ቤት አመታዊ መጽሔት፤ ሰኔ 2007)[35]፡፡

ወረዳው ከባህር ጠለል በላይ ከ2,040- 2,900 ሜትር ይሆናል፡፡ የአየር ንብረቱም 70% ደጋማና 30% ወይና ደጋ ሲሆን አማካኝ የሙቀት መጠኑ ከ10-28 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ነው፡፡ ዓመታዊ የዝናብ መጠኑም ከ 1540 - 3572 ሚ.ሜ ይደርሳል (የጓ/ ሽ/ ወረዳ ገ/ ኢ./ል/ት/ጽ/ቤት አመታዊ መጽሔት፤ ሰኔ 2007)፡፡ ይህም የተለያዩ የአዝርዕት አይነቶችን ለማብቀል ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡

### 4.2.2. የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ ህዝብ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

በጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ የሚኖረው የብሔረሰቡ አባል እንስሳትን በማርባት ለምግብነት (ወተትና ስጋን)፣ ለእርሻ ስራ (ፈረስ፣ ላምና በሬን በማጣመድ)፣ ለመጓጓዣነት (ፈረስና አህያን ለሰውና ለእቃ) እንዲሁም በመሸጥ ከፍተኛ የሆነ የገቢ ማግኛ አድርጎ ይጠቀማል፡፡

በዚህ መሰረት በወረዳው የሚገኘው እንስሳት ብዛት የዳልጋ ከብቶች 56544፣ የጋማ ከብቶች 16688፣ በግና ፍየል 35342፣ ዶሮ 34346፣ ናቸው፡፡ ገበሬዎች የመስኖና የዝናብ ውኃ በመጠቀም በክረምት አንድ ጊዜ በበጋው ደግሞ ሁለት ጊዜ በጠቅላላው በዓመት ሶስት ጊዜ የተለያዩ አዝርዕትን፤ የደጋ ፍራፍሬዎችንና አትክልትን በማምረት ለገበያ ያቀርባሉ፤ በምግብነትም ይጠቀማሉ፡፡ 88% የሚሆነው የወረዳው ህዝብ በ13 የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ የሚኖር በመሆኑ በእርሻ ሥራ የሚተዳደር ነው፡፡ በደጋውና በዝቅተኛ ወይና ደጋማ አካባቢ የሚኖረው የወረዳው ህዝብ በፈረስ የሚያርስ ሲሆን ሌላው ማህበረሰብ ፈረስን ከበሬ ወይም ከላም ጋር በማጣመድ፣ እንዲሁም በሞቃታማው የአየር ንብረት አካባቢ የሚኖረው ደግሞ በበሬ ብቻ የሚያረስ ነው፡፡

35 የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ጽሕፈት ቤት

በወረዳው ውስጥ በርካታ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የመስህብ ሀብቶች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም 13 የተፈጥሮ የአዲስ አለም ዋሻዎች፣ 4 ጥንታዊ ገዳማት፣ 4 ፏፏቴዎች፣ 1 የማእድን ውኃና 4 የአምቦ ውኃዎች፣ የተፈጥሮ ደኖችና ሶስቱ የኩርብ ተራሮች ናቸው (የጓ/ ሽ/ ወረዳ ገ/ ኢ/ት/ል/ት/ጽ/ቤት አመታዊ መጽሔት፣ ሰኔ 2007)፡፡

### 4.2.3. የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ ህዝብ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታ

በወረዳው አንድ አፀደ ህጻናት የሚገኝ ሲሆን በደረጃ ሁለት 23 ወንድ፣ 18 ሴት በድምሩ 41 ተማሪዎች ና 3 ሴት መምህራን፣ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፕግራም 475 ተቋማት ሲኖሩ በነዚህ ትምህርት ቤቶችም 116,682 ወንድ፣ 121,321 ሴት፣ በድምሩ 238,003 ተማሪዎች እና 3,657 ወንድ፣ 2,656 ሴት፣ በድምሩ 6,313 መምህራን ይገኛሉ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ከ9-10ኛ ክፍል ባለው 13 ተቋሞች አሉ፡፡ በዚህ ውስጥም 10,769 ወንድ፣ 12,811 ሴት፣ በድምሩ 23,850 ተማሪዎችና 678 ወንድ፣ 147 ሴት፣ በድምሩ 825 መምህራን ይገኛሉ፡፡ የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ተቋም አንድ ብቻ ሲሆን 3,914 ወንድ፣ 3,148 ሴት፣ በድምሩ 7,062 ተማሪዎች እና 310 ወንድ፣ 39 ሴት፣ በድምሩ 349 መምህራንን የያዘ ነው፡፡

ጤናን በተመለከተ በአሁኑ ሰአት አራት ጤና ጣቢያና አስራ አራት የጤና ኬላዎች በድምሩ አስራ ስምንት አገልግሎት የሚሰጡ የጤና ተቋማት ያሉ ሲሆን በውስጣቸውም 45 ወንድ 33 ሴት በድምሩ 78 ባለሙያ፣ 39 ወንድ፣ 27 ሴት በድምሩ 66 ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች እንዲሁም 42[36] የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ይገኛሉ፡፡ (የጓ/ ሽ/ ወረዳ ገ/ ኢ/ት/ል/ት/ጽ/ቤት አመታዊ መጽሔት፣ ሰኔ 2005)፡፡

የጓጉሳ ሽኩዳድ ማህበረሰብ እንደሌሎቹ የዞኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ሁሉ የበርካታ ባህላዊ እውቀቶች ባለቤት ነው፡፡ በአካባቢው በብዛት የሚበቅለውን የቀርከሃ ተክል በመጠቀም ወንዶች ባህላዊ እቃዎችን ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ መደርደሪያ፣ የእህል ጎተራ፣ ጋዘና፣ አገልግል፣ የእንጀራ ማስቀመጫ ሌማትና የእንጀራ መብያ ቀለምሻሽ፣ ማንኪያ...

[36] ሁሉም ሴቶች ናቸው

ይሰራሉ፤ ከበሬና ከላም ቀንድ መለኪያ፣ ዋንጫ፣ ቆርሽ፣ መቀንጠቢያ፣ ዋገምት፣ የልብስ ቁልፍ… ይሰራሉ፤ ሴቶቹም ከሳር ስፌቶችን መሶብ፤ አገልግል፤ ላዳን[37]፣ ቁና፣ ወራንታ[38]፣ ሰፌድ… ይሰፋሉ፡፡ ከነዚህ ባህላዊ እውቀቶች በተጨማሪ ገበሬው ባህላዊ የእርሻ መሳሪያዎችን ተጠቅሞ በባህላዊ ዘዴ ሰብልን ያመርታል፣ በባህላዊ ዘዴ የሰውና የእንስሳትን በሽታ መከላከያ መድሃኒት ያዘጋጃል፡፡ ባህላዊ የመሬት ማዳበሪያ ያዘጋጃል፡፡ የዝናብ ሁኔታዎችን ይተነብያል…፡፡ እነዚህ እውቀቶች ሁሉ ወረዳው ማህበረሰብ እውቀቶች ናቸው፡፡ ከነዚህ ከተጠቀሱት ባህላዊ እውቀቶች መካከል ይህ ጥናት የሚያተኩረው በባህላዊ ግብርና ከማሳ ዝግጅት እስከ ሰብል ስብሰባ ድረስ ባለው የገበሬው ዕውቀት ላይ እና ከእውቀቱ ጋር ከተያይዘው ስነ-ቃሎች፣ ልማዶችና እምነቶች ነው፡፡

### 4.2.4. ባህላዊ አደረጃጀትና ማህበራዊ ግንኙነቶች

የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ ህዝብ የሞተን ለመቅበር፤ የተቸገረን ለመርዳት፣ በስራ ለመተጋገዝ፣ የተጣላን ለማስታረቅ፣ ለመወያየት፣ ለመማማር፣ እርስ በእርስ ለመገናኘትና ለመጨዋወት ብሎ ከራሱ ልምድና ባህላዊ ከሆነ ዕውቀት ተነስቶ የመሰረታቸው የተለያዩ ባህላዊ አደረጃጀቶች አሉት፡፡ ይህም እቁብ፣ እድር፣ የጽዋ ማህበር (የአቦ፣ የሚካኤል፣ የገብሬል… ) ሰንበቴ፣ ወበራ ወይም ወንፈል (ደቦ)፣ የፈረስ ማህበር የሚባሉ ተቋማትን አካቶ ይይዛል፡፡

**እቁብ፡-** በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የሚዘወተሩ ሁለት የእቁብ አይነቶች አሉ፡፡ እነሱም የገንዘብና የጥጥ እቁብ ናቸው፡፡ የገንዘብ እቁቡ በየትኛውም የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሴቶችም ሆነ ወንዶች የሚሳተፉበት ሲሆን የእለት፣ የሳምንት የወር ሊሆን ይችላል፡፡ አቅምንና ኪስን (መቀነትን) ያገናዘበ በመሆኑ ፍላጎቱ ያለው እንደ አቅሙ የሚሳተፍበት ነው፡፡ ይህም ገንዘብ እየተሰበሰበ እጣ በመምታት ለባለ እጣው ወይም ችግር ላለበት እንደ ችግሩ እየታየ ቅድሚያ የሚሰጥበት መረዳጃ መንገድ ነው፡፡ በዚህ መንገድ ሁሉም እስኪደርሳቸው ድረስ ይቀጥላል፡፡ እቁቡም በባህላዊ መንገድ የተዋቀረ

[37] እስከ ሃምሳ ኪሎ እህል የሚይዝ ቁና

[38] ከመቶ ኪሎግራም በላይ የሚይዝ ቁና

አወቃቀር የእቁብ ዳኛ (ሰብሳቢ)ና ጸሐፊ አለው፡፡ የእቁቡ ዳኛ በየወቅቱ የሚጣለውን የእቁብ ገንዘብ ይሰበስባል፤እጣ ያስጥላል፣ እጣ ለደረሰው ሰው ዋስ ያስጠራል፡፡ እቁቡን የበላ ሰው(እጣውን የወሰደ) ዋስ መሆን አይችልም፡፡ ይህ የእቁብ ህግ ነው፡፡ ፀሐፊው ደግሞ የተሰበሰበውን ገንዘብ ይመዘግባል፣ ዋሱን ያስፈርማል፡፡[39]

ሁለተኛው የእቁብ አይነት የጥጥ እቁብ በመባል የሚታወቀውና ሴቶች ብቻ የሚሳተፉበት ነው፡፡ ከአምስት እስከ አስር የሚሆኑ እናቶች በአንድ ላይ ተሰባስበው በሳምንት በሳምንት ጥጥ በ "ባህላዊ ሚዛን"[40] በመመዘን እየተከፋፈሉ በመውሰድ ፈትለው በሳምንቱ ልቃቂቱን ይዘው ተረኛዋ ቤት በመሄድ ያስረክቡና የሌላዋን ጥጥ ይዘው ይሄዳሉ፡፡ በተረኛዋ ቤት ቡናና አብዚ ተዘጋጅቶ ይጠብቃል፤ ጥጡ ከተመዘነና ከታደለ በኋላ ቡና ጠጥተውና አብዚ በልተው ጥጣቸውን ይዘው ይሄዳሉ፡፡ በዚህ መንገድ የተፈተለው ጥጥ ልቃቂት ተሰብስቦ ጋቢ፣ ነጠላ፣ ቀሚስ፣ መቀነት ያሰሩታል፡፡

**እድር፡-** ይህ ባህላዊ አደረጃጀት በሞት ጊዜ አልቅሶ የሚቀብርና ለተጎጂው ቤተሰብ እርዳታ የሚያደረግበትና የሟችን የቀብር ስርዓት የሚያስፈጽም፣ ለቀስተኛውን፣ የሚያስተናግድ እንዲሁም ከሟች ቤተሰብ ጎን በመሆን ከእለት እስከ አርባ ድረስ ያለውን (ሰልስት፣ ሰባት፣ አስራ ሁለት፣ ሰላሳና አርባ) ክንውን የሚጋራ ነው፡፡ ይህም በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ የመተሳሰብና የመቀራረብ ስሜትን ይፈጥራል፡፡ እድር ማህበራትንም የሚያካትትበት ሁኔታ አለ፡፡

በጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ በርካታ ባህላዊ ማህበራትና አደረጃጀቶች አሉት፡፡ ማህበር ሰዎች በጋራ ተሰባስበው ችግራቸውን የሚወያዩበት፣ ሃሳብ የሚለዋወጡበትና አንድነታቸውን የሚገልጹበት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ምርምር ማእከል የተዘጋጀው መዝገበ ቃላት "ማህበር ማለት ተመሳሳይ እምነት ያላቸው የተወሰኑ ሰዎች በፈጣሪ ወይም በሌላ ቅዱስ

[39] የባህላዊ አደረጃጀቶችና ማህበራትን አሰራር በቦታው በቆዩሁባቸው 10 አመታት የማውቀው፣ የቆየሁበት እና የጽዋ ማህበር ላይ እሳተፍበት የነበረ በመሆኑ ሃሳቡ የእኔ ነው፡፡

[40] ከቆዳ፣ ከእንጨትና ከገመድ የተሰራ ሆኖ በመለኪያነት ድንጋይን የሚጠቀሙበት ባህላዊ የጥጥ ሚዛን ነው፡፡

ስም እየተዘጋጁ በበዓሉ ቀን አንድ ላይ በመገናኘት የሚቀምሱበት የፀበል ፀዲቅ ግብዣ ነው" (1993፡63) በማለት ሲገልጽ፣ ማህበር በተለያየ መንገድ ይመሠረታል፡፡ መንግስታዊ የሆኑና መንግስታዊ ያልሆኑ ማህበራት፣ የሙያ ማህበራት ...ተብለው የሚታወቁ አሉ፡፡ እነዚህ ህጋዊ የሆነ ደንብና መተዳደሪያ ወጥቶላቸው ባለሙያ የሆኑ የአመራር አካላት የሚመደብላቸው፣ ቢሮ ወይም ጽህፈት ቤት ያላቸው ናቸው (Desalegn, 2001፡2)፡፡ ሌሎች ማህበራት እንደጽዋ ማህበር፣ የፈረስ ማህበር፣ እድር፣ ደቦ፣ ወንፈል፣ እቁብ የመሳሰሉት ደግሞ ባህላዊ በሆነ መንገድ የሚመሠረቱ ናቸው፡፡ ሁሉም አይነት ማህበራት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው ማለት ግን አይቻልም፡፡ አንዳንዶቹ በባህሉ አስገዳጅነት አንዳንዶቹ በመንግስት አስገዳጅነት ሲመሰረቱ አንዳንዶቹ ደግሞ በፈቃደኝነት ይመሠረታሉ (Desalegn, 2001፡3)፡፡

የተለያዩ ማህበራት ሲመሠረቱ ለተለያየ አላማ ወይም ጥቅም ተብለው ይመሠረታሉ፡፡ ይህም ሰዎች አንድም የራሳቸውን ቡድን ለመመስረትና ተከታይ ለማፍራት፣ አንድም በማህበሩ ተጠቃሚ ለመሆን፣ ወይም ራስንም ሆነ ማህበረሰቡን ለመጥቀም ይመሠረታሉ፡፡ በዚህም መሰረት እንደየ ፍላጎታቸው ይሳተፋሉ፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት የቀረቡት የማህበር አይነቶች በፈቃደኝነት ላይና ራስንና ማህበረሰብን ለመጥቀምና በማህበሩም ተጠቃሚ ለመሆን የተመሰረቱ ባህላዊ ማህበሮች ናቸው፡፡

**የፈረስ ማህበር፡-** የፈረስ ማህበሩ በየአካባቢው ወር በገባ በ23ተኛው ቀን የሚከበር ሲሆን የግልቢያ ፈረስ ያላቸው ሰዎች የሚሳተፉበት ሲሆን በቀበሌ ደረጃ ያለ ማህበር ነው፡፡ አደረጃጀቱ ባህላዊ ቢሆንም መዋቅሩ ከወረዳ እስከ ዞን ድረስ የተዘረጋ ሲሆን በዞን ደረጃ በዓመት አንድ ጊዜ ጥር 23 የሚከበር ነው፡፡ የፈረስ ማህበሩ አባላት የሚሳተፉባቸው የተለያዩ የክዋኔ አውዶች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ የፈረስ ማህበሩ አመታዊ በዓል፣ የፈረስ ማህበሩ ወርሃዊ የጽዋ ማህበር፣ ንግስ (ታቦት ማጀብ)፣ ለቅሶ፣ ሰርግ፣ ማድመቅ ... ናቸው (ሰዋገኝ፣ 2002)፡፡

**የጽዋ ማህበር፡-** ይህ የጽዋ ማህበር በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን አንድም ለነፍስ፣ አንድም ለስጋ ተብሎ የሚደረግ ነው፡፡ አንድ ሰው አቅሙን ባገናዘበ መልኩ አንድ ወይም ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የጽዋ ማህበር ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህ ስርዓት የሚከናወነው በቤት ውስጥ ሲሆን የበዓሉ ዋዜማና በእለቱ የሚደረግ ነው፡፡ በዋዜማው ጥንስስ ቅመሱ ተብሎ ጠላ ብቻ ጠጥተው የሚመለሱበት ሲሆን በእለቱለት ደግሞ ዳቦ ወይም አብዚ[41] በልተውና ጠላ ጠጥተው ለተረኛው ጽዋ መርተውና አስረክበው ለወሩ በሰላም እንዲያደርሳቸው ተመራርቀው የሚለያዩበት ነው፡፡ ሌላው ሰንበቴ ሲሆን ይህም ከጽዋ ማህበር ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ልዩነቱ ሰንበቴ የሚጠጣው ወር በገባ በመጀመሪያው እሁድ ሆኖ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሰንበቴ ቤት ነው፡፡

**የጽጌ ማህበር፡-** ይህ በየአመቱ ከመስከረም የመጨረሻው እሁድ ተጀምሮ እስከ ታህሳስ ስድስት ቀን ባሉት እሁዶች በየሳምንቱ ለስድስት እሁዶች የሚጠጣ ማህበር ነው፡፡ አብዛኛው ሰው የሚሳተፍበትና እንደየቀረቤታቸው የሚገናኙበት ማህበር ነው፡፡ በዚህ ወቅት በየአካባቢው የሚገኙ የተቸገሩና አቅመ ደካማ የሆኑ ሰዎች በቦታው የመገኘትና የመሳተፍ ግዴታ አለባቸው፡፡ እንዲከፍሉ ሳይሆን አብረው እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡ የቆሎ ተማሪዎች እነሱ እራሳቸው የት የት መሄድ እንዳለባቸው ተመዳድበው ይሳተፋሉ፣ በመጨረሻም እራታቸውን ይዘው እንዲሄዱ ይደረጋል፡፡ ይህም ማህበር በዛፍ ጥላ ስር፣ በቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ እና በየአካባቢው ሆኖ ከቤት ውጭ የሚከናወን ሲሆን ስርዓቱ ከሌሎች ማህበሮች ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቢሆንም የጽዋ ማህበር ግን አይደለም፡፡

በአጠቃላይ ይህ ጥናት የሚጠናበት የአዊ ብሄረሰብ ታሪክን በተመለከተ የብሄረሰቡ አባላት እንዴት አሁን ወዳሉበት ቦታ ሊመጡ እንደቻሉ አፈታሪኮችን መሰረት አድርገው የተጻፉ ጽሁፎችን በመቃኘትና የብሄረሰቡ አባላት ስለራሳቸው የሚናገሩትን አፈታሪኮች መሰረት በማድረግ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ የብሄረሰቡ አባላት የሚኖሩበት

[41] አይኑና ጀርባው ተደርቦ የተጋገረ እንጀራ ላይ በአይንና በአይኑ ሽሮ ወጥ ተቀብቶ እንደ አነባበሮ የተደፋ እንጀራ፣ አንድ አብዚ ማለት አራት እንጀራ ነው፡፡ ይህም የሚቆረሰው አራት ቦታ ላይ ነው፡፡

ቦታ መልክዓ ምድራዊ ሁኔታው፣ ተጎራባች አካባቢዎች፣ የአየር ንብረት፣ የህዝብ አሰፋፈር፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን የተመለከቱ መረጃዎች ከቀዳማይና ከካላይ የመረጃ መንጮች ተሰብስበው ተተንትነው የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ እንዲሁም በመሰረታዊነት የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ መልክዓ ምድራዊ ሁኔታ፣ የህዝቡ ብዛት፣ የህዝብ አሰፋፈር፣ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታ እና የማህበረሰቡ ባህላዊ አደረጃጀቶችና ማህበራዊ ግንኙነቶች የቀረቡበት እና የጥናቱ ትኩረት የሆኑ ቦታዎች የተጠቁሙበት ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# የባህላዊ ግብርና ዕውቀት የመረጃ ትንተና

ይህ ክፍል የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ከማሳ ዝግጅት እስከ ሰብል ስብሰባ ድረስ ያለው የባህላዊ ግብርና እውቀት ክንውንና እና ከዚሁ ጋር ተያይዘው የሚባሉና የሚደረጉ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ትንታኔ ተሰጥቶባቸው የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ ጥናቱ በወረዳው ውስጥ በሚገኙ ሶስት ቀበሌዎች ውስጥ የተካሄደ ሲሆን ከመረጃ አቀባዮች በቃለ-መጠይቅ፣ በምልከታና በተተኳሪ የቡድን ውይይት በተሰበሰበው መረጃ መሰረት በወቅቶች ተከፋፍሎ የቀረበበት ነው፡፡

## 5.1. የእርሻ መሳሪያዎች

ባህላዊ የግብርና መሳሪያዎች ሲባል ከእርሻ መሳሪያዎች በተጨማሪ እንደመኮትኮቻ፣ መቆፈሪያ፣ ማጭድና ሌሎችን ያካትታል፡፡ ግብርናን ከእርሻ መሳሪያው ውጭ ማሰብ ይከብዳል፡፡ ስለዚህም ስለ እርሻ ከመናገሬ በፊት ጥቂት ነገር ስለባህላዊ የእርሻ መሳሪያዎች ማለት ግድ ይለኛል፡፡

ባህላዊ የእርሻ መሳሪያ በአካባቢ የሚገኙትን ጥሬ ዕቃዎች በመጠቀም በቀላል መንገድ በገበሬዎች የሚዘጋጅ ነው፡፡ በዚህ መንገድ የተዘጋጀውን የኢትዮጵያን ባህላዊ የእርሻ መሳሪያ McConn ሲገልጹ ፡-

> The Ethiopian version consists of eight basic parts, all available locally: the beam *(mofer),* the plowshare *(marasha* lit. "that which plows"), the sheath *(wogal),* the stilt *(erf),* two wooden ears (sg. *diggir)* inserted into the plow share's sheath, a yoke *(qanbar),* and a leather strap *(mangacha)* which adjusts plowing depth (McConn, 1995:45).


McConn የኢትዮጵያ ባህላዊ የግብርና መሳሪያዎች ዋና ክፍሎች ስምንት እንደሆኑና እነሱም ሞፍር፣ ማረሻ፣ ወገል፣ እርፍ፣ ሁለት ድግር፣ ቀንበር እና ማንገቻ ናቸው በማለት ይገልጻሉ፡፡ እሳቸው ይህን ይበሉ እንጂ የባህላዊ ግብርና መሳሪያዎች ከስምንት በላይ ናቸው፡፡ ምናልባትም እሳቸው የመጠናቸውን ማነስ ወይም ቀላልነት አይተው ትተዋቸው ካልሆነ በስተቀር ለእርሻ ስራው በጣም አስፈላጊ የሆኑ የእርሻ መሳሪያዎችን አልጠቀሱም፡፡ እሳቸው ከጠቀሷቸው በተጨማሪ ሌሎችም አሉ፡፡ በገበሬው በቀላሉ ባህላዊ መንገድ ስለሚዘጋጁት የእርሻ መሳሪያዎች አቶ የትዋለ ሲናገሩ፣-

> እኛ የበሬ እቃ የምንለው (1) ቀንበር፣ (2) ሞፈር፣ (3) እርፍ፣ (4) ሁለት ድግር (5) ወገል፣ (6) ምራን፣ (7) ማረሻ፣ (8) ቅጭርት (በሞፈር አፍንጫ ገብቶ ሞፈሩንና ቀንበሩን በምራን የሚያያይዝ)፣ (9) የአንገት ቅጭርት (10)መወላወል (በቀንበሩ መሐል ላይ ባለ ቀዳዳ የሚገባና ምራኑ ወዲያና ወዲህ እንዳይል የሚይዝ)፣ (11) መርገጫ (ወገሉን ከሞፈሩ ጋር የሚያያዝ ገመድ)፣ (12) ማነቂያ (ከጠፍር ወይም ከገመድ የተዘጋጀ የበሬዎች አንገት ላይ ያሉ ቅጭርቶችን ማሰሪያ/ ማበቻ)፣ (13) የድግር እንጨት (ድግሩን ከሞፈሩ ጋር የሚያያይዝ ) (14) ጅራፍ ናቸው፤ ተነዚህ አንዱ ቢጎል በሬ ፈቶ ይውላል እንጂ ማረስ አይችልም በማለት ይገልጻሉ፡፡[42]

McConn ሁለቱን ድግር እና አራቱን በበሬዎች አንገት የሚያልፉ የአንገት ቅንጭርቶች፣ ጨምረው ስምንት ያደረጓቸውን መሳሪያዎች የሙያው ባለቤቶች ጥንድ ጥንድ የሆኑትን እንደ አንድ በመቁጠር አስራ አራት ያደርጓቸዋል፤ ከነዚህ አንዱ ቢጓደል የእርሻ ስራን ማከናወን ሰለማይቻል ሁሉም አስፈላጊ ናቸው፡፡

---

[42] የትዋለ ከበደ፣ ቲሊሊ፣ ቃለመጠይቁ ተደረገበት ቀን 15/09/2006



ፎቶ 7፡- የበሬ ዕቃ[43]




ፎቶ 8፡-የፈረስ ዕቃ፣አግዛ10/7/2007

1. **ቀንበር**፡- ከበሬ ጫንቃ ላይ የሚውል ከባድ ሸክም ነው፡ ቀንበር ከሌሎች የበሬ እቃዎች ሁሉ ጠንካራና ወፍራም ነው፡፡ ሁለቱንም በሬዎች የሚያያይዝ፣ የሚያስተሳስር ነው፡፡
2. **ሞፈር**፡- በቀንበሩና በእርፉ መካከል የሚውል ማረሻውን የሚጎትት ቀንበሩን ከማረሻ፣ ከእርፍ፣ ከድግር ጋር ሁሉ የሚያስተሳስር ነው፡፡
3. **እርፍ**፡- በመጠኑ ከሁሉም ቀጠን ያለ ሲሆን ሁልጊዜም በገበሬው መሀል እጅ ስር ያለ ደግሞ ሞፈርን ሰርስሮ የገባ ነው፡፡ ሞፈር ወፍራም ሲሆን ቀጭኑ እርፍ በሞፈሩ ውስጥ አልፎ በርካታ ተግባራትን እንደሚያከናውን ነው፡፡
4. **ማረሻ**፡- ወደ መሬት ውስጥ በመግባት አፈሩን ፈነቃቅሎ/ገለባብጦ ለዘር የሚያዘጋጅ ነው፤
5. **ድግርና የድግር እንጨት**፡- ድግር በድግር እንጨት አማካኝነት ከሞፈሩ ጋር ተያይዞ ማረሻውን አቅፎ በመያዝ አፈሩን ግራና ቀኝ ይገፋል፡፡ የድግር እንጨት በጫፍ በኩል በተበሳው የሞፈሩ ቀዳዳ ውስጥ አልፎ ሁለቱን ድግሮች ያያይዛል፡፡

---

[43] ከስዕላዊ መዝገበ ቃላት (1984፡141) ለጥናቱ እንዲስማማ ሆኖ ተወሰደ



ፎቶ 7፡- የበሬ ዕቃ[43]



ፎቶ 8፡-የፈረስ ዕቃ፣አግዛ10/7/2007

1. **ቀንበር**፡- ከበሬ ጫንቃ ላይ የሚውል ከባድ ሸክም ነው፡ ቀንበር ከሌሎች የበሬ እቃዎች ሁሉ ጠንካራና ወፍራም ነው፡፡ ሁለቱንም በሬዎች የሚያያይዝ፣ የሚያስተሳስር ነው፡፡
2. **ሞፈር**፡- በቀንበሩና በእርፉ መካከል የሚውል ማረሻውን የሚጎትት ቀንበሩን ከማረሻ፣ ከእርፍ፣ ከድግር ጋር ሁሉ የሚያስተሳስር ነው፡፡
3. **እርፍ**፡- በመጠኑ ከሁሉም ቀጠን ያለ ሲሆን ሁልጊዜም በገበሬው መሀል እጅ ስር ያለ ደግሞ ሞፈርን ሰርስሮ የገባ ነው፡፡ ሞፈር ወፍራም ሲሆን ቀጭኑ እርፍ በሞፈሩ ውስጥ አልፎ በርካታ ተግባራትን እንደሚያከናውን ነው፡፡
4. **ማረሻ**፡- ወደ መሬት ውስጥ በመግባት አፈሩን ፈነቃቅሎ/ገለባብጦ ለዘር የሚያዘጋጅ ነው፤
5. **ድግርና የድግር እንጨት**፡- ድግር በድግር እንጨት አማካኝነት ከሞፈሩ ጋር ተያይዞ ማረሻውን አቅፎ በመያዝ አፈሩን ግራና ቀኝ ይገፋል፡፡ የድግር እንጨት በጫፍ በኩል በተበሳው የሞፈሩ ቀዳዳ ውስጥ አልፎ ሁለቱን ድግሮች ያያይዛል፡፡

[43] ከስዕላዊ መዝገበ ቃላት (1984፡141) ለጥናቱ እንዲስማማ ሆኖ ተወሰደ

6. **ቅንጭርትና ማነቆ**፡- ቅንጭርት ሞፈሩን ከቀንበርና ከምራን ጋር አድርጋ የምታያይዝ ቀጭን እንጨት ናት፡፡ ማነቆ በሁለቱ በሬዎች አንገት አልፎ የሚሄደውን የአንገት ቅንጭርት ለማሰር የሚያገለግል ከጠፍር ወይም ከገመድ የሚሰራ ነው፡፡
7. **መርገጫና ወገል**፡- መርገጫ ወገሉን ከሞፈር ጋር በማሰር ለማጥበቂያነት ያገለግላል፡፡ ይህ ገመድ ድግሩ ማረሻው እርፉ፣ ባንድ ከሆነ በኋላ ከሞፈር ጋር ወገሉን የሚያስር ነው፡፡ ወገል፡- ደግሞ ከብረት የተሰራ ክብና ቆልማማ እጀታ ያለው ነው፡፡ ማረሻውንና ድግሩን በውስጡ በማስገባት በአንድ ላይ በገመድ ከሞፈሩ ጋር ይታሰራል፡፡
8. **ጅራፍ**፡- ከብቶቹ ከመስመር ሲወጡና አቅጣጫ ሲስቱ መመለሻ ነው፡፡
9. **ምራን**፡- ቀንበሩንና ሞፈሩን በመወላወል የሚያያይዝ ከቆዳ ተጎንጉኖ የሚሰራ ነው፡፡
10. መወላወል፡- ምራኑንና ሞፈሩን የሚያያይዝ ከቀጭን የወይራ ወይም የኪያ እንጨት የሚዘጋጅ ነው፡፡

እያንዳንዱ የእርሻ መሳሪያ ጥምረትን ፈጥሮ በአንድነት ካልሆነ በስተቀር ትልቁ ያለ ትንሹ ምንም ነገር ማከናወን አይችልም፡፡ እንዲሁም ማረሻው ብቻውን ያለገበሬና መሬት ትርጉም አልባ ነው፡፡

እነዚህን መሳሪያዎች ለማስተካከል የእርሻ መሳሪያ አሰራር ዕውቀት ያለው ሰው መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ሰው ተመሳሳይ የሆነ ዕውቀት የለውም፣ የተለያየ ሙያ ያለው ሰው ስላለ ዝግጅቱ ከሙያና ከባህላዊ ዕውቀት ጋር የተያያዘ ነው፡፡

ለጥናት በተንቀሳቀስሁባቸው ቀበሌዎች የማሳ ዝግጅት የሚጀምረው በጥቅምት ሲሆን የአካባቢው ማህበረሰብ በሬን ከበሬ፣ ፈረስን ከፈረስ፣ ፈረስን ከላም/ ከበሬ ጋር በመጥመድ የእርሻ ስራውን ያከናውናል፡፡ በተለይ በደጋማው አካባቢ የሚኖሩት ገበሬዎች የእርሻ ስራን የሚያከናውኑት በፈረስ ነው፡፡ የፈረስ እርሻ በአካባቢው

የተጀመረው ከ50 ዓመት በፊት እንደሆነ በአካባቢው ማህበረሰብ ይነገራል፡፡ ቄስ ወርቁ የፈረስ እርሻ አጀማመርን በተመለከተ፡-

> በ1957 አመተ ምህረት "ጉመድ ወተቴ" የሚባል የከብት በሽታ ገብቶ ከብቱን ሙልጭ አድርጎ ፈጀው፤ ተዚያ ወዲያ በሬው አለቀ በምን ይታረስ? መሬቱ ጦም ሊያድር! የማይሆን ነገር ነው፣ ሰውም ሊያልቅ ነው፤ "ችግር ብልሃትን ትፈጥራለች" እንደሚባለው ገበሬው ሲጨንቀው ፈረሶችን እየጠመደ ማረስ ጀመረ፤ ተዚያ ወዲያ በሬ ሁለት ቀን የሚውልበትን እርሻ በፈረስ እስተ ረፋድ ሆነ! አሁን ደሞ የበሬው ዋጋም ሰማይ ነካ! በማለት ይገልጻሉ፡፡[44]

ገበሬው የእርሻ በሬዎቹ ሲሞቱ ዝም ብሎ እጁን አጣጥፎ ከሰማይ መና እንዲወርድለት አልጠበቀም ወይም ፈጣሪውን አልለመነም፡፡ በጊዜው ያደረገው ነገር ቢኖር ከሞት የተረፉትን ፈረሶችን ጠምዶ ማረስ ነበርና ያንንም በተግባር ሞክሮ ውጤቱን አየው፡፡ ለዚያን ጊዜ ለችግር ማሳለፊያ ይሆናል ብሎ የጀመረው ስራው ግን ከበሬ የተሻለ ሆኖ ስላገኘው አሁን ድረስ በሰፊው እየሰራበት ይገኛል፡፡

በሬን ከበሬ ወይም ከላም ጋር ጠምደው ሲያርሱ የሚጠቀሙት አንድ ቀንበር ብቻ ሲሆን ፈረስን ከፈረስ ጋር ሲጠምዱት ደግሞ ሁለት ቀንበር ይጠቀማሉ፤ ይህም ከፈረሱ ጋማ ላይ የሚውልና ከፊቱ የሚሆን ሲሆን በፈረሱ እርሻ ሁለት ቀንበርን ብቻ ሳይሆን ሁለት ምራንንም[45] ይጠቀማሉ፡፡ እንዲሁም ቀንበሩ የሚያርፍበት ከፈረሱ ጋማ ላይ የሚውል "ኮር"[46] አለው፡፡

የፈረሱን ቀንበር ሁለትነት አስመልክቶ አቶ ይሁን ሲገልጹ፡-

---

[44] ቄስ ወርቁ ወልደ ጊዮርጊስ፣አግዛ ጋርዳ አሊያስ ቀበሌ፣ ቃለ- መጠይቅ 09/07/2007፡፡
[45] ከቆዳ የሚሰራና እንደገመድ በወፍራሙ የተገመደ ፣ ቀንበርንና ሞፈርን የሚያያይዝ
[46] ከቆዳ የተሰራና ገለባ ተሞልቶ ለቀንበሩ ማስቀመጫ በፈረሱ ትከሻ ላይ የሚሆን

ይኸ ታባቶቻችን የወረሥነው ነው፤ ፈረስ እንደበሬ ጫንቃ ስለሌለው ቀንበሩ ወዲያና ወዲህ እንዳይል ሁለት ቀንበር ሆኖ ከሞፈሩ ጋር ደግሞ በሁለት ምራን ይያያዛል፤ ኮሩ ደሞ የፈረሱ ጫንቃ እንደ በሬው አይጠነክርም ስለዚህ ቀንበሩ እንዳይበላው ኮር ተጫንቃው ላይ አድርገን ተዚያ ላይ ቀንበሩን እናደርገዋለን፡፡ ተበሬ ጋር ሲሆን ደሞ በፈረሱ ፊት እንዳለ ሆኖ በበሬው ገጣ[47] ያለውን ተላይ ተጫንቃው ላይ እናስረዋለን፤ በበሬው በኩል አንድ ሆነ ማለት ነው፡፡[48]



ፎቶ 9፡- በፈረስ ሲታረስ አግዛ 15/9/ 2006

ከላይ የተጠቀሰውን ሃሳብ ስንመለከት በበሬና በፈረስ መካከል ያለው የእርሻ መሳሪያ ልዩነት ቀንበር፣ ምራንና ኮር ላይ ብቻ ሲሆን ሌሎቹ ግን ተመሳሳይ ናቸው፡፡ለበሬ አንድ ቀንበር ሲሆን የፈረስ ደግሞ ሁለት ቀንበር ነው፡፡ ፈረስ ላይ ከቀንበሩ በስር ኮር አለው፡፡ በዚህ ነው ከበሬ ጋር የሚለያዩት፡፡


[47] በበሬው ገጣ፡- በበሬው በኩል/ በበሬው አቅጣጫ
[48] በዶጋማውና በወይና ዶጋማው አካባቢ ያሉት መረጃ አቀባዮች የሚጋሩት ሃሳብ ነው፡፡

ይህ ባህላዊ የግብርና መሳሪያ በባህላዊ መንገድ የሚዘጋጅና ብዙ ወጪን የማይጠይቅ ከመሆኑ በተጨማሪም የግብርና መሳሪያው እዚያው ባሉ ሰዎች በቀላሉ በካባቢው ከሚገኙ ቁሶች የሚዘጋጅ ነው፡፡

ስለ ኢትዮጵያዊያን የእርሻ መሳሪያዎች ሲገልጹ "የኢትዮጵያ የባህላዊው ግብርና መሳሪያ ማረሻ ጥሩና በቀላሉ የሚለመድ ነው" (McConn, 1995፡45)፡፡



ፎቶ 10፡- በበሬና በፈረስ ሲታረስ፣ አብስላ፣ 25/6/2007



ፎቶ 11፡- በበሬ ብቻ ሲታረስ፣ 17/7/ 2007

የሚፈለጉትን የግብርና መሳሪያዎች ለማዘጋጀት የሚሆኑ እንጨቶች በማንኛውም ጊዜ አይቆረጡም፡፡ በተለይ ደግሞ በግንቦት ወራት ምንም አይነት እንጨት አይቆረጥም፡፡ ይህን አስመልክቶ ብላታ ዳኛው[49] እና አቶ አየለ[50] ሲናገሩ በግንቦት የሚቆረጥ እንጨት ለቤት መስሪያ አይሆን፣ ለመኮትኮቻ፣ ለመቆፈሪያ እጀታ አይሆን፣ ከማገዶ ውጭ ለምንም አይውልም፣ ቅንቀን ይበላዋል፣ የተቆረጠውም ቢሆን መልሶ አያቀጠቅጥም በማለት ይናገራሉ፡፡ ድሮ ዱሩ ሞልቷል ተዚያ ወይራው፣ ዝግባው፣ ኮሶው፣ ስኒ[51]ው ነበር አሁን እሱ ቀርቶ ባህርዛፍ ሆኗል፣ ማንኛውም እንጨትም አይሆንም ተሱም የተመረጠ ትክክል የሆነ እንጨት ነው የሚሆነው፡፡ "ትንጨት መርጦ ለታቦት ተሰው መርጦለ ሹመት" አደል ይህንም ሞፈሩን ቀንበሩን የሚያርቅ ባለሙያን ይጠይቃል፣ ዝም ብሎ ተቆርጦ ሞፈር አይሆን! ቀንበር አይሆን! በማለት ይገልጻሉ፡፡[52]

ጥናቱን ባካሄድሁበት አካባቢ ያሉ ገበሬዎችም የሚጠቀሙት በበጋ ማረሻው ቀጠን ሾል ያለና ከባድ ሲሆን በክረምቱ ደግሞ አጠር ሰፋና ቀለል ያለ ነው፡፡ ድግሩም የበጋው ቀጠን ያለ ሲሆን የክረምቱ ሰፋ ያለ ነው፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት የበጋው እርሻ ደረቅ ስለሆነና ዝናብ እንዲገባው ጠለቅ ተደርጎ ስለሚታረስ ነው፡፡ የክረምቱ እርሻ መሬቱ እርጥበት ስላለውና ጭቃው ስለሚከብድ ቀለል ባለ ማረሻና ድግር ነው የሚታረሰው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በድንበር አካባቢ የሚገኙትን አላስፈላጊ የሆኑና ለማረሻ አመቺ ያልሆኑትን ተክሎች ለማስወገድ ሌሎች አጋዥ መሳሪያዎችንም እንደ መኮትኮቻና መጥረቢያ ያሉትን ይጠቀማል፡፡

ገበሬው በህይዎት ተሞክሮውና በልምድ ባካበተው ዕውቀት ተመስርቶ እያንዳንዱን ተግባር የሚያከናውነው ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ ነው፡፡ ከአቅም በላይ ካልሆነ በስተቀር በግዴለሽነት የሚያባክነው ጊዜ የለም፡፡ ከዚህም የተነሳ በቤቱ ውስጥ መጠባበቂያ አንድና ከዚያም በላይ የበሬ እቃዎችን አዘጋጅቶ ያስቀምጣል፡፡

[49] ቃለ መጠይቁ የተደረገበት አግዛ፣ ቀን፡ 09/07/2007
[50] ቃለ መጠይቁ የተደረገበት አደጋ ጓሽታ፣ ቀን፡27/07/2007
[51] የተፈጥሮ እጽዋት አሁን ግን የጠፋ
[52] ብላታ ዳኛው ሞገሴ፣ አግዛ ቀበሌ ሹምታ ደሽ፣ ቃለመጠይቁ የተደረገበት ቀን 09/07/2007 እና አቶ አየለ አንተነህ፣ አደጋ ውባጅ ቀበሌ፣ ሰባት አይና ጎጥ ቃለመጠይቁ የደረገበት ቀን 27/07/2007

ምክንያቱም አንዱ ቢሰበር ሌላውን ይተካል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን እስኪያዘጋጅ ሳምንት ሁለት ሳምንት እርሻ ሊፈታ ይችላል ወይም የበሬ እቃ በመለመን የሰው ፊት ይገርፈዋል፣ ወይም ደግሞ በማህበረሰቡ ዘንድ ይነቀፋል፣ እያንዳንዱን የበሬ እቃ የሚያዘጋጀው ከተመረጡ የእንጨት አይነቶች ነው፡፡ አቶ አየለ ስለዚህ ሲነገሩ

> አንድ ቀን በሬ ስጠምድ በሬዎቼ ፈርጥመው እንጣጥ አሉና ማን ይቻላቸው በአንድ ቀን ሁለት ጊዜ ቀንበር ሰበርሁ፣ ሌላ ተካሁ እንዲች ብዬ ከሰው ደጅ እንጨትም አላነሳ፣ ዛሬም በድሮው ጊዜ ያዘጋጀሁት ቆብር[53] አለ ብጭጭም አላለ፣ ድሮ ስኒ የሚባል እንጨት ነበር፣ ልምጭ፣ ቅንጭር ልምጭ ነው የሚሆነው፣ አሁን ደግሞ በብዛት የባህር ዛፍ እንጨት ነው የሚሆነው፡፡ ሌላ እንጨት የለም፣ ዱሩ ሁሉ የለም ይላሉ፡፡[54]

ይህም ገበሬው አካባቢውንና ባህላዊ ዕውቀት ተጠቅሞ እንደ ሁኔታዎች መሳሪያዎችን በማዘጋጀት የሚጠቀም መሆኑን ያሳያል፡፡ የእርሻ መሳሪያዎችንም ለማዘጋጀት የሚመረጡ ሀገር በቀል የሆኑ እጽዋቶች ቢኖሩም እነሱ በማይገኙበት ደግሞ ባህላዊ እውቀታቸውን ተጠቅመው ሌላ መንገድን በመፈለግ ባህር ዛፍን በአማራጭነት ይጠቀማሉ፡፡ ከእርሻ መሳሪያዎች በተጨማሪ ለዚሁ ለግብርናው ተግባር አገልግሎት የሚሰጡ አጋዥ የግብርና መሳሪያዎች አሉ፡፡ እነሱም ማጭድ፣ መኮትኮቻ፣ አካፋ፣ ገሶ፣ መጥረጊያ፣ መንሽ፣ ቅርጫት፣ የስፌት እቃዎች (ሰፌድ፣ ወንፊት፣ ቁና…) ወዘተ. ናቸው፡፡

ገበሬው የባህላዊ ግብርና ዕውቀቱን በባህላዊ እርሻ መሳያዎች አማካኝነት ስራውን በወቅቶች ከፋፍሎ ይገለገልባቸዋል፡፡ የባህላዊ ግብርና ዕውቀትም በባህላዊ የወቅቶች አከፋፈል መሰረትነት በዚህ ክፍል ይቃኛል፡፡

---

53 መንሽ (ባለ ሁለት ወይም ባለ ሶስት ጣት እንጨት)

54 አቶ አየለ አንተነህ፣ አደጋ ውባጅ ቀበሌ፣ ሰባት አይና፣ ቃለመጠይቁ የተደረገበት ቀን 27/07/2007

ይህን በተመለከተ ቄስ ታዬ ወቅቶቹ እኩል የጊዜ እርዝማኔ (ሶስት፣ ሶስት ወራት) ሲሆን ስያሜያቸውንም ያገኙት ከተግባሩ ወይም የስራ ክዋኔውና ከጊዜው አንጻር ነው፡፡ ግቢ/ በልግ የክረምቱ መግቢያ መሆኑንና አነስተኛ ዝናብ የሚጥልበት ወቅት ነው፡፡ ክረምት ደግሞ የዝናብ ጊዜነው፡፡ ጥቢ የሚባለው ደግሞ የክረምቱ ጊዜ አልቆ ብርሃን የሚታይበትና የዝናቡ መጠን የሚቀንስበት ወቅት ነው፡፡ እንዲሁም መኸር የሰብል መሰብሰቢያ ወቅት በመሆኑ የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡[55]

## 5.2. ግቢ /በልግ (ከመጋቢት እስከ ግንቦት)

ይህ ወቅት ለገበሬው የስራ ጫና ወቅት ሆኖ ማሳዎች ለዘር የሚዘጋጁበትና አንዳንድ ሰብሎችም የሚዘሩበት ወቅት ነው፡፡ በነዚህ ወራት የተለያዩ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ በዋናነት የእርሻ ጊዜ ቢሆንም እንደ ድንች፣ ማሽላና ጎመን የሚዘሩበት፣ የሚታረሙበትና የሚኮተኮቱበት ጊዜ ነው፡፡ ይህ ወቅት በገበሬው ዘንድ የዝግጅት ጊዜ ነው ወቅቱ በግራጫ ቀለም ይመሰላል፡፡ ድካሙ የሚበረታበት የስራ ጊዜ ሆኖ ለክረምቱ ዝግጅት የሚደረግበት ነው፡፡

ገበሬው በእነዚህ ወራቶች የዘርን ጊዜ ለመወሰን በተለመደው የዘር ጊዜ ውስጥ ወደፊትና ወደኋላ ለማድረግ እንዲያስችለው የመጪውን ጊዜ የአየር ሁኔታ ይተነብያል፡፡ ይህንን አየር ትንበያ የሚተገብሩት በዕድሜ የገፉ አባቶች ሲሆኑ የወቅቱ ዝናብ መጣል ከመጀመሩ በፊት ድንጋይ በመፈንቀልና ከድንጋዩ ስር የሚወጡትን ነፍሳት በመመልከት ዝናቡ ቀድሞ ይጀምራል ወይም ይዘገያል በማለት ይናገራሉ፡፡

በመኸሩ መጨረሻ አካባቢ መስክ ላይ የሚገኝ ድንጋይ ፈንቅለው ሲያዩት ቁጫጬ ግንፍል ብሎ ከወጣ ቶሎ ዝናብ ይዘንባል፡፡ ከሌለ ደግሞ ዝናብ ይዘገያል ይላሉ፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ አቶ አየለ፡-

[55] ቄስ ታዬ ታፈረ፣ አብስላ ዋርዳ ቀበሌ፣ ዋህሳ ደሽ፡ ቃለ መጠይቅ 3/7/2007 ዓ.ም.

ቡክር ብለን በየካቲት እርሻ ሳንጀምር መስክ ላይ ያለውን ድንጋይ ፈንቅለን ስናየው ኩጫጪ[56] ከነ እንቁላሏ ግንፍል ታለች ዝናቡ ቀደም ብሎ ይዘንባል ማለት ነው፡፡ ዝናቡ የሚጀምርበትን ጊዜ ለመገመት ዝናብ ከመዝነቡ በፊት መሬቱ ስለሚለብጥ ሙቀቱ ነፍሳቱን እንዲፈሉ ስለሚያደርጋቸው ከመሬት ውስጥ ወደላይ ግንፍል ብለው ይወጣሉ፡፡ እንዲህ ሲሆን እርሻችንን ቶሎ ቶሎ ብለን እስተ እኩሌታ ተሆነ የሚዘራው ያው ዝናቡን ሽሚያ እስታምስት ባላት ታላስቸገረን እንዘራለን፤ ቡክር የመጣ ዝናብ በፍሬው ጊዜ ሊያጥጥ ይችላል፤ ያው ኩጫጪ በየካቲት ታልታዬች ግን ዝናቡ ዘግይቶ ይመጣል፤ እንዲያ ወደኋላም አይጠፋም በመዝሪያው በስተ መጨረሻ ባለው እንዘራዋለን፡፡ በተረፈ ደሞ በዝናቡ ጊዜ ጨረቃ ሲሆነ ሌሊት አይዘንብም እንዲህ ታጠባቡ ነው፤ ሰማዩን አይተን የጠቆረ ደመና ታለ፤ ንፋሱን አነፋፈስ አይተን የዝናቡን ቅለትና ክብደቱን እናውቀዋለን፤ ተኛ የሚጥልና የሚያልፍ መሆኑን እናውቃለን፡፡[57]

ከአቶ አየለ ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው የዝናብ ወቅት ከመድረሱ በፊት የዝናብ ጊዜያቸውን የሚተነብዩበት መንገድ ነው፡፡ በዚህ ትንበያም ተነስተው የዘር መዝሪያውን ጊዜ ሳይለቁ ወደፊትና ወደኋላ በማድረግ ለመዝራት ይጠቀሙበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዝናብ ወቅትም ቢሆን የነፋሱን አቅጣጫ፣ ነፋሱ ከሰሜን ወደ ምእራብ ከነፈሰ አልፎ (ካፊያ ጥሎ)የሚሄድ ዝናብ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ በስተ ምስራቅ በኩል የጠቆረ ደመና ከታየ ከብቶቹም ሆኑ ልጆች እንዲጠለሉ ይደረጋል፡፡ ጨረቃ ሙሉ ስትሆን የዝናብ ሁኔታው ንጋት ላይ እንደሚጠነክር ይናገራሉ፡፡ የፀሐይ ሙቀቱ ጠንክር ካለ ደግሞ ሀይለኛ ዝናብ እንደሚዘንብና በረዶም ሊቀላቅል እንደሚችል ይናገራሉ፤ ይተነብያሉ፡፡ የዝናብ ትንበያውን የሚያደርጉት በዕድሜ የገፉ ሰዎች

[56] ጉንዳን የሚመስሉ ትናንሽ ጥቁር ነፍሳት
[57] አቶ አየለ አንተነህ፣ አደጋ ውባጅ ቀበሌ፣ ሰባት አይና ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 2/07/2007

ናቸው፡፡ ምክንያቱም ከቀደሙት አባቶች በመማርና ከልምድ ባዳበሩት ዕውቀት ተነስተውና የነፍሳቱን ከጉድጓዱ አወጣጥ አይተው ይናገራሉ፡፡

አቶ በየነ[58]ና አቶ ሃብታሙ[59] "ተመጋቢት አንድ ጀምሮ አይዳ[60] እናርሳለን"[61] ተመጋቢት ጀምሮ የእርሻ ጊዜ ነው፤ እነ ጤፍ፣ ስንዴ ዳጉሳ ብዙ እርሻ ይላሉ፤ ሰባት ስምንት ጊዜ፣ አገራችን ገብስ ከአራት ጊዜ በላይ አይታረስም፡፡ ተልባና ኑግ በጣም ቀላል ነው እርሻው ከሶስት ጊዜ በላይ አይታረስም፡፡

በምዕራፍ ሁለት በቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ በHenery (2012) እንደታየው ገበሬው የእርሻ መሬቱን በሶስት እንደሚከፍለው ታይቷል፡፡ በዚህ ጥናት ግን የገበሬው የእርሻ ማሳዎቹን የጓሮ መሬትና የገጠር መሬት በማለት በሁለት ይከፍለዋል፣ የጓሮ መሬት በቤቱ አቅራቢያ የሚገኝ መሬት ሲሆን አዘውትሮ የቤት ጥራጊ፣ አመድ፣ የከብቶች ፍግ የመሳሰሉት ስለሚደፉበት ለም መሬት ነው፡፡ የጓሮ መሬቱም ድንች፣ ገብስ፣ ጤፍ የመሳሰሉትንና ቋሚ ተክሎችም እንደ ግራዋ፣ ባህር ዛፍ፣ ጌሾ፣ ቡና እንዲሁም ቅመማ ቅመምን አካቶ ይይዛል፡፡ ከቤቱ ከ1-3 ኪ.ሜ. በርቀት ያለውን መሬት ደግሞ የገጠር መሬት[62] በማለት ይጠራዋል፡፡

ወደ እርሻ የሚሰማራ ገበሬ በጥዋት ተነስቶ ለበሬዎቹ ገለባ ይሰጥና እርሱም ቁርሱን ቀማምሶ ከደጅ የበሬ እቃውን (ድግሩን፣ እርፉን፣ ማረሻውን፣ ወገሉንና ሞፈሩን) ረግጠ[63] በአንድ ትከሻው፣ በሌላ ትከሻው ደግሞ ቀንበሩን ተሸክሞ በሬዎቹን ወይንም ፈረሶቹን እየነዳ ወደ እርሻው ይሄዳል፡፡

---

58 አቶ በየነ ሃይሉ፣ አብስላ ዋርዳ ሳሙኤል ቀበሌ፣ ዋህሳ ደሽ ቃለመጠይቅ 17/07/2007፡፡
59 አቶ ሃብታሙ ጌታነህ፣ አደጋ ጓሽታ ውባጅ -መሀል አምባ ቃለመጠይቅ 21/07/2007፡፡
60 ለስላሳ እርሻ
61 አቶ ሽመካ ገዳሙ፣ አደጋ ውባጅ ቀበሌ፣ መስቀለኛ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 24/6/2007፡፡
62 የገጠር መሬት፡- ከጓሮ መሬት ሰፋ ያለና የተለያ ሰብሎችን የሚያመርትበትን የእርሻ መሬት የገጠር መሬት በማለት ይጠራዋል፡፡
63 ማረሻ፣ እርፍ፣ ወገል፣ ድግር እና ሞፈርን አንድ ላይ ማስተሳሰር

አንድ ገበሬ በመደበኛነት ከ12-20 ኪ.ግ. የሚመዝን የእርሻ መሳሪያ ተሸክሞ በቀን ከ3-6 ኪ.ሜ. ይጓዛል፡፡ ገበሬው ማሳው ላይ እንደደረሰም ቀድሞ የግራው በሬ ትከሻ ላይ ቀንበሩን ያሳርፍበታል፡፡ የግራው በሬ ሀይለኛና አመጸኛ በመሆኑ በቀላሉ በጄ ብሎ ስለማይጠመድ በመጀመሪያ ቀንበሩን ያሳርፍበታል፡፡ የግራው በሬ አዲስ ለሚገሩ ወይፈኖችም አሰልጣኝ ነው፡፡ ቀጥሎም የቀኙ በሬ[64]ላይ ያስቀምጥና ይጠምዳቸዋል፡፡ የቀኙ በሬ ገራገር እና ቀና ነው፡፡ በመቀጠልም ከደጁ ረግጦ ይዞት የመጣውን ሞፈሩን ከቀንበሩ ጋር በምራን እና በሞፈር አፍንጫው ውስጥ ቅንጭርት በማስገባት እንዳይሾልክ እድርጎ በመወላወል ያያይዘዋል፡፡ ይህን አስመልክቶ ቄስ ወርቁ የሚከተለውን

> በመጀመሪያ እርፉ ከወገል፣ ከድግር ከማረሻ፣ ከሞፈር ጋር ሆኖ በመርገጫ ገመድ ይረገባል፣ ተዚያ በመጀመሪያ የግራው በሬ ጫንቃ ላይ ቀንበሩ ይጫናል፣ የግራው በሬ ሀይለኛ ነው፣ ተዚያ የቀኙ በሬ ጫንቃ ላይ ሆኖ ቅንጭርት (በማነቆ እንጨት) እና በተፈተለው የማነቂያ ገመድ አንገታቸው ይታበተል፣ ተዚያ ሞፈር አለ ሞፈሩን በምራን ከቀንበር ጋር በቅንጭርት ይያያዛል፣ ምራኑ ወዲያ ወዲህ እንዳይልም መወላወል ይይዘዋል፣ ተዚያ ጅራፍን ይዞ እየተለሙ ሂድበል ማለት ነው፣ "በሬና ገበሬ ቢጣሉም አይበጅ እንዲያው ሰተት ብሎ ይጠመዲል እንጂ" ይባላል፡፡[65]

የቄስ ወርቁን ሃሳብ አቶ አበራ[66] አቶ ይሁን[67] እና አቶ አያና[68] ይጋሩታል፡፡ በዚህም መሰረት በመስከረምና በጥቅምት የተሰነጠቀው መሬት በሁሉም አካባቢ ከመጋቢት 1 ቀን ጀምሮ በደንብ ተገልብጦ የሚታረስ ሲሆን በጥቅምትና በሚያዚያ የማይታረሰው የጤፍ መሬትም ዝናብ ተጠብቆ ሁለት ጊዜ የሚታረሰው በዚሁ ወር ነው፡፡ የድንች

---

[64] በሬ እያልሁ ስገልጽ ፈረስንም ያካትታል፡፡ ልዩነት ሲኖር ግን ልዩነቱን አስቀምጣለሁ፡፡
[65] ቄስ ወርቁ ወልደ ጊዮርጊስ፣ አግዛ ጋርዳ ቀበሌ፡ ወዳሽቲ ደሸ፣ ቃለመጠይቅ 27/07/2007፡፡
[66] አቶ አበራ መኩሪያ፣ አደጋ ውባጅቀበሌ፣ ጓሽታ ደሸ፣ ቃለመጠይቅ 18/06/2006፡፡
[67] አቶ ይሁን አድማስ፣ አግዛ ጋርዳ ቀበሌ፡ ሹምታ ደሸ፡ ቃለመጠይቅ 04/09/2007፡፡
[68] አቶ አያና አለማየሁ፣ አሰኑና ጊዮርጊስ ቲሊሊ አግኝቻቸው መረጃ የሰጡኝ በ29/07/2007፡፡

መሬትም በዚሁ ወር በደንብ ለስልሶ ለዘር ይዘጋጃል፡፡ በዚህ መንገድ በሬዎቹን ከጠመደ በኋላ ጸሎት ያደርጋል፡፡ ይህን በተመለከተ ቄስ ወርቁ ሲነገሩ

> እንኩዋን እርሻን ያህል ነገር ስንጀምር ቀርቶ ተምኝታችን ስንነሳ በሰላም ያሳደርኸ አምላክ በሰላም አውለን እንላለን፤ ተቤታችንም ስንወጣ ደግሞ አንተው ተከተለን እንላለን፣ እርሻውንም ስንጀምር እንደዚያው ሶስትዜ አማትበን ስራውን እንዲባርክልን፣ መሰናክል እንዳይገጥመን፣ የኛንም ሆነ የከብቶችን ጉልበት እንዲባርክልን እሱን ተማጽነን ስናበቃ ትልማችንን አውጥተን እናርሳለን፡፡[69]

ገበሬው የቀኝ እጁን ጣቶች ከመሐል እስከ ትንሽ ጣቱ ያሉትን እና አውራ ጣቱን ወደውስጥ በማጠፍና አመልካች ጣቱን በመዘርጋት ከላይ ከግንባሩ በመጀመር በሰውነቱ ላይ የመስቀል ቅርጽ በመስራት ከላይ ከግንባሩ ወደታች ወደ ደረቱ ከዚያም ወደ ግራ ትከሻው፣ ቀጥሎም ወደ ከግራ ትከሻው በማድረግ ሶስት ጊዜ የማትብና ስራው የተቃና እንዲሆን፣ በሰላም (በቀኝ) አውለኝ፣ ጉልበቴን ባርክልኝ፣ መሬቱንም ባርከው፣ ከብቶቼን ባርክልኝ፣ በማለት ጸሎት ያደርሳል፡፡

> ይህም ከላይ ሲጀምር ሌባ ጣቱ ሰማይን ያመለክታል ይህም ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት መውረዱን፣ ወደልቡ የሚያመለክተው ከድንግል ማሪያም ማህጸን መወለዱን ወደ ግራ ትክሻው ሲያመላክት ደግሞ ወደ መቃብር መውረዱን ወደ ቀኙ ሲያመላክት ደግሞ ሞትን ድል መንሳቱን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህም ከሰማየ ሰማያት ወርዶ፣ ከድንግል ማሪያም ተወልዶ ሞቶ ሞትን ድል አድርጎ እንደተነሳ የሚገልጽ ነው(እንደ ላይኛው)፡፡

[69] ቄስ ወርቁ ወልደ ጊዮርጊስ፣ አግዛ ጋርዳ ቀበሌ፡ ወዳሽቲ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 27/07/2007፡፡

ከለይ ከተገለጠው ሀሳብ መሰረት ሞትን ድል አድርገህ የተነሳህ አምላክ የኛንም ሀሳብ አሟላልን፡፡ ሶስት ጊዜ የሚያደርገውም በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ለሶስትነታቸው ነው፡፡ አንተ የሚሳንህ ነገር የለምና አንተው ታደገን፤ ጠብቀን በማለት በእለቱ ሊያርስ የፈለገውን ልክ አልፎ አልፎ በመሰንጠቅ ትልም ያወጣል፡፡ በሌላ በኩልም ገበሬው በቀኝም በግራም፣ በላይም በታችም፣ በፊትም በኋላም ያለውን ለስራው እንቅፋት ይሆኑብኛል ብሎ የሚያስባቸውን እንዳትደርሱብኝ በማለት የሚያስጠነቅቅበትና የሚያንገራግርበት ወይም የሚያስፈራበት መንገድም ሊሆን ይችላል፡፡

የማሳ ዝግጅት ሲደረግ እንደ አየር ንብረቱ፣ እንደየ አካባቢው የአፈር አይነት፣ የሚያበቅለው የእህል አይነትና የእርሻ መሳሪያውም የተለያየ ቢሆንም አብዛኛው ስራ ግን በተመሳሳይ ሁኔታ የሚከናወን ነው፡፡ የማሳ ዝግጅቱን አስመልክቶ አቶ ሽመካ እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፤ "የማሳ ዝግጅቱ የተለየ ነው፤ የዳጉሳውም የተለየ ነው፤ የማሽላውም የተለየ ነው፤ የገብሱም የተለየ ነው፣ የስንዴውም የተለየ ነው፤ የጤፉም የተለየ ነው፡፡"[70]

እንደ አቶ ሽመካ አገላለጽ የእያንዳንዱ ሰብል የማሳ ዝግጅት የእርሻው ድግግሞሽ መጠን ልዩነት ያለው መሆኑን ያሳያል፤ ከጊዜው ቀድሞ ወይም ዘግይቶ ቢዘራ፣ እንዲሁም ማሳው ከሚዘጋጅበት ወቅት ውጭ ቢታረስ የሚፈለገውን ያህል ምርት አይሠጥም፤ ወይም ጨርሶ ሊጠፋ ይችላል፡፡ ይህን በተመለከተ ቄስ ወርቁ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> ቦዘኑን መሬት በጥቅምት ሰንጥቀን እንተወዋለን ጸሐይ እንዲገባው፣ ያን እንግዲህ በመጋቢት አንድ ብለን ፈረሳችንን ጠምደን እናርሳለን፤ የጤፍ የሆነ እንደሆነ ያው እንደ ገበሬው ቢሆንም እሰቲደቅ ድረስ ደጋግመን እናርሰዋለን፡፡ ሰባት ጊዜም ስምንት

[70] አቶ ሽመካ ገዳሙ፣ አደጋ ውባጅ ቀበሌ፣ ጓሽታ ደሽ፣ ቃለመጠይቁ 24/06/2007፡፡

> ጊዜም ደጋግመን እናርሰዋለን፡፡ የፈለገ ነገር ቢሆን ግን የጤፍና የስንዴ እርሻ በጥቅምትና በሚያዚያ አይነካም፡፡ አንድ ዓመት ግብርናዎች በግድ እረሱ ብለው በሚያዚያ አሳርሰውን ለፍሬ ሳይበቃ ዋግ[71] በልቶት ቀረ፡፡ በፍሬው ጊዜ ነው የሚመታው፤ በዚህ ምክንያት የጤፍና የስንዴን መሬት በጥቅምትና በሚያዚያ ማንም አያርሰውም፡፡ ይህን እኛ ያመጣነው ሳይሆን ታባቶቻችን የወረስነው ነው፡፡[72]

እንደ ቄስ ወርቁ ገለጻ የእርሻው ስራ እንደ ገበሬው ድካምና ጥንካሬ የሚለያይ ቢሆንም የማሳ ዝግጅቱ እንደ እህል አይነቱ ከሰባት እስከ ስምንት ጊዘ ተደጋግሞ ይታረሳል፡፡ በማሳ ዝግጅቱ ወቅት በጥቅምትና በመጋቢት የስንዴና የጤፍ ማሳ አይታረስም፡፡ ይህን ገበሬዎች ከአባቶች የወረስነው ነው ይበሉ እንጂ እነሱም በተግባር ሞክረው የሚያስከትለውን ጉዳት አይተውታል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ገበሬው ካባቶቹ የወረሰውንና በልምድ ያገኘውን ዕውቀት በመፈተሽ በተሞክሮ አዳብሮ ጥቅሙንንና ጉዳቱን አመዛዝኖ በተግባር ያውላል፡፡ ለቀጣዩ የምርት ዘመን ከተፈጥሮ አደጋ ውጭ ያሉትን ችግሮች የሚፈታበትን መንገድ መሰረት አድርጎ ማሳውን ያርሳል፡፡ የእያንዳንዱንም የሰብል አይነት መዘሪያ ጊዜያቸውን ታሳቢ አድርጎ በማረስ መሬቱን ለዘር ዝግጁ ያደርጋል፡፡

የእርሻውና የእርሻ መሳሪያዎች ተምሳሌታዊነት በሚከተለው መንገድ ቃኝቸዋለሁ፡፡ መሬትና ሴት አንድ ናቸው፡፡ መሬት እንደ ሴት ዘር ተቀባይ ማረሻው ደግሞ እንደ ወንድ ዘር ዘሪ ነው፡፡ እንዲሁም ማረሻው የወንድ የመራቢያ ክፍልን የሚወክል ሆኖ ከማረሻው ግራና ቀኝ የሚገኙት ሁለቱ ድግሮች ደግሞ የወንዱን የዘር ፍሬዎች ይወክላሉ፡፡ በማረሻው መሬትን የማረሱ ሂደትም በወንዱና በሴቷ መካከል ያለውን ጾታዊ ግንኙነት ያሳያል፡፡ ገበሬው ዘርን መሬት ላይ የመዝራቱ ሂደት በሴቷ ማህጸን ከሚረጨው የዘር ፍሬ ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡ መሬት የሰጡትን ተቀብሎ በከርሱ

[71] በፍሬው ወቅት ስንዴንና ጤፍን የሚያጠቃ በሽታ

[72] አቶ አሰጋ አየነው፣ አግዛ ጋርዳ ቀበሌ፡ ስሚዞ ደሽ፡ የቡድን ውይይት 09/07/2007

አቅፎ ከሶስት እስከ አምስት ወር ባለው ቆይታ አዲስ ፍሬ፣ አዲስ ዘር ይሰጣል፡፡ ሴትም የተቀበለቸውን የወንድ ዘር በማህጸኗ ዘጠኝ ወር ከስድስት ቀን ተሸክማ አዲስ ዘር ትተካለች፡፡ ሰብልንና ልጅን መንከባከብ ተመሳሳይ ናቸው፡፡

በእርሻ ወቅት ጎበዙን ለማትጋትና ሰነፉን ለመውቀስ ሥነቃላዊ ግጥሞች ይነገራሉ፡፡ ገበሬው ባህላዊ ዕውቀት ተጠቅሞ በየእለቱ ከስራው፣ ከጊዜው፣ ከወቅቱ፣ ከሁኔታው በመነሳት ስለራሱ፣ ስለሌላው ቃላዊ ግጥሞችን በመፍጠር ይጠቀማል፡፡ በዚህም ጎበዙን ለማበረታታት፣ ሰነፉን ለመውቀስ፣ ራሱን ከድካም ለማውጣት ይጠቀምበታል፡፡ ግቢ /በልግ የእርሻ ወቅት በመሆኑ በዚህ ጊዜ የእርሻ ስራውንና ገበሬውን የተመለከቱ ቃላዊ ግጥሞችን ይጠቀማል፡፡ የስራ ላይ ግጥሞች መፈጠር መንስኤ የሚሆኑት አጋጣሚዎች ከሞላ ጎደል አድካሚና አሰልቺ ስራዎች ናቸው፡፡ ቃላዊ ግጥሞችም የማዝናናት ሚናን በመወጣት በስራው ላይ የሚሳተፉትን ሰዎች ስራዎቻቸውን በተዝናና መንፈስ ለማከናወን ያግዟቸዋል (Finnegan,1977:231)፡፡ በስራ ቦታ ላይ የተፈጠሩ ተዝናኖቶች ለጊዜውም ቢሆን ከአድካሚው ስራ አምልጠው በምናብ ወደ አዲስ የምናብ አለም እንዲገቡ ያግዟቸዋል (Bascom, 1965:279; ፈቃደ፣ 1991፡17-18)፡፡ በዚህ ጊዜ የሚዜሙ የቃል ግጥሞች እየሰሩ ያሉትን ብቻ ሳይሆን የስራ ፍላጎት የሌላቸውም ቢሆኑ በዜማዎቹ ለመዝናናት ሲሉ በስራው ላይ እንዲሳተፉ ያደርጋቸዋል (Gecall, 1970:5)፡፡

በእርሻ ወቅትም የሚባሉ ቃላዊ ግጥሞችን ገበሬው በራሱ የገጠማቸው ወይም በሌላ ሰው ሊገጠሙ የሚችሉ በርካታ ቃላዊ ግጥሞችን ለማንሳት ቢቻልም ለአብነት ያህል ጥቂቶቹ ይቀርባሉ፡፡ የስራ ላይ ግጥሞችን በተመለከተ አቶ ሽመካ የሚከተለውን ብለዋል፡-

አርሶ በበላ በወይፈኖቹ
ይቀኑበታል ጐረቤቶቹ፡፡[73]

[73] አቶ ሽመካ ገዳሙ፣ አደጋ ውባጅ ቀበሌ፣ መስቀለኛ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣ 24/6/2007 - ግጥሞቹ በመረጃ አቃባዮቹ የተነገሩኝ ቢሆንም ግጥሞቹ የማህበረሰቡ ግጥም እንጂ በነሱ (በመረጃ አቀባዮቹ) የተፈጠሩ አይደለም

ግጥሞቹ አውድን መሰረት አድርገው የሚነገሩ በመሆናቸው ይህ ቃላዊ ግጥም የተነገረበት አውድ የእርሻ ወቅት ነው፡፡ ገበሬው እያረሰ ባለበት ስለራሱ የተባለውን ነገር መሰረት አድርጎ የገጠመው ነው፡፡ ገበሬው ስለራሱ ጥንካሬ በመግለጽ ሥነልነቦናውን ይገነባል፡፡ ጠንክረህ ከሰራህ ለራስህ አታንስም አይዞህ በርታ በማለት ለራሱ ስሜት ይነግረዋል፡፡ ስለራሱ የሚወሩትን አሉባልታና ወሬ ከንቱነት ለማስረገጥ በራስ የመተማመን ስሜትን ለመገንባት ይጠቀምበታል፡፡

ከተግባር አንጻር ሲታይ ደግሞ ገበሬው በእርሻ ወቅት እራሱን የሚያነቃቃበትና የሚያበረታታበት፣ እንዲሁም የድካም ስሜቱን የሚረሳበት መንገድ ነው፡፡ ዋናው ተግባሩ እራስን ከድካም ለማውጣት ወይም የድካም መንፈስን ለማስወገድ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ በአንድ አካባቢ ከሚኖረው ማህበረሰብ፣ ጎረቤት… መጣላትን አይፈልግም፡፡ ምናልባትም በሱ ላይ የሚነዛ ወሬ፣ አሉባልታ ካለ በግልጽ ከሚናገርና ከሚጣላ በግጥም ቢናገር ስም ስለማይጠራ ከሱ ጋር የሚጋጭ አይኖርም፡፡ ሊከሰስም ሆነ ሊወቀስ አይችልም፡፡ ያው መልእክቱ ግን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተናጋሪው ይደርሰዋል፡፡ ተናጋሪውም ውስጥ ውስጡን ያፍራል ይሸማቀቃል፡፡ በዚህ መንገድ መልእክቱ ለሚመለከተው አካል እንዲደርሰው በማድረግ ማህበራዊ ኑሮውን ሳያዛባ እና ሳያናጋ መቀጠል ያስችለዋል፡፡

የቡሬ ጌታ የቀኙ በሬ
የኮሎ ጌታ የግራው በሬ
እርፍ እስኪናገር አራሽ ገበሬ

በዚህ ግጥም የቀረበው ጉዳይ የገበሬውን ጠንካሮ አራሽነት ለማሳየት የቀረበ የእርሻ ላይ ግጥም ነው፡፡ ገበሬው ልክ እንደሰው (እንደልጆቹ) ለከብቶችም ስም ያወጣላቸዋል፡፡ “ቡሬ” እና “ኮሎ” በሬዎቹ ናቸው፡፡ የቀኙ በግራ አይጠመድም የለመደው በቀኝ በኩል በመሆኑ ቢጠመድ እንኳን እሺ በሎ አያርስም፤ ያስቸግራል፡፡

የገበሬው ጠንካራ አራሽ መሆን በማህበረሰቡ ዘንድ የመከበርን፣ የመመስገንን እና የመወደድን ስሜት የሚያጎናጽፍ ሲሆን ለራሱ ውስጣዊ ስሜት እርካታን፣ በራስ የመተማመን መንፈስንና ውስጣዊ ኩራትን ይፈጥርለታል፡፡ ማህበረሰቡ በሚፈልገው መንገድ እየሄደ መሆኑን የሚገልጽ በመሆኑ ታላቅ የስሜት እርካታን ይፈጥርለታል፡፡ ይህም ማህበረሰቡ በገነባውና ባበጀው የህልውና መሰረት በሆነው የስራ ልማድ ውስጥ እራሱን አስገብቶ በትክክለኛው መንገድ ላይ መሆኑን ያስመሰክርበታል፡፡ ግጥሙ በሰውኛ ዘይቤ የቀረበ ነው፤ በትክክል እርፉ እንደሰው ይናገራል ሳይሆን በስራ ብዛት እርፉን ገበሬው አዘውትሮ በመያዙ ምክንያት ወዝ ጠግቧል፡፡ ለረጅም ጊዜ እንደሰራበት እጁ የዋለበት እርፍ ይናገራል፡፡

ጎበዙን አራሽ እንደሚያወድሱት ሁሉ በስራው የደከመውንም በሥነቃል መንቀፍ የተለመደ ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ ሽመካ እንደሚከተለው ይገልጹታል፡-

ሀ. እንጀራው የብድር ወጡ የልመና
 አርሶ የማይበላ ያልታደለ መና፤

ለ.ማረስ ነበረ እንጅ ፀሃይ እስከሚከር፣
 ከሰው ደጃፍ ሂዶ አንገት ከማቀርቀር፡፡

ሐ. በበጋም እንዳያርስ ፀሐዩን እየፈራ፣
 በክረምት እንዳያርስ ዝናብ እየፈራ፣
 ልጁ እንጀራ ቢለው በጅብ አስፈራራ፡፡[74]

እነዚህ ሶስት ቃላዊ ግጥሞች ለሰነፍ ገበሬ የተነገሩ ናቸው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ስንኞች የማይሰራ ሰነፍ ገበሬ ኑሮውን ማሸነፍ ስለማይችል ሁልጊዜም በሰው ድጋፍ

[74] አቶ ሽመካ ገዳሙ፣ አደጋ ውባጅ ቀበሌ፣ መስቀለኛ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣ 24/6/2007

የሚኖር መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ብድር በሆነ ወቅት የሚመለስ/ የሚከፈል ሲሆን በልመና የሚገኘው ደግሞ የማይመለስ ነው፡፡ ብድርም ሆነ ልመና ደግሞ የሰው ፊትን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ለመበደርም ሆነ ለመለመን ከሰው ፊት መቆምን ግድ ይላሉ፡፡ የመስራት አቅሙ፣ ጤናው፣ መሬቱ እያለው ሊጠቀምበትና ሊለወጥ ያልቻለ እንደሆነ የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ ለሰነፍ ገበሬ ስድብ ነው፡፡ ስድቡም ለሱ ብቻ ሳይሆን ለልጆቹ፣ ለሚስቱና ለቤተሰቡ ይተርፋል፡፡ ያሳፍራል፤ አንገት ያስደፋል፡፡ ከውጭ የተባለው እቤቱም ድረስ ተከትሎት ይገባና እረፍት ይነሳዋል፡፡ ይህም ጸጸትን ይፈጥራል፡፡ ጸጸት ደግሞ ቁጭትን ይወልዳል፡፡ ሰሜቱ አጥንትን ሰርስሮ የሚገባ በመሆኑ ወደቀድሞው አድራጎቱ እንዳይመለስና ለስራ እንዲነሳሳ ያደርገዋል፡፡ ይህ ገበሬው ከዚህ አድራጎቱ ተቆጥቦ መሬቱን በአግባቡ እንዲያርስና ጠንክሮ እንዲሰራ የማድረግ መንፈስን ያዳብራል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቃላዊ ግጥሞች ለልጆችም የስነምግባር መቅረጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ የትዋለ ሲናገሩ ለሰነፍ ገበሬ ተብለው የሚገጠሙ ግጥሞች ለተገጠመለት ሰነፍ ገበሬ ብቻ አይደለም፡፡ ለልጆችም ነው፡፡ ይህን የሰማ ሕጻን ነገ መሰደቢያ መሆንን አይፈልግም፡፡ ስለዚህ እንደዚ ለላመሰደብ ጠንካራ ይሆናል፡፡ ይህን ሲሰማ እኔማ ሳድግ እንደከሌ አልሰደብም ይላል፡፡ ተግጥሙ ተነስቶም ሰብል እንዴት ነው የሚጠበቀው? በማለት መጠየቅ፣ ማየት፣ ይጀምራል፡፡ በዚህ መንግድ ቃላዊ ግጥሞች ዕውቀት የማስተላለፊያነት ፋይዳ አላቸው፡፡

ገበሬው በሁሉም ወቅቶች የሚያከናውነው በርካታ ተግባራቶች አሉት ከነዚህም ውስጥ አንዱና ዋነኛው ተግባር ተፈጥሯዊ የሆነ የመሬት ማዳበሪያ ብስባሽ ማዘጋጀት ነው፡፡ ይህም ከዓመት ዓመት የማያቋርጥ ተግባር ነው፡፡ ይህንን ተግባር የምታከናውነው ሴቷ ናት በየቀኑ ከከብቶች በረት እየተጠረገ የሚወጣውን የከብቶች አዛባና ጥራጊ፣ የበጎችን በጠጥና የፈረሶችን ፋንድያ በአንድ ላይ በማድረግ በእርሻው ማሳ ላይ በአንድ ላይ በመከመር አየር እንዳይገባው ላዩን በእበት ትመርግና ትተወዋለች፡፡ ይህም ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ከላይ የደረቀውን በመቀርፋት ለማገዶ እንዲሆን ሌላውን

የበሰበሰውን ደግሞ እዚያው ማሳው ላይ በመፈንጨት ትተወዋለች፡፡ በዚህ መንገድ ባህላዊ ማዳበሪያን ለሰብል ምርት ይጠቀማሉ፡፡

> ድሮ የምናደርገው አዛባውን ፍጉን አንድቦታ በመከመር ስናርስ ማሳው ላይ ደፍተን እናርሰው ነበር፡፡ እኔ አሁን የተጋኔን[75] የመንግስቱን ማዳበሪያ አላሥነካውም፡፡ እኔ ብቻ እንዳልመስልሽ ሁሉም ነው፡፡ ድቡሽቱን[76]፣ ጥራጊውን፣ አዛባውን ነው የምንጠቀመው፡፡ የጓሮ መሬት እኮ ቀልዝ[77] ነው፡፡ በድቡሽቱ በምኑ የቀለዘ ነው፤ ሌላ አይፈልግም፤ በተረፈ የጤፉን መሬት ገብስ፣ ገብሱን ድንች፣ እያደረግን ስንዘራው ይሻለዋል፤ እምቢ ሲል ደሞ ግብጦ መሬት ያቀልዛል እሱን ዘርተን እንተወዋለን፣ የግብጦ መሬት አይታረስም፡፡[78]

ገበሬው በውርስ ከማህበረሰቡ ያገኘውን ዕውቀት መሰረት በማድረግ ከአካባቢው ያየውን፣ ያገኘውን ነገር፣ በማሰባሰብና የግል ችሎታውን በመጠቀም ወደ ዕውቀት ለውጦ በተለያዩ ተግባራት ላይ ይከውነዋል፡፡ ከነዚህም አንዱ ባህላዊ ማዳበሪያ በማዘጋጀት ለራሱና ለአካባቢው ማህበረሰብ የሚሆን ዕውቀት ፈጥሯል፡፡ ይህን ባህላዊ ማዳበሪያም በጓሮአቸው አዘጋጅተው በከብት በማጓጓዝና ወደ ገጠር መሬታቸው በመውሰድ ከአምስት እስከ ሰባት ቀን ከእርሻው ላይ ጸሐይ እንዲመታው አልፎው አልፎው ቁጭ ቁጭ ያደርጉታል፡፡ ከሳምንት በኋላም እያገላበጡ በማረስ ካፈሩ ጋር እንዲዋሃድ ያደርጉታል፡፡ ይህም የሚሆነው በጉድጓድ ውስጥ ሲቆይ በእርጥበቱ የተፈጠረው ሙቀት መሬቱን እንዳያቃጥለው (ለበጥ/ ምቺ እንዳይመታው) ለማድረግና መቀዝቀዝ ስላለበት

---

[75] የጓሮ መሬቱን

[76] ድቡሽት፡- የእህል ንፋሽ ገለባና ከቤት ውጪ (የደጅ) ጥራጊ የተደበላለቀና ብዙ አይነት ነገሮችን የያዘ ቆሻሻ ማለት ነው፡፡

[77] ቀልዝ፡- ለም የሆነና የዳበረ መሬት

[78] አቶ አለማየሁ ምትክ፣ አብስላ ዋርዳ ሳሙኤል ቀበሌ፣ ዳምቢሲ ደሽ፣ ቃለ-መጠይቁ የተደረገበት ቀን 24/06/2007፡፡

ነው፡፡ ከዚህም ሌላ በእርጥበቱ ምክንያት የተፈጠሩ ነፍሳት እንዲጠፉ፣ እንዲሁም መዋሃድ ያለባቸው ነገሮች በፀሐይ ብርሃን አማካኝነት እንዲዋሃዱ ለማድረግ ነው፡፡

ሀገሬው ሰው ከውጭ የመጣለትን ዕውቀት በዘፈቀደ አይቀበልም፡፡ ከሚሰጠው ጥቅም አንጻር ለራሱ በሚመች መንገድ ከነባሩ ዕውቀት ጋር በማጣጣም ይተገብረዋል፡፡ እንዲሁም በዚህ መንገድ የተቀበለውን ባህላዊ የግብርና ዕውቀት በየጊዜው እያዳበረው ይሄዳል፡፡ ሁለቱንም አይነት ሳይንሳዊውን ባህላዊውን ማዳበሪያ አጠቃቀም አስመልክቶ ቄስ ወርቁ ሲናገሩ

> ባህላዊው ማዳበሪያ (ኮምፖስቱ) ከጉድጓድ ይወጣና አልፎ አልፎ በታረሰው በማሳው ላይ ይደፋል፡፡ ይህ የተደፋው ብስባሽ ከ5-7 ቀን ድረስ በማሳው ላይ ይቆያል፡፡ ይህ የሚሆነው በእርጥበቱ የተፈጠሩ ነፍሳት ካሉም ይጠፋሉ፡፡ ሙቀቱም ይበርዳል፡፡ ከ7 ቀን በኋላ እየታረሰ ከአፈሩ ጋር እንዲደባለቅ ይደረጋል፡፡ ተደጋግሞም ስለሚታረስ በደንብ ይዋሃዳል፡፡ ዩሪያና ዳቡን የምናደርገው ስንዘራው ነው፡፡[79]

ገበሬዎቹ የማዳበሪያዎቹን በተለያየ ጊዜ መጠቀም የሚመርጡበት ምክንያት ሁለቱ ባንድ ላይ ቢጨመሩ አንደኛ መሬቱን ሊያቃጥሉት ይችላሉ ብለው በማሰባቸው ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ኮምፖስቱ ከአፈር ጋር ለመዋሃድ የሚወስድበትን ጊዜ በማሰብና ሁለቱ አንድላይ ሲሆን ምን እንደሚፈጠር ስለማይታወቅ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡[80]

---

[79] ቄስ ወርቁ ወልደ ጊዮርጊስ፣ አግዛ ጋርዳ ኤሊያስ ቀበሌ፡ ስሚዞ ደሽ፡ ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣ 09/07/2007

[80] አቶ ሽመካ ገዳሙ፣ አደጋ ጓሽታ ውባጅ ቀበሌ፣ መስቀለኛ ደሽ፣ ቃለመጠይቁ የጠደረገበት ቀን 27/07/2007



ፎቶ 12፡- ባህላዊ ማዳበሪያ/ ኮምፖስት የተደፋበት የእርሻ መሬት፣ ወዳሽቲ፣ 9/7/2007

ባህላዊ ማዳበሪያን አስመልክቶ የሚባሉ ቃል ግጥሞችን በተመለከተ አቶ ይሁን እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

ሀ. ማዳበሪያ ዘርቶ አንድ ዓመት ከመሆን
በፍግ መጠቀም ነው በራስ መተማመን፡፡



ፎቶ 13፡-ቄስ ወርቁ ባህላዊ ማዳበሪያውን ከአፈሩ ጋር ሲያዋህዱ ወዳሽቲ፣ 9/7/2007

ለ. ማዳበሪያ ዘርቶ መሬት ከማስበላት
ፍግን መጠቀም ነው ጭቅጭቅ የሌላት፡፡[81]

የዚህ ጥናት አካባቢ ማህበረሰብ በቃላዊ ግጥሞች አማካኝነት ገበሬው ሃሳቡን፣ ስሜቱን፣ ፍላጎቱን፣ መጥላት፣ መውደዱን፣ ይገልጽበታል፡፡ አካባቢው ማህበረሰብ በከብቶች ፍግ፣ በቤት ጥረጊ አዘውትሮ ይጠቀማል፡፡ በዚህም መሰረት በ "ሀ" የተገለጸው የመጀመሪያው ግጥም ማዳበሪያ ጥሩ ምርት የሚሰጠው ለአንድ ዓመት ብቻ ነው፡፡ ማለትም ሁልጊዜ መጨመር ያለበት መሆኑን ነው፡፡ ባህላዊ ማዳበሪያ አንድ ዓመት ቢጨመር ቢያንስ ለሁለት ዓመት የመሬቱን ለምነት ይጠብቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በራስ የተዘጋጀ በመሆኑ አያስፈራም የሚል ስሜት አለው፡፡ ማዳበሪያው ግን ምን ሊያስከትል ይችላል የሚል ስጋትን እንደሚፈጥርና እንደማይተማመኑበት ያሳያል፡፡

በ"ለ" የተጠቀሰው ግጥም ደግሞ ሃሳቡ ከመጀመሪያው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ የሁሉም ስጋት ማዳበሪያው የመሬቱን ለምነት ያጠፋዋል፡፡ ካለሱ ምንም ማድረግ እንደማይቻሉ የሚገልጽ ነው፡፡ ከዚህ ይልቅ ምንም ወጪ የማያስወጣውንና ከማንም ጋር እሰጥ-አገባ የማያስነሳውን ባህላዊ ማዳበሪያ መጠቀም እንደሚገባ በስንቃሉ ይገልጻል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በብድር በሚመጣው ማዳበሪያ መዝራት ወቅቱ ጠብቆም ቢሆን አዳው መከፈሉ ስለማይቀር ክፈሉ በሚል በየጊዜው ከባለሙያዎች ጋር ሰለሚያጣላቸው ከዚህ ሁሉ በባህላዊው ብንጠቀም ይሻላል የሚል ነው፡፡

በቀደመው ጊዜ እንደዚህ እንዳሁኑ በተስፋፋ መልኩ ሳይንሳዊ ማዳበሪያን አይጠቀሙም ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን መሬቱ ስለተራቆተና ካለማዳበሪያ ስለማያበቅል ሳይንሳዊው ማዳበሪያና ብስባሽን ይጠቀማሉ ገበሬው ባህላዊውንም ሆነ ሳይንዊውን ማዳበሪያ የተመለከተ የተለያዩ ቃላዊ ግጥሞችን ይጠቀማል፡፡ የሳይንሳዊ ማዳበሪያ እና ባህላዊ ማዳበሪያ ጠቀሜታ፣ የሚያስከትለውን ችግርና በወቅቱ አለመድረሱንና የተመለከቱ ቃላዊ ግጥሞችን በመጠቀም ደስታውንም ሆነ ብሶቱን ይገልጻል፡፡

[81] አቶ አድማስ ይሁን ፣አግዛ ጋርዳ ኤሊያስ ቀበሌ፣ ሹምታ ደሽ፣ ቃለመጠይቁ የተደረገበት ቀን 27/09/2006

ዋጋው ባይወደድ በወቅቱ ቢመጣ
የአስር ዓመት ቀለብ በአንድ ዓመት በወጣ፡፡
ዘሩ ሰባት መቶ ማፋፊያው በሺ አስር
መንግስት አልሰማም ወይ ገበሬው ሲከስር፡፡
ዝናቡ ዘነበ እርሻውም ደቀቀ
ዩሪያና ዳቡ ከሰማይ እራቀ፡፡[82]

እነዚህን ስነቃሎች ስንመለከት በአሁኑ ሰዓት ገበሬው እየተጠቀመ ያለው ሳይንሳዊ ማዳበሪያ የዋጋውን ውድነትና በወቅቱ በሚፈለግበት ጊዜ እንደማይደርስ የሚገልጹ ናቸው፡፡ ገበሬው የምርጥ ዘሩና የማዳበሪያውን ለመጠቀም አስፈላጊ ቢሆንም የዋጋው ውድነት ለምን መንግስት ዝም ይላል መፍትሄ ይስጠን እኛ ልንቋቋመው አልቻልንም ይላል፡፡ ሌላው ቀርቶ መሬታቸውን አለስልሰውና አዘጋጅተው የሚፈልጉትን በወቅቱ እንደማያገኙና ያም ቢሆን ዋጋው ገበሬውን እያከሰረውና መሬቱንም እንዳራቆተበት ይገልጻል፡፡ ገበሬው ካየው፣ ከሰማው፣ ከደረሰበት ነገር በመነሳት የፈጠራ ዕውቀቱን ተጠቅሞ የስነቃሎችን/ ቃላዊ ግጥሞችን በመፍጠር ይጠቀማል፡፡ ገበሬው ምርጥ ዘሩንም ሆነ ማዳበሪያውን በግልጽ አልጠቀምም ቢል የሚደርስበትን ነገር ለመከላከል ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ በስነቃሉ አማካኝነት ይተነፍሳል፡፡

ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውንና በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የተደነገጉትን ህጋጋቶች ማፍረስ ዋጋ ያስከፍላል ብለው ያምናሉ፡፡ ለዚህም የጤፍና የስንዴን ማሳ በጥቅምትና በመጋቢት ማረስ ሰብሉ ለፍሬ በሚደርስበት ጊዜ በጥቅምት ዋግ ይበላዋል፣ ምርቱም ይቀንሳል በማለት በእነዚህ ወራቶች የጤፍና የስንዴን ማሳ በፍጹም አያርስም፡፡

[82] ወጣት ዳኚ ይሁን፣ (የመስክ እረዳቴ) አግዛ ጋርዳ ኤሊያስ ፣ ሹምታ፣ 27/07/2007( ሰዎቹ ስለማዳበሪያ የሚናገሩትን ሲሰማ እኛም እንደዚህ እየተባለ ይዘፈናል/ ይገጠማል በማለት የነገረኝ ግጥሞች ናቸው፡፡

ሁሉም የአዝርዕት አይነት አንድ አይነት የማሳ ዝግጅት የላቸውም፡፡ እያንዳንዱ የአዝርዕት አይነትም የራሱ የሆነ የማሳ ዝግጅት ያለውና እንደ ማሳ ዝግጅቱ ሁሉ የየራሱ የሆነ የመዘሪያ ወቅትም ያለው መሆኑን ነው፡፡

ከመጋቢት እስከ ግንቦት ያለው ጊዜ በስፋት የእርሻ ስራ የሚከናወንበት ጊዜ ቢሆንም አንዳንድ የሰብል አይነቶችም ድንች፣ ገብስና በቆሎ የሚዘሩበት ወቅት ነው፡፡ ድንች የሚዘራው በመጋቢትና በሚያዚያ በደረቅ ወቅት ነው፡፡ በደንብ ታርሶና ለስልሶ በተዘጋጀው መሬት ላይ በበሬ ወይም በፈረስ ፈሰስ እየተቀደደ በፈሰሱ ላይ የድንች ዘር ይዘራል፡፡

አቶ ሃብታሙ ስለ ድንች ያዘራር መንገድ ሲናገሩ፣ "በዚህ በኛ ድንችን በደረቁ ዝም ብለን ነው የምንጥለው በመጋቢት ላይ እስከ ሚያዚያ አጋማሽ ማለት ነው፤ ራሱ ውኃ ስላለው አይሞትም፤ በዝናብ ከዘራነው ግን በሽታ ያጠቃዋል፤ራሱን ተቋቁሞ ፍሬ አይሰጠንም በደረቁ እንዘራውና ዝናብ መጠበቅ ነው"[83] ይላሉ፡፡

አያይዘውም የድንች ዘር ሲዘሩ ያገኘኋቸው አቶ ሃብታሙ ስለ ድንች አዘራር የሚከተለውን ብለዋል፡-

> እኔ በበሬው በቀደድሁት ቦይ ላይ ዘሩን እየጣሉ ይከተላሉ፡፡ ስመለስ ደግሞ በበሬው አፈር እያለበስሁ እመለሳለሁ፡፡ ሁለት ጊዜ ሄጄ በሶስተኛው ላይ እየጣሉ ይከተላሉ፡፡ በሽናው[84] መሀል የሚቀረው መሬት ለመኮትኮቻና አፈር ማሳቀፊያ ሲሆን ሐምሌ ላይ ደግሞ ተጎንና ተጎኑ ሴት አተርና ባቄላ እተክልበታለሁ፡፡[85]

[83] አቶ ሀብታሙ ጌታነህ፣ ፣ አደጋ ውባጅቀበሌ፣ መሀል አምባ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 18/09/2006፡፡
[84] ድንች የሚዘራበት እያንዳንዱ መስመር
[85] አቶ ሀብታሙ ጌታነህ፣ አደጋ ውባጅ ቀበሌ፣ መሀል አምባ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 03/07/2007

ይህንን ሃሳብ እነ ቄስ ወርቁ[86]፣ ቄስ አወቀ[87]፣ አቶ ሀብታሙ[88]፣ አቶ ሞላ[89]፣ ሲያጠናክሩ ድንች መዝራት ሳይሆን የሚባለው መጣል ነው። ድንች በሚጣልበት ወቅት የመጀመሪያው ከተጣለበት መስመር የሚቀጥለው እስኪጣል ድረስ በከብት ሶስት ጊዜ ይመላለሳል (ሶስት መስመር ያርሳል)። ይህም ድንቹ ከተጣለበት ቀጥሎ ያለው ለዘሩ አፈር ማልበሻ ሲሆን ቀጣዩ ደግሞ እንዲሁ ለመስመሩ እርቀት መስጫ፣ ሶስተኛው ደግሞ ለቀጣዩ መስመር መጣያ ነው ይላሉ። በመጋቢትና በሚያዚያ በደረቁ የተዘራው ድንች ዝናብ ካገኘ ቶሎ ይበቅላል። አቶ ይሁን ስለ ድንች ሲገልጹ፡-

> ንሺ መሬት ብለን በደረቁ የጣልነው ድንች ዝናብ ሲያገኝ ሽክክ ብሎ ይወጣል፤ ያ ሁለት ጆሮ እንዳወጣ አፈሩን ብድግ ብድግ በማድረግ ያልወጣም ቶሎ እንዲወጣ እንቀሰቅሰዋለን፤ ተዚያ ወዲያ በደንብ ሲበቅል በሁለት ሰንበቱ[90] በደንብ ይኮተኮታል። አሁንም በሁለት ሰንበቱ በከብት እንደግረዋለን። ተዚያ ወዲያ መቆፈሪያ አየነካውም። ተተነካ ያፍራል፤ ይደነግጣል ፍሬም አይሰጥም በማለት ይገልጻሉ።[91]



ፎቶ 14፡- ድንች ዘር ሲጣል (ሲዘራ) ጓሽታ፣ 8/8/2007

[86] ቄስ ወርቁ ወልደ ጊዮርጊስ፣ አግዛ ጋርዳ ቀበሌ፣ ስሚዞ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ፣ 09/07/2007
[87] ቄስ አወቀ ተፈራ፣ አብስላ ዋርዳ ቀበሌ፣ ሳሙኤል ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 03/07/2007
[88] አቶ ሀብታሙ ጌታነህ፣ አደጋ ውባጅ ቀበሌ፣ መሀል አምባ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 03/07/2007
[89] አደጋ ውባጅ ቀበሌ፣ መስቀለኛ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 0607/2007
[90] ሰንበት ማለት እሁድ ሲሆን አንድ ሰንበት፣ ሁለት ሰንበት ሲል አንድ ሳምንት ሁለት ሳምንት ማለት ነው።
[91] አቶ ይሁን አድማስ፣ አግዛ ጋርዳ ቀበሌ፣ ሹምታ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣ 04/09/2006።

በጥቅሱ መግቢያ ላይ የተጠቀሰው "ንሺ" መሬት ተብሎ የተቀሰበት ምክንያት መሬት ልክ እንደ ሴት ዘር ተቀብላ በመያዝ ለፍሬ እንዲበቃ ታርጋለች፡፡ እህል ተዘርቶ ለፍሬ እስኪበቃና እስኪሰበሰብ ድረስ ከፍተኛው ሚና የመሬት ነው፡፡ ሴትም ተቀበለችውን የወንድ ዘር በማህጸኗ ተሸክማ የመያዝ ሃላፊነት አለባት ስለዚህ ሴት መሬት ተምሳሌት በመሆኗ ነው፡፡ ድንች ሁለት ቅጠል እንዳወጣ የመጀመሪያ ዙር ኩትኳቶ ይከናወናል፡፡ ይህም የጠበቀው አፈር እንዲቀል/እንዲላላ ለማድረግ ሲሆን የመጀመሪያው ኩትኳቶ በተከናወነ በአስራ አምስት ቀን ለሁለተኛ ጊዜ ይኮተኮታል፤ በድጋሚ ለሶስተኛ ጊዜ ይኮተኮታል፤ በመጨረሻም በፈረስ (በበሬ) ይደገራል፡፡ ከዚህ በኋላ ይደነግጣል[92] ስለሚባል ምንም አይነት መቆፈሪያ አይነካውም፡፡



ፎቶ 15፡- ድንች ሲኮተኮት[93]



ፎቶ 16፡- ድንች ሲደገር/አፈር ሲታቀፍ[94]

ገበሬው በአካባቢው ባገኘው ዕውቀት ተጠቅሞ በድንች ዘር መሃል ለመኮትኮቻና አፈር ማሳቀፊያ ቦታ በመተው በእያንዳንዱ መስመር መሀል የሚኖረውን ክፍት ቦታ


[92] "ይደነግጣል" የሚሉት ድንቹ በስሩ የሚያፈራ በመሆኑና ስር እየሰደደና እያሰፋ ስለሚሄድ ስሩ ከተነካ ያፍራል ማለታቸው ነው፡፡ ይህም በሚኮተኮትበት ወቅት ስሩ ሊቆራረጥ ስለሚችል አጥጋቢ ፍሬ እንዳይሰጥ ይሆናል፡፡

[93] ሹምታ፣ 4/9/2006

[94] ሹምታ፣ 15/10/2006

በሚያርሰው መስመር በመለካት ይተዋል፡፡ ኮትኮቶ እና አፈር አሳቅፎ ሲጨርስም በሚኖረው ባዶ ቦታ ሌላ ዘር ይዘራበታል፡፡

አቶ የኔት "በፊት መሬቱ ሰፊ በነበረበት ጊዜ ሁሉም፣ ሴት አተሩም፣ ባቄላውም እራሱን በቻለ ማሳ ይዘራ ነበር አሁን ግን በድንቹ መሃል ይዘራል፤ ከጤፉ መሬትም አንድ ሁለት ሽና ተቀንሶ ይዘራል፡፡ ኑግና ተልባም እንደዚሁ ነው የሚዘራው"፤[95] በማለት ይገልጻሉ፡፡ በገበሬዎች ዘንድ የምትባክን የእርሻ መሬት የለችም፡፡ ሌላው በዚህ ወቅት የሚዘራው በቆሎ ነው፡፡ በቆሎ የሚዘራው በብተና ሲሆን የሚዘራበት ወቅት ደግሞ በአእዋፋት የመለቀም ሁኔታው ሰፊ ነው፡፡ የተዘራው በቆሎ ወፍ እንዳይለቅመውም ለማድረግ በማሳ ውስጥ "አምሳያ"[96] በመስራት ይከላከሉታል፡፡




ፎቶ 17፡- አምሳያ የተደረገበት የቦቆሎ ማሳ አግዛ 12/9/2006

[95] አቶ የኔት ፈንታሁን፣ አብስላ ዋርዳ ቀበሌ፣ ባኳ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ፣ 06/07/2007
[96] ማሳ ላይ እንጨት በመትከል ሰው እንዲመስል ያረጁ ልብሶችን በማድረግና አሮጌ ባርኔጣ በመሰካት የሚሰራ

ሌላው በዚህ ወቅት የሚዘራው ማሽላ ነው፡፡ በአካባቢው አጠራር ማሽላ በመባል የሚታወቅ ሲሆን በቆላ ሰም አካባቢ ከመጋቢት 25 እስከ ሚያዚያ 15 ይዘራል፤ በደጋውና በወይና ደጋው አካባቢ ደግሞ በግንቦት ይዘራል፡፡ ስለ ማሽላ አቶ ልመንህ ሲናገሩ ሁለት አይነት የማሽላ ዘር አለ ይላሉ፡፡ አገሬ ማሽላ ሃረርጌ (ነጭና ቀይ)ና ቸኮለች[97] ማሽላ የሚሉት ናቸው፡፡ ሃረርጌ ማሽላ በሚያዚያ መጨረሻ ተዘርቶ በጥቅምት የሚደርስ ሲሆን ፈጠኔ ማሽላ ደግሞ የሶስት ወር በመሆኗ በነሃሴ ትደርሳለች፡፡ ስያሜዋን ያገኘችው ለፍሬ ከምትደርስበት የጊዜ ማጠር ጋር በተያያዘ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡[98] ማሽላ በተዘራ በአንድ ሳምንት ውስጥ ይበቅላል፤ ሶስት ቅጠል ማውጣት ሲጀምር ይኮተኮታል፤ ሶስት ቅጠል ሲወጣ ተክሉ ጠንክሯል ስርም ሰዷል ስለሚባል ነው፡፡ ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ የኮተኮታል፣ ከአንድ ወር በኋላ ምንጣሮ ይመነጠራል፡፡

የገብስ መሬት በመጋቢት፣ በሚያዚያና በግንቦት ከአራት እስከ አምስት ጊዜ ተደጋግሞ ከታረሰ በኋላ ከግንቦት አስራ አምስት እስከ ግንቦት ሰላሳ ድረስ ይዘራል፤ ቄስ ታዬ "ገብስ ዝናቡ ተሰጠ ተግንቦት ይዘን እስተ ሰኔ መባቻ እንዘራለን" ይላሉ፡፡[99] ገብስ መታረም ስለማያስፈልገው አይታረምም፡፡

የዳጉሳ መሬት ልክ እንደ ጤፍና ስንዴ ተደጋግሞ መታረስን ይፈልጋል፡፡ ከአምስት እስከ ስምንት ጊዜ መታረስና መሬቱ በሚገባ መለስለስ አለበት፡፡ ከተዘራና ከበቀለ በኋላም አንድ ጊዜ ብቻ አረሙ ይነቀላል (ይታረማል)፡፡

ይህ ወቅት የእርሻ ጊዜ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም ገበሬ እኩል ሰራተኛና ስራ ወዳድ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ጠንካራ ገበሬ ያለውን ያህል ሰነፍና ደካማ የሆነም ገበሬ አለ፡፡ አንዳንድ ገበሬ አቅሙ እያለውና መስራት እየቻለ መሬቱን አከራይቶ ቤተሰቡን በርሀብ የሚቀጣም አለ፡፡ ቄስ ወርቁ ሲናገሩ "በስመ ገበሬ ሁሉም አንድ አይደለም

[97] ከሌላው ማሽላ ዘር ቀድማ በሶስት ወር በነሃሴ የምትደረስ
[98] አቶ ልመን ዳኛው፣ አግዛ ጋርዳ ቀበሌ፣ ሹምታ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን 29/07/07፡፡
[99] ቄስ ታዬ ታፈረ፣ አብስላ ዋርዳ ቀበሌ፣ ዋህሳ ፣ ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን፣ 24/06/2007፡፡

ቤተሰቡን በረሀብ እየቀጣ መሬቱን አከራይቶ አረቄ ሲጠጣ የሚውልአለ፡፡ እንዲህ አይነቱ አገር አሰዳቢ እንዲህ እየተባለም ይሰደባል፡፡" እያይዘውም ቄስ ወርቁ ግጥሙን እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡-

ያላረሰ ጎበዝ እርፍ ያልነቀነቀ
በሐምሌ መባቻ ተጣጥፎ ወደቀ፡፡[100]

ማህበረሰቡ ከሳሽና ነቃሽ በሌለበት ቃላዊ ግጥሙ አማካኝነት ባገኘው አገጣሚ ሁሉ ደካማውን/ሰነፉን ይወቅሳል፤ ምክንያቱም Bascom (1954፡ 333-349) እንደሚሉት የፎክሎር አንዱ ተግባር ማስተማር በመሆኑ ከስህተታቸው እንዲማሩ በስም እየተጠቀሱ ይገጠምባቸዋል፡፡

በዚህም መሰረት በእርሻ ስራው ደካማ የሆነ ገበሬ ክረምቱን መውጣት አይችልም፤ ያንን የችግር ወቅት ሊያሳልፍ የሚችለውን ጎመን እንኳን መዝራት ባለመቻሉ እስከ ሐምሌ እንኳን መድረስ አልቻለም፤ የሚል ነው፡፡

ሲነግዱ አትነግድ ሲያረሱ አትረስና
አሟረቱብኝ በል ተጥላው ዋልና፡፡[101]

ተኝቶ እየዋለ ተምሳናው ጥላ
ሰው ዋለብኝ ይላል አልሽ አይበለኝና፡፡[102]

አንዳንድ ስራ የማይወድ ሰው የራሱን ድክመት በሰው በማላከክ ከጥፋቱ ለማምለጥ ሲሞክር ይስተዋላል፡፡ ለምን አትሰራም ቢባል እንዳልሰራ ተውሎብኛል (ተደግሞብኛል)

[100] ቄስ ወርቁ ወልደ ጊዮርጊስ፣ አግዛጋርዳ ኤሊያስ ቀበሌ ፣ ስሚዞ ደሸ፣ ቃለመጠይቅ 09/07/2007፡፡
[101] አቶ ጥሩነህ ቢተው፣ ፣ በቡድን አንድ ወይይት ወቅት የተናገሩት፣ 21/07/2007፣ጓሽታ፡፡
[102] ወ/ሮ ውዴ ተካ፣ አብስላ ዋርዳ ሳሙኤል ቀበሌ፣ ሳሙኤል ደሸ፣ ቃለመጠይቅ 03/07/07፣

ይላል፡፡ የመጨረሻውን ስንኝ ብንመለከት "ተውሎብኛል ይላል አልሸ አይበለኝና"[103] የተሰመረበት ሃረግ የሚያመለክተው ፈጣሪ ይህን ተናገርሽ ብሎ ከግፍ አይቁጠርብኝ፤ እኔንም እንደሱ ከመሆን ያውጣኝ ነው የምትለው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ለልጆቻቸው የስራን አስፈላጊነት ይነግሩበታል፡፡ ማንም ሰው ካልሰራ ስለሚቸገር ከዚህ ለማምለጥ ጠንክረው መስራት እንዳለባቸው በግጥሙ ይነግሯቸዋል ያንን እያዜሙ ያድጋሉ፤ ይሰራሉ፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ "ግፍ መናገር/ በሰው መፍረድ" ጥሩ አይደለም በራስ ይደርሳል ስለሚባል ያንን በመፍራት ፈጣሪ ይህን ተናግረሻል ብሎ ከግፍ አይቁጠርብኝ የሚል ነው፡፡ ሰነፉን እንደሚወቅሱት ሁሉ በተቃራኒው ደግሞ ጠንካራውንም ያበረታታሉ፡፡

"ያረሰማ ጎበዝ እርፍ የነቀነቀ
ወፍጮው እንዳገሳ መስከረም ዘለቀ፡"[104]

እነዚህን ሁለት ስንኞች ብንመለከታቸው ጠንክሮ ያረሰ ገበሬ ምን ጊዜም ቢሆን በችግር አለንጋ አይገረፍም፡፡ ቤቱ ሙሉ ነው፡፡ የክረምቱን ወራት ያለ ምንም ችግር ያልፈዋል፡፡ መስከረም የብርሃን እና የተስፋ ጊዜ ነው፡፡ ሌላው ቢቀር በመስከረም ሰመሬታ ገብስ ይደርሳል ስለዚህ ጠንክሮ በግንቦት የዘራው በነሐሴ ስለሚደርስለት መሸጋገሪያ አለው ማለት ነው፡፡ የበልጉ እርሻ የተዘራው ተዘርቶ ያልተዘራው ደግሞ ለዘር ዝግጁ ሆኖ ወደ ክረምቱ ይሸጋገራል፡፡

## 5.3. ክረምት (ከሰኔ እስከ ነሃሴ)

እነዚህ ወራቶች የእርሻ በሰላ፣ የዘር፣ የኩትኳቶ፣ የአረም፣ በደጋውና በወይና ደጋው አካባቢ የአጨዳና የውቂያ ጊዜያቶች ናቸው፡፡ በሚያዚያና በግንቦት የተዘሩት ድንችና

---

103 አጽንኦቱ የኔ ነው

104 ወ/ሮ ውዴ ተካ፣ አብስላ ዋርዳ ሳሙኤል ቀበሌ፣ ሳሙኤል ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 03/07/07፡፡

ማሽላ (በቆሎ) በሰኔ የሚታረሙበትና የሚኮተኮቱበት ጊዜ ነው፡፡ በግንቦት ግልሻሽ[105] የታረሰው እርሻ በሰኔ ተደጋግሞ ይታረሳል፣ ለዘርም ይዘጋጃል፡፡ የክረምቱ ወራት በገበሬው ዘንድ የጨለማ ጊዜ ነው፡፡ "የሐምሌ ጨለማ" ይባላል፡፡ የችግር፣ የሥጋት፣ የሰቀቀን ጊዜ በመሆኑ በጥቁር ይመሰላል፡፡

የዳጉሳ እርሻ ከስድስት እስከ ሰባት ጊዜ ተደጋግሞ የሚታረስና የሚለሰልስ ሲሆን እስከ ሰኔ አስራ አምስት ባለው ጊዜ ውስጥ ይዘራል፡፡ ጤፍ ከሐምሌ አምስት ጀምሮ እስከ ሐምሌ አስራ አምስት ቀን በቆላ ሰም (በሞቃት)፣ ከሐምሌ አስራ አምስት እስከ ሐምሌ ሰላሳ ድረስ ያለው ደግሞ በደጋና በወይና ደጋ እንዲሁም በነሐሴ መጀመሪያ ሳምንት፣ በነሐሴ መጨረሻ እና በጳጉሜ በደጋው ጤፍ መዝሪያ ወቅት ነው፡፡ ይህ ጊዜ በግቢ የታረሰው መሬት በደንብ ለስልሶና ተጎልጉሎ ለጤፍ፣ ለዳጉሳና ለስንዴ ዘር የሚዘጋጅበት ጊዜ ነው፡፡

በመጋቢትና በግንቦት የታረሰው የጤፍ መሬት ከሰኔ ሃያ በኋላ መጎልጎልና ለጭቃ በራይ መዘጋጀት አለበት፡፡ መሬቱ ተደጋግሞ ይታረስና ይደቃል፡፡ በአካባቢው ሰርገኛ፣ ቀይ፣ ፊሶ[106] እና ቢመሾ[107] የሚባሉ የጤፍ አይነቶች ይዘራሉ፡፡ ሰርገኛ ጤፍ የነጭና የቀይ ጤፍ ድብልቅ ሲሆን ቀይ ጤፍ ደግሞ ስጋ የመሰለ መልክ ያለው በመሆኑ ቀይ ጤፍ ሲባል ፊሶ የሚባለው ጤፍ ጥቁር ጤፍ ሆኖ ብቻውን ለእንጀራነት የማይውል ነው፡፡ በተለይም ፊሶና ቢመሾ በደጋው አካባቢ ብቻ የሚበቅሉ የጤፍ አይነቶች ናቸው፡፡ ፊሶ በነሐሴ መጀመሪያ ተዘርቶ በህዳር የሚደርስ ሲሆን ቢመሾ ደግሞ በነሃሴ መጨረሻ የምትዘራና ከሌሎች እኩል በህዳር የምትደርስ ጤፍ ናት፡፡ ለጤፍ መዝሪያ የሚዘጋጀው መሬት በቅድሚያ መጎልጎል አለበት፡፡

በጉልጓሎ ወቅት የደቀቀውን እርሻ አራሹ በተወሰነ እርቀት ቦይ እየተቀደደ ይተዋል፣ ሴቶቹ፣ ወንዶቹ፣ ልጆቹ ለጉልጓሎ ወጥተው ሳሩን በሚገባ ከእርሻው መሃል አፈሩን

105 ግልሻሽ፡- የቅስቀሳ እርሻ
106 በጣም ጥቁር ጤፍ ነው
107 በነሃሴ መጨረሻ ተዘርታ በህዳር ለአጨዳ የምትደርስ ቀይ ጤፍ ናት

አያራገፉና እያወጡ በተቀደደው ቦይ መሀል ስሩን ወደላይ እየገለበጡ ያስቀምጣሉ፡፡ በዚህ መንገድ ጉልጓሎው ይከናወናል፡፡ ይህ ታርሶ የደቀቀው የጤፍ መሬት በሚገባ ተጎልጉሎ ከዘጠኝ እስከ አስራ አምስት ቀን አረሙ እንዲወጣ (እንዲበቅል) ይተዋል፤ ለጭቃ በራይና ለዘር ዝግጁ ሆኖ ዝናብ ይጠብቃል፡፡ ስራውን አስመልክቶ የጤፍ መሬት ጭቃ በራይ ሲያበራዩና ሲዘሩ ያገኘኋቸው አቶ ፈንቴ የሚከተለውን ይላሉ፡-

> የጤፍ እርሻ በደንብ ከደቀቀ በኋላ አፈሩ እየተራገፈ የሳሩ ስር ወደላይ ተገልብጦ በተቀደደው ፈሰስ ይቀመጣል፤ ይጎለጎላል፤ ከዘጠኝ እስከ አስራአምስት ቀን በኋላ አረሙ በደንብ ሲወጣ በርከት ያሉ ከብቶች በጤፉ እርሻ ላይ እየነዳን እንዲ ደቀድቁትና እንዲጠቀጥቁት እናደርጋለን፡፡ በከብት ጭቃ በራይ[108] እናበራያለን፡፡ ጭቃ በራዩን የምናከናውነው ደህና የተመቻቸ ካፊያ ስናገኝ ነው፡፡ ሀይለኛ ዝናብ ከሆነም ዘሩ ይቀልጥብናል፡፡ በከብት አበራይተን ስንጨርስ ወዲያውኑ በብተና እንዘራለን፡፡ ወዲያው ነው የምንዘራው፣ በብተና ስንዘራ ዘሩ እንዳይደራረብ አንድ ጊዜ የምንዘራባትን ቦታ በአይናችን መትረን ስናበቃ በእግራችን ምልክት እናወጣለን፤ እንደዚያ እያደረግን ተሐምሌ አምስት እስከ ሐምሌ እኩሌታ ጤፍን እንዘራለን፡፡[109]

ከዚህ ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው በጉልጓሎው ወቅት የሳሩ ስር ወደላይ የሚሆንበት ምክንያት አፈር አግኝቶ በድጋሚ እንዳይበቅል ለማድረግ፣ ስሩን ለጸሐይ ለማጋለጥና አፈርና ውኃ ለማሳጣት ነው፡፡ በከብት የሚደቀደቀው ዘሩ ድቃቅ ከመሆኑ የተነሳ ሲበቅል አፈሩን ፈንቅሎ የመውጣት አቅም ስለሌው ይበሰብሳል፡፡ ይህ እንዳይሆንም በሚገባ መሬቱ በከብት መደቅደቅና መተምተም አለበት፡፡ የዝናቡ መጠንም ወሳኝነት አለው፡፡ ሀይለኛ ዝናብ ከሆነ ጤፍ በጎርፍ ተጠራርጎ ይወሰዳል፤ወይም ይበሰብሳል፡፡

108 በተጎለጎለው የጤፍ እርሻ ላይ ብዙ ከብት እየነዱ ማስጠቅጠቅ
109 አቶ ፈንቴ ወርቁ፣ አግዛ ጋርዳ ኤሊያስ ቀበሌ፣ ሹምታ ደሽ፣ ቃለመጠየቅ፣ 24/11/2007

ዝናብ ስለጣለ ብቻ ዘር አይዘራም፡፡ ዝናብ በሌለበትም አይዘራም ስለዚህ ጭቃ በራይ የሚከናወነው ደህና ካፊያ ዝናብ ሲኖር ብቻ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ መሬቱ በሚገባ በከብት ተደቅድቆ ልትም ሲል የጤፍ ዘር ይዘራል፡፡ ዘር በብተና በሚዘራበት ወቅት በአንድ ቦታ ላይ ተደራርቦ እንዳይዘራ እና ዘር እንዳይባክን በአይን እየገመቱ በእግራቸው መስመር በማውጣት፣ ቅጠል ምልክት በማድረግ ይለዩታል፣ ያን ሲጨርሱ ደግሞ አሁንም መስመር ያወጣሉ፡፡ ይዘራሉ፡፡ ይህንን ለመከላከል ከላይ የተጠቀሱትን ዘዴዎች ይጠቀማል፡፡ ይህም ከልምድ ያገኘውና ያዳበረው እውቀት ነው፡፡ እንዲሁም እንደጤፉና አየር ንብረቱ የዘሩ ጊዜ የተለያየ በመሆኑ በደጋማው አካባቢ የሚበቅለው ቢመሾ ጤፍ ነሐሴ መጨረሻ ላይ ተዘርቶ ህዳር ላይ ይደርሳል፡፡ ይህም ሁሉም ጤፍ በሐምሌ ተዘርቶ ያልቃል ማለት አይደለም፡፡

የጤፍ መሬት በዚህ መንገድ ተዘጋጅቶ ነው የሚዘራው፣ በከብት በደንብ የሚጠቀጠቀው ከጉልጓሎ በኋላ የሚወጣው አረም እንዲጠፋ ለማድረግ እና የጤፉ ዘር ደቃቅ በመሆኑ ወደውስጥ እንዳይገባና ሳይበቅል እንዳይቀር ነው፡፡ እንዲሁም ዘሩም እንዳይደራረብ (በተዘራበት ቦታ ተደግሞ እንዳይዘራ) በእግራቸው መስመር (ምልክት) እያወጡ ይዘራሉ፡፡ ጤፉ ከተዘራ በኋላም ጎርፍ ጠራርጎ እንዳይወስደው ለማድረግ በእርሻው ውስጥ የጎርፍ መውረጃ ቦይ ይቀደዳል፡፡ በቦዩ መካከል የሚገኘውን አፈር ለማውጣትም አካፋን ወይም ሌላ መሳሪያን አይጠቀሙም፡፡ ባህላዊ በሆነ መንገድ በቀላል ዘዴ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን በማያባክን መልኩ ይጠቀማሉ፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ ፈንቴ ፡-

> የጎርፍ መውረጃ ፈሰስ ስንቀድ ሳብር[110] ነው የምናርሰው፣ አንድ ጊዜ ከተከፈተ በኋላ በሁለተኛው ስንሄድበት አፈሩንም ለማንሳት አካፋ አንጠቀምም፣ በድግሩና በእርፉ መካከል እርጥብ የስሚዛ[111] እንጨት ሰባብረን አስገብተን በቦዩ ስንሄድ እንጨቱ አፈሩን ግራና

[110] ሳብር፡- አግድመት
[111] ስሚዛ፡- ሰንሰል

ቀኝ እየጠረገ መሀሉን ክፍት ያደርገዋል፡፡ በቃ ፈሰሱ እንደዚህ ነው የሚሆነው በማለት ይገልጻሉ፡፡[112]

ከዚህ ገለጻ መረዳት የሚቻለው ገበሬው የባህላዊ ግብርና ዕውቀቱን ተጠቅሞ ጊዜውንና ጉልበቱን ሳያባክንና ተጨማሪ ሌላ መሳሪያም ሳያስፈልገው በቦዩ መካከል የሚገኘውን አፈር በበሬ እቃው፣ በእርፉና በድግሩ መካከል እርጥብ የስሚዛ እንጨቶችን በመሰካት የቦዩን አፈር እንዲያስተካክለውና መሃሉ ክፍት እንዲሆን በማድርግ በቀላል ዘዴ ይጠቀማል፡፡ እንዲሁም የጎርፍ መውረጃ ቦዮችን አግድመት በማረስ ያዘጋጃል፡፡



ፎቶ 18፡-የጤፍ እርሻ ሲጎለጎል፣ ሹምታ፣ 11/11/2007፡፡



ፎቶ 19፡-የጤፍ እርሻ ጭቃ በራይ ሲበራይና ለዘር ሲዘጋጅ፣ ሹምታ፣ 25/11/2007፡፡

112 አቶ ፈንቴ ወርቁ፣ አግዛ ጋርዳ ኤሊያስ ቀበሌ፣ ሹምታ ደሽ፣ ተደረገበት ቀን 25/11/2007፣

ፎቶ 21 :- የጤፍ ዘር ሲጠራ/ ሲበጠር 25/11/2007

ፎቶ 20:- የጤፍ ዘር በብተና ሲዘራ 25/11/2007

ስንዴ የሚበቅለው በአብዛኛው በቆላ ሰም (በሞቃት) አካባቢ ሲሆን አልፎ አልፎ በወይና ደጋው አካባቢ የሚበቅል ሲሆን ደጋማው የአየር ንብረት ባለበት አካባቢ ግን አይበቅልም፡፡ የመዘሪያ ጊዜውም ከሐምሌ አስራ አምስት ጀምሮ እስከ ሐምሌ ሰላሳ ድረስ ነው፡፡ የስንዴ ማሳ ዝግጅት እንደጤፍ በመሆኑ እርሻው በሚገባ ታርሶ ይለሰልሳል፡፡ ስለዚህም ቢያንስ ከአምስት እስከ ሰባት ጊዜ ይታረሳል፡፡ አቶ ጌትነት እንደሚሉት "ስንዴ ብዙ እርሻ የሚፈልግ ቢሆንም በጋ ላይ አይታረስም፤ ዝናብ ተጠብቆ ነው የሚታረሰው፡፡ ዝናብ ሲዘንብ ግንቦትን ሰኔን ይዘን እስከ ሐምሌ እኩሌታ እሰቲዘራ ድረስ ተደጋግሞ ይታረሳል፡፡ ልዩነቱ የጤፍ እርሻ ጭቃ በራይ ሲኖረው የስንዴ ግን አይበራይም፡፡"[113]

ባቄላ ሐምሌ መጀመሪያ ላይ ይዘራል፡፡ አተር የሚዘራው ደግሞ ሐምሌ መጨረሻ ላይ ነው፡፡ ቄስ ታየ እንደሚሉት "ወንድ አተርን[114] ቡክር /ቀደም ብለን/ እንዘራዋለን፤ ሴት

---

[113] አቶ ጌትነት አድማስ፣ አደጋ ጓሽታ ውባጅ ቀበሌ፣ ጓሽታ ደሽ፣ ቡድን አንድ ውይይት 21/07/2007)
[114] ባቄላ

አተሩ[115] ቶሎ ስለሚደርስ እንዲያ ወደ ሐምሌው መጨረሻ ዳ ብለን ነው የምንዘራው፡፡ ተልባ፣ ኑግ የመሳሰሉትም የሚዘሩት በዚሁ ጊዜ ነው፡፡ ይህ ወቅት ያለው ሁሉ እየተሟጠጠ የሚዘራበት ጊዜ ነው፡፡"[116]

ገበሬው ተፈጥሮ በለገሰችው ላይ የራሱን ጥረት በማከል አካባቢውን ለመቆጣጠር ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ ይስተዋላል፡፡ በአካባቢው በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቋቋም የሚያደርገው ጥረት ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ በዚህ በክረምት ወቅትም የሚያከናውናቸው ልማድና እምነቶች አሉ፡፡ ዋነኛውና የማይቀረው በጊዜውና በውቅቱ በየዓመቱ የሚከናወናው አንዱ "ጠለተ በረድ"[117] ማዞር ነው፡፡ ሌላው ደግሞ የከብቶችን በዓል ማክበር ነው፡፡ የገበሬው ስጋት የሆነውን በረድ ባህላዊ በሆነ መንገድ ለመከላከል ሲጠቀም ይስተዋላል፡፡ ቄስ ወርቁ ስለዚህ ሲናገሩ፡-

> በአካባቢያችን በረዶ በጣም ያስቸግረናል፤ ስለዚህ ድሮ እህል ነበር የምናዋጣው አሁን ግን ገንዘብ በጢስ እናዋጣና ለደብተራው እንሰጣለን፤ ደብተራውም ያን መድሃኒት ይሰጠናል፤ መድሃኒቱ የተክል ስር ነው፡፡ ደሞ መሬት ስለማይነካው ያን በቀበሌው ድንበር አዙረን በረጅምና ደረቅ የቅርቀሃ እንጨት ላይ አስረን ሜዳ ላይ ተክለን እንተወዋለን ይላሉ፡፡[118]

በአካባቢው በረዶ ብዙ ጊዜ እህል ስለሚያጠፋባቸው ገበሬዎች እያዋጡ ለባህላዊ መድሃኒት አዋቂዎች (ደብተራዎች) በየአመቱ ገንዘብ እየሰጡ የሚሰጣቸውን የባህል መድሃኒት በቀበሌው አካላይ ድንበር አዙረው አማካኝ በሆነ ሜዳማ ቦታ ላይ ይሰቅሉታል፡፡ መሬት ከነካውም ድግምቱ ይረክሳል ተብሎ ስለሚታመን መሬት

---

115 አተር

116 ቄስ ታዬ ታፈረ፣ አብስላ ዋርዳ ቀበሌ፣ ዋህሳ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ፣ 07/07/2007

117 ጠለተ በረድ፡- ሰብላቸውን በረዶ እንዳያጠፋባቸው ለማድረግ የሚከላከሉበት ባህላዊ በደብተራዎች የሚዘጋጅ ድግምት ነው፡፡ ይህ ግን አሁን ተለውጧል፡፡ ለውጥና ቀጣይነት በሚለው ምዕራፍ ስር ተጠቅሷል፡፡

118 ቄስ ወርቁ ወልደ ጊዮርጊስ፣ አግዛ ጋርዳ ኤሊያስ ቀበሌ፡ ስሚዞ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ፡ 29/07/2007

አይነካውም፡፡ የቅርከሃን ተክል የሚጠቀሙት ለረዥምነቱ ሲሆን እጹ ድግምት ተደርጎበት ነው የሚሰጣቸው፡፡ ሜዳ ላይ የሚሆንበት ምክንያት መብረቅ መድሃኒቱ ላይ ብቻ እንዲያርፍና ለማድረግ ነው፡፡ ሌላ እንዳያጠፋ፡፡ ያን በማድረጋቸው ከበረድ እንደሚድኑ፣ ባለማድረጋቸው ደግሞ በበረድ እንደሚሙቱ ያምናሉ፡፡ አካባቢው በበረድ ከተመታ የሆነ ነገር አድርገናል ብለው ያስባሉ፡፡ ለዚህም አጋላጭ ናቸው ብለው የሚያምኑባቸው የሞተን ሰው በእለቱ ያለመቅበር፣ በአላትን (በሰንበት ማረስ፣ መፍጨት፣ መቆፈር...) መሻር የተሰረቀ ታቦት የሆነ ቦታ ላይ ሲጣል፣ በሰው እጅ የጠፋ ሰው ሲኖር... በረድ ይመታናል ብለው ያምናሉ፡፡ ይህም የፈጣሪ ቁጣ ነው ይላሉ፡፡ በተለይም በአካባቢው ድንገተኛና ከወትሮው የበረታ በረዶ ከጣለ በረዶው ሲያባራ አካባቢያቸውን የማሰስ ተግባርን ያከናውናሉ፡፡ ይህን በተመለከተ ቄስ ታዬ እንዲህ በማለት ይገልጹታል፡-

> “በረዶው አካባቢውን ደጋግሞ የሚመታው ከሆነ በአካባቢያችን የተጣላ ሰው ታለ ይቅር ለግዜር እንዲባባል፣ እንዲታረቅ፣ የተበደለም ሰው ካለ እንዲካስ ተደርጎ በቤተክርስቲያናችን ጾም፣ ጸሎት ወይ ለሶስት፣ ወይ ለሰባት ቀን ይታወጃል፡፡ ሁሉም ይጾማል እግዞታ ይደረጋል፡፡ በዚህ ፈጣሪ ይቅር ይለናል፡፡ ይህን የምናደርገው ለበረዶ ብቻ አይደለም፡፡ ዝናብም ሲጠፋ እንደህ እናደርጋለን፡፡[119]”

እንደ ቄስ ታዬ ገለጻ ጥናቱ የሚካሄድባቸው ማህበረሰቦች የክርስትና እምነት ተከታዮች በመሆናቸው በተደጋጋሚ በረዶ ሲመታቸው ወይም ዝናብ ሲጠፋ ጾም፣ ጸሎትና ምህላ ለሃጢያት ማስተሰሪያ ያደርጋሉ፡፡ በሰሩት ክፋት/ ሃጢያት ምክንያት መጠነኛ ቅጣት ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ይህ ሲሆንም ሊያስተምረን ነው ብለው የሚያምኑት አንድ ኃይል/ ልዕለሰብ አለ፡፡

---

[119] ቄስ ታዬ ታፈረ፣ አብስላ ዋርዳ ቀበሌ፣ ዋሀሳ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ፣ 07/07/2007

የክረምት ወቅት በገበሬው ዘንድ የችግር ጊዜ ነው፡፡ ይህ ችግርም አጠቃላይ በመሆኑ በማህበራዊውም ሆነ በኢኮኖሚውም የሚያስከትለው ጫና ቀላል አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት ማህበረሰቡ ከወዲሁ የሥነልቦና፣ ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርግ፣ ለዘር የሚሆነውንም እህል ከመብላት እንዲቆጠብና የዘሩን እህል እንዲያዘጋጅ የሚጠቁም ነው፡፡

በሚያዚያ በጓሮ መሬት ላይ የተበተነው የጎመን ዘር ከሰኔ ጀምሮ ለመብል የሚደርስበት ወቅት በመሆኑ በአብዛኛው ገበሬ ቤት የሚበላው ጎመን ነው፡፡ በመጋቢትና በሚያዚያ የተዘራው ድንችም ሰኔ መጨረሻ ጀምሮ ለመብል የሚደርስ ቢሆንም እንደጎመን አይበላም፡፡

በጓሯቸው የዘሩትን ጎመን ሲያርሙ ያገኘኋቸው አቶ ይሁን እንደሚሉት "ክረምቱ ይዞት ከሚመጣው ዝናብና ስራ ጋር ተያይዞ በቤት ሁሉም ነገር ያጥራል፤ ያለው ተሟጦ የሚዘራበት ወቅት ነው፡፡ ስለዚህ ቀለባችን ጎመን ነው፡፡ 'ምን ቢያርሱ እንደጎመን አይጎርሱ' ነው፡፡"[120]

"እንግዲህ ጀመረ ሰኔ አቀለቀለ

በኩርማን እንጀራ ጎመን ተቀለለ" እያለ ይዘፍናል (እንደ ላይኛው)፡፡

ይህ ቃላዊ ግጥም የተነገረበት አውድ በግቢው መጨረሻ እና በክረምቱ መግቢያ ወቅት ላይ እንደሆነ ከግጥሙ መንፈስ መረዳት ይቻላል፡፡ በክረምት ወራት ቀድሞ የሚደርሰው ጎመን በመሆኑ በገበሬው ቤት ለምግብነት የሚውለው ጎመን ነው፡፡

በዚህ ወቅት በጎመኑም፣ በገብሱም፣ በማሽላውም ይዘፈናል፤ ከክረምቱ ችግር ጋር ተያይዞ፡፡ አዳንድ ቀጣቢም ይኖራል፡፡ ለዚህም በአካባቢው "የክረምት መሻገሪያህን በጋ ላይ ተመልከት" የሚል ብሂል አለ፡፡ ገበሬው ቀድሞ የሚዘራው ለችግር ደራሽ የሆነውን

[120] አቶ ይሁን አድማስ፣ አግዛ ጋርዳ ኤሊያስ ቀበሌ፣ ሹምታ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ፣ 04/09/2006

ኅመን ነው፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚሉት የክረምቱ የችግር፣ የስራ ጫና ጊዜ በመሆኑ በአጠቃላይ በጣም ከባድ ነው፡፡[121]

አቶ አየለ የችግሩን ሁኔታ ሲገልጹ "ተስራ ጫናው በቤት ውስጥ የባልና የሚስት ሁኔታም እንዳይኖር ያደርጋል ተችግሩ አኳያ ተወደደም ተጠላም መብል ነው የሰውን ልጅ የሚያፋቅረው፣ 'ሆድን በኅመን ቢደልሉት ጉልበት በዳገት ይለግማል' ይባላል በማለት ነው፡፡"[122]

በዚህ ወቅት የሚከናወነው ሌላው የከብቶች ጭፊ[123]ነው፡፡ በአዊ ብሄረሰቡ ዘንድ ጭፊ ማድረግ የተለመደ ነው፡፡ ጭፊው ለሰው ሲሆን በግል ለከብት ሲሆን ደግሞ በጋራ ይከናወናል፡፡ በአካባቢው ለእንስሳት በዓመት ሁለት ጊዜ በሐምሌና በህዳር ጭፊ ይከናወናል፡፡ በሐምሌ የሚከናወነው በአጠቃላይ ለከብቶች ሲሆን ከብት ያለው ሰው በሙሉ እንደየአቅሙ ገንዘብ በማዋጣት በግ ይገዛል፡፡ እንደ ገንዘቡ የመግዛት አቅም በጉን በመያዝ ከስምንት ሰዓት በኋላም ከብቱ ወደሚሰማራበት መስክ በመሄድ ይታረዳል፡፡ ከዚያም በእርጥብ ቅጠል የበጉ ደም እየተነከረ ለከብቱ ይረጫል፡፡ ስጋውም ተጠባብሶ በቦታው ለተገኘው ሰው ይቃመሳል፡፡ ይህም የሚደረገው አንድም ከብቶችን ከተለያዩ በሽታዎች ለመከላከል፣ አንድም የከብት በዓል ለሆነው አቡነ ኪሮስ[124] መስእዋት ለማቅረብ ነው፡፡ ለዚህም ስጋው ወደ ቤትም አይሔድም፣ ቢተርፍ እንኳን እዚያው ሜዳ ላይ ነው የሚቀረው፡፡ የዚህ ምክንያቱ መስዋዕት የሆነ ነገር ወደቤት ስለማይገባ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከብቶች ላይ ያድራል ተብሎ የሚታሰበው በሽታ ወደቤት እንዳይገባ ለማድረግ ነው፡፡

የክረምቱ ችግር በኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን በማህበራዊ ሕይወት በኩልም የሚያስከትለው ጫና ቀላል አይደለም፡፡ ማህበረሰቡ የፎክሎር ዘርፎች የሆኑትን ቃላዊ ግጥሞችን

---

[121] አቶ ይሁን አድማስ፣ አግዛ ጋርዳ ኤሊያስ ቀበሌ፣ ሹምታ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ፣ 04/09/2006

[122] አቶ አየለ አንተነህ፣ አደጋ ጓሽታ ውባጅ ቀበሌ፣ ሰባት አይና ደሽ፣ ቃለመጠይቅ፣ 22/06/07

[123] ጭፊ፡- ለአምልኮ የሚደረግ የበግ እርድ

[124] ሐምሌ 13 ቀን የሚከበር የከብት በዓል ሲሆን አቡነ ኪሮስ ከብት ጠባቂ ናቸው ተብሎ በማህበረሰቡ ዘንድ ይታመናል፡፡

በመጠቀም ችግሩን፣ ብሶቱን፣ መጎዳቱን፣ መደሰቱን ማግኘቱን ማጣቱን ሁሉ ይገልጽበታል፡፡ አቶ አየለ ስለዚህ ሁኔታ ሲገልጹ፡-

"እስኪ በሶ ብላ እስኪ ገንፎ ብላ
ይሻለው እንደሆን ገመምተኛው "ገላ"[125]፡፡

የተነገረበት ሁኔታ የሰመሬታ ገብስ እየፈጨች ነው፡፡ ሰመሬታ ገብስ ደግሞ የሚደርሰው በነሐሴ ውስጥ ነው፡፡ ይህን መልእክት የምታስተላልፈው ለባሏ ነው፡፡ የክምረቱ ችግር የሆድን መራብ ብቻ ሳይሆን የስሜት መራብንም በማስከተል ሥነልቦናዊ ጫናን ይፈጥራል፡፡ በባህሉ ስሜትን አውጥቶ በቀጥታ መናገር ነውር ነው፡፡ ይህንን ችግርም ለመግለጽ የተጠቀመችበት ቃላዊ ግጥምን ነው፡፡ በባልዋ የደረሰባትን በደል ሳትፈራ በቀጥታ ሳይሆን በዘፈንና በእንጉርጉሮ ወፍጮ ስር ሆና የተናገረችው፡፡ ለምናልባትም ከጎመኑ በዚያ ወቅት የሚሻለው ምግብ በሶና ገንፎ በመሆኑ ባሏ ይህንን ገንፎና በሶ ቢበላ ከድካሙ አገግሞ ስሜቱ እሷን እሷን ያሰኘው ይሆናል ብላ በማሰብ በምግብ ልትጠግነው አሰባና ደካማነቱንም ለመግለጽ ባሏን በግጥም ትናገረዋለች፡፡

ባል የተነገረው ነገር በቀጥታ ለእሱ መሆኑን ሲረዳ፣ እሱም በነገር እንደሸነቆጠችውና ደካማ ጎኑን እንደነካችበት ስለሚገባው የመልስ ምቱን ወንድነቱ አስገድዶት ዱላ በመምዘዝ ሳይሆን የሚወጣው እንደሷው በነገር አለንጋ በመግረፍ በመሆኑ በግጥም መልስ ይሰጣል፡፡

"በሶውን ብበላ ገንፎውን ብበላ
ክፍቱን የከረመው መች ይሆናል ጤና" በማለት ይመልሳል፡፡[126]

ባል ይህን ሲል ጾታዊ ግንኙነት ሳታደርግ ብዙ ጊዜ በመቆየቷ ስሜቷን ለማርካት የሚጠይቀውን ጉልበትና ሀይል በዚህ በአጭር ጊዜ ማግኘት እንደማይችል ይነግራታል፣

[125] የወንድ የመራቢያ ክፍል፡፡
[126] አቶ አየለ አንተነህ፣ አደጋ ጓሽታ ውባጅ ቀበሌ፣ ሰባት አይና ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 22/06/07

ይህን ሲላት እሷ ግን ማታ ላይ በምድጃ ዙሪያ ተቀምጠው ስለሚያመሹ ተሰብስባና ገመናዋን ሸፍና አለመቀመጧን የነገራት መስሏት ብድሯን በሌላ ግጥም ስትመልስ ይስተዋላል፡፡ ምክንያቱም የቃል ግጥሞች ትርጉም እንደያንዳንዱ የምናብ፣ የጊዜና የሁነት ሁኔታ መሰረት የሚያደርግ በመሆኑ እሷ በተረዳችበት ሁኔታ እንዲህ በማለት ምላሹን ትሰጣለች፡-

"ይከፈት ይከደን የታባህ አየኸው
በጎመኑ ቶፋ አይንህን ተክለኸው"፡፡ (እንደ ላይኛው)

ይህም የክረምቱ ወቅት ቀለብ ጎመን በመሆኑ ትኩስ ይሁን እየተባለ የሚቀቀለው ማታ ላይ በመሆኑ የደከመው አባወራ በጊዜ ጎኑን ተምኝታው ለማሳረፍ ስለሚቸኩል ከምድጃው ዳር ተቀምጦ በሰለ አልበሰለ በማለት ሲጠባበቅ ያመሻል፣ ስለዚህ እሷም ለመሆኑ ሌላ ነገር የምትመለከትበት ምን አይን አለህ ሁሉም ነገርህ ምግቡ ላይ ነው በማለት ትናገረዋለች፡፡ እሱም፡-

"የተውሁትን ነገር አንቺ ታመጣሽው
ቀርድደሽ[127] ሳትጨርሽ ሁለት ጊዜ ቃምሽው፡፡ (እንደ ላይኛው)

እሱም የክረምቱ ወቅት ጎተራ ተሟጦ የሚዘራበት ወቅት ቢሆንም ከውጭ ያለው እስኪገባ ድረስ ያለችዋም ቢሆን ጨርሳ እንዳትጠፋ ለማድረግ ለምግብነት የሚጠቀመው ጎመንን ነው፡፡ ጎመን ደግሞ አንድ ጊዜ ተከትፎ አይጨመርም፤ እየተከተፈ የፊት የፊቱ ነው ወደ ቶፋው የሚጨመረው፣ መጀመሪያ የተደረገው ገርገብ ሲል የሚቀጥለው ይጨመራል፤ ምክንያቱም የሚቀቀለው ጎመን ብዙ ስለሆነ አንድ ጊዜ ቢጨመር ስለማይችለው ሲጎድል ሲጎድል ነው የሚጨመረው፡፡ ታዲያ የራብ ማስታገሻ ገርገብ ካለው ጎመን ይቀምሳሉ፡፡ ያንን የተመለከተው አባወራ ደግሞ ይህንን ጎመኑ ተከትፎ ሳያልቅ አንቺው ቀድመሽ በቅምሻ ጨረስሽው ይላታል፡፡ በዚህ መንገድ

[127] መቀርደድ፡- ለጎመን ብቻ ሲሆን በማጭድ ጎምን መክተፍ ማለት ነው፡፡

ቅሬታን በማያጭር መልኩ የልብ የልባቸውን፣ የስሜታቸውን ይጨዋወታሉ፤ የልባቸውን ይተነፍሳሉ፡፡

በዚህ ግዜ በሰዎቹ ብቻ ሳይሆኑ በቅደም ተከተል ፊትና ኋላ እየሆኑ የሚደርሱት የምግብ አይነቶቹም እንዲሁ በሰውኛ ዘይቤ ይገጠምላቸዋል፡፡ ቀድሞ ለነፍስ የደረሰው ጎመን በገብስ ዘፈነም ይባላል፡፡

"ጎመን ባወጣው ነፍስ
እሪጥ አለች ገብስ"፤
ደጃች ሰመሬታ ተው አንጠል[128] አትናገር
አንገቴን ታርጄ ባቆየሁት አገር፡፡[129]

የሰመሬታ ገብስ በነሃሴ ሲደርስ ቶሎ ታጭዶና ተበራይቶ (ተወቅቶ) ለምግብነት እንዲውል ይደረጋል፤ ገብሱ እንጀራም፣ በሶም፣ ገንፎም፣ ቆሎም እየሆነ ለምግብነት ይዘጋጃል፡፡ በዚህም ጊዜ ገብስ ተወዳጅ ስለሚሆን የጎመን ነገር ቀነስ እያለ ይሄዳል፤ እሱም ቢሆን ያብብና ማዘርዘር ይጀምራል፤ እንደበፊቱ እየተቀነጠሰ ሳይሆን እንዳንዱ ቅጠል እየተለቀመች ለምግብነት ትውላለች፤ ነገር ግን አቅርቦቷም ይቀንሳል፤ በዚህም ጊዜ ገብስ ብልጫውን ስለሚወስድ ነው እንደዚህ የተገጠመው፡፡ ሁሉም ተራውን ጠብቆ ፊትና ኋላ መሆኑ ስለማይቀር ገብስም ቦታውን ለማሽላ ይለቃል፡፡ ቶሎ የሚደርሰው የማሽላ ዘር "ፈጠኜ" ሲደርስም እንዲህ ተብሎ ይዘፍናል፡-

"ፈታውራሪ ጎመን ደጃች ሰመሬታ
ማሽላ ደረሰ ባለዘጠኝ ኩታ" (እንደላይኛው)፡፡

[128] "አንጠል" ግፍ አትናገር ነገም ያንተ ተራ ይደርሳል፤ በኛ ደረሰው ባንተም ስለሚደርስ አትኩራራ ለማለት ነው

[129] ወ/ሮ ገነቴ ደምለው፣ ቲሊሊ፣ ከመስክ መልስ ስለውሎዬ ስንጋገር የነገሩኝ

እህሎች እንደጠቀሜታቸው ማለትም እንደ ነፍስ አድንነታቸው ደረጃ አላቸው፡፡ ቀድሞ ለችግር ጊዜ የሚደርሰው ጎመን በመሆኑ የፊታውራሪነት ማእረግ፣ ሰመሬታ ገብስ የደጃዝማችነት ማእረግ፣ ቢሰጣቸውም ፈጠኔ ማሽላ ነሐሴ ላይ በመድረሱ ምክንያት እንደ በፊቱ ሊሆኑ እንደማይችሉ በግጥም ይነገራል፡፡ ይሁን እንጂ ዋናው መልእክት ቢያንስ ቢያንስ አሁን ማሽላ ስለደረሰ በመጠኑም ቢሆን ለውጥ እናገኛለን ነው፡፡ ምክንያቱም ብቻውን እንጀራ ይሆን የነበረው ገብስ ከማሽላ ጋር ሆኖ እንጀራ ይሆናል፣ እንዲሁም እሸቱ ማሽላ እየተጠበሰም፣ እየተቀቀለም፣ ተፈልሎ እየተቆላም ለምግብነት ይውላል፡፡ ስለዚህ አሁን ትንሽም ቢሆን ለውጥ አግኝተናል በማለት እራሳቸውን ያጽናናሉ ከራሳቸውም ያመልጣሉ፡፡ ከራስ፤ ከአካባቢ፣ ከባህል… ማምለጥ የፎክሎር አንዱ ባህሪው ነው (ፈቃደ፣ 1990)፡፡

ይህ ሁሉ የሚሆነው ጥቢው እስኪደርስ ነው፡፡ በሰልጣን ደረጃም ቢሆን ተዋረዱ ከላይ ወደታች ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተሻለ ከመጣ ወይም የነበረው በሌላ ከተተካ ያ ይወደድና ይከበር የነበረው እንደ ተራ ነገር መታየት ይጀምራል፡፡ ልክ እንደጎመኑ፤ “ሁሉም የሚያምረው በጊዜው ነው” “ጎመን ባፍላው እጅ ይጠብሳል” አይነት ነው፡፡

## 5.4. ጥቢ (ከመስከረም እስከ ህዳር)

ከመስከረም እስከ ህዳር ድረስ ያለው ጊዜ ጥቢ በመባል የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ ወቅት ለገበሬው ሁለት ተቃራኒ ስሜቶችን የሚያስተናግድበት ነው፡፡ እነዚህም የመልካም ብስራትና የጭንቅ ጊዜ ናቸው፡፡ “መስከረም ጠባ” ይባላል፡፡ ይህ ጊዜ የንጋት፣ ተስፋ ጊዜ ነው፡፡ ይህንን ጊዜ ንጋት ላይ ፀሐይ ልትወጣ ስትል ሰማዩ ላይ በሚታየው ብርቱካናማ ቀለም ይመስሉታል፡፡

በክረምቱ ወራት ከብቱንና ቤተሰቡን ደራሽ ውኃ እንዳይበላባት፣ ከብቶቹን ዋኘርማ/ጉድይ[130]እንዳይገድልበት፣ ሰብሉን በረዶ እንዳይመታበት… ሲጨነቅ የከረመው ገበሬ መስከረም ሲጠባ በሰላም መድረሱን ምስጋና ለፈጣሪው የሚያቀርብበት ነው፡፡ ለዚህም

[130] የከብቶችን ሆድ በመንፋት የሚገድል ተክል

"መስከረም ሲጠባ አደይ ሲፈነዳ እንኳን ሰው ዘመዱን ይጠይቃል ባዳ፡፡" በማለት ያዜማሉ፡፡ ክረምቱን እንደ ጨለማ ጊዜ በመቁጠርም ያ የጭንቅ፣ የዝናብና የጨለማ ወራት አለፈ በማለት ወቅቱን ጥቢ ይሉታል፡፡ ለዚህም "የዘንድሮን ክረምት ወጣናት በመላ በኩርማን እንጀራ ጎመን ተቀልላ" በማለትም የክረምቱን በሰላም ማለፍ ብሰራታቸውን ይገልጻሉ፡፡

የጭንቅ ጊዜው ደግሞ አሽቶ፣ አብቦና ጎምርቶ የሚያየው ሰብሉ በሰላም ለፍሬ ደርሶ ወደቤት ይገባ ይሆን? የሚል ስጋት ነው፡፡ ገበሬውን ለስጋት የሚጥሉት ነገሮች በተፈጥሮ ያለወቅቱ የሚጥለው ዝናብ አስከትሎት ሊመጣ የሚችለው በረዶ እንዲሁም ውርጭ ከባድ ስጋቶች ናቸው፤ አባቶች የህዳር በረዶን አስከፊነት ለማሳየት "ከህዳር በረዶ ከልጅ አጋሚዶ[131] ያድናችሁ" በማለት ሲመርቁ ይሰማል፡፡ የህዳር በረዶ የዘረዘረውን፣ ለፍሬ የደረሰውን እህል እንዳልሆነ የሚያደርግ የገበሬ ስጋት ነው፡፡ የልጅ ሌባም ውስጥ አዋቂ በመሆኑ ድርጊቱ አደገኛ ነው፡፡

ሌላው ስጋት ከራስ ቸልተኝነት የሚከሰት ሲሆን የአዝመራ በወፍ፣ በእንስሳትና በአውሬ መበላት... ናቸው፡፡ አዝመራን በወፍና በአውሬ (ጦጣ፣ አሳማ፣ ጃርት[132]...) ከመበላት ለመጠበቅ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡ ይህን አስመልክቶ ቄስ አወቀ ሲናገሩ፡-

> በገመድ እየፈተልን ብር አንጉድ[133] እንሰራና ተማሳው ውስጥ አልጋ ሰርተን ድንጋይ ለቅመን አሱን ይዘን አልጋችን ላይ ሁነን በብር አንጉድ እየተጋገዝን ወፍ ስንጠብቅ እንውላለን፡፡ ወፍ ቢመጣም ባይመጣም ድንጋይ በብር አንጉድ አድርገን መወርወራችን አይቀርም፤ ድንጋዩ ሲሄድ የሚያሰማው ድምጽ ለጉድ ነው፡፡ ዥውውውው... ሲል የዛፉን ቅጠል ሁሉ ያንቃንቀዋል፤ ሳናያት የተቀመጠጭ ወፍ ካለችም ያኔ ድራሿ

[131] ወንበዴ፣ ሌባ
[132] እሾኻማ አካል ያላት የዱር እንስሳ
[133] በገመድ ተፈትሎ መሃሉ ላይ የድንጋይ ማስቀመጫ ያለው የወፍ ማባረሪያ (ወንጭፍ/ ወፍ ከልካይ)

ይጠፋል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ አዝመራን አሳማ እንዳይበላው መከላከል ነው፤ ሌሊት ደግሞ ዣርት የምትባል አለች፤ እሷ እንዳትበላ ደግሞ የሆነ ሸቆ[134] የሚባል አለ እንጨት እንተክልና እሱን አስረን ስንተወው ትንሽ ንፋስ ሲነካው ኳኳኳኳ… ስለሚል ሰው መጣ ብላ ትታ ትሄዳለች፡፡[135]

ጠንቃቃ ገበሬ ሰብሉን ባህላዊ በሆነ መንገድ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ከእንስሳትና ከአዋፋት ይጠብቃል፡፡ በእኔ የጥናት አካባቢ የቅርከሃ ተክል በብዛት ስለሚበቅል የሱን ሁለት፣ ሶስት ልፋፊ ረዘም ባለ እንጨት ላይ አስረው በተወሰነ እርቀት በማሳው ውስጥ ይተክላሉ፡፡ ይህም ንፋስ ሲነካው በሚያሰማው ድምጽና እንዲሁም አምሳያ በመስራትና በመትከል ይከላከላሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉት ወፎችን ለማባረር የሚወረወረው ድንጋይ እህሉን እንዳያረግፈው፣ እንዲሁም ወፎችንም ሆነ እንስሳትን ለማባረር የሚገባው ሰው ሰብሉን እንዳይረጋግጠው ለማድረግ ነው፡፡ ሌላው በማሳው ውስጥ ማማ በመስራት በብር አንጉድ ድንጋይ በመወርወር፣ ከከብቶች ለመከላከል ደግሞ በማሳው ዙሪያ እሾኻማ ተክሎችን በማጠር ይጠብቃሉ፡፡ የሰብል ጥበቃን ቄስ አወቀ እንደሚከተለው ገልጸውታል፡-"'እህልን በጥቅምት ልጅን በጡት' እንደሚባለው ሰብል ፍሬ እንዲሰጥ ተተፈለገ መጠበቅ ያለበት በእሸቱ ወቅት ነው፡፡ ታለዚያማ በእሸትነቱ ወቅት ወፌት ትጠጣውና ግንዱ ብቻ ይቀራል፡፡ ልጅም በልጅነቱ ባህሉን፣ ደንቡን፣ ወጉን፣ ካልተማረና ካለወቀ ዝምብሎ ቁመና ብቻ ነው የሚሆነው፡፡ ለራሱም ሳገርም አይጠቅምም፡፡ ጠንካራ ገበሬ እንዲህም ይባላል፡፡"[136]

ሀ. "በልቼ ላልበላ ጎኔ ላይንሳ
ልጄን አሳለፍኳት በ እገሌ ማሳ፡፡"
ለ. እንደ እገሌ ቢሆን እነደ መውደርደሩ
እንኳንስ ተህሉ አናድርም ተዱሩ፡፡

[134] የቀርከሃ ተክል የደረቀ ልፋፊ.
[135] ቄስ አወቀ ተፈራ፣ አብስላ ሳሙኤል ቀበሌ ሳሙኤል ደሽ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ 02/07/2007፡፡
[136] ቄስ አወቀ ተፈራ፣ አብስላ ሳሙኤል ቀበሌ ሳሙኤል ደሽ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ 02/07/2007፡፡

ሐ. ያ አያ የከሌ ቢያውጨፈጭፍብኝ
እኔስ ብዬ ነበር ልጆቼን ፈጀብኝ፡፡(እንደ ላይኛው)

እንደ ቄስ አውቀ ገለጻ ጠንቃቃ ገበሬዎች ሰብላቸውን ተግተው ነው የሚጠብቁት፡፡ ወጥመድ በማጥመድ ሁሉ ይጠብቃሉ፡፡ ከላይ ያለው ግጥም የሚያመለክተው በጠንቃቃው ገበሬ ማሳ የገባች ጦጣ እሷም ሳትበላ ልጇ በወጥመድ ተይዛባት እንደቀረችና እሷም ምንም እንዳልበላች ለማመላከት የተገጠመ ነው፡፡ ቀጣዩም ስንኝ በጠንካራ ገበሬ በዚህ ጊዜ ነው ሰብሉ በንቃት ከአእዋፋት፣ ከእንስሳት፣ ከአውሬ… የሚጠበቀው፡፡ ይህ ካልሆነ ለፍሬ ደርሶ ሊሰበሰብ አይችልም፤ ልጅም በህጻንነቱ በስነምግባር ካልታነጸ ውስጡ ባዶ ነው የሚሆነው ተመለስ ቢሉት ፈጽሞ መመለስ አይቻልም፤ ለዚህም ነው እህልንና ልጅን በማመሳሰል የሚናገሩት፡፡ እህልና ልጅ በጭርቃነታቸው ነው መጠበቅ ያለባቸው፡፡ በጥቅምትና በህዳር አዝመራን ለመጠበቅ የራስን ብልሃት፣ ዕውቀትና ዘዴ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

ሰብሉን በንቃት የማይጠብቅ ሰነፍ ገበሬም ካለ በጦጣ ወይም በሌሎች ሰብልን በሚያጠቁ እንስሳት እያስመሰሉ ይተቿቸዋል፡፡ ይህን አስመልክቶ ወ/ሮ ገነቴ፡-

አያ የከሌ[137] ምላሰ ለስላሳ
አይናገረኝም ተዝንቦ ብፈሳ፡፡
እገሌ ሲሎህ እገሌ ሲያቅራራ
ጠግቤ ወጣሁኝ ከልጆቼ ጋራ፡፡[138]

አዝመራውን በአግባቡ የማይጠብቅና ቀስ ብሎ የሚሄድ፣ ፍጥነት የሌለውና ግዴለሽ የሆነን ሰው ልክ ጦጣ እንደዘፈነበት በማስመሰል በአካባቢው ገበሬዎች ይዘፈንበታል፡፡ በተከታታይ የቀረቡት ሁለቱ ስንኞችም ተመሳሳይ ሃሳብን የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡ አቶ

---

[137] በጥናታዊ ጽሁፉ ውስጥ ስማቸውን እንዳላስገባ ስለተጠየቅሁ ስማቸውን በሙተው ይህን ሃረግ ለመጠቀም ተገድጃለሁ፡፡

[138] ወ/ሮ ገነቴ ደምለው፣ ቲሊሊ፣ 15/9/2006

ሞላ ስለራሳቸው እንዲህ በማለት ነበር የገለጹት፡- "እኔ በወጣትነቴ ዘመን ግዴለሽ ነበርሁ እና አንድ ቀን ጥጓት አዝመራዬ ላይ ጦጣ ሰፍሮበት ነበር፡፡ ተዲያ ያንን ጦጣ አንዱን ሳባርር ሌላይቱ ትገባለች፡፡ አልቻልሁም፡፡ ተዚያ ሰዎች መጡና ተባብረን አስወጣናቸው፡፡ ወዲያው እንዲህ ተብሎ ተዘፈነብኝ ፡-

ያ ሞላ እንዳላማው የአድዮ ዘለሳ

ጠግቤ እነሳለሁ እግሩን እስኪያነሳ፡፡"[139]

የመጀመሪያው ስንኝ ሀሳብ የአደይ አበባ ተክል ሲደርቅ ግንዱ ለአጥር መከለያ ይሆናል፡፡ ዘለሳ ማለት አጥር ማለት ነው፡፡ ምናልባት ነፋስን ሊከልል ይችል እንደሆነ እንጂ ምንም ነገርን አያስቀርም፣ አቅም (ጥንካሬ) የለውም፡፡ ለዚህም ነው ጠግቤ እነሳለሁ እግሩን እስኪያነሳ የሚሉት፤ እሱ ፈጥኖ ደርሶ አያባርር፣ አቅምም ሆነ ጉልበት የለውም ልፍስፍስ ነው፡፡ ስለዚህ ሰብሉ የጦጣ መፈንጫ ነው ይሉታል፡፡ ይህም ለተገጠመበት ሰው ትልቅ መልዕክት አለው፡፡

ከዚያ በኋላ ሰብሌ ላይ እንኳን ጦጣ ልትገባ ወፍም አታርፍበትም፡፡ ጠንቃቃ ገበሬ ሆንሁኝ ደሞ በዚህ ሌላ ተዘፈነ፡፡

ያ ሞላ እንዳላማው ቢያወጨፈጭፍብኝ

እኔስ ብዬ ነበር ልጆቼን ፈጀብኝ (እንደ ላይኛው)፡፡

አለች ጦጣዋ ተባለና ተዘፈነብኝ" ይላሉ፡፡ እኔም መመለስ ነበረብኝና "እንዲህ አልኳቸው" አሉ፡፡

"ትገብር ካላችሁ ጦጣዋም ትገብር

የንጉስ አይደለም ወይ የምትጭረው ምድር" (እንደ ላይኛው)፡፡

---

[139] አቶ ሞላ እንዳላማው፡ አደጋ ውባጅ ቀበሌ፤ በቡድን ውይይት በ24/06/2007

በዚህም ከስህተታቸው ተምረው ለቀጣይ ጥሩ እንዲሆኑ ያስተምራቸዋል፤ በተለይም የሚዘፈንባቸው በጓደኞቻቸውና በእረኞቹ በመሆኑ በየሜዳው ይዘፈንባቸዋል፤ በዚህ ምክንያት ያንን ጥፋት ላለመድገም ይረዳቸዋል፤ ያስተምራቸዋል፡፡

የክረምቱ የችግር ጊዜ አልፎ ጥቅምት በቆላ ሰም አካባቢ ህዳር ደግሞ በደጋው አካባቢ የእሸት ወቅት በመሆኑ ያ የክረምቱ ጊዜ አልፎ መስከረም፣ ጥቅምትና ህዳር ልጆችና እረኞች በሜዳ ጠግበው የሚገቡበት ጊዜ ነው፡፡ አቶ ሀብታሙ የሚከተለውን ብለዋል፡-

> እየው እንግዲህ እኛ ልጆች ሆነን በጥቅምት የሴት አተሩ፣ የወንድ አተሩ፣ የስንዴው እሸት በጊዜ በጊዜው ሲደርስ ተዚያው ተመስኩ እሳት እናነድና ከየማሳው የሰበሰብነውን እንኩቶ እያነኮትን ስንበላ እንውላለን፡፡ ማታ ወደ ጎጆችን ስንገባ ማንም ሌላ እህል መብላት አያስብም፡፡ እህል ብሉ ብሎም የሚጠይቅም የለም፡፡ ያንዜ መስክ ውሎ የገባ ልጅ ይርበዋል ብሎ የሚያስብ ማንም የለም፡፡ ለዚህ ነው 'የጥቅምትን ርሃብ የሃምሌን ውኃ ጥም እናት አታውቀውም' የሚባለው፡፡[140]

አልፎ የሚሄድ ማንኛውም መንገደኛ ሰው እሸትን ቆርጦ ቢበላ ከልካይ የለበትም፡፡ ለሌላውም እሸት ቅመሱ ተብሎ ይሰጣል፡፡ ከብት እንጂ ሰው አይከለከልም፤ ማጥፋት እንጂ መብላት አይከለከልም፡፡

በአጠቃላይ ከመስከረም እስከ ህዳር ድረስ ያለው ጊዜ የሰብል መንከባከቢያ ይሁን እንጂ በህዳር የመስኖ ገብስ፣ ፊሶ ጤፍ ይታጨዳል፤ እርሻ የሚጀምረው በጥቅምት ወራት ነው፡፡ ቧች[141] መሬትና የገብስ ማሳ የነበረው መሬት ይገመሳል/ ይሰነጠቃል፤ ይታረሳል፡፡

---

[140] ሀብታሙ ጌታነህ፣ አደጋ ጓሽታ ውባጅ ቀበሌ፣ መሀል አምባ ደሽ፡ቃለ-መጠይቅ፣29/06/2007፡፡
[141] "ቧች" እዳሬ መሬት፣ ሳይታረስ እንዲሁ የከረመ መሬት

## 5.5. መኸር (ከህዳር እስከ የካቲት)

ይህ ወቅት ለገበሬው የልፋቱን ዋጋ የሚያገኝበት፣ ፍሬውን የሚሰበስብበትና የሚያስገባበት ወቅት ነው፡፡ ለዚህም ነው "መኸር" በማለት የሚጠራው፣ ይህን ወቅት ከመብሰል ከመጎምራት ጋር በማያያዝ በቀይ ቡናማ ቀለም ይወከላል፡፡

ገበሬው በባህላዊ የግብርና ዕውቀት ተጠቅሞ ያመረተውን ሰብል የደረሰ የደረሰውን የሚያጭድበትና ወቅቶ የሚያስገባበት ጊዜ ነው፡፡ አጨዳው የሚከናወነው በተናጠል ወይም በወንፈል ሊሆን ይችላል፡፡ አቶ ሞላ "ትሳስ፣ ጥር፣ የካቲት የአጨዳ የበራይ ወቅት ነው፡፡ ድሮ ድሮ በወንፈል ነበር የምናጭደው አሁን ደሞ ስሙ ተለውጦ በአንድ ለአምስት አደረጃጀት[142] ነው" በማለት ይገልጻሉ፡፡[143]

በአጨዳ ወቅት በደጋው አካባቢ የሚኖሩት ተቀምጠው በሞቃታማው አካባቢ ደግሞ አጎንብሰው ነው የሚያጭዱት፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የደጋማው አካባቢ እህል ቁመቱ አጭር በመሆኑ ሲሆን በሞቃታማው አካባቢ የሚበቅለው እህል ቁመቱ ረዘም ያለ ስለሆነ ነው፡፡ የታጨደው ሰብልም ያልደረቀ ካለው እንዲደርቅ በማሳው ላይ ተዘርግቶ ከ3-5 ቀናት ይቆያል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እህሉ "ይጨምታል" ገለባው ሲጠነክር ፍሬው በርከት ይላል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ከዚያም በበአላት ቀናት በነዶ በነዶ[144] ይታሰርና ከ10-15 የሚሆኑ ነዶዎች ባንድ ላይ ተሰብስበው በዚያው በማሳው ላይ ተቆምጮ /ተጎብሶ/[145]ይቆያል፡፡ ይህም የሚሆነው ሰብሉን አንስቶ መከመር ብቻ ስለሆነ በዓላትን አያሽርም፡፡ እንዲሁም ብዙ የሚያግዝ ሰው የሚገኘው በዚሁ በበዓላት ቀን ነው፡፡

---

[142] አንድ ለአምስት አደረጃጀት፡- በመንግስት ትእዛዝ መደራጀት አለባችሁ ተብለው የተደረጁት እንጂ ባህለዊ አደረጃጀት አይደለም፡፡

[143] አቶ ሞላ ፈቃዴ፣ አደጋ ጓሽታ ውባጅ ቀበሌ፣ መስቀለኛ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 24/06207፡፡

[144] ነዶ፡- በእቅፍ ሙሉ የሚሆን የታጨደ ጤፍ አንድ ላይ ይታሰራል ይህ የታሰረው ነዶ ይባላል፡፡

[145] መቆመጭ ፡- ማለት የተወሰኑ የእህል ነዶዎችን አልፎ አልፎ በአንድ በአንድ ላይ በማሳው መከመር/ማስቀመጥ፡፡

በመጨረሻም ቁምጮው እየተሰበሰበ በሸክም አውድማ በሚዘጋጅበት አካባቢ ይጓዝና በአንድ ላይ ይከመራል፡፡ ችግር ያለበት ሰው ቶሎ ወቅቶ ሊያስገባ ይችላል፡፡ በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ ግን ጥምቀት ሳይውል ጤፍ አይወቃም፡፡ ምክንያቱም አይበረክትም፣ ረድኤት አይኖረውም ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡

በውቂያ ወቅት በቅድሚያ አውድማ ይዘጋጃል፡፡ ለአውድማ የሚሆነው መሬት በሚገባ ከተመነጠረና ከተፈቀፈቀ በኋላ ውኃ እየተርከፈከፈ ይጠረጋል፣ ከዚያም በከብቶች በደንብ ይጠቀጠቃል፡፡ ስለ አውድማ አዘገጃጀት ወ/ሮ ሰገዱ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> አውድማ ሲዘጋጅ ይበጠራል፣ ይፈቀፈቃል፣ ውኃ ይረበረባል፣ በላፋት[146] ይጠረጋል፣ በከብት ይደቀደቃል፣ ይተመተማል፣ ተዚያ በትልቅ ቅርጫት እበት ተበጥብጦ ይለቀለቃል፡፡ ሲደርቅ በደንብ እንዲጠብቅም መጀመሪያ ጥራጥሬ ይበራይበታል፡፡ ተዚያ እንደገና በደንብ ተለቅልቆ ጤፍ ይበራይበታል፡፡[147]

ከወ/ሮ ሰገዱ ሃሰብ ለጤፍ የሚደረገው ዝግጅት ከእርሻው ጀምሮ ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚጠይቅ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከላይ ካየናቸው በተጨማሪ በአውድማ ዝግጅቱም ላይ የተለየ ሁኔታ ይታያል፡፡ ጤፍና ስንዴ የሚበራየው ሌሎች እህሎች በአውድማው ላይ ከተበራዩና የተሰነጣጠቀው መሬት በደንብ ከተደፈነና ድጋሚ ከተለቀለቀ በኋላ ነው፡፡

እህል በሚበራይበት ወቅት የራሱ የሆነ ቅደም ተከተልና አካሄድ ያለው መሆኑን ከላይ ያለው ገለጻ ያሳየናል፡፡ የመጀመሪያው ተግባር ለአውድማ የሚሆን ቦታ ማዘጋጀት ነው፡፡ አውድማው በሚዘጋጅበትም ወቅት ለአውድማነት የተመረጠው ቦታ በደንብ ተፈቅፍቆ ይጠረጋል፣ ከሳር ከሌሎች ነገሮች ይጸዳል፣ ውኃ እየተርከፈከፈም በከብቶች ይደቀደቃል፣ በመጨረሻም በእበት በደንብ ይለቀለቃል፡፡ ይህም የሚሆነው የተመረተው

---

146 ከቀርከሃ ቀጫጭን ቅርንጫፍ የሚዘጋጅ መጥረጊያ

147 ወ/ሮ ሰገዱ ሞላ፣ አብስላ ዋርዳ ቀበሌ፣ ባኳ ደሸ፡ ቃለ-መጠይቅ 27/06/2007

ምርት ጥራቱ እንዳይጓደል ለማድረግ ነው፡፡ የተለቀለቀው አውድማ ሲደርቅም ቀጣዩ ስራ እህሉን ማበራየት ነው፡፡



ፎቶ 22፡- አቶ ልመንህ ዳኛው በመንሽ ውቻሬ ሲያወጡ ሹምታ፣ 17/06/2007፡፡

የእህል በራይን በተመለከተ አቶ ልመንህ የሚከተለውን ብለዋል፡-

> እህል በራይ ከመጀመሩ በፊት የተቃና፣ በራይ በምርቃት የሚጀመረው ምርቱ የተትረፈረፈ እንዲሆንና በረከት እንዲኖረው ነው፡፡ በበራይ ወቅት በተለይም ጤፍ ሲበራይ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ከክምሩ እየተመዘዘ ከ"ተዘረዘረ"[148]በኋላ በከብት እግር ይበራያል፤ ከብት እየዞረበት በመንሽ እየተገላበጠ በደንብ ይበራያል፤ ወደ ላይ ማለት ሲጀምር ውቻሬ[149] ይሳባል፤ ያው

[148] ተዘረዘረ፡- እህሉ ከክምሩ እየተናደ አውድማው ላይ ተነሰነሰ (ለመበራየት ተዘጋጀ) ማለት ሲሆን በበራይ ሂደት ይህም የመጀመሪያው ደረጃ ነው፡፡

[149] ውቻሬ፡- በበራይ ሂደት ሁለተኛው ደረጃ ነው፡፡

እንዳይደክመን፣ ከብቶችን እያሞጋገስን እንዘፍናለን፤ "በርዬ ጐንዬ በእግርህም አሻሽ፣ በቀንድህም መንሽ፣ እንጨርሰ ሳይመሽ፡፡" "በርዬ ኑርልኝ፣ ገለባውን ብላ ፍሬውን ተውልኝ፡፡" እያልን እናበራያለን ውቻሬው በመንሽ እየተበረበረ ታውድማው ዳር ይሆናል እንጂ ወደ ውጭ አይወጣም፤ ተዚያ ውቻሬው በትንሽ በትንሹ እየገባ በደንብ ተተረገጠ በኋላ ገለባው[150] ወደውጭ ይወጣል፤ ተዚያ በእግር እየተበረበረ በላፉት እየተንጣረበ በደንብ ተለይቶ ቅልጥሙ ይወጣል፤ ተዚያ ወዲያ እህሉ መሀል ላይ ይሰበሰብና ወደ ምስራቅ ለሁለት ተከፍሎ መሃሉ ክፍት ይሆናል፤ ተዚያ ሁለት ሆነው ወደላይ ቡናን[151] ማባነን ነው፤ ከዚያም በ"ማዝራት"[152]ይለያል፤ በመሀል በመሀሉም ለሰራተኞች ጠላ፣ ቆሎ አብዚው አለ ይበላል ይጠጣል፤ ምርቱ ተጣርቶ ተመግባቱ በፊትም ታውድማው ድግስ አለ፤ ቆሎ በኑግ፤ እንጀራ ጠላ ይመጣል፡፡[153]

በበራይ ወቅት ውቻሬው ከአውድማው ዳር የሚሆንበት ምክንያት ሙሉ በሙሉ ምርቱ ያልተለየለት በመሆኑ ተመልሶ በድጋሚ ወደ አውድማ ይገባና እንደገና በከብት ይደቀደቃል፡፡ ይህ የሚሆነው ከስር ያለውን ገለባ ወደላይ እንዲወጣ ለማድረግና ለማነሳሳት እንዲመች ነው፡፡ በዚህ የተለያዩ መሳሪያዎችን የሚጠቀሙ ሲሆን በዋናነት ለዚህ ተግባር የሚያገለግሉት መንሽና ላፉት መጥረጊያ ናቸው፡፡

መንሽ ለበራይ ጊዜ ገለባን ከምርት ለመለየት የሚያገለግል ባለ ሁለት ወይም ባለ ሶስት ጣት ሹካ መሰል እንጨት መሳሪያ፣ ላፉት ለደጅ መጥረጊያ የሚያገለግል ቢሆንም

---

150 ገለባ፡- በከብቶች እግር በደንብ ታሽቶ ምርቱ ከተለየ በኋላ የሚወጣው ተረፈ ምርት ሲሆን ገለባ የማውጣቱ ሂደት ሶስተኛው ደረጃ ነው፡፡

151 ቡናን፡- ገለባው ከወጣ በኋላ በንፋስ ኃይል ተባኖ የሚወጣው ሲሆን በምርት ሂደቱ አራተኛው ደረጃ ነው፡፡

152 ማዝራት፡- ይህ በምርት ሂደት ወቅት የመጨረሻው ደረጃ ሲሆን ምርቱንና ግርዱን የሚለይበት ሂደት ነው፡፡

153 አቶ ልመንህ ዳኛው፣ ፣ አግዛ ጋርዳ ኤሊያስ ቀበሌ፣ ሹምታ ደሽ፣ቃለ-መጠይቅ፣ 10/07/2007፡፡

በአውድማ ላይ የሚገኘው መጥረጊያ ግን ቁመቱ ረጅም እና ለማንጣረቢያ የሚያገለግል፣ እንዲሁም ከብቶቹ እህሉን እንዳይበሉ ለመከላከል ከተክል ልጥና ከቀጫጭን እንጨት ጎድጎድ ብሎ በክብ የተሰራ የአፍ መለጎሚያ፣ እና ለከብቶች መንጃ እረዘም ያለ ቀጭን ለበቅን ይጠቀማሉ፡፡ ከነዚህ መሳሪያዎች በተጨማሪ ከቅጠል የተሰራ ጊዜያዊ ዳስ አለ፤ ይህ ጊዜያዊ ዳስ ሲደክማቸው ለማረፊያነትና ለመመገቢያነትም ያገለግላል፡፡

ወዳጀ በሬ በሬ  በርዬ በልና በርዬ በልና
አንተም ወደ ሳርህ እኛም ወደ ቡና፡፡[154]

እያሉ ከብቶቻቸውን ወደ ወንዝ ውኃ እንዲጠጡ ከሰደዱ በኋላ ውቻሬውን አውጥተው እንደጨረሱም ሰዎቹ  ከእርጥብ ቅጠል በተሰራ ዳስ መሰል ጥላ ውስጥ አረፍ ብለው ምሳቸውን አብዚ ይበላሉ፤ ጠላ ይጠጣሉ፡፡



ፎቶ 23፡-አውድማ ላይ ምሳ እየበሉ ጠላ ሲጠጡ፣ ሹምታ፣10/7/2007

[154] አቶ ጌታሁን ብሩ፤ አግዛ ጋርዳ ቀበሌ፣ሹምታ ደሽ፣ቃለመጠይቅ፣10/7/2007

በመቀጠልም ውቻሬው ተመልሶ በትንሽ በትንሹ እየገባ በድጋሚ በከብቶች ከተደቀደቀ በኋላ ገለባው መውጣት ሲጀመር ከብቶቹ ምርቱን እንዳይበሉ በድጋሚ አፋቸው ይለጎማል፡፡ በመሀል በመሀሉ እየተተካኩ የሚያበራዩት ሰዎች ጠላ ይጠጣሉ፤ ቆሎ ይበላሉ፤፡ በዚህ መንገድ ስራቸውን ካከናወኑ በኋላ ምርቱን ከገለባውና ከግርዱ ለይተው ምርታቸውን ያስገባሉ፡፡ በዚህ መንገድ ነው የእህል በራይ የሚከናወነው፡፡ ምርታቸውን አጥርተው ሲያስገቡም እንዲህ እያሉ ይዘፍናሉ፡-

በሐምሌ ጐልጉዬ መስከረም አርሜ፣
በዘርዛራ ማጭድ በህዳር አጭጄ፣
መኸሩን ሽክፌ እበላለሁ እኔ፣
ጥርስ የመሰለውን ነጭ ጤፍ አብቅዬ፡፡

በማለት ከላይ ያለውን አጠቃላይ ምርት የማምረት ሂደት የአራቱን ወቅቶች አጠቃለው ይገልጹታል፡፡ እያንዳንዱ ተግባራት የሚከናወንበት ራሱን የቻለ ጊዜ ያለው መሆኑ በግጥሙ ተገልጿል፡፡ ገበሬው ወቅቱን ጠብቆ መሰራት ያለበትን ስራ በጊዜው ከሰራ ምንግዜም ውጤታማ እንደሚሆን ግጥሙ ያሳያል፡፡

ምርቱ ወደ ቤት ከገባ በኋላም እንደሚውልበት ተግባር ተለይቶ ይቀመጣል፡፡ በተለይም ለዘር የሚሆኑ የእህል አይነቶችን በመምረጥ በኩል ከወንዶች የተሻለ ዕውቀት ሴቶች አላቸው፡፡ በዚህ በኩል የሴቶቹ ሚና ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ወ/ሮ ሰገዴ ይህን ሃሳብ ሲያጠናክሩ ዘር የማበጠሩና የመምረጡ ስራ ከወንዶች በበለጠ የሴቶች ስራና ኃላፊነት ነው፡፡ የእያንዳንዱን ሰብል ወደ ቤት ከገባ በኋላ በአይነት በአይነት መለየትና የዘሩን፤ የቀለቡን ለይቶ ማስቀመጥ የሴቶች ድርሻ ነው፡፡ ወንዱ ሴቷ አዘጋጅታ ያቀረበችለትን ዘር መዝራት ነው፡፡ ከቤት ቢያልቅባት እንኳን መግዛቱም ሆነ ዘር የመለወጡ ተግባር የሴቷ ነው፡፡

> አንዳንድ ጊዜ የተመረተው ምርት ለዘር የማይሆንበት ሁናቴ ይፈጠራል፤ ክምሩን ዝናብ ተመታው ሊደልብ ይችላል፡፡ ይኸ ደሞ ለዘር አይሆንም፡፡ በመጀመሪያ ዘር አይበላም፡፡ ምርቱ ሲገባ ገና ለቀለብ፣ ለዘር፣ ለማቅናት[155] ተብሎ ነው የሚቀመጠው፤ ትል ያልወጋው፣ ያልታመከ፣ ያልደለበ ድንችም ተሆነ መቆፈሪያ ያልሸረፈውና ያልታመመ ነው ዘር የሚሆነው፡፡ ገብስም ተሆነ ያልዋራ[156]፣ እንዲህ ታልሆነ ግን መግዛት ወይም ደህና ንጹህ ዘር ካለው መለወጥ ነው፡፡ ማሽላም ተሆነ ገና ሲሸለቀቅ እስተጫፉ ድረስ የያዘና ሙሉ የሆነና ትል ያልበላው ነው፡፡ ድንችም ተሆነ አንድ ሁለቱ ሽና እዚያው ሳይቆፈር ይቀመጣል፡፡ ታለዚያ ተመርጦ ወይ ባልጋ ወይ በመደብ ተዘርግቶ ይቀመጣል፡፡ በተረፈ ግን ዘር አይበላም፡፡ ተበላችው ዘረ በላ ትባላለች፡፡ ይህን ስራ ደግሞ የሴቷ ነው፡፡ ዘርን መጠበቅ ያለባት ሴቷ ናት ዘርና ልጅ አንድ ነው፡፡[157]

እንደ ወ/ሮ ሰገዴ አገላለጽ አዝመራው ወደቤት እንደገባ ምርቱን በአይነት በአይነት መለየት፣ እንዲሁም ለሚቀጥለው አዝመራ የሚሆን የዘር እህልን አጣርቶና አዘጋጅቶ ከሌላው ለይቶ ማስቀመጥ የሴቷ ስራ ነው፡፡ የበቆሎ ዘር የሚመረጠው ከማሳው ገና በሚሸለቀቅበት ወቅት ነው፡፡ ምክንያቱም ልባሱ አስፈላጊ ስለሆነ በማሳ ላይ በሽልቀቃ ወቅት ዘሩን ይመርጣሉ፡፡ የሚመረጠው የበቆሎ ዘር እስከጫፉ ሙሉ ለሙሉ የያዘ መሆን አለበት በምንም አይነት ቀረቆንዳው መታየት የለበትም፤ ከታች እስከላይ ድረስ ሙሉ መሆን አለበት፡፡ ጎደሎ የሆነ ነገር ጥሩ እንዳልሆነ ስለሚታመን ዘርን በእንደዚህ ሁኔታ መምረጡ ተገቢ እንዳለሆነ ይታመናል፡፡ በዚህ መንገድ የተመረጠው ለዘር የሚሆን በቆሎ ልባሱ ወደላይ ይነሳና ተሰብስቦ ከ7-10 የሚሆነው በአንድነት ከታሰረ

---

[155] ለማቅናት፡- ለመሸጥ

[156] "ያልዋራ" ያልታመከና ያልደለበ ወይም በዝናብ ምክንያት መልኩ ወደቢጫነት ያልተቀየረ ትክክለኛ ቀለም / መልክ ያለው ማለት ነው፡፡

[157] ወ/ሮ ሰገዴ ሞላ፣ አብስላ ሳሙኤል ቀበሌ፣ ባኳ ደሽ፣ ቃለመጠይቁ፣ 27/11/2007፡፡

በኋላ በቤት ጥግ አየር ንፋስና ጭስ በሚያገኝበት ቦታ ላይ ይሰቀላል፡፡ ይህም የሚሆነው በቆሎ በቀላሉ በተባይ ስለሚበላ እንዳይነቅዝና እንዳይበላሽ ለማድረግ ነው፡፡ ሌሎቹ ወደቤት ከገቡ በኋላ መረጣው ይከናወናል፡፡

ባቄላና አተር፣ ፍሬው ትላልቅ እና ያልተሰባበረና ያልተጨማደደ እንዲሁም ትል ያልወጋው ይመረጣል፡፡ ይህንንም በሳር ከተሰፋ ሰፌድ አበጥረው አንጓለውና አጥርተው በመለየት ያስቀምጡታል፡፡ የገብስ የጤፍና የስንዴ ዘርም ሲመረጥ መልኩ ቢጫ ያልሆነ የመድለብ (እምክ እምክ) የሚል ሽታ የሌለው፣ ዋግ ያልበላው ተመርጠውና ተለይተው በጎታ[158] ወይም በጉሽጉሽ[159] ከስር የጤፍ ገለባ በማድረግ ያስቀምጡታል፡፡

የድንች ዘርም ንጹህ ንጹሁ ተመርጦ ይቀመጣል፡፡ በሚዘራበት ወቅትም ትል ያልወጋው፣ ያልበሰበሰ፣ መቆፈሪያ ያልነካው፣ መሆን ስላለበት ከመዘራቱ በፊትም፣ በየጊዜውም ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም በውስጡ ውኃ ስላለውና ሊበላሽ ስለሚችል በየጊዜው እየተመረጠ ለዘር ይዘጋጃል፡፡ ለዘር የሚዘጋጀው ድንችም በቆጥ ላይ ወይም መደብ ላይ አየር እንዲያገኝ ሆኖ ተዘርግቶ ነው የሚቀመጠው እንጂ በኬሻ አይከተትም፡፡ ይህን ሁሉ ተግባር የምታከናውነው ሴቷ ናት፡፡ ይህም በሴትነቷ ልጅ የመውለድና የመንከባከብ ተግባር የሴቷ ተፈጥሯዊ ተግባር እንደሆነው ሁሉ የእህልን ዘርም የመምረጡና የማስቀመጡ ተግባር ለሴቷ የተሠጠ ነው፡፡

በአካባቢው በማህበረሰብ ዘንድ የእህል ዘር እንደልጅ ነው የሚታየው፡፡ ልጅ አድጎ ትውልድ እንደሚተካ ሁሉ ዘርም በአግባቡ ከተያዘ ጥሩ ፍሬ ይሰጣል፡፡ ያለበለዚያ ግን የተዘራው ዘር ፈሬ አይሰጥም፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ "ሴትና መሬት የሰጧትን

---

158 ለእህል ማስቀመጫነት የሚያገለግል ከጭቃና ከገለባ በሴቶች የሚሰራ ሆኖ ከሁለት እስከ አስራአምስት ኩንታል ጤፍ መያዝ የሚችል ሆኖ እናትና ደልገን የሚባሉ ክፍሎች አሉት፡፡ እናት የሚባለው ከአንድ አስከ ሁለት ኩንታል የሚዝ የጎታው የታችኛው ክፍል ሲሆን ደልገን የሚባሉት ብዛታቸው በእናት ጎታው ስፋትና ጥበት የሚወሰን ሆኖ ከ3 እስከ 7 ሊደረሱ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ደልገኖች በመጠን የተለያዩ ሆነው በእናት ጎታው ላይ እየተደራረቡ ተሰካክተው የሚቀመጡ ናቸው፡፡ ለጎታ ስራ የመረጠው ቀይ አፈር ሆኖ እስከ ሶስት ወር ድረስ ቤጊዜው በገለባ እየታሸ ሊቆይ ይችላል፡፡

159 ጉሽጉሽ በመጠኑ አነስተኛ ሆኖ ከጭቃ የሚዘጋጅ ሲሆን በእናት ጎታና በደንገልም የተከፋፈለ አይደለም፡፡ ይህም ለዘር እና ለዱቄት ማስቀመጫ የሚሆን ነው፡፡

ታበቅላለች" እንደሚሉት ጥሩ ዘር እንዲሆን ዘሩን በአግባቡ መርጣ ታስቀምጣለች፡፡ ምን ቢቸግራትም ለዘር የተባለውን እህል አትበላም፡፡ ለዘር የተባለን እህል መብላት በማህበረሰቡ ዘንድ ያሥነቅፋል፡፡ ልጅን እንደመብላትም ስለሚቆጠር "ዘረበላ" ተብላ ትሰደባለች፡፡

የሴቶችን ስራ ብዙ ነው፡፡ እንደ አቶ ሞላ አገላለጽ "የሴቶች ድርሻ ምግብ ማብሰልና ልጅ ማሳደግ ቢሆንም ግብርናው ላይ ማለዳ እኔ ቁርስ ቀምሼ ወደ እርሻ ስሄድ እሷ ደሞ ጓሮ ላይ ማሽላ ስትኮተኩት ትውላለች፤ ምናልባትም ጦስኙን ጤናዳሙን ምኑን ትተክላለች፣ ያደሰው አትቦዝንም፣ ወደገጠር ስንወጣ ደሞ ዳጉሳ እናርማለን፣ ማሽላ እንኮተኩታለን በዘሩ ጊዜ ደሞ ሲዘራ ዘር ታቀብላለች ያን ያን ትሰራለች፣ ታርማለች ትኮተኩታለች"፡፡[160] ስለዚህ ሁኔታ ወ/ሮ ጥሩም እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፡-

> የኔ ስራ መጎልጎል፣ ማረም፣ በአረም ጊዜ አረም፣ እሱ (ባለቤታቸው) እርሻ ሲሄድ እቤት አበስላለሁ፣ ጓሮ አርማለሁ፣ እጎለጉላለሁ፣ ባጨዳው ጊዜ እጭዳለሁ፣ ነዶ አስራለሁ፤ ዘር አቀብላለሁ፤ ምርቱን አምርቶ ሲያስገባ ደሞ ይኸ ለቀለብ፣ ይኼን ታህል ዘር ይፈጃል ብዬ ለዘር አስቀምጣለሁ፡፡ አሜጅ ከሌለ ደግሞ ያው የሚዘራውን ለዘር የሚበቃኝን አጥርቼ፣ አዝርቼ፣ ጤፍም ቢዘራ አጥርቼ አበጥሬ፣ ገብስም ቢሆን አጥርቼ አዘጋጅቼ ነው የምሰጠው ፡፡[161]

እንደ አቶ ሞላና እንደ ወ/ሮ ጥሩ ገለጻ ሴቶች ከቤት ውስጥ ስራቸው በተጨማሪ በሬ ያጣምዳሉ፤ በጉልጓሎው ጊዜ ይጎለጉላሉ፤ በአረሞ ጊዜ ያርማሉ፤ በኩትኳቶው ጊዜ ይኮተኩታሉ፤ በዘር ጊዜ ዘር ያበጥራሉ፤ ዘር ያቀብላሉ፤ በአሁኑ ሰዓት አብረው ይዘራሉ፤ በእርሻ ወቅትም ለማረሻ አስቸጋሪ የሆኑትን በመኮትኮቻና በመቆፈሪያ

[160] አቶ ሞላ ፈቃዴ፣ አደጋ ውባጅ ቀበሌ፣ መስቀለኛ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 03/07/2007
[161] ወ/ሮ ጥሩ ጌታነህ ፣ አደጋ ውባጅ ቀበሌ፣ መስቀለኛ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 2/07/2007

ይነቅላሉ፡፡ እንጨት ይፈልጣሉ፡፡ በበራይ ወቅትም አውድማ ይለቀልቃሉ፤ አብዛኛውን ስራ ከወንዶች እኩል ያከናውናሉ፡፡ የጓሮ አትክልት እና ቅመማ ቅመም ይተክላሉ፤ ይንከባከባሉ፡፡

በባህላዊ ግብርና ስራ በወቅቶች የተከፋፈለ ተግባር እንዳለ ሆኖ ወቅትን ሳይጠብቁ አመቱን ሙሉ የሚከናወኑ ተግባራትም አሉ፡፡ የጓሮ መሬትን የመንከባከቡ ተግባር በአብዛኛው የሴቶች ነው፡፡ በዚህ መሰረት በቤት ጓሮ የሚገኝ መሬት በርካታ አይነት ተክሎችንና እጽዋትን ከመያዙም በተጨማሪ ለእርሻ ተግባርም ይውላል፡፡



ፎቶ 24፡- ሴቶችና ወንዶች ባንድነት የጤፍ አረም ሲያርሙ፣ ጓሽታ፣

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደሚገልጹት በጓሮ በሚገኘው መሬት ላይ የሚደረገው ባህላዊ ማዳበሪያ እንደ ተክሉ ወይም እንደሚዘራው ሰብል አይነት ይወሰናል፡፡ ወ/ሮ ገነቴ ስለ ባህላዊ ማዳበሪያ ሲናገሩ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

የጓሮ መሬት ዘመሚትና ምስጥ ያለው ተሆነ በተክሎቹ ዙሪያ አመድ እንጨምራለን፡፡ አመድ ደረቅ ነው ዘመሚት[162] ደግሞ እርጥበትን ይፈልጋል፡፡ ለድንች የሚዘጋጅ መሬት ተሆነ ደሞ የከብቶቹ እዳሪ አይጨመርበትም፡፡ ውስጡ ቆራጭ ትል ስለሚፈጥር፣ ድንቹን ይበላዋል፡፡ በድንች መሬት ላይ የሚጨመረው የፈረሶችን ፋንድያ፣ የቤቱን ጥራጊ እየደፋን እናቀልዘዋለን፡፡ እንደዚያ ታልሆነ ይበላሻል፡፡ የሚዘራው ገብስ፣ ስንዴ፣ ጤፍ… ተሆነ ደሞ የከብቶችን እዳሪ እንዲያ ደሞ ጥራጊውን እንደፋበታለን፡፡[163]

እንደ ወ/ሮ ገነቴ አገላለጽ የቤቱ ጥራጊም ሆነ የከብቶች ፍግ በማንኛውም የእርሻ መሬት ላይ ዝም ብሎ አይደፋም፡፡ በመሬቱ ላይ ቀደም ብሎ የሚዘራው እህል ስለሚወሰን እንደ ሰብሉ አይነት ተለይቶ ይደፋል፡፡ ያለበለዚያ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል፡፡ ይህንን በልምዱና በሕይወት ተሞክሮው ያዳበረውን ባህላዊ የግብርና ዕውቀት ተጠቅሞ እያንዳንዱን ነገር በትኩረት በመከታተልና በመመልከት ምን ማዳበሪያ ቢደረግበት ይጎዳዋል? የትኛውስ ይጠቅመዋል በማለት ለይቶ ይጠቀማል፡፡ በጓሮ አትክልቶች ላይም የሚደረገው ነገር ተመሳሳይ ነው፡፡ ለምሳሌ በጤናዳም ተክል ላይ አመድ ይደረጋል፡፡ ይህም ዘመሚት የሚባል ነፍሳት የተክሉን ስር እንደይቆራርጠው ለማድረግ ነው፡፡

ምርትን በማምረት ሂደት ውስጥ በርካታ ተግባራቶች፣ እምነቶችና ልማዶች የሚከናወኑ ሲሆን አብዛኞዎቹ በመኸር ወቅት በተለይም በበራይ ወቅት የሚከናወኑ ናቸው፡፡ እነዚህን ልማዶችንና እምቶችን አንዳንዶቹ ለምን እንደሚፈጽሟቸው እንኳን ሳያውቁ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው በሚል ብቻ ይተገብሯቸዋል፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ የልማዶቹን ምክንያት ተረድተው የሚፈጽሟቸው ናቸው፡፡

162 ዘመሚት ቀይ ትንንሽ ጉነዳን የተክሎችን ስር የሚቆራርጥ
163 ወ/ሮ ገነቴ ደምለው ቲሊሊ በተለያየ ወቅት መረጃን ያቀበሉኝ

## 5.6. ከግብርናው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ልማዶችና እምነቶች

በምዕራፍ ሁለት ስር እንደተብራራው ለዚህ ጥናት የተጠቀምሁት የSchoemaker (1990፡3) የፎክሎር ምደባን ነው፡፡ በዚህም መሰረት ሰዎች "የሚያደርጉት" ልማድና እምነት አንዱ የፎክሎር ዘርፍ ነው፡፡ ይህን የፎክሎር ዘርፍ የሆነውን ልማድና እምነት ከግብርናው ጋር በተያያዘ መንገድ ይተነተናል፡፡ ስለዚህም Schoemaker ሰዎች የሚያደርጉት ብሎ ባስቀመጠው መሰረት ልማድና እምነትን ሁለቱንም ለማየት ሞክሪያለሁ፡፡

በዚህ በመኸር ወቅትም ገበሬው የባህላዊ ግብርናው ዕውቀት አካል ከሆነው ምርትን ከመሰብሰብና ከማስገባት ጋር ተያይዞ ገበሬው የሚያከናውናቸው በርካታ "እምነቶች" እና "ልማዶች" እንዳሉት በምልከታዬ ወቅት ያየሁትንና በቃለመጠይቅ ያዳበርሁትን መረጃ በቅደም ተከተል ቀጥሎ አቀርባለሁ፡፡

በምርት ሂደቱ ማለትም በበራይ ወቅት ሁለት አይነት የምረቃ ሥርዓት ይከናወናል፡፡ የመጀመሪያው አውድማ ከመጣሉ (እህሉ ከመነሥነሱ) በፊት የሚከወነው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከብቶቹ ከአውድማው ጨርሰው ሊወጡ ሲሉ የሚደረገው ሥርዓት ነው፡፡ የመጀመሪያው የምርቃት ሥርዓት የሚከናወነው ምርቱን ከመበራየቱ ወይም ክምሩ ከመጣሉ በፊት ለአምላካቸው ምስጋናና ጸሎት የሚያቀርቡበትና አምላካቸው ጥሩ ነገር እንዲያደርግላቸው የሚጠይቁበት ነው፡፡ ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ ወቅት በሥራው ከሚሳተፉት መካከል በዕድሜ አንጋፋ የሆነው ሰው ቆሞ ይመርቃል፡፡ ይህን ምርቃት ባህል አስመልክቶ የዚህ ጥናት መረጃ አቀባይ ብላታ ዳኛው እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡-

> አውድማው ላይ እህሉ ከመነሥነሱ በፊት ይመረቃል፤ ሽመጋግሌዎች ይመርቃሉ፡፡ እንግዲህ ሲመረቅም አገሩን አማን፣ ገበያውን ጥጋብ ያድርገው፣ ታገሱ ተመለሱ የሚል መንግስት ይስጠን፣ እህል በልቶ ከሚጣላ ያድነችሁ፡፡ "በዝናብ አብቅሎ

በጸሐይ አብስሎ" ለዚህ ያደረሰን አምላክ አሁንም በሰላም እንድናስገባ ይርዳን፡፡ እህሉን ረድኤት በረከት ያውርድበት፡፡ የጣናን ያህል ምርት ይስጠን፤ የጤና ቀለብ ያድርገው፤ እየተባለ ይመረቃል፤ ተቀባዮችም አሜን! አሜን! በማለት ምርቃቱን ይቀበላሉ፤ ከዚያም ተመረቁት ሽማግሌዎች አንዱ የመጀመሪያውን ከክምሩ ስቦ ይጥላል (ይነሰንሳል)፤ ከዚያ ወዲያ አንድ ሰው፣ በርከት ያለ ከሆነ ደግሞ ሁለት ሁነው ክምሩን እየናዱ ይጥላሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ አፋቸውን ለጉመው በተነሰነሰው እህል ላይ ከብቶቹን ይነዳሉ፡፡[164]

እንደ ብላታ ዳኛው ገለጻ ምርቃት በዚህ ማህበረሰብ ዘንድ ትልቅ ቦታ ያለው ትውፊት ነው፡፡ የምርቃትን ስርዓት የሚያከናውኑት በዕድሜ ጠና ያሉ ወንዶችም ሴቶችም ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በራይ ሲጀመር ግን የሚመርቁት ወንዶች ናቸው፡፡ ይህም በባህሉ ሴት አውድማ ስለማትገባ ነው፡፡ ምርቃቱን በዕድሜ ተዋረድ ከታች ወደ ላይ ሶስት ሰው ይመርቃል፡፡ ሶስት ቁጥር ከብዙ ነገር ጋር ይገናኛል፤ ማህበረሰቡ የክርስትና እምነት ተከታይ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የስላሴን ሶስትነት፣ የክርስቶስን ሶስት ቀን በከርሰ ምድር መቆየት፣ ዮናስ በአሳ ነበሪ ሆድ ሶስት ቀን ማደር (ት.ዮ፡2÷1)፣ ... ሲያያዝ፣ ምስክርነት በሶስት ይጸናል፣ ምርቃት በሶስት ሰው ያሳርጋል፡፡

ሌላው ደግሞ በምረቃ ወቅት የሚባክን ጊዜን ለማስቀረት ሲባልም በሶስት እንዲጸና የተደረገ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም እኔ እንዳየሁት አንዳንዶቹ ሲመርቁ ረጅም ጊዜን ጊዜን ይወስዳሉ፡፡ ስለዚህ ቁጥሩ ከዚህ ከፍ ካለ በርካታ ጊዜን ቆመው ምርቃትን ብቻ ሲቀበሉ ሊያሳልፉ ይችላሉ፡፡

በዕድሜ ከፍተኛው ምርቃቱን ያሳርጋል፤ በዚህ ወቅት በአድሜ ዝቅ ያሉት ሁሉም ቆመው ምረቃቱን ይቀበላሉ፡፡ መራቂውም ቢሆን ቆሞ ነው ምርቃቱን የሚሰጠው፡፡

[164] ብላታ ዳኛው ሞገሴ፣ አግዛ ጋርዳ ኤሊያስ ቀበሌ፣ ሹምታ ደሽ፣ ቃለ-መጠይቅ፣ 09/ 07/ 2007

ምርቃቱን የሚያሳርጉት በዕድሜ ከሁሉም ታላቅ የሆኑ ናቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ስለሀገር ሰላምና ስለህብረተሰቡ ጤና፣ ስለ ገበያ ጥጋብ፣ ስለአካባቢው፣ ስለ ምርቱ፣ ስለ ከብቱ፣ ስለ መንግስቱ… ይመረቃል፡፡ የሚመረቀው ሰው ቶሎ ቶሎ አሜን ካላለና ቀድሞት ሌላው አሜን ካለ የምርቃቱ በረከት ለዚያ ይተላለፋል ተብሎ ይታመናል፡፡ የኤሳውን ምርቃት ያቆብ እንደወሰደ (ዘፍ፤27÷1-33) "ምርቃት ከአሜን ይቀራል" እንደሚባለው ማለት ነው፡፡ ታላቅን ማክበር በባህሉ ትኩረት የሚሰጠው እሴት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በእድሜ ትልቁ በመመረቅ ያሳርጋል በዚህም ምርቃቱ ይጸናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በባህሉ በእድሜ ትልቁን እንደ ፈጣሪ መመልከት አለ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአውድማ ላይ የከብት ምርቃትም ልማድም ይከናወናል፡፡

የከብት ምርቃት የሚከናወነው በበራይ ወቅት ነው፡፡ ይኸውም በበራይ ሂደቱ ሶስተኛው ደረጃ መገባደጃ አካባቢ የሚፈጸም ተግባር ነው፡፡ ከብት የመመረቅ ስርዓት ከብቶቹ የማበራየቱን ተግባር ጨርሰው ከአውድማው ከመውጣታቸው በፊት ይከናወናል፡፡ ይህን ስርዓት የሚያከናውነው አባወራው ሲሆን እርጥብ አባሎ ቅጠል በሁለት እጆቹ በመያዝ ቀድሞ ያበራይ የነበረው ሰው ሌላ ከሆነ እሱ ይገባና ይቀበላል፡፡ ከዚያም ከብቶች ይዞሩበት የነበረውን አቅጣጫ በመቀየር ከግራ ወደ ቀኝ እያዞረ በአውድማው መሐል ላይ ካለው ጀምሮ እስከ ዳር አዟሪው ድረስ በእጁ በያዘው የአባሎ ቅጠል የከብቶቹን ጀርባ ያሥነካና ምርቱን ያሥነካል፡፡ ከብቶቹን ነክቶ ምርቱን በነካ ቁጥርም የተለያዩ ወንዞችንና ሀገራትን በመጥራት "የአንከሻውን፣ የጓጉሳውን፣ የባንጃውን አውርድ!" ጣና ያህል ምርት አውርድ! ይላል፡፡ የከብቶቹን ጀርባ ነክቶ ምርቱን በነካ ቁጥርም ከከብቶቹ ጭራ ትንሽ ትንሽ ጸጉር ይነጫል፡፡ እንዲህ እያደረገም አውድማውን ሶስት ጊዜ ይዞርና ከብቶቹን ከአውድማው በስተቀኝ በኩል ያስወጣቸዋል፡፡ ይህ ሂደትም ከብት መመረቅ ይባላል፡፡

በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ቀኝ የመልካም ነገር ምሳሌ ነው፡፡ ቀኝ የብርሃን መውጫ ነው፡፡ ከምኝታው ሲነሳ በቀኝ ጎኑ ነው፡፡ ሲጸልይ በቀኝ አውለኝ ይላል፡፡ በዚህ

መሰረት ቀኝ ለማህበረሰቡ የሰኬቱ ምልክት፡፡ የምኞቱ ማስፈጸሚያ ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ ቄስ ታየ የሚከተለውን ብለዋል፡-

> ከምሩ ተደቀቀ በኋላ አባወራው ከብቶቹን በቀኝ እያዞረ በእርጥብ አባሎ ቅጠል የከብቶቹን ጀርባና ምርቱን በመንካት አውርድ! አውርድ! እያለ ሶስት ጊዜ ያዞራቸዋል፡፡ የከብቶቹን ጀርባ በመታ ቁጥርም ካንዳንዳቸው ከብቶች ጠጉር ይነቅላል፡፡ የሽኩዳድን አውርድ! የጓጉሳን አውርድ! እያለ በምርቱ ላይ ያለውን የሚመኘውን፣ የሚፈልገውን ተሰፋውን፣ ይናገራል፡፡ ተዚያም ሶስትዜ ታዞረ ወዲያ ከብቶቹን ታውድማው በስተቀኝ በኩል ያስወጣቸዋል፡፡[165]

እህሉ ተንጣርቦ ሲያበቃ ከመባነኑ (ባ- ይጠብቃል) በፊት ከሚነዱት ከብቶች ጭራ የተነጨው ጸጉር በተመቱበት እርጥብ የአባሎ ቅጠል ተጠቅልሎ በምርቱ መሀል ይቀመጣል፡፡ ለመባነን ለሁለት ከመከፈሉ በፊት ከመሀል ይወጣና ለብቻ ተቀምጦ ይቆያል፡፡ በመጨረሻ እህሉ ወደ ቤት ሲገባ አብሮ ይገባል፡፡ ይህም እህሉን ወሳጅ[166] እንዳይወስደው መከላከያ ነው፡፡ እርጥብ ነገር በማህበረሰቡ ዘንድ የመልካም ነገር ምሳሌ ነው፡፡ የአባሎ ቅጠል ደግሞ አመቱን ሙሉ ለምለምና ድርቅን መቋቋም የሚችል ተክል ነው፣ አይደርቅም፣ እርጥብ ነገር ሁልጊዜም ይለመልማል፣ ያብባል፣ ያፈራል፣ ይበዛል፡፡ ስዚህም ምርቱ ልክ እንደዚሁ እንዲበዛ ስለሚፈለግ ነው፡፡ ከዚሁም በተጨማሪ አባሎ በማህበረሰቡ ዘንድ ለሰላቢ[167] መንፈስ መድሐኒትም ነው ተብሎ ይታመናል፡፡

---

165 ቄስ ታየ ታፈረ፣ አብስላ ዋርዳ ሳሙኤል ቀበሌ፣ ዋህሳ ደሽ፣ ቃለ-መጠይቅ 3/7/2007

166 "ወሳጅ"፡- የሰውን እህል፣ ገንዘብ… በአይን በማየት የሚወስድ (የሰላቢ መንፈስ ያለበት) ይሉታል

167 ሰላቢ፡- ልዕለ ሰብ የሆነና ለሰው የማታይ ረቂቅ መንፈስ ሆኖ በሰው ላይ የሚያድር መንፈስ ሆኖ ያለፋበትንና ያልደከመበትን የሰው ላብ፣ ገንዘብ፣ እህል፣ ሀብት… ይወስዳል ተብሎ የሚታሰብ መንፈስ

ከብቶቹ ወደ አውድማው ሲገቡ ምናልባትም የሰላቢው መንፈስ አብሮ ይገባል ተብሎ ስለሚታሰብ ከብቶቹ ላይ ሆኖ የሰበሰበውን እህል ጥሎ እንዲሄድ ለማድረግ የከብቶቹን ጀርባ እየመቱ አውርድ! አውርድ! ይላሉ፡፡ ከላያቸው የተነቀለውም ጸጉር በከብቶቹ ላይ የነበረውን እህል እንዲያስቀር ከብቶቹ ላይ አለ ብለው ለሚያምኑት መንፈስ ማስደነገጫ ከመሆኑ በተጨማሪ ከብቶቹ ላይ ያለውንም ይዞ ይመጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለዚህም ከጭራቸው ተነቅሎ ከእርጥብ አባሎ ጋር የሚታሰረውና ምርቱ ውስጥ የሚጨመረው ምርቱ እንዲበዛና እንዲበረክት ነው፡፡ ከብቶቹም እርጥብ እንዲሆኑና እንዲወልዱ እንዲረቡ ሲባል ነው፡፡ ከምርቃቱ ሌላ የሚከናወኑ ሌሎች ልማዶችና እምነቶችም አሉ፡፡

ከነዚህ እምነቶችና ልማዶች ጋር የተገናኘው ሌላው ፎክሎራዊ ትውፊት ከቁሳቁሶች ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው፡፡  በመኸር ወቅት አውድማን ጠርቦ ከማዘጋጀት ጀምሮ ሰብሉ ተበራይቶ እስኪገባ ድረስ ባለው ሂደት በርካታ ቁሳቁሶች አገልግሎት ላይ ይውላሉ፡፡ በተለይም በአውድማ ዝግጅት ወቅት ከድቅደቃ ጀምሮ አገልግሎት ላይ የዋሉ እቃዎች እህሉ ተበራይቶ እስኪገባ ድረስ እዚያው በአውድማ አካባቢ ይቀያሉ እንጂ ወደ ቤት አይገቡም፡፡ ይህንንም በተመለከተ ቄስ አወቀ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> አውድማ ስናዘጋጅ የእበት መበጥበጫው ቅርጫት፣ ጭራንፎው /ላፋት መጥረጊያው ወደቤት አይሄድም፡፡ ሴትዮዋ ውኃ የምትቀዳበት ማድጋ[168] እንኳን ታፉ ላይ በጥርሳችን ሸረፍ ሸረፍ አድረግን ታውድማው እናስቀምጠዋልን፡፡ ታለዚያማ ያውድማው ረዴት ይሄዳል፡፡ እህሉን አበራይተን ስንጨረስ በቅርጫቱ እንሰፍርበታለን፡፡ ተዚያ ወዲያ ላፋቱም ምርቱና ግርዱ ተተለየ ወዲያ እየተጠረገ ይሰበሰብበታል፡፡ ይህ ብቻ አደለም አውድማ ስንጥል ደሞ ተቤታችን እሳት የሚጭርም ሆነ እቃ የሚዋስ፣ ከብት

[168] ማድጋ፡- ከሃያ እስከ ሰላሳ ሊትር ሊይዝ  የሚችል ከሸክላ የተሰራ የውኃ መቅጃ/ መሸከሚያ እንስራ ("ን" ይላላል)

የሚለምን የለም፡፡ ያን ታደረገ ደሞ ሰላቢነቱ ታውቆ ተማህበር ይወጣል፤ ተሰው ይገለላል፡፡ ሁሉም ያነውረውና እንደውሻ ነው የሚታየው፡፡[169]

እንደ ቄስ አወቀ ገለጻ ይህ ክንውን የሚደረገው የአውድማው በረከት ከዕቃው ጋር አብሮ ይሄዳል፣ በዚህም ምርቱ ይቀንሳል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ በአውድማው ዙሪያ አውድማውን የሚተያይ ክፉ መንፈስና የአውድማውን በረከት የሚጠብቅ ነገር አለ ተብሎ ስለሚታሰብ በአውድማው ዙሪያ የሚገኙ ነገሮች ሁሉ እህሉ ተበራይቶ እስኪያልቅ ድረስ ከዚያው አካባቢ እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡ ይህም መጥፎውን መንፈስ መሄጃ ማሳጣት ሲሆን ለጥሩው ደግሞ ክብርን መግለጫ ነው፡፡

**በአጉማስ[170] መደቃት፡-** በአውድማ አካባቢ የሚያለፍ ማንኛውም መንገደኛ ሰው ከአውድማው ድግስ ጥሬ (ቆሎ፣ ንፍሮ) ሳይቀምስ መሄድ የለበትም፡፡ ምክንያቱም የአውድማው አጉማስ ይደቃዋል፡፡ በዚህም ሰበብ ይታመማል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአውድማውን እህል ረዴት፣ በረከት ይወስደዋል በሚል ነው፡፡ ስለዚህ አውድማው ላይ ካለው እህል ይልቅ አይኑም ሆነ ቀልቡ በበሰለው እህል ላይ እንዲያርፍ ለማድረግ ቢቻል በውዴታ ካልሆነ ደግሞ በግዴታም ቢሆን እንዲቀምስ ይደረጋል፡፡


**የአባወራው ውኃ አለመንካት፡-** እህል ተበራይቶ (ተወቅቶ) ወደ ቤት እስኪገባ ድረስ የቤቱ አባወራ ሲበላም ሆነ ሲጠጣ እጁንም እግሩንም አይታጠብም፤ በአጠቃላይ ምንም አይነት ውኃ አይነካውም፡፡ ይህም የሚሆነው አባወራው ከታጠበ የእህሉ በረከት ታጥቦ ይሄዳል፤ ምርቱ ገለባ ብቻ ሆኖ ይቀራል፡፡ በሚል እምነት ነው፡፡

[169] ቄስ አወቀ ተፈራ፣ አብስላ ዋርሰዳ ሰሙኤል ቀበሌ፣ ሳሙኤል ደሽ፣ ቃለ-መጠይቅ 03/07/2007

[170] አጉማስን አንዳንዶች በአይን የማይታይ ረቂቅ መንፈስ ሆኖ አውድማውን ከሌላ ነገር የሚጠብቅ፣ አልፎ አልፎም ጥቃት ሊያደርስ የሚችል ብለው ሲገልጹት አንዳንዶቹ ደግሞ የአውድማው መንፈስ የረበበበት የቤቱ አባወራ ነው በማለት ይገልጹታል፡፡ እኔም ሁለቱንም በማቻቻል ለመጠቀም ሞክሬአለሁ፡፡

በአውድማ ወቅት የቤቱ አባወራ ወደቤት አይሄድም እህሉ ተጣርቶ እስኪያበቃ ድረስ አውዳማው ዘንድ ይቆያል፡፡ አውድማው ላይ የሚመጡ ምግቦችም አብዛኛው ቆሎ በመሆኑ የእጅን መታጠብ ልብ ብሎ የሚያስበው የለም፡፡ ለመጠጥነት የሚቀርበውም ቢሆን አቅም በፈቀደ መጠን ጠላ ነው፡፡ ስለዚህ አውድማው ውኃን እንደልብ ማገኘት አይቻልም፡፡

**ሴት አውድማ ያለመግባት፡-** እህሉ ተባኖ ለመሰፈር እስኪደርስ አውድማ ውስጥ ሴት አትገባም፡፡ ይህ ሲባል ግን ሁሉንም ሴቶች የሚመለከት አይደለም፡፡ የሚመለከተው ያገቡ ሴቶችን ነው፡፡ ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱትን ልጃገረዶች ግን እንደ ወንድ ስለሚቆጠሩ በአውድማው ውስጥ ገብተው ከብቶችን በማዞር ይረዳሉ፡፡



ፎቶ 25፡- ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰች ሴት አውደማ ውስጥ ከብት ስታዞር/ ስትነዳ፣ ሹምታ፣ 17/06/2007፡፡

በዚህ ወቅት ያገቡ ሴቶች ተግባር እህል አብስሎ ለሰራተኞቹ ማቅረብ ነው፡፡ ተበራይቶ ካለቀ በኋላ የቤቱ አባወራ ላምብታውን[171] አንስቶ አውድማው በተለቀለቀበት ቅርጫት

[171] እህሉ ከመሰፈሩ በፊት መጀመሪያ የሚነሳና ለቤተክርስቲያን የሚሰጥ አስራት በኩራት

ምርቱን ያፍስና መልሶ በመገልበጥ ለሚስቱ ሰፍራ እንድታነሳ ያስረክባታል፡፡ ወጣቶቹ ሴት አውድማ እንዳትገባ የምትከለከልበትን ምክንያት እንደማያውቁ ይገልጻሉ፡፡ ነገር ግን በልምድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባህል እንደሆነ ያምናሉ፡፡ በዕድሜ የገፉት አቶ አየለ እንደሚሉት ደግሞ፡-

> አውድማ ሲጣል ሁሉም ነገር ንጹህ መሆን አለበት፣ ሰውም ሁሉም ጥዱ ነው የሚሆነው፣ ተጥላው[172] "ተምኑ" ሁሉ፡፡ አውድማ ተተጣለ ጀምሮ አባወራው ወደቤት አይሄድም ሊሳሳት ይችላል፡፡ እሷም ወደ አወድማው አትመጣም እሷን ሲያይ ልቡ ይከጅልና ይሳሳታል፣ በማለት ነው፡፡ አውድማው ላይ የሚረበው መንፈስ ንጹህ ነገር ይወዳልና ነው፡፡ [173]

በአውድማው አካባቢ በአይን የማይታይ መንፈስ አለ ብለው ስለሚያስቡ ያ መንፈስ ደግሞ እንዲቆጣ አይፈልጉም፡፡ ከተቆጣ ምርታቸውን በሆነ መንገድ እንደሚያሳጣቸው ያስባሉ፡፡ ስለዚህም ሴቷ ከተፈጥሮዋ ጋር ተያይዞ የወር አበባ ላይ ልትሆን ትችላለች፡፡ ባትሆንም እንኳ ወንዱ በሴትነቷ ሊሸነፍ ስለሚችል ወደ አውድማ እንዳትመጣ ይደረጋል፡፡

**ምርትን ከምስራቅ ወደ ምዕራብ መክፈል፡-** የተንጣረበው እህል ለመባነን ሲደርስ አውድማው ላይ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ይከፍሉታል፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ ጌታሁን እንዲህ ይገልጻሉ፡፡

> ጤፉን ታውድማው ላይ አንጣርበን ስንጨርስ አንድ ላይ ሰበስበን ቁጭ እናደርገዋለን፡፡ እየው እንግዲህ (በእጃቸው ወደ ፀሐይ

[172] ጥላ፡- ጾታዊ ግንኙነት መፈጸም ሲሆን ከጥላ አድሯል ማለት ከሴት ጋር አድሯል ማለት ነው፡፡ ይህን የፈጸመ ሰው ቢያንስ ከአምስት እስከ ሰባት ቀን መቆየት አለበት፡፡ ስለዚህ ግብርስጋ ግንኙነት የፈጸመ ሰው አውድማ እንዲገባ አይደለም ወደ አውድማው እንዲቀርብ አይፈቀድለትም፡፡

[173] አቶ አየለ አንተነህ፣ አደጋ ጓሽታ ውባጅ ቀበሌ፣ ሰባት አይና ደሽ፣ ቃለ-መጠይቅ 17/07/2007

መውጫ እያመላከቱ) ተዚህ ወደዚህ ተጀምበር መውጫ ወደ ማዘቀዘቂያዋ ለሁለት እንከፍለዋለን፡፡ ሁለት ሆነው ተግራና ተቀኝ እንዲያባንኑ ነው፡፡ የፀሐይ መውጫ የንጋቱ ማብሰሪያ ናት፡፡ መጥለቂያዋ ደግሞ የጨለማውን መንገስ የሚያሳይ ነው፡፡ እህሉም ዛሬ እንዲህ ያየሽው ሰኔ ላይ የለም፡፡ ምስራቅ ቀኝ ናት፣ የብርሃን መውጫ ናት፡፡ ብርሃኑን ስናይ ተስፋችን ይለመልማል፣ ጨለማውን አንወደውም፡፡ ተምኝታችን ስንነሳ ቀኝ አውለን እንላለን፡፡[174]

እንደ አቶ ጌታሁን ገለጻ "ምስራቅ" የሁሉ ነገር መነሻ፣ የብርሃን መውጫ፣ የንጋት፣ የተስፋ፣ የአዲስ ነገር መገኛ ምልክት ነው፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ የክርስትና እምነት ተከታዮች በመሆናቸው ምስራቅ ቀኝ ነው፡፡ ለዚህም እንደ ማሳያ ሰው ከምኝታው "በቀኝ ጎኑ" ይነሳል፡፡ በጥዋት ተነስቶ ሲታጠብ "በቀኝ አውለኝ" ይላል፡፡ የቤቱን ደፍባል[175] በምስራቅ ያደርጋል፡፡ "ምዕራብ" ደግሞ የጸሐይ መጥለቂያ፣ የጨለማው መንገሻ የመጥፎ ነገር፣ የችግር፣ የመከራ ምልክት ነው ይላሉ፡፡ ሰው ከሰው ጋር ሲጣላ፣ ስራ አልሳካለት/ አልቀናው ካለ ዛሬ በቀኝ ጎኑ አልተነሳም፣ ቀኝ አውለኝ አላለም ማለት በማህበረረሰቡ ዘንድ የተለመደ ነው፡፡ በቀኝ ጎኑ ካልተነሳ በግራው በምዕራብ ነው እንደ ማለት ነው፡፡ ከብቶቹንም ከአውድማ ሲያስወጣ በቀኝ በኩል ነው፡፡ እንዲሁም በመጨረሻው ከአውድማ ከብት የማውጣት ስርዓት ከመድረሱ በፊት ከግራ ወደኝ ይዞሩ የነበሩ ከብቶችን ከቀኝ ወደ ግራ እንዲዞሩ ይደረጋሉ፡፡

ስለዚህም ምርቱን አውድማ ላይ ለማባነን የሚከፍሉት "ከምስራቅ ወደ ምዕራብ" ነው፡፡ ይህም ምስራቅ የጸሐይ መውጫ ናት፤ ቀኝ ናት፤ የጨለማው መገፈፍ የሚታወቀው በምስራቅ በኩል የብርሃን ወገግታ ሲታይ ነው፡፡ ምዕራብ ግራ ነው፣ የምሽት፣ የጨለማ ምልክት፣ የጸሐይ መጥለቂያ፣ መሸሸጊያ ነው፡፡ ጨለማው የክረምቱ ተምሳሌት ብርሃኑ

174 አቶ ጌታሁን ብሩ፣ አግዛ ጋርዳ ቀበሌ፣ ሹምታ ደሽ ፣10/9/2007
175 ደፍባል፡- ዋና የቤት መውጫ በር/ የወንድ በር በጓዳ በር ወንድ አይወጣም በዋናው በር እንጂ ይህም ወንድ በር ይባላል፡፡

ደግሞ የበጋው ተምሳሌት ነው፡፡ እንዲሁም ከምስራቅ ደምቃ የታየችው ጸሐይ እያዘቀዘቀች… እያዘቀዘቀች.. ብርሃኗን እየቀነሰች ሄዳ የምትጠልቀው /የምትሸሸገው/ በምዕራብ በኩል ነው፡፡ ምርቱም እንደዚያው ባለበት አይቆይም እየቀነሰ፣ እየቀነሰ… ሄዶ በመጨረሻም ልክ እንደ ጸሐይ ምሽት እንደምትጠፋው በክረምት ይጠፋል/ያልቃል/፡፡ ጸሐይም በማግስቱ ትወጣለች፤ ክረምቱም አልፎ በጋው ይመጣል፤ የሕይወት ኡደቱም ሆነ የምርት ሂደቱ በዚሁ መንገድ ይቀጥላል፡፡

**ነጠላ ማልበስ፡-** ምርቱ ተጣርቶ ካበቃ በኋላ ነጠላ ይለብሳል፡፡ ይህ የሚሆንበትን አቶ ጌታሁን እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

> ምርቱን አባንንና አጥርተን ስንጨርስ ሴትዮዋ ተቤት ድግስ እህል ውሃና ኩታ ይዛ ትመጣለች፡፡ ንጹህ የሴቶች ኩታ ተዘርግቶ ምርቱ ይለብሳል፡፡ ሲሰራ የዋለ ያደረው ሰው በአውድማው ዙሪያ ይቀመጥና ሲጀመር እንደተደረገው ምረቃ አድረግን ፈጣሪያችንነ አመስግነን ተመጣው ተመጣው ድግስ ተቆሎውም ተጠላውም ታረቂውም ሰው ተመቅመሱ በፊት ታውድማው ላይ እናነጥበበታለን፡፡ ምርቱን የሚተያይው ሁሉ ተዚያ ተበሰለውና ተተነጠበው ይቋደሳል፡፡ ተዚያ ወዲያ ላምበታውን ለቤተክርስቲያን አንስቶ ሰፍሮ ይተውላታል፡፡ ሴትዮይቱ ሰፍራ ታስገባለች፡፡[176]

በዚህ ጊዜ ከቤት ተዘጋጅቶ የመጣው ቆሎ በኑግ፣ አበዚ (ፍስክ ከሆነ የቅቤ፣ የእርጎና የአይብ)፣ ጠላ፣ አረቂ  በእህሉ ዙሪያ ይሆንና ምረቃት ይከናወናል፡፡ ከዚያም ከቆሎው፣ ከጠላው ይፈስበታል /ይነጥብበታል/ ይህም በአካባቢው ያለው እህሉን የሚተያየው ነገር ሁሉ የፈሰሰው ላይ ያርፋል ወይም ከፈሰሰው ይቋደሳል፡፡ ምርቱም የማሸፈነው እሱን ትቶ ከበሰለው እንዲቋደስ ለማድረግ ነው፡፡ ከዚያም ያለው ሰው ሁሉ ከእህሉ እንዲበላ

[176] አቶ ጌታሁን ብሩ፣ አግዛ ጋርዳ ቀበሌ፣ ሹምታ ደሽ ፣ 10/07/2007

ወይም እንዲቀምስ ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም ነጠላው ከምርቱ ላይ ከተነሳ በሐዋላ ከመሰፈሩ በፊት ላምብታ ይነሳል፡፡

**ላምብታ ማንሳት፡-** በተጠኚው ማህበረሰብ ዘንድ የመጀመሪያውን ወይም ቀዳሚውን ያከብራሉ፣ (በዕድሜ፣ በችሎታ፣ ወይም በትልቅነት) ለሚያምኑት ይሰጣሉ፡፡ በዚህም መሰረት የተመረተው እህል ተሰፍሮ ወደ ቤት ከመግባቱ በፊት በመጀመሪያ ከእህሉ ላይ በግምት ወይም ተለክቶ ይነሳል፡፡ ከላይ አቶ ጌታሁን እንደገለጹት "በዘናብ አብቅሎ በፀሐይ አብስሎ ለሰጠን አምላክ" እህሉ መሰፈር ከመጀመሩ በፊት ላምብታው ይነሳል፡፡ ይህም እህል ተሸጦ እጣንና መብራት ተገዝቶ ወይም እህሉ የተሸጠበት ገንዘብ ለቤተክርስቲያን መባ /አስራት/ ይሰጣል፡፡ ገንዘቡ ለቤተክርስቲያን እስካልተሰጠ ድረስ እህሉ እቤት ቢገባም አይቀመስም፡፡ ምክንያቱም ከሁሉም በፊት ቀዳሚው የመጀመሪያውን ማግኘት ስላለበት ነው፡፡ ቀዳሚያቸውም ፈጣሪያቸው ነው፡፡ የማህበረሰቡ ቀዳሚውን ማክበር ለተከታዩ የምግባር መቅረጫ ተከታዩ ካባቶቹ ዕውቀትን ለመቅሰም በቅድሚያ ምግባሮችን ማየትና መማር ይኖርበታል፡፡ አቶ ጌታሁን ሲናገሩ ልጆቹ ከኔ መማር ያለባቸው ጥሩ ጥሩውን ነው ይላሉ፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ካሉት እሴቶች አንዱና ዋነኛው ቀዳሚውን ማክበር፡፡ ቀዳሚውን (ታላቁን) ያላከበረ ለሰውም ሆነ ለፈጣሪው ታዛዥ አይደለም ተብሎ ይታሰባል፡፡ በስራውም ውጤታማ አይደለም ይባላል፡፡ ይህ እንዳይሆን ደግሞ ሁሉም ወላጅ ልጁ የሚያስተምረው ታላቅን ማክበርንና ታዛዥ መሆንን ነው፡፡ ወላጅ ለልጁ ዕውቀት ማስተላለፍን የሚጀምረውም በዚህ መንገድ ነው፡፡ ይህም በሰዎች ዘንድ ተወዳጅነትን፣ በረከትን ምርቃትን ያስገኛል፡፡ በፈጣሪ ዘንድም እንደዚሁ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለዚህ ይህንን ምርቃት ለማግኘት ሲባል ታላቅ ወደ ቤት ሲገባ ኖሩ በማለት ተነስቶ መቀበል፣ በትሩን መቀበልና ማስቀመጥ፣ በመንገድ ቅድሚያ መስጠት፣ አቅመ ደካማን ማገዝ... ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡

ይህ ወቅት ገበሬው ከዚህ ሁሉ ልፋትና ድካም በኋላ ምርቱን አስገብቶ መጠነኛ እረፍት የሚያገኝበት እራሱን የሚያዝናናበትም ጊዜ ነው፡፡ ከህዳር 21 (ማሪያም) ጀምሮ በየአካባቢው የንግስ በአላት ስለሚኖሩና እንዲሁም የሰርግ ጊዜያቶች በመሆናቸው ይህ ወቅት ለገበሬው የደስታና የፈንጠዝያም ወቅትም ነው፡፡

በአጠቃላይ የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን መሰረት በማድረግ በዚህ ምዕራፍ በወቅቶች ተከፋፍሎ የቀረበው ተግባር ላይ በየወቅቶቹ በድግግሞሽ የሚቀርቡ ስራዎች ይታያሉ፡፡ ይሁን እንጂ በወቅቶቹ የሚቀርቡት ተግባራት የተለያዩ ከመሆናቸው በተጨማሪ የአንዳንድ ሰብሎች ማሳ ፈጽሞ የማይታረስበት ጊዜ እንዳለም ተገልጿል፡፡ ከሰብሎቹ የመዝሪያ ወቅት ጋርም ተያይዞ በተለያዩ ወቅቶች የተለያዩ ሰብሎች ስለሚዘሩ ተግባራቶቹ ሲደጋገሙ ይስተዋላል፡፡ ይህም የገበሬው ባህላዊ ዕውቀት ከተፈጥሮ ጋር ቁርኝት ያለው በመሆኑ እያንዳንዱን ተግባር የሚያከናውነው ወቅቶቹን መሰረት አድረጎ ሲሆን ይህም የህይወቱ ኡደት ከነዚሁ ወቅቶች ጋር በጥብቅ የተሳሰረ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በደጋው፣ በወይና ደጋውና በሞቃታማው የአየር ንብረት አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ለእርሻ የሚጠቀሙባቸው እንስሳት የተለያዩ መሆናቸውና በወይና ደጋውና በሞቃታማው አካባቢ የማይበቅልና በደጋማው የአየር ንብረት ብቻ የሚበቅሉ የጤፍ ዝርያዎች መኖራቸውን በጥናቱ ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ እንዲሁም ገበሬው በአዝመራ ወቅት የሚያጋጥሙትን ወይም ሊያጋጥሙ ይችላሉ ብሎ ያሰባቸውን ነገሮች ቀድሞ በባህላዊው መንገድ ለመከላከል ሲሞክር በጥናቱ ተስተውሏል፡፡

እንዲሁም ገበሬው ዘር ጊዜው ላይ ተመስርቶ ወደፊትና ወደላ አድረጎ ለመዝራት ቀድሞ የዝናብ አመጣጡን ሁኔታ ማወቅ የሚችልበት ባህላዊ መንገድ እንዳለው በዚህ ጥናት የታዩ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ሰብሉን እያፈራረቁ በመዝራትና ለከብቶች የሚሆን ሳር በማድረግም ሌላው የመሬቱን ለምነት የሚጠብቁበት የባህላዊ ግብርና እውቀታቸው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በግብርና የሚሰጠውን ዘመናዊ ማዳበሪያና ገበሬው እራሱ የሚያዘገጀውን የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ባህላዊውንና ዘመናዊውን) በመጠቀም የመሬቱን ለምነትና ምርታማነቱን አቻችሎ ሲሄድ ተስተውሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በጓሮ መሬቱ ላይ የሚጨምራቸው ባህላዊ ማደበሪያዎች እንደ እህሉ ሁኔታ የሚወሰኑ እንጂ በዘፈቀደ የሚጨምራቸው እንዳልሆኑ ጥናቱ አሳይቷል፡፡

ለዘር የሚሆኑ እህሎችን የመምረጡ ዕውቀት ከወንዶቹ ይልቅ የሴቶቹ እንደሆነ ጎልቶ ታይቷል፡፡ ዘር የማዘጋጀትና የማስቀመጡ ስራና ሃላፊነት ሙሉ ለሙሉ የሴቷ እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በሰብል ስብሰባ ወቅት የሚፈጽማቸው በርካታ የሆኑ ልማዳዊ እምነቶች አሉት፡፡ እነዚህም የከብት ምርቃት፣ ከአውድማ ቁሳቁሶች ጋር የተያያዙ፣ በአውድማ ወቅት የአባወራ ውኃ ያለመንካት፣ ለአቅመ ሂዋን የደረሰች ሴት አውድማ ያለመግባት፣ ምርትን ከምስራቅ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ መክፈል፣ ምርቱን ነጠላ ማልበስ፣ ላምብታ ማንሳት የመሳሰሉት ልማዶችን እንዴትና ለምን እንደሚፈጸሙ ለማየት ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# የባህላዊ ግብርና ዕውቀት አይነቶችና የዕውቀት ተስተላልፎ

ይህ ምዕራፍ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል የባህላዊ ግብርና ዕውቀት አይነቶች ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ተስተላልፏዊ መንገድ ነው፡፡

## 6.1. የባህላዊ ግብርና ዕውቀት አይነቶች

የባህላዊ ዕውቀት በሁለት ይከፈላል፡፡ ይህም የመጀመሪያው በውርስ የሚገኘውና ሁለተኛው ደግሞ በልምድ የሚዳብር የግብርና ዕውቀት ነው፡፡[177] በዚህ ጥናት የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ግን በመሰረታዊነት በሶስት እንደሚከፈል ለማየት ችያለሁ፡፡

ከላይ ተብራርቶ እንደቀረበው የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ሶስት አይነት ናቸው፡፡ እነሱም በውርስ የሚገኘው **የማህበረሰብ** የባህላዊ ግብርና ዕውቀት፣ በግል ጥረት፣ በጥልቅ ምልከታና ትርጓሜ የሚመሰረተው **የቡድን** የባህላዊ ግብርና ዕውቀት እና **የግለሰብ** የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ናቸው፡፡ እነዚህም አንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

177 Brosius et.al (1986:187) broadly speaking, such indigenous knowledge falls into two categories. On the one hand, there is knowledge that is inherited from generation **to** generation and is generally shared by most of the members of the society. This cultural information is often passed on as folk wisdom in the context of folktales or is preserved and transmitted in the context of rituals and various religious ceremonies.The second category includes information gained through individual experience-empirical observations made by individual farmers during the course of agricultural activities. The two categories of indigenous knowledge are not mutually exclusive. Information collected by an individual may become knowledge that is shared by members of the group through time. The larger pattern of shared social knowledge also provides a contextual framework in which an individual's empirical observations can be interpreted and translated into knowledge.

### 6.1.1. የማህበረሰብ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት

የመጀመሪያው የማህበረሰብ ዕውቀት ነው፡፡ በአንድ አካባቢ የሚኖር ማህበረሰብ የጋራ የሆኑ በርካታ እሴቶች ባለቤት ነው፡፡ ይህ የጋራ የሆነ እሴትም ማህበረሰቡን በአንድ አስተሳስሮ ያኖረ ክር ነው፡፡ ይህ ክር ደግሞ ጥብቅ ቁርኝትን ፈጥሮ እስካሁን ያዘለቀው አካባቢው፣ ባህሉና ዕውቀት ነው፡፡ ይህ ክር በምንም መንገድ ሊበጠስ ወይም ሊቋረጥ የማይችል ነው፡፡ ይህ ቁርኝት ከአሁን በፊት የነበረ ያለና ወደፊትም የሚቀጥል ነው፡፡ ትውልድ አልፎ ትውልድ በተተካ ቁጥር ይህ በውርስ የሚገኘው ባህላዊ የግብርና ዕውቀት እንደ ሰንሰለት እየተያያዘና ትውልድን እያስተሳሰረ ይቀጥላል፡፡ ይህ ዕውቀት በሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ዘንድ ያለና የሚታወቅ ዕውቀት ነው፡፡

ይህ የጋራ የሆነው ዕውቀት በተለያየ መንገድ ይገለጻል፡፡ ለምሳሌም በእርሻ መሳሪያው፣ በአስተራረስ ዘዴው፣ በማዳበሪያ አጠቃቀሙ፣ የተፈጥሮ ሃብት አጠባበቁ፣ የመስኖ ውኃ አጠቃቀሙ፣... ብንመለከት በተመሳሳይ መንገድ የሚከወኑ ድርጊቶች ናቸው፡፡

ይህ የማህበረሰብ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ማህበረሰቡ በጋራ የሚጠቀምበት ዕውቀት ነው፡፡ ዕውቀት ከአያት ቅድመ አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ በመሆኑ ሁሉም በተመሳሳይ መንገድ ይጠቀምበታል፡፡ በመሆኑም በሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ዘንድ የተለመደና የታወቀ ዕውቀት ነው፡፡ ማህበረሰቡ በጋራ ወይም በግል በሁሉም ቦታ በተመሳሳይ መንገድ የሚተገብሩት እና ሁሉም በጋራ የሚያውቁት የዕውቀት አይነት ነው፡፡

የባህላዊ ግብርና ዕውቀት በረጅም ዘመናት ጊዜና ትውልድ የተለመደና አሁንም ድረስ እየተተገበረ ያለ የማህበረሰብ ዕውቀት ነው፡፡ የአካባቢውን የአየር ጠባይ መሰረት አድርገው የሚበቅሉት የእህል አይነቶች አሁን ላይ የተፈጠሩ ወይም የተገኙ ሳይሆኑ ከጥንት ጀምሮ በዚያው አካባቢ ሲዘሩና ሲበቅሉ የነበሩና አሁንም እየተጠቀሟቸው ያሉ ናቸው፡፡ እንዲሁም የሰብል አይነቱን መሰረት ያደረገ የማሳ ዝግጅትና የመዝሪያ ጊዜው ወጥ የሆነ ነው፡፡ በሞቃታማው አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ ጤፍን ከሐምሌ 5 እስከ

ሐምሌ 15 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ የሚዘራ ሲሆን በደጋማው አካባቢ ደግሞ እነ ቢመሾ በነሐሴ መጨረሻ ተዘርተው ከሌላው እኩል የሚደርሱ የጤፍ አይነቶች ናቸው፡፡ ይህም የማህበረሰቡ አካል የሚተገብረው ሆኖ እንደ አየር ንብረቱና እንደእህሉ የመዘሪያ ጊዜያቸው ይለያያል፡፡

ሌላው ውኃ ባለበት አካባቢ ድንች በበጋ ሁለት ጊዜና በክረምት አንድ ጊዜ በጠቅላላው ሶስት ጊዜ ይመረታል፡፡ ውኃ በሌለበት አካባቢ ደግሞ በግቢው (በመጋቢት)ና በክረምቱ (በሐምሌ) ሁለት ጊዜ ይዘራሉ (ላልቶ ሲነበብ)፡፡ የማሳ የዝግጅት ጊዜውና ሰብሎችን የመዝሪያ ጊዜው የበሬ እቃዎች እርሻ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን እየተሰራባቸው ያሉ ናቸው፡፡ እነዚህ እውቀቶች ባጠቃላይ የማህበረሰቡ ሃብቶች ናቸው፡፡ ባጠቃላይ የማህበረሰቡ ባህላዊ የግብርና ዕውቀት በውርስ ያገኘው ሆኖ እንደ አካባቢውና እንደ ሁኔታው ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት የሚቀበሉት፣ የሚከውኑትና የሚጠቀሙበት የዕውቀት አይነት ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥም የተለያየ ቡድን አለ፡፡

### 6.1.2. የቡድን ዕውቀት

ሁለተኛው የቡድን ዕውቀት ነው፡፡ ይህ ዕውቀት የተከፋፈለ (የጥቂት ሰዎች) ተመሳሳይ ሙያ ባላቸው እና ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች የተያዘ ዕውቀት ነው፡፡

ይህ ዕውቀት በሁሉም የማህበረሰቡ አባላት የተያዘ ዕውቀት ሳይሆን ከማህበረሰቡ መካከል በሚኖሩ የተወሰኑ ሰዎች ብቻ የተያዘ ዕውቀት ነው፡፡ የቡድን ዕውቀት ከግለሰብ ግለሰብ እንደሚለያይ ሁሉ ከቡድን ቡድን በዕድሜ፣ በጾታ፣ በመደብ፣ በስራ/በሙያ ወዘተ. ይለያል፡፡ በቡድን ውስጥ ከሁለት እስከ ብዙ ቁጥር ድረስ አባላት ሊኖር ይችላል፡፡ ቡድን ከቤተሰብ ሊነሳም ይችላል፡፡ የቡድን ዕውቀት ሲባል በጋራ የሚሰራ ሳይሆን ተመሳሳይ ሙያ ወይም ዕውቀት ያላቸው በተለያየ አከባቢና ቦታ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የቡድን እውቀቶች በተለያየ መንገድ ሊገለጹ ይችላሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የባህላዊ የእርሻ መሳሪያዎች የማረቅ ዕውቀት፣ የቆዳ ስራ ዕውቀት፣

የብረታ ብረት ስራ ዕውቀት... ናቸው፡፡ እነዚህ የዕውቀት ባለቤቶች ለባህላዊ ግብርና እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎች ናቸው፡፡

የባህላዊ ግብርና ዕውቀት የማህበረሰብ ዕውቀትነቱ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ሲፈተሽና ሲረጋገጥ መሆኑ የፎክሎር ዘርፍነቱን ያመላክታል፡፡ እነዚህን በቡድን የተፈጠሩ እውቀቶችን ማህበረሰቡ ፈትሾ ካላጸደቃቸው በስተቀር ተግባራዊ አይሆኑም፡፡ ወይም ደግሞ የማህበረሰብ ዕውቀት መሆን አይችሉም፡፡ የፎክሎር አፍላቂው፣ አድናቂውና አጽዳቂው ማህበረሰቡ ነው፡፡ ዕውቀት ግለሰቡ በራሱ የሚፈጥረው የተባይ መከላከያ፣ የዘር አያያዝ፣ የማዳበሪያ አጠቃቀም... ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ዕውቀት ካልተረጋገጠ በስተቀር ወደተግባር ሊገባ አይችልም፡፡

## 6.1.3. የግለሰብ ዕውቀት

ሶስተኛው ደግሞ የግለሰብ ዕውቀት ነው፡፡ ማንም የማህበረሰቡ አባል ተጽእኖ ሳያሳድርበት ግለሰቡ በራሱ የሚፈጥረው ዕውቀት ነው፤ ይህም በግለሰብ የተያዘ ዕውቀት ነው፡፡ ግለሰቡ በራሱ ጥረት በጥልቅ ምልከታ እና ትርጓሜ የሚፈጥረው ዕውቀት ነው፡፡ የግለሰብ ዕውቀት እያንዳንዱ ግለሰብ፣ የማህበረሰቡም ሆነ የቡድን አባል ነው፡፡ ምክንያቱም እንደ ማህበረሰብ አባልነቱ በውርስ ያገኘው ዕውቀት ባለቤት ነው፤ እንደ ሙያው ሁኔታ ደግሞ የቡድን አባል ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም መሰረት ግለሰቡ ከማህበረሰቡ ያገኘውን ዕውቀት መነሻ በማድረግ በካባቢው የሚያየውንና የሚመለከተውን እንዲሁም በተለያየ ጊዜ በተፈጥሮ የሚከሰተውን ሁሉ ባንድ ላይ በማጣመር ከልምዱና ከሕይወት ተሞክሮው በመነሳት ለሚያየው ነገር ሁሉ ትርጉም ይሰጣል፤ ለእያንዳንዱ ነገር መከላከያና ማለፊያ መንገድ ያበጅለታል፡፡

ገበሬው በራሱ ተለምዶ ያዳበራቸው በርካታ እውቀቶች ባለቤት ነው፡፡ ለዚህም የእህል ዘሮችን በማየት በማዳበሪያ የበቀለ መሆኑን አለመሆኑን የሚለዩበት የየራሳቸው መንገድ አላቸው፡፡ አንድ ስማቸውን መግለጽ ያልፈለጉ አባት የሚከተለውን ብለዋል፡-

መረጃ አቀባዬ ከሆኑት አንዱ በሁለት እጃቸው ጤፍ በመያዝ እስኪ የትኛው ነው በማዳበሪያ የበቀለው በማለት ጠየቁኝ፡፡ እኔም አላውቅም ብዬ መለስሁላቸው፡፡ አሳቸውም መሬት ላይ ሁለቱንም ጤፍ በድንጋይ መቱት፣ አንደኛው ጤፍ ብን ብሎ ዱቄት ሲሆን ሁለተኛው ጤፍ ጠንካራ በመሆኑ በአንድ ጊዜ ሊበተን/ ዱቄት ሊሆን አልቻለም፡፡ ምክንያቱን ሲነግሩኝ ቶሎ ደቄት የሆነው በመንግስቱ ማዳበሪያ የበቀለው ሲሆን ጠንካራው ደግሞ ያለማዳበሪያ የበቀለ ነው አሉኝ፡፡ በእንጀራውም ቢሆን በማደበሪያ የበቀለ አንድ ኩንታል ጤፍ ከ400 እስከ 600[178] እንጀራ ሲሆን ፣ ካለማዳበሪያ የበቀለው ደግሞ ከ600 እስከ 800 ድረስ ይሆናል፡፡ ምርቱ ሲታይ የማዳበሪያው ይበልጣል ግን ውኃ እሚባል አያነሳም፡፡[179]

ከላይ በቀረበው ሃሳብ መሰረትነት ገበሬው ይህንን የሁለቱን እህል በሳይንሳዊ ማዳበሪያ የበቀለውንና ያለማደበሪያ የበቀለውን የለዩበት መንገድ ደመነፈሳዊ አይደለም፡፡ በተግባር ሞክረውና ፈትሸው ያገኙት በመሆኑ በማዳበሪያ እና ያለ ማዳበሪያ የበቀለው ጤፍ በእንጀራ ላይ የሚያመጣውን ልዩነት ይናገራሉ፡፡ ገበሬው እንዲህ አይነቱን ተግባር ሲያከናውን አካባቢውን፣ ተፈጥሮንና ባህሉን ሳይጥስ አውዱን መሰረት አድርጎ መረጃዎችን በመተንተንና በተርጎም ነው፡፡ ከአውዱ ካፈነገጠና ባህሉን ከጣሰ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ መናቅ፣ መወገዝ ብሎም መገለል ይደርስበታል፡፡ ይህ እንዳይሆን በማህበረሰቡ የተደነገጉ ባህላዊ ህግጋቶች እንደበዓላትን መሻር (በማይታረስበት ቀን ማረስ፣ መቆፈር) ታላቅን አለማክበር (የሚሉትን አለመተግበር) በደስታና በሀዘን ቦታዎች አለመገኘት) በሽምግልና ቦታ አለመገኘት፣ ድንበር መግፋት፣ መስረቅ…ናቸው፡፡ ይህ እንዳይሆን በማህበረሰቡ የተደነገጉ ህግጋቶቹንና ደንቦቹን ጠብቆ፣ ነውር የተባሉትን ከእሱ አርቆ አውዱን መሰረት በማድረግ የራሱን የፈጠራ ስራ ከልምዱ ተነስቶ ይፈጥራል፡፡

178 የእንጀራው መጠን የሚለካው በምጣዱ አይነት ነው፡፡ ዝቅተኛው ቁጥር በቤት ምጣድ ሲሆን ከፍተኛው ቁጥር ደግሞ ለድርጅት በሚሆኑ/ ለገበያ የሚቀርቡ እና በአነስተኛ ምጣድ የሚጋገር

179 ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ፡ አደጋ ጓሽታ ውባጅ ቀበሌ፣ ሰባት አይና ደሽ፣ ቃለ-መጠይቅ 22/06/07)፡፡

አብዛኞቹ የተደነገጉ ህግጋቶች የማህበረሰቡን ወግና ባህል የሚደግፉና የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡ በደስታ ቦታ፣ በሽምግልና ቦታ፣ መገኘት አንድ የሃሳብ መለዋወጫ መንገዶች በመሆናቸው የዕውቀት ማስተላለፊያ መንገዶች ናቸው፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ ሽመካ ሲናገሩ፡-

> ያው በዓላት ሲሆኑ በማይታረስበትና ስራ በማይሰራበት ቀን ወይሽምግልና ይኖርል፣ ወይ ልቅሶ ይኖራል፡፡ ተዚያ መልስ ተድንበር ቁጭ ብለን ስለግብርናው፣ ስለጠጥታው፣ ስለልማቱ... እናወራለን፡፡ የሞተን የማይቀብር፣ መገኘት ባለበት ቦታ የማይገኝ ተሆነ ተብዙ ነገር ይገለላል፡፡ ተነዚህ ቦታዎች ብዙ እናወራለን፡፡ ብዙ ቁምነገር እንጨብጣለን፡፡ እገሌ ይህን አደረገ ሲባል እንዴት አደረገው? መቼ ነው? ለምን ሰራው?... ብለን እናወራለን፡፡ ስለ ስራችን እንነጋገራለን፡፡ በሱ ብዙ ብዙ አውርተን እሽሽ... ብለን ያንን ሁላችንም በልባችን ይዘን እንሽዳለን፡፡ ብዙ ቁምነገርም እናወራለን፣ እንጨዋወታለን፡፡[180]


እንደ አቶ ሽመካ ገለጻ ሀይማኖታዊ በዓላትን ሲያከብሩ ስራን አይሰሩም፡፡ በዚህ ወቅትም በጋራ ወይም በቡድን በመሆን ስላገኙት ልምድና ዕውቀት ሀሳባቸውን ያስተላልፉበታል፡፡ እነዚህ ህግጋቶችና ደንቦችን ማክበር በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖር ከማድረጋቸውም በተጨማሪ ባህላዊ ዕውቀትን ለመፍጠርም ሆነ ለማስተላለፍ የሚረዱ ዋና መንገዶች ናቸው፡፡

ይህንንም ዕውቀት ሲፈጥር በደመንፈስ ሳይሆን ካየውና ከሰማው በመነሳት አዲስ ሃሳብ ይፈጥራል፣ የፈጠረውንም ሀሳባዊ ዕውቀት ደጋግሞ ይሞክራል፣ ይፈትሻል፡፡ በዚህ መንገድ የሚፈጠረው ዕውቀት ከግለሰብ እስከ ማህበረሰብ ድረስ በተለያዩ አጋጣሚዎችና መንገዶች ይተላለፋል፡፡

---

[180] አቶ ሽመካ ገዳሙ፣ አደጋ ውባጅ ቀበሌ፣ መስቀለኛ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 24/6/2007፡፡

## 6.2. የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ተስተላልፎ




ምስል 1፡-የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ተስተላልፎ ሞዴል[181]

በሞዴሉ ላይ ለማየት እንደተሞከረው በአንድ ሰፊ ክብ ውስጥ መጠናቸው የተለያዩ ሶስት ክቦች ይታያሉ፡፡ እነዚህ ክቦች የየራሳቸው የሆነ ውክልና አላቸው፡፡ ከላይ በተራ ቁጥር 6.1. የተገለጹት የዕውቀት አይነቶች በነዚህ በእያንዳንዱ ክብ ተወክለዋል፡፡ ክቦችም የየራሳቸው የሆነ ትርጉም ተሰጥቷቸዋል፤ ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ተስተላልፎ ሞዴልን ምንነት በዝርዝር ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡

181 ካነበብሁትና አንጋፋ መረጃ አቀባቹ ከሰጡኝ በመነሳት እኔ እረሴ የሰራሁት ሞዴል

**አውድ፡-** ሁሉን ክቦች አቅፎ የያዘው ሰማያዊ ቀለም ያለው ክብ፣ አውድ ነው፡፡ አውድ የሁሉ ነገር መነሻ ነው፡፡ የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን ለማፍለቅም ሆነ ለማስተላለፍ አውድ መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ አውድ ሲባል ተፈጥሮን፣ አካባቢን፣ ሰውን፣ እጽዋትን፣ እንስሳትን... ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡ አውድ የአንድ የፎክሎር ዘር የተገኘበት ቦታ፣ የተከወነበት ጊዜ፣ ባህላዊ ና ማሕበራዊ ሁኔታና አጠቃላይ ድባቡ እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ይገልፃሉ (Sims and Stephens; 2005, Catherina, Bell; 1997, Ben-Amos; 1975)፡፡ በመሆኑም ለባህላዊ ግብርና ዕውቀት መፈጠርም ሆነ መኖር ወሳኝ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ስለዚህም ገበሬው በአውድ ላይ ሆኖ አዳዲስ የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን ያመነጫል/ይፈጥራል፡፡ ያን የፈጠረውን ዕውቀት ደግሞ ለሰዎች ለማስተላለፍ አውድ ያስፈልገዋል፡፡ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ተግባራዊነትም አውድ ላይ ይሞከራል፤ ይፈትሻል፡፡ ስለዚህ ባህላዊ ግብርና ዕውቀት ከአውድ ይነሳል/ ይመነጫል ተመልሶ አውድ ላይ ያርፋል፡፡ ምክንያቱም አውድ ሁሉም ነገር ነው፡፡

**የማህበረሰብ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት፡-** ይህ ዕውቀት በውርስ እንደሚተላለፍ በምዕራፍ ሁለት ስር ተጠቅሷል፡፡ በሞዴሉ ውስጥ በመጠኑ አነስ ብሎ በአውዱ ውስጥ የሚገኘው አረንጓዴ ቀለም ያለውና በውስጡም መጠናቸው የተለያዩ ሁለት ክቦችን የያዘው ክብ የማህበረሰብ የባህላዊ ግብርና ዕውቀትን እንዲወክል ሆኖ የቀረበ ነው፡፡ ቡድንና ግለሰብ በማህበረሰብ ውስጥ ያሉና የማህበረሰቡ አካል መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ ይህ በውርስ የሚገኘው ዕውቀትም ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት የሚጠቀሙበት የጋራ የሆነ ዕውቀት ነው፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የእርሻ መሳሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም ነው፡፡ ይህ የእርሻ መሳሪያ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣና የማህበረሰቡ አካል የሆነ ሁሉ ሳይጠራጠርና ሳይፈራ የሚጠቀምበት ነው፡፡ ይህ የማህበረሰብ ዕውቀትም በተለያዩ የድርጊቱ መከወኛ አውዶች በስነቃሎች፣ በተረኮች፣ በተረቶች፣...በቃል በመንገር በልማዶች፣ በእምነቶች፣... በተግባር በማሳየትና ከትውልድ ትውልድ እስካሁን ድረስ በልምድ ሲተላለፍ የቆየና ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ነው፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ አየለ ሲናገሩ፡-

ገና ኮመቻ ነኝ የናቴ ብርቅ ነኝ ከብት ጠብቅ፣ በግ ጠብቅ ሲሉኝ ሽጂ ያንዱን እርፍ ለቀም አቁሞት ያለውን፣ ያንም አባባ እስቲ ልረስ ልቀቀውማ! ታለቀቀው ልብ አይሆነኝም! ስሄድ በፌሰሱ ስወድቅ፣ ለመድሁት ኋላ እነሱ ተጥላ ላይ ሆነው ቀን እስተ ቀን ያሳርሱኛል፡፡ ዝም ብዬ የማንም ሳርስ ለመድሁት በልጅነቴ የስምንት ዓመት ልጅ ብሆን ነው፣ ኋላ ኋላ ግን እንዲህ አርገው፣ እንዲህ አይሆንም እየተባልሁ ለመድሁት ይላሉ፡፡[182]

እንደ አቶ አየለ ገለጻ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ተስተላልፎ በቃል በመንገርና በድርጊት በማሳየት የሚለመድ በመሆኑ አቶ አየለ በልጅነት ዕድሜያቸው በራሳቸው ጥረት ሰዎች ሲያርሱ የሚያደርጉትን በመመልከትና በመተግበር፣ የሚሉትን በትኩረት በማዳመጥ ነው የእርሻ ስራን የለመዱት፡፡ አቶ አያና ደግሞ "የአያት የቅድመ አያታችን ልምድ ሆኖ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው፣ አባቶቻችን ሲያርሱ እንረስ እንላለን፣ በዚያው መንገድ ካባቴ ተማርሁት፣ አሁንም ልጆቼን ሳስተምር እርሻ ቦታ ይመጣሉ በሉ እንደዚህ አርጋችሁ እረሱ እያልሁ ማረሻው ሲዘል ብድግ እያደረግሁ፣ እያወጣሁ፣ አይዟችሁ እያልሁ፣ እየተከተልሁ አስተማርኋቸው በማለት ይገልጻሉ፡፡"[183]

የማህበረሰቡ አካል የሆነ ሁሉ የግብርና ሙያን ከማን ተማርኸው ተብሎ ሲጠየቅ የሚሰጠው ምላሽ ከአባቴ የሚል ሲሆን እንዴት ተማርኸው ሲባልም አባቴን፣ ታላቅ ወንድሜን፣ ከብት ስጠብቅ... እነ እገሌ ሲያርሱ አይቼ ተማርሁት የሚል ምላሽ ይሰጣል፡፡ ይህም የዕውቀት ተስተላልፎ በቃልና በድርጊት በልምድ የሚተላለፍ መሆኑን የሚያመላክት ሲሆን የማህበረሰብ ዕውቀት ሁሉም የሚያውቀው የወል ሀብት ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥም የተለያየ ዕውቀትና ችሎታ ያላቸው ቡድኖች ይኖራሉ፡፡

**የቡድን ዕውቀት፡-** ቡድን ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች ይመሰረታል፡፡ አንድ ቤተሰብ አንድ ቡድን ሊሆን ይችላል፡፡ ከላይ ያለው በሁለት ክቦች ውስጥ ያለ የቡድን ዕውቀት

182 አቶ አየለ አንተነህ፣ አዴጋ ውባጅ ቀበሌ፣ ሰባት አይና ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 27/07/2007
183 አቶ አያና አለማየሁ፣ አግዛ ጋርዳ ቀበሌ፣ ሹምታ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 29/11/ 2007

በውስጡ የግለሰብ ዕውቀትን ይዟል፡፡ ይህ ክብ ከማህበረሰብ ክብ በመጠኑ አነስ ከግለሰብ ደግሞ ሰፋ ያለ ነው፡፡ በውስጡም ብዙ ግለሰቦችንና ቡድኖችን የያዘ ነው፡፡ ቡድኖቹ እንደየ እውቀታቸውና እንደየ ሙያቸው አይነት ቁጥራቸው ብዙ ወይም ትንሽ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ቡድኑን የሚፈጥሩትም የተለያየ ዕውቀትና ችሎታ ያላቸው ግለሰቦች ናቸው፡፡ ይህ ቡድንም ተመሳሳይ ሙያ ያላቸው ግለሰቦችን ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ለምሳሌ የባህላዊ ግብርና መሳሪያ የሆነውን ሞፈርና ቀንበር የሚያርቁ ሰዎች፣ ማረሻን የሚሰሩ ሰዎች፣ ምራንን ከቆዳ የሚሰሩ ሰዎች... ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የቡድኑ አባላት የሚቀበሉት ዕውቀት ተመሳሳይ ቢሆንም እንደ አቀባበላቸው ከግለሰብ ግለሰብ ግን ልዩነት ሊኖር ይችላል፡፡

በተጠኚ ማህበረሰቡ ውስጥ የተለያየ ሙያ ባለቤት ቡድኖች አሉ፡፡ ይህን በተመለከተ ቄስ ወርቁ ሲገልጹ፡-

> ሁሉም ገበሬ አንድ አይነት ችሎታ የለውም፡፡ አፈጣጠራችንስ ለየቅል አይደል? የአንድ እናት ልጆች እንኳን አንድ አደሉም፡፡ አንዳንዱ የሰማውን፣ ያየውን ቶሎ ይይዛል፡፡ አሁን በዚህ በኛ አካባቢ ሁሉም ገበሬ ሞፈር አይቀድም፡፡ አሉ በዚህ የታወቁ፡፡ እርፍን እንኳ ማንም የሚሰራት ናት፡፡ ሞፈርና ቀንበር ግን ባለሙያን ይፈልጋል፡፡ እንኳን ሞፈርና ቀንበር ቀላሉን ጅራፍ መፍተል እንኳን ታለሙያ አይሆንም፡፡ እንደገመድ አይፈተልም፡፡ ይኸው ነው ሁሉም ሙያን ይጠይቃል፡፡ ምራን የሚሰሩ የቆዳ ሰራተኞች አሉ፡፡ ሞፈር ቀንበርን አራቂዎች አሉ፡፡ ማረሻንና ወገልን የሚሰሩ፣ እንኳን ሌላ በየጊዜው ማረሻን የሚስሉልን ባለሙያዎች አሉ፡፡ እነዚህን በፊርጃቸው አስቀምጦ ማየት ነው፡፡ ማረሻ የሚሰራው ሁሉ አንድ አይደለም፡፡ ተከሌ እከሌ ይሻላል ብለን እንመርጣለን፡፡ እኔ እንዲሰራልኝ የምፈልገውን ሌላው አይፈልገው ይሆናል፡፡ ተኔ ፍላጎት ጋር

የሚስማማውን መርጬ እሸጻለሁ፡፡ ሌላውም እንደዚያው ነው የሚያደርገው፡፡ ግን በሙያቸው የሚከበሩና ሙያቸውን የሚያስከብሩ ቆፍጣኖች አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች እንደኛው ገበሬዎች ናቸው፡፡ ያርሳሉ፣ ይዘራሉ፣ ያመርታሉ፡፡[184]

እንደ ቄስ ወርቁ ገለጻ ለግብርና ስራ አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን የሚያሟሉ የተለያየ ዕውቀት ባለቤት የሆኑ ገበሬዎች በመካከላቸው አሉ፡፡ ይህም የልዩ ሙያ ባለቤትነታቸው ነው፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች እንደየ ሙያቸው የቡድን ዕውቀት አላቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቡድን ዕውቀት በተለያየ ሁኔታ ሊንጸባረቅ /ሊከሰት ይችላል፡፡

እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖሩ የተለያየ የሙያ ዕውቀት ያላቸው ቡድኖችም አሉ፡፡ እነዚህ የተለያየ ሙያ ባለቤት የሆኑት ቡድኖች ከባህላዊ ግብርና ዕውቀት ጋር የጠበቀ ቁርኝት አላቸው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ የቡድን አካላት ይህንን የቡድን ዕውቀት የሚተገብሩት ከግብርናው ጎን ለጎን በተለይም የእርሻ ስራ በማይከናወንበትና የእጅ ስራ[185] በሆኑት ቀናቶች ነው፡፡ ለምሳሌ ማረሻ፣ ወገልና መኮትኮቻ የሚሰሩት፣ ምራን የሚሰሩት ቆዳ በማለስለስ ስራ የተሰማሩት፣ ሞፈርና ቀንበርን የሚያርቁ የሙያ ባለቤቶች የማህበረሰቡ አባል የሆኑና ገበሬዎች ናቸው፡፡ እንደ ገበሬነታቸው አራሾች ናቸው፡፡ የተጨማሪ ዕውቀት ባለሙያዎችም ናቸው፡፡ በዚህ ተጨማሪ የሙያ ባለቤትነታቸው ከገበሬው ጋር ከእርሻው ባለፈ የሚያስተሳስራቸውና የሚያቀራኛቸው ነገር አለ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ባለሙያዎች የተጨማሪ ሙያ ባለቤቶች በመሆናቸው በየሙያቸው አግባብነት ቡድን በሚል ሊከፈሉ ችለዋል፡፡

እውቀታቸውም ከቡድን ቡድን ይለያያል፣ ምክንያቱም መሰረት የሚያደርገው የቡድኑን ዕውቀት በመሆኑ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ አለማየሁ "ማረሻና ወገል ለማሰራት

---

[184] ቄስ ወርቁ ወልደ ጊዮርጊስ፣ አግዛጋርዳ ኤሊያስ ቀበሌ ፣ ስሚዞ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 29/07/2007

[185] እርሻ የማይታረስባቸው ነገር ግን አረም ፣ ኩትኳቶና አጨዳን… የማይከለክሉ የበዓላት ቀናት የእጅ ስራ ይባላሉ

ስንፈልግ ብረቴዎች ዘንድ፣ ኮር ስንፈልግ ቆዳ ፋቂዎች ዘንድ፤ ሞፈር ቀንበር ስንፈልግ አራቂዎች ዘንድ እንሄዳለን፤ እነሱም ታለኛ እኛም ታለነሱ ነገሩ ሁሉ አጓጉል ነው" ይላሉ፡፡[186] እነዚህ የሙያ ባለቤቶች እንደ ገበሬነታቸው አራሾች ናቸው፡፡ የተጨማሪ ዕውቀት ባለሙያዎችም ናቸው፡፡ በዚህ ተጨማሪ የሙያ ባለቤትነታቸው ከገበሬው ጋር ከእርሻው ባለፈ የሚያስተሳስራቸውና የሚያቆራኛቸው ነው፡፡

ይህም በባህላዊ ግብርና ዕውቀት ምክንያት አንዱ ቡድን ከሌላው ቡድን የሚጋራው ዕውቀትና ችሎታ መኖሩንና ቡድኖችም እርስ በራሳቸው የዕውቀት ትስስር ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ማረሻ የሚሰራ ሰው ሞፈርና ቀንበር አራቂ ያስፈልገዋል፡፡ ምራንም የሚሰራው ሞፈርና ቀንበር አራቂ፣ ማረሻ የሚሰራ ያስፈልገዋል፡፡ ሁሉም እንደ ሀረግ የተሳሰረ ነው፡፡ ይህም ትስስርም በቡድኖች መካካል ያለውን የዕውቀት ተያያዥነት ያመላክታል፡፡ እያንዳንዱ ቡድንም መሰረት የሚያደርገው ሙያዊ ዕውቀቱን ይሆናል፡፡ ይህ የቡድን ዕውቀትም በመሰረታዊነት ከግለሰብ ዕውቀት ይነሳል፡፡

**የግለሰብ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት፡-** በሁሉም ክቦች መሃል የሚገኝ በመጠኑ አነስ ያለ ክብ ነው፡፡ ይህ ክብ የግለሰብን ዕውቀት የሚያመላክት ነው፡፡ ግለሰብ፣ በቡድን ብሎም በማህበረሰብ ውስጥ ይገኛል፡፡ በምዕራፍ አምስት ላይ እንደተመለከትነው ዛሬ ላይ የቡድን ዕውቀት ብሎም የማህበረሰብ ዕውቀት ሊሆን የቻለውን የማሽላ የተባይ ማጥፊያና ባህላዊ ማዳበሪያ ብስባሽ አዘገጃጀትን ብንመለከት መጀመሪያ በግለሰቦች የተፈጠረ ነው፡፡

ግለሰብ በራሱ ጥረት ባካባቢው ካየውና በትኩረት ከተመለከተው፣ በራሱ ላይ ከደረሰው መጥፎም ሆነ ጥሩ ነገር፣ ባጠቃላይ ከሕይወት ተሞክሮው ተነስቶ አዲስ ነገር ይፈጥራል፤ ያፈልቃል፡፡ ይህንም በተግባር ይሞክራል፤ ትክክለኛ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በተግባር ፈትኖ ውጤቱን ሳያይ ግን ለማንም ትንፍሽ አይልም፡፡

[186] አቶ አለማየሁ ምትክ፣ አብስላ ሰሙኤል ቀበሌ፣ ዳምቢሲ ደሽ፣ ቃለ መጠይቅ የተደረገበት ቀን፡ 24/06/2007

ምክንያቱም ባይሳካ ያገር መሳቂያ መሆንን አይፈልገውም፡፡ ይህንንም በዘር አጠባበቅ፣ በጓሮ መሬት አያያዝ፣ በተባይ መከላከያ፣ በእርሻ መሳሪያ አዘገጃጀት… ይተገብረዋል፡፡ ተግባራዊነቱን ሲያረጋግጥ ለጓደኛ፣ ለጎረቤት ያወራል፣ ያሣያል፡፡ ይህ ሃሳብ አቶ ጌታሁን እንዲህ በማለት ያጠናክሩታል፦

> በዚህ በአካባቢያችን ቀበሌ ያለ አንድ ወጣት ማሽላውን ነቀዝ እየበላች አስቸገረችው፡፡ ተግብርና የሚመጣው መድሃኒትም ቢሆን ብዙም አላጠፋትም ማሽላውን ዱቀት እያረገች አስቸገረች፡፡ ታዲያ ይኼ ልጅ አረቄውን ተውኃ ጋር ባንዱ ማዳበሪያ ኬሻ ማሽላ ደባልቆ አሸና አስቀመጠ ልክ በሰባት ወሩ ቢያየው አንዲት ፍሬ እንኳን አልተበላችም፣ ተዚያ ወዲያ እሱ ነገረን፣ መጀመሪያ ማንም አላመነውም ነበር ኋላ ግን አንድ ሲል ሁለት ሲል መጠቀም ጀመረ አሁን እንኳ ሁላው ገበሬ ገብቶበታል፡፡[187]

ግለሰቡ እንዲህ አይነቱን ተግባርም ሲያከናውን ሰባት ወር ሙሉ ለማንም ሳይነግር በግሉ በሚስጥር ይዞ ነው፡፡ ምናልባትም የጀመረው ሃሰብ፣ ስራ እውን ሳይሆንና ሳይሳካ ቢቀር በማህበረሰቡ ዘንድ ይናቃል፣ መዘባበቻና ጣት መቀሰሪያም ይሆናል፡፡ እንደ እገሌ እንዳትሆኑ እየተባለም ይተረትበታል፡፡ "የሰው ማስጠንቀቂያ የመዝጊያ ማጥበቂያ" መሆንን ስለማይፈልገው በብርቱ ይጠነቀቃል፡፡

ይህ ዕውቀት የሰብል ተባይ መከላከያ፣ የተፈጥሮ ማዳበሪያ አዘገጃጀት፣ የዘር አጠባበቅ፣ የእንስሳት በሽታ መድሃኒት፣ የእርሻ መሳሪያ አዘገጃጀት … ሊሆን ይችላል፡፡ ማህበረሰቡም ሆነ ቡድኑ ትክክለኛነቱን ሳያረጋግጥ ለመተግበር አይሞክርም፡፡ ሙከራው ከተሳካ መጀመሪያ ለቤተሰቡና በጣም ቅርብ ለሆኑት ሰዎች ይናገራል፣ ተግባራዊነቱንም ያሳያል፡፡ ይህንንም በመጀመሪያ ደረጃ እራሱ ሞክሮ ተግባራዊነቱን

[187] አቶ ጌታሁን ብሩ፣ አግዛ ጋርዳ ቀበሌ፣ ሹምታ ደሽ ቃለመጠይቅ፣ 4/9/2006፡፡

ሳያረጋግጥ ለአንድ ሰውም ትንፍሽ አይልም፡፡ ተግባራዊነቱ ሲረጋገጥ ግን ይህ በግል የፈጠረው ዕውቀት ከባለቤቱ ይወጣና ወደሌሎች ይተላለፋል፤ መተላለፊያ መንገዱም ቃላዊ ወይም ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ከፈጣሪው ከወጣ በኋላ የቡድን ዕውቀት ይሆናል፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ የዕውቀቱ ፈጣሪ በመሆኑ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ "ዕድሜ ለእገሌ" እየተባለ ስሙ ይነሳል፡፡ በባህላዊ መንገድም ቢሆን የባለቤትነት መብቱ ይጠበቅለታል፡፡ ይህ ዕውቀት ከአንዱ ወደ አንዱ የሚተላለፍበትን ሂደት ከዚህ በታች ለመግለጥ ተሞክሯል፡፡

ከላይ በምስሉ በስተግራና በስተቀኝ በኩል ያሉትን ሁለት ቀስቶች ብንመለከታቸው ቀስቶቹ በተቃራኒ አቅጣጫ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ከምስሉ በስተግራ በኩል የሚገኘው ቀስት ከላይ ወደታች ያመላክታል፤ ይህም ዕውቀት ከአውድ ተነስቶ እስከ ግለሰብ ድረስ የሚሄድ መሆኑን ሲያሳይ በስተቀኝ በኩል ያለው ቀስት ደግሞ ከታች ወደላይ የሚያመላክት ነው፤ ይህም ዕውቀት ከግለሰብ ተነስቶ እስከ ማህበረሰብና አውድ ድረስ የሚሄድ መሆኑን ያሳያል፡፡

እንዲሁም በስተግራ በኩል ወደ ምስሉ የሚገቡ ቀስቶች ዕውቀት በተለያየ መንገድ ከተጎራባች አካባቢ፣ ከቴክኖሎጂው፣ ከግብርና ሰራተኛው... ወደ ማህበረሰቡ የሚገቡ የተለያዩ የባህላዊ ግብርና ማለትም እውቀቶች የማዳበሪያ አዘገጃጀት፣ የዘር አያየዝ፣ የተባይ መከላከያ... የሚያመለክት ሲሆን በስተቀኝ በኩል ወደ ውጭ የሚያመላክቱት ቀስቶች ደግሞ ዕውቀት ከማህበረሰቡ ወደ ተለያዩ አካባቢዎች በሥነ-ቃሉ፣ በተረትና ምሳሌው፣ በልማዱ፣ በእምነቱ፣ በምልከታው... መውጣቱን የሚያመላክት ነው፡፡ የቀስቶቹ ቀለማቸው መለያየት የተለያየ አይነት ዕውቀት መሆኑንና ይህ ዕውቀት ወደ ሌላ ሲተላለፍ በቀጥታ የመጣው ዕውቀት ሳይሆን በተለያየ ምክንያት ሊለወጥና ሊሻሻል ወይም ሊቀነስና ሊጨመርበት ስለሚችል ወደውስጥ በገባበት መንገድ እንደማይመለስ የቀለሞቹ መለያየት ያመላክታል፡፡ እንዲሁም ዕውቀቱ በገባበት በኩል ካሉት ቀስቶች

በወጣበት አቅጣጫ በኩል ያለው በመጠን የጨመረው ዕውቀቱ ተሸሽሎና ተለውጦ ወይም ተጨምሮበት እንደሚተላለፍ ለማሳየት ነው፡፡

በክቡ ውስጥ ያሉት እያንዳንዳቸው ቀስቶች ደግሞ ዕውቀት ከአንዱ የማህበረሰብ ክፍል ወደ ሌላው እንዴት እንደሚተላለፍ የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ ቀስቶቹ እኩል መጠን አላቸው ብዬ አስባለሁ፡፡ ይህም ሁሉም ዕውቀት ሲተላለፍ በእኩል መንገድ ነው የሚል እሳቤን ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ የዕውቀት አቀባበል ግን እንደየግለሰቡ፣ ቡድኑ ወይም ማህበረሰቡ የአቀባበልና የአተገባበር ሁኔታ ልዩነት ሊኖረው ይችላል፡፡ ሁሉም ማረሻና ወገል የሚሰሩ ሰዎች አንድ አይነት ችሎታ ሊኖራቸው አይችልም፡፡ እንደየግለሰቡ የዕውቀት ሁኔታ የሚወሰን በመሆኑ እንደ ቡድን ተመሳሳይ ሙያ ያላቸው ቢሆንም እንደግለሰብ ደግሞ የተለያየ ችሎታ አላቸው፡፡ ለዚህም ነው ገበሬዎች ከእገሌ እገሌ ይሻላል በማለት አማርጠው የሚያሰሩት፡፡

የክቦቹ በመጠን መለያየት እያንዳንዱ ማለትም የግለሰብ፣ የቡድንና የማህበረሰብ ዕውቀት በደረጃ መጠናቸው የሚለያይ መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም ግለሰብ ነጠላ፣ ቡድን ከአንድ በላይ እና ማህበረሰብ ደግሞ ብዙ ቁጥር ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም ባህላዊ ግብርና ዕውቀት ከግለሰብ፣ ቡድን ብሎም ማህበረሰብ እያለ ሲሄድ እየሰፋ የሚሄድ ሲሆን የዕውቀት ልዩነቱም በዚያው መጠን እየተለያየ ይሄዳል፡፡

ምስሉን ስንመለከተው ሁሉም አንድ ቦታ ላይ ከምስሉ መጨረሻ ላይ ይገናኛሉ፡፡ ይህ የመገናኛ ነጥባቸው ሁሉንም ያስተሳሰራቸውና አንድ ያደረጋቸው ዋናውና መሰረታዊ ነገሩ አውድ ነው፡፡ ግለሰብም ቡድንም ሆነ ማህበረሰብ በአውድ ውስጥ የሚገኙ፣ በአንድ አይነት የኑሮ ዘይቤና ባህል ተሳስረው፣ ተግባብተውና ተስማምተው የሚኖሩበት አካባቢ ወይም አውዱ (መሬቱ፣ አየሩ፣ ወንዙ፣ ባህሉ...) ሲሆን ሌላው ያስተሳሰራቸው ነገር ሙያዊ የሆነው የጋራ እሴታቸው እና የህልውና መሰረታቸው የባህላዊ ግብርና እውቀታቸው ነው፡፡

ይህ ዕውቀት ደግሞ የሚተገበረው አውድ ላይ ነው፤ ስለዚህ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ከሚኖሩበት አካባቢያዊ ሁኔታ ጋር ተዳምሮ ማህበረሰቡን በአንድ አስተሳስሯል፡፡ ስለዚህም በአንድ በተመሳሳይ አውድ ውስጥ የሚገኙ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ እውቀታቸውን የሚጋሩና የጋራ እሴት ያላቸው ማህበረሰቦች ናቸው ማለት ነው፡፡

ለመተንተኛነት የተቀመጠውን የእርሻ መሳሪያ እዚህ ላይ ማየት ይቻላል፡፡ አንዱን በሬ የግለሰብ ዕውቀት ይወክላል፡፡ ሁለቱ በሬ ደግሞ የቡድን ዕውቀት ይሆናል፡፡ ጥንድ ጥንድ የሆኑት የእርሻ መሳሪያዎችም የተለያየ ቡድንንና እውቀትን ይወክላል፡፡ እንዲሁም በነጠላ በነጠላ ሆነው የሚገኙት ሌሎችን የእርሻ መሳሪያ ክፍሎች ስንመለከት ደግሞ የተለያየ መጠን፣ አገልግሎት እና አይነት ያላቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ይህ በተለያየ መጠንና አይነት የተገለጸው የእርሻ መሳሪያ ማህበረሰቡን የሚወክል ነው፡፡ እነዚህ መሳሪያዎች ከበሬዎች ጋር ባንድ ላይ ህብር ሰርተው እናያቸዋለን፡፡ ይህም የዕውቀት ትስስሩን ያሳያል፡፡ የእነሱ መኖር ብቻ ደግሞ የሚያስገኘው ምንም ነገር የለም፡፡ ገበሬው መኖር አለበት፤ የገበሬው መኖርም ብቻውን ትርጉም አልባ ነው፡፡ ትርጉም ይኖራቸው ዘንድ የሚታረሰው የእርሻ መሬት መኖርን ግድ ይላል፡፡ መሬቱ አውድን የሚወክል ነው፡፡ ስለዚህ ማህበረሰቡ ዕውቀትና አውዱ የጠበቀ ትስስር እንዳላቸው ያሣየ ነው፡፡

ጅራፉ ደግሞ ባህልን እንዲወክል የተቀመጠ ነው፡፡ በሬዎቹ መስመራቸውን ሲስቱ በጅራፍ እየተገረፉ ይመለሳሉ፡፡ በሬው ሳይገረፍበት ድምጹን ሲሰማ ወደ ለቀቀው መስመር ይገባል፡፡ ጅራፍ መግረፊያ ሳይሆን ማስፈራሪያ ነው፡፡ በሬው ወደወጣበት መስመር አልመለስ ሲል ግን መገረፉ አይቀሬ ነው፡፡ ማህበረሰቡም ከደንቡ ሲያፈነግጥ በባህሉ መሰረትነት ይመከራል/ ይወቀሳል፡፡ አልመለስ ሲል ግን ባህሉ በሚፈቅደው መሰረት ይቀጣል፡፡ ገበሬው ደግሞ እውቀቱን ማህበረሰቡንና አውድን የሚያስተሳስር ክር ነው፡፡

የበሬዎቹ፣ የእርሻ መሳሪያውና የገበሬው ተግባር የሚገለጠው በመሬት ላይ በመሆኑ በአንድነት የእነሱ ህብር ሲገለጽ ህልው ናቸው እንላለን፡፡ ያለበለዚያ ግን አንዱ ያለ አንዱ እርባና ቢስ ይሆናል፡፡ ይህን የተዘረዘረውን ነገር ከባህላዊ ግብርና ዕውቀት ምስል ጋር ማመሳሰሉ ተገቢ ነው፡፡ የእርሻ መሳሪያው በራሱ የተሰናሰለበት መንገድ የማህበረሰቡን አጠቃላይ አወቃቀርና እዛዊ ሰንሰለት ያሣያል፡፡

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለማየት የተሞከረው የባህላዊ ግብርና ዕውቀት በተለያየ ደረጃ በግለሰብ፣ በቡድን ብሎም በማህበረሰብ የሚፈጠርና ተግባራዊነቱም ሲረጋገጥ ዕውቀቱን በጋራ የሚጋሩት መሆኑን ለማየት ሞክሪያለሁ፡፡ ከዚሁም በተጨማሪ የዕውቀት ፈጣሪ ባለቤት ማህበረሰቡ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሲመርቀው፣ ሲያመሰግነውና የባለቤትነት መብቱን ሲጠብቅለት ይስተዋላል፡፡ በገበሬዎች መካከል ምንም አይነት የፈጠራ መብትን የመንጠቅ ተግባር ሲከናወን አይስተዋልም፡፡ ማህበረሰቡ በአንድ ቦታ/አካባቢ የሚኖርና የባህላዊ ግብርና ዕውቀት የጋራ ተጠቃሚ በመሆኑ በአውድና በባህላዊ ዕውቀት የተሳሰረ መሆኑን በዚህ ጥናት ለማየት ችያለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

## ለውጥና ቀጣይነት

ይህ ምዕራፍ በጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ የሚኖሩ ገበሬዎች የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ለውጥና ለለውጡ መከሰት ምክንያት ስለሆኑት ጉዳዮችና ቀጣይነት የሚቀርብበት ነው፡፡ ማህበረሰብም ሆነ ባህል በውስጣዊም ይሁን ውጫዊ ጉዳዮች መነሻነት፣ በሰው ሰራሽም ሆነ ተፈጥሯዊ ለውጥ ምክንያት እየተለወጠ መሄዱ አይቀሬ ነው። ለለውጡ መፋጠን የበለጠ ጎልቶ የሚጠቀስና የሚቀርብ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ጉዳዮቹ ለውጡን ማስከተላቸው አይቀሬ ነው። ለውጥ ደግሞ የፎክሎር አንዱ ባህሪ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በተጠኚው ማህበረሰብ ዘንድ ለለውጥ የተጋለጠውን ወይም ለውጡ ያረፈበትን እና ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውና እስካሁን ድረስ ጠብቆት ያቆየውን በተለያዩ ሁኔታዎች ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

### 7.1. ለውጥ

ለውጥ፣ በነበረው ተጨባጭ ሁነት ላይ በጊዜ በሂደት የተፈጠሩ ማሻሻያዎች መኖራቸውን የሚያሳይ ነው (sisms and stephens 2005)፡፡ ለውጥ በማኛውም ባህል ውስጥ የሚከሰት ጉዳይ ነው፡፡ ለውጥ የፎክሎር አንዱ ባህሪ እንደሆነ በምዕራፍ ሁለት ስር ተጠቅሷል፡፡ በዚህም መሰረት ባህላዊ የግብርና ዕውቀትም በዚህ ውስጥ ማለፉ የማይቀር ነው፡፡ ባህል ተለዋዋጭ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ የባህላዊ ግብርና በማይለወጥና በረጋ አለም ውስጥ የሚኖር አይደለም፡፡ ሁሌም በለውጥና በእንቅስቃሴ ውስጥ ያለ ነው፡፡ ለውጡ በአንድም ሆነ በሌላም መንገድ ሊከሰት ይችላል፡፡ ይህም ለውጥ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ሊከሰት ይችላል፡፡[188]

[188] Traditional agriculturalists do not live in static worlds. They are surrounded by change, especially cyclical change, and are well aware of it and capable of conceptualizing it (Brousile et al. 1986:194).

ለባህላዊ ግብርና ዕውቀት ለውጦች መከሰት ሰው ሰራሽ ነገር እና በተፈጥሯዊ ሁኔታ የሚከሰት ብሎ በመክፈል ማየት ይቻላል፡፡ ይህም የሰው ቁጥር መብዛት፣ የደኖች መጨፍጨፍ፣ የመሬት መራቆት፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የዝናብ ከወቅቱ ቀድሞ ወይም ዘግይቶ መምጣት… ለለውጡ መከሰት እንደ ምክንያት ሊቆጠሩ ይችላሉ፡፡ የሰው ቁጥር ከዕለት ወደዕለት እየጨመረ በመሆኑ ለእርሻ የሚሆን መሬት ማግኘት እጅግ አስቸጋሪ እየሆነ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ ሽመካ ሲናገሩ፡-

> …ህዝቡ አሁን በጣም በዛ ድሮ የነበሩት፣ በጓሽታ ማሪያም የነበሩት ቤተክርስቲያን ሲሰሩ በ 55፣ በ 56፣ በ 57 ዓ.ም. በዚህ በኔ ዕድሜ አርባ ምናምን ሰዎች ናቸው የነበሩት፡፡ ዛሬ ግን ወደ 500 ምናምን ደርሷል፤ ለዚያውም አባወራው ብቻ፡፡ በየቤቱ ያለውን እዚያው ቤቱ ይቁጠረው፡፡ ስለሆነ መሬት ተራቆተች፣ ደን አለቀ፡፡[189]

እንደ አቶ ሽመካ አገላለጽ አባወራው ብቻ ከ500 በላይ ነው ማለት ልጆችን፣ ሴቶችንና አረጋዊያን ሳይጨምር መሆኑ ነው፡፡ ለመሬት መራቆት አንዱ ምክንያት መሆኑ ነው፡፡ ይህ የመሬት መራቆት ደግሞ ለባህላዊ ግብርና ዕውቀት መለወጥ እንደ አንድ ምክንያት ሊወሰድ ይችላል፡፡ የሰው ቁጥር እየጨመረ በመጣ ቁጥር ለመኖሪያ ቤት ያስፈልገዋል፤ ቤት ለመስራትም መሬት፣ ማገር፣ አውራጅና አቋም፣ ልጥና የክዳን ሳር (ሰንበሌጥ) ያስፈልገዋል፡፡ እነዚህን ነገሮችም የሚያገኘው ከጫካና ከዱር ነው፡፡ ስለዚህ ፍላጎቱን ለማሟላት ሲል መሬቱንና እንጨቱን ለማግኘት ሲል ደኑን ይጨፈጭፋል፤ ቤቱንም ይሰራል፣ የቀረውንም መሬት ለእርሻ ይጠቀማል፡፡ ይህም ለአየር ንብረት ለውጥ የድርሻውን አበርክቷል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በአካባቢው ከተለወጡ ነገሮች አንዱ በባህላዊ መንገድ መሬትን ለማልማት የሚጠቀሙበት መንገድ ነው፡፡ በቀደመው ጊዜ መሬት ለም እንዲሆንና

[189] አቶ ሽመካ ገዳሙ ፣አደጋ ጓሽታ ቀበሌ፣ ጓሽታ ማሪያም ደሽ፣ ቃለመጠይቁ የተደረገበት ቀን 24/06/2007

እንዲዳብር ለማድረግ ክረምቱ ሲመጣ በየአካባቢያቸው በ "ላም ራስ" አማካኝነት ከ10-12 የሚሆኑ ሰዎች በአንድ ላይ በመደራጀት ከሰኔ 12 እስከ ህዳር 12 ድረስ ቅራት ይቀሩ ነበር፡፡ በየቤቱ ያሉ የቀንድ ከብቶች በአንድ ላይ በማድረግ በማህበር ተደራጅተውና እጣ ተጣጥለው በየተራ በየማሳቸው ላይ በማሳደር የከብቶቹን እዳሪ ለመሬቱ ማዳበሪያነት ይጠቀሙ ነበር፡፡ በአሁኑ ሰዓት ግን ቅራት የለም፡፡ አቶ አወቀ እንዲህ ይላሉ

> ድሮ የምንጠቀመው በሁራ[190] ነበር፡፡ ድሮ ከብታቴው ብዙ፣ መሬቱም ሰፊ ነበር፡፡ ከሰኔ 12 እስከ ህዳር 12 ድረስ ወይ አስር ወይ አስራ አምስት ሆነን ባንድ ላይ የላም ራስ አለን በሱ አማካኘነት እጣ ተጣጥለን ተመዳድብን እንዲያ አንድ ሰባትም ሆነ ሁለት ሰባት በተራችን ደገሌ[191] እየሰራን በማሳችን ላይ ስንቀራ እናድር ነበር ያው የከብታቴው ሽንቱም ሆነ እበቱ እዚያው እየተደቀደቀ ጥሩ ማዳበሪያ ይሆን ነበር፡፡ አሁን ግን የለም ቀርቷል፡፡ ከብቱም አልቋል፡፡ አማጋም[192] የለም፣ ያሉትንም ተደጅ አስረን ነው የምንጠብቅ፡፡ ሌባውም አስቸገረ ሰውም ተጨካከነ፡፡ መስኩም እርሻ ሆነ፣ ሰውም፣ ሌባውም በረከተ፣ ከብቱም ጠፋ ያችን ያለችዋንም ሁሉም በየቤቱ አስሮ ይጠብቃል፡፡[193]

የአቶ አወቀን ሃሳብ የቡድኑ ተወያዮች ሁሉም የሚስማሙበት ሃሳብ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት እንኳን ጾሙን የሚያድርና ከብት የሚታሰርብት መሬት ለእርሻ የሚሆነውም መሬት እያነሰ ነው፡፡ በቀን ከብት የሚሰማራበት ቦታ የለም፡፡ ሌባውም እጅግ በርክቷል፡፡ ከብት ይውልባቸው የነበሩት ተራራማ መሬቶችም አሁን ተከልለዋል፡፡ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ አንድ አባት ስለ ግጦሽ መሬት የሚከተለውን ብለዋል፡፡

---

190 ብዙ ከብቶችን በአንድ ማሳ ላይ ከ5-10 ቀን በመቅራት (በማሳደር) የከብቶችን እዳሪ ለመሬት ማዳበሪያነት መጠቀም

191 የከብት ማሰሪያ ግንድ

192 የከብት መሰማሪያ ሜዳ /መስክ/

193 አቶ አወቀ ታዬ አብስላ ዋርዳ ቀበሌ፣ ዋህሳ ደሽ ፣ ቡድን ውይይት 21/11/2007

በጎቼንም ሽጬ ትኋን አረባለሁ
ከብቶቼንም ሽጬ ቅማል አረባለሁ
ጋራ ተከልክሏል ጎኔን አግባለሁ፡፡[194]

ይህ ግጥም በአሁኑ ሰዓት ያለውን የመሬት ጥበት ያመላክታል፡፡ የጊዜው ሁኔታ ያስከተለውን ለውጥ በማየት ገጣሚው ጊዜውን ያማርራሉ፤ ይህ ሁሉ ጊዜው ያመጣብን ነው፡፡ ሰው ከቆዬ ብዙ ነገር ያያል እኛም እዚህ ደርሰን ብዙ ነገር አየን የሚሉ ይመስላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ለለውጡ መከሰት ምክንያቶች እራሳቸው እንደሆኑ ማወቅ የፈለጉ አይመስሉም፡፡ ወይም እራሳቸውን ከተጠያቂነት ለማውጣት በግጥሙ ውስጥ ሲደበቁ ይስተዋላል፡፡

ገበሬው ከብቶቹን ይወዳል፤ የእነሱን ትንፋሽ እያሸተተ መኖርን የለመደ ነው፡፡ አሁን ግን እነሱን የሚያውልበት ቦታ የለውም፡፡ ድሮ ያውልበት የነበረው መስክ ዛሬ የለም ለእርሻ ውሏል፡፡ የማይታረሱ መሬቶችም ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነጻ ይሁኑ ተብለው ተከልለዋል፡፡ ስለዚህ ደጁ ላይ አስሮ ሁሉንም መቀለብ አይችልም፤ አንድ ወይም ሁለትና ሶስት ቢኖረው ነው፡፡ ከብቶች ለገበሬው ሲቸግረው አውጥቶ የሚሸጣቸው ልብሱና ጉርሱ ናቸው፡፡ እነርሱን ሽጬ በችጋር ልገረፍ ነው የሚለው፡፡ ትኋንና ቅማል የችግር ምልክቶች ናቸው፡፡

ባህላዊ ማዳበሪያ አዘገጃጀቱም ለውጡ ያረፈበት ነው፡፡ በቀደመ ጊዜ ባህለዊ ማዳበሪያውን የሚያዘጋጁት በማሳው ላይ ነበር አሁን ግን ገበሬው በቤቱ አቅራቢያ ለኮምፖስት መስሪያ የሚሆን ጉድጓድ ቆፍሮ ያዘጋጃል፡፡ በየእለቱ የከብቶቹን እዛባ፤ የቤት ጥራጊ፣ አመድ፣ የተክሎቹን ቅጠላ ቅጠልና የተረጋገጠ የከብቶች መኖ በተዘጋጀለት ጉድጓድ ውስጥ ትጨምራለች፤ በዚህ መንገድ ኮምፖስት ይሰራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አቶ አለማየሁ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

---

194 ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ አባት በእድሜያቸው ወደ 80 የሚገመቱ፣ መረጃውን የሰጡበት ቀን 16/11/2007

ባህላዊ ማዳበሪያን አስመልክቶ ቄስ ታዬ የሚከተለውን ብለዋል፡-

> አሁን የጠቀመን ብስባሽ ነው፡፡ እደጃችን አዘጋጅተን በከብት ጭነን እንወስደዋለን፡፡ የ"ግብርናውን"ም[195] ብስባሹንም አንድ ማሳ ላይ እንጠቀማለን፤ ኮምቦስቱ የመሬቱን ለምነት ሁለት ዓመት ሶስት ዓመት ይጠብቃል፤ የግብርናው ግን ባንድዜ መሬቱን ገሎ ለአንድ ዓመት ጥሩ ምርት ይሰጣል፡፡ ታዲያ መሬቱ ይደርቃል፡፡ ለመሬቱ ኮምቦስቱን ለፍሬው ደሞ "ዩሪና ዳቡ"ን እንጠቀማለን፡፡[196]

ገበሬው በባህላዊ ግብርና ዕውቀት ተጠቅሞ ያዘጋጀውን ባህላዊ ማዳበሪያ እና በግብርና በኩል የሚሰጠውን ዘመናዊ ማዳበሪያ (ባህላዊውንና ዘመናዊውን) የወራት ጊዜ በመስጠት በአንድ ማሳ ላይ በመጠቀም የመሬቱን ለምነትና ምርታማነቱን አቻችሎ ሲሄድ ይስተዋላል፡፡ ይህም በመጀመሪያ ባህላዊው ማዳበሪያ ከአፈሩ ጋር እንዲዋሃድ የሚያደርጉት ደጋግመው በማረስ ሲሆን የለመደውና የሚያውቀው፣ ራሱ ያዘጋጀው ማዳበሪያ የመሬቱን ለምነት እንደሚጠብቅለትና ሳይንሳዊ ማዳበሪያው ደግሞ በዘር ጊዜ የሚጨመር እና ለጊዜው ጥሩ ምርት ቢሰጥም የመሬቱን ለምነት ግን እንደሚያሳጣው በልምድ ባዳበረው ዕውቀት ተገንዝቦታል፡፡ ስለዚህም ሁለቱን በማቻቻል መጠቀምን እንደ አማራጭ ወስዶታል፡፡ ሌላው መሬትን ለማልማት የሚጠቀሙበትን የነበረውን ዘዴ ቄስ ታዬ ሲናገሩ፡-

> ድሮ መሬቱ አላበቅል ሲለን አንድ ዓመት ሁለት ዓመት ቦዘኑን እንተወዋለን ወይ ሳር ያበቅላል ወይ ግብጦ በትነን እንተወዋለን፡፡ ግብጦ ዝም ብሎ ነበር የሚበተነው እርሻ አይልም፤ መሬትንም ያቀልዛል፤ እንዲያ አድርግን እንተወዋለን፡፡ ተዚያ ወዲያ ሲታረስ

195 በግብርና በኩል የሚመጣውን ዘመናዊ ማዳበሪያ ዩሪያና ዳፕ

196 ቄስ ታዬ ታፈረ፣ አብስላ ዋርዳ ሳሙኤል ቀበሌ፣ ዋህሳ ደሽ፣ ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቀን 24/06/2007

ምርቱ ሌላ ነው! አሁን እንኳን ጠም የሚያድር መሬት ላለው ቤተሰብም የሚበቃ አይደለም፡፡ መሬቱ አንድዜ ሁለትዜ ካልተሰነጠቀ በስተቀር እንደድሮው ዝም ብሎ ግብጦ አያበቅልም፡፡ መሬቱ እምቢ ብሏል፡፡[197]

መሬቱ የሚሰጠው ምርት ከቀነሰ ለአንድ ዓመት፣ ለሁለት ዓመት፣ ጾሙን ያድራል፤ አይታረስም ነበር፡፡ ሳር ሆኖ ከብት እንዲውልበት ይደረጋል፡፡ ይህም የከብቶቹ እዳሪ መሬቱን ያዳብረዋል፡፡ አቶ ይሁን ስለ መሬት ማሳደር ሲናገሩ

ድሮ ድሮ ይህ (በአካባቢው ያለውን የእርሻ መሬት በእጃቸው እየጠቆሙ) የምታይው ሁሉ መስክ የከብት መዋያ ነበር፡ ብዙ የእርሻ መሬትም ስለነበረን ወይ ሳር እናድረገዋለን፤ ወይም ደግሞ ግብጦ ተበትኖበት ይከርማል፡ ዛሬ ግን እንደምታይው አዝመራ ብቻ ሆኗል፡፡ እንኳን ቦዘኑን የሚያድር የሚታረሰውም እያጠጠ ነው፡፡ ያንኑ አንድ ዓመት ገብስ አንድ ዓመት ጤፍ አንድ ዓመት ድንች እንዘራዋለን፡፡[198]

እንደ አቶ ይሁን ገለጻ የእርሻ መሬታቸው ሰፊ በነበረበት ሰዓት መሬታቸውን ያለ እህል በማከረም ወይም ግብጦ በመዝራት ያከርሙት ነበር፡፡ የግብጦ መሬት አይታረስም ከብትም አይበላውም፤ ለማዳበሪያነት ነው የሚዘራው የመሬትን ለምነት ይጠብቃል ብለው ይዘሩታል፡፡ በዚህ መንገድም መሬታቸው መልሶ እንዲያገግም ያደረጉት ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን ይህን ማድረግ በቤተሰባቸው ጉሮሮ ላይ መቆም ነው፡፡

ለዚህ ምክንያት ሆኖ የሚጠቀሰው የህዝብ ቁጥር መብዛት ነው፡፡ በአሁኑ ሰሃት አብዛኛው በአስራዎቹ ክልል የሚገኘው ወጣት መሬት አልባ ነው፡፡ የሚያርሰው መሬት

[197] ቄስ ታዬ ታፈረ ፣አብስላ ዋርዳቀበሌ ዋህሳ ደሽ፣ ቃለ መጠይቁ የተደረገበት ቀን24/6/2007
[198] አቶ ይሁን አድማስ

የለውም በዚህም ምክንያት ወደ ከተማ እየፈለሰ በቀን ሰራተኝነት እየተሰማራ ነው፡፡ የወጣቶች ከገጠር ወደ ከተማ መፍለስ አንዱ የለውጥ ሁኔታ ማሳያ ነው፡፡ ማህበረሰብም ሆነ ባህል በውስጣዊም ይሁን ውጫዊ ጉዳዮች መነሻነት፣ በሰው ሰራሽም ሆነ ተፈጥሯዊ ለውጥ ምክንያት እየተለወጠ መሄዱ አይቀሬ ነው። ለለውጡ መፋጠን የበለጠ ጎልቶ የሚጠቀስና የሚቀርብ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ጉዳዮቹ ለውጡን ማስከተላቸው አይቀሬ ነው። ለውጥ ደግሞ የፎክሎር አንዱ ባህሪ ነው፡፡

ሌላው የመሬትን ለምነት መጠበቂያ የነበረው በመሬታቸው ዙሪያ የሚገኘውን ድንበር ሳያርሱ መተው ነበር፡፡ ይህም ከእርሻው በዝናብ አማካኝነት የሚጠረገው አፈር እዚያው እንዲቀር ያደርገዋል፡፡ ይህም በአሁኑ ሰዓት የለም፡፡ በድንበር መካከል የሚተወው መሬት አንድ ወይም ሁለት ፈሰስ ስለሚሆን ያንን ከመተው ይልቅ መጠቀሙን ይመርጣሉ፡፡ ምክንያቱም የእርሻ መሬት እጥረት አለ፡፡ አሁን የመጣው ይላሉ አቶ አየለ "አሁን የመጣው የመሬት መንከባከቢያ ዘዴ በእርከኑ መሬታችንን ቢባክንም ትንሽ የተራራውን ጎርፍ ይከላከለዋል፡፡ ገጦ የነበረውን መሬት እየመለሰው ነው፡፡"[199]

በቀደመ ጊዜ ብዙ ማዳበሪያ የማይፈልገው መሬትም ዛሬ ያለ ማደበሪያ ምንም አያበቅልም ለማንኛውም የእህል አይነት ማዳበሪያ መጠቀም ግድ ይላል፡፡ ይህን አስመልክቶ የዘመኑ ወጣት ገበሬዎች ከሆኑት አንዱ ወጣት ሀብታሙ የሚከተለውን ብሏል፡፡

ረጅም ዛፍ አይቶ ይሰፍራል ጉሬዛ

ምነው በኛ ዘመን ማዳበሪያው በዛ፡፡[200] በማለት

በአሁኑ ሰዓት ሁሉም ነገር በማዳበሪያ የሚዘራ በመሆኑ ወጣቶቹ ይህንን በምሬት ይናገራሉ፡፡ ምንም በማዳበሪያ ተጠቅመው ብዙ ምርት ቢያመርቱም ደስተኞች

199 አቶ አየለ አንተነህ፣ አደጋ ውባጅ ቀበሌ፣ ሰባት አይና ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 27/7/2007 ፡፡

200 ወጣት ሀብታሙ ጌታነህ፣ ቃለመጠይቅ የደረገበት ቀን 21/7/2007 አደጋ ጓሽታ - መሀል አምባ፡፡

አለመሆናቸውን የግጥሙ መንፈስ ያስረዳል፡፡ "ብዙ ብናመርትም ተጠቃሚዎች አይደለንም ዞሮ ዞሮ ተገደን ለምንወስደው የማደበሪያ እዳ ነው የሚውለው እኛስ ያቺው የበፊቷ ትሻለን ነበር"፡፡

ገበሬው ያመረተውን ምርት በብዙ ዋጋ የሚሸጥ ቢሆንም ደስተኛ አይደለም፡፡ ምክንያቱ የዋጋው ውድነት በጊዜ ሂደት የመጣ ቢሆንም ባንድም ሆነ በሌላ መንገድ የኑሮ ውድነቱ ተቋዳሽ ነው፡፡ "የምናመርተውን እህል ሽጠን ያው ለማዳበሪያና ለምርጥ ዘር እዳ ነው የምንከፍለው ለኛ ጠብ ያለ ነገር የለውም፡፡ በሁለትና በሶስት ሽልንግ ይገዛ የነበረ በሬ ዛሬ ላይ አስርና አስራ አምስት ሺ ብር አወጣ አምስት ብር ይገዛ የነበረ ዳውላ ጤፍ ዛሬ ሁለት ሺ ብር ነው፡ "ከቆየን ገና ብዙ እናያለን" በማለት በጊዜ ሂደት የተለወጠውን ነገር ይገልጻሉ፡፡[201]

በጥናት አካባቢዬ በቀደሙት ጊዜያት በርካታ የሰብል አይነቶች በብዛት ይበቅሉ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት አብዛኞቹ የገብስ ዝርያዎች (ስንዴ መና፣ ጎረንጅ፣ ሳልደሚ፣ አጃ፣ ሰመሬታ ገብስ ...) የሚባሉተ በመጥፋት ላይ ናቸው፡፡ የሰማኒያ አመቱ አቶ አየለ ስለዚህ ሲናገሩ፡-

> ይህ አሁን ያለንበት ቦታ በውስጡ ሰው ደፍሮ አያለፍበትም ነበር፡፡ ቀፎ ለመስቀል በውስጡ ለማለፍ በልባችን እየተሳብን ነበር የምንገባው እልም ያለ ጫካ ነበር፡፡ እኔ ወደዚህ ቦታ ስመጣ ገና የ25 ዓመት ኮመቻ ነበርሁ፡፡ ያን ጫካ እየመነጠርን በዱላ ጫር ጫር አድርገን ማሽላ ስንዘራ ይተኛ ነበር፡፡ ዛሬ ግን እንደምታይው ምድረ በዳ ነው፡፡ እንኳን ተጭሮ መካራ አይተንም አርሰን የረባ አናገኝም፡፡ መሬቱን ግጠን የበላነው እኛ ነን ጥቅሙን ሳናውቀው፣ ሳይቸግረን፣ ዛሬ ነገር ተተበላሸ ምን ዋጋ አለው፡፡ ድሮ የምናፍሰው ሰነፍ ቆሎ፣ ሳልድሚ፣ ጠመዥ፣ ስንዴ

[201] አቶ አየለ አንተነህ፣ አዲጋ ውባጅ ቀበሌ፣ ሰባት አይና ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 27/7/2007

> መና ጠፋ፡፡ መሬቱ እምቢ አለ፡፡ አጃን እንኳ እኛ ነን የተውነው! ልፋቱ መከራ! ውጤቱ የረባ አደለም በማለት ይናገራሉ፡፡ ምርቶች በመሬቱ መበላት ምክንያት አለበቅል አሉ፡፡ አጃን ግን የሚገኘው ምርት የልፋቱን ያህል ባለመሆኑ፣ እንደ ተልባና ኑግ ያሉትን ደግሞ ከመሬት ጥበት የተነሳ ከጤፍ አንድ ሁለት መስመር ቀንሶ ለቀለብ ብቻ የምንዘራቸው ሁነዋል፡፡[202]

የስራ ባህላዊ አደረጃጀቶች (ደቦ፣ወንፈል) የመሳሰሉት ባህላዊ የስራ አደረጃጀቶች በሌላ አደረጃጀት ተተክተዋል፡፡ ደቦ አምስትም ስድስትም የሚፈላለጉ ሰዎች በአንድ ላይ ሆነው የሚሰሩበት የስራ ማህበር ነው፡፡ ስራ ካለ መቅረት አይቻልም፣ ካቅም በላይ ከሆነ ደግሞ ሰው መተካትና ማሰራት ይቻላል፡፡ የደቦ አባላት የሚሳተፉት በግብርና ስራ ብቻ ሳይሆን ለቤት ስራ የሚሆን እንጨት በመፍለጥ፣ ልጥ በማዘጋጀት፣ ቤት በመስራት፣ ወዘተ. ይሳተፉሉ፡፡ ወንፈል ማህበር ሳይሆን ለተዋለለት የጉልበት ስራ በተናጠል ወይም በቡድን የሚከፈል የጉልበት ብድር ነው፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ ሽመካ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> አሁን ያለው አደረጃጀት እኛ በፈለግነው ሳይሆን በግብርናዎችና አመራሮች አምስት አምስት አድርገው አቧድነው ይተውናል፡፡ ያው እንግዲህ ስናርስም፣ ስናጭድም፣ ስናርምም አብረን ነው፡፡ አንዳንድ ዋልጌ ታለ የሱ ምርት ሲወድቅ በግምገማ አብረህ ትወድቃለህ፣ በዚያ ያው መጣላት፣ መፋጀት ነው፡፡[203]

የአሁኑ አደረጃጀት በገበሬው ውዴታ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በአደራጆች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በዚህም በአንዱ ምክንያት ሌላው ሊጎዳ የሚችልበት አጋጣሚም ሊፈጠር እንደሚችል ያሳየናል፡፡ ባህላዊ አደረጃጀቶች ባህላቸውን መሰረት አድርገው የውዴታ የሚቋቋሙ በመሆናቸው የራሳቸው የሆነ ያልተጻፈ ባህላዊ መተዳደሪያ

[202] አቶ አየለ አንተነህ፣ አደጋ ውባጅ ቀበሌ፣ ሰባት አይና ደሽ፣ ቃለመጠይቅ 27/7/2007
[203] አቶ ሽመካ ገዳሙ ፤ አደጋ ውባጅ ቀበሌ፣መስቀለኛ ደሽ፣ ቃለ-መጠይቅ፣24/06/2007

ያላቸው ነበሩ፡፡ በዚህም እርሻ፣ ጉልጓሎ፣ አጨዳ፣ ውቂያ፣ የቤት ስራ፣ እና የመሳሰሉትን ስራዎች በጋራ ይሰራበት የነበረ ነው፡፡ የአሁኑ ግን በግብርናው ስራ ላይ ብቻ የሚያተኩር እና በመመሪያ የሚሰራ በመሆኑ ቅጣቱ ወይም እርምጃው የሚከናወነው ከመመሪያና ደንብ አኳያ በአመራርና አስፈጻሚ አካለት ነው፡፡

ሌላው የሰብል አዘራር ዘዴ ነው፣ ገበሬው ከአያት ቅድመአያቶቹ የተቀበለው የሰብል አዘራር ዘዴ ብተና ነው፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛው ገበሬ በመስመር እንዲዘራ እየተደረገ ነው፡፡ ይህም አንዱ የለውጥ አይነት ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ አቶ ይሁን ሲናገሩ፡-

> ድሮ ድሮ እኛ የለመድነውና የኖርንበት የአዘራር ዘዴ ብተና ነው፡፡ አሁን አሁን ግን በመስመር ዝሩ እየተባልን እየተገደድን ነው፡፡ በብተና በምንዘራበት ጊዜ ካፈያው እንደተመቸን አበራይተን አንድ ሰው ምልክት እያደረገ ይዘራው ነበር፡፡ አሁንም እየተደበቅን ነው የምንዘራው፡፡ የመጣው ቴክኖሎጂው ግን ጊዜን ጉልበትን እና የሰው ብዛትን ይጠይቃል፣ መስመር የሚያወጣ አለ፣ ዘሩን እየዘራ የሚሄድ አለ፣ ማዳበሪያ የሚጨምር አለ፡፡ በዚያ ላይ ሳያለቅ ዝናብ ተዘነበ ይቋረጣል፡፡ በዚያ ላይ በመስመሩ መሀል የሚቀረው መሬት ይባክናል፡፡ ላራሙቻ ነው የሚሆነው፡፡

በምልከታዬ ወቅት እንዳየሁት ግማሽ ሄክታር በሆነ በአንድ የግብርና ስርቶ ማሳያ ጣቢያ ላይ ጤፍን በመስመር ሲዘሩ ያገኘኋቸው የግብርና የልማት ጣቢያ ሰራተኞች መስመር የሚያወጣ አንድ ሰው አለ፣ ክዳኑ በተበሳ በውኃ መያዣ ፕላስቲክ የጤፉን ዘር የያዘ አለ፣ ማዳበሪያ የያዘ ሌላ ሰው አለ፡፡ በመጀመሪያ መስመር ይወጣል፣ በመቀጠል ዘሩን የያዘው ሰው መስመሩን ተከትሎ አፉ በተበሰው ፕላስቲክ ጤፉን እየዘራ ይሄዳል ቀጥሎ ማዳበሪያውን የያዘው ማዳበሪያውን እየጨመረ እንዲሁ እየተከተለ ይሄዳል፡፡ በዚህ በሩብ ሄክታር ቦታ ላይ ጤፍ ለመዝራት የወሰደው ጊዜ ከአራት ሰዓት በላይ ነው፡፡



ፎቶ 26፡- ጤፍ በመስመር በእጅ ሲዘራ[204]



ፎቶ 27፡- ጤፍ በአንድ በውኃ መያዣ ፕላስቲክ ሲዘራ፣ 11/11/2007

204 ከጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ የኮሙኒኬሽን ቢሮ ለጥናቱ እንዲስማማ ሆኖ የተወሰደ



ፎቶ 28፡- በአንድ ጊዜ 13 መስመር ጤፍና 13 መስመር ማዳበሪያ የሚዘራ በገበሬው የተፈጠረ እና የተሸሻለው ዘዴ[205]

ይህንን ችግር ለመፍታት ገበሬው በራሱ ጥረት አዳዲስ ፈጠራዎችን በመፍጠር ጊዜውን ለመቆጠብ ሲሞክር ይስተዋላል፡፡ "ችግር ብልሃትን ይፈጥራል" እንዲሉ በዘር ወቅት የተፈጠረባቸውን የጊዜና የሰው ሃይል እጥረት ለመከላከል በራሳቸው ጥረት ከአንድ የውኃ መያዣ ፕላስቲክ በአንድ ጊዜ አስራ ሶስት መስመር የሚዘራ ባህላዊ መዝሪያዎችን በመስራት ችግሩን ለመቅረፍ ሲሰራ ይስተዋላል፡፡ በዘመናዊ የአዘራር ዘዴዎችም ውስጥ የገበሬው ባህላዊ የግብርና እውቀቱ መፍትሄ ሰጪ ወይም ችግር ፈቺ ሲሆን ይስተዋላል፡፡ ምክንያቱም የጤፍ ማሳ ጭቃ በራይ ከተበራየ በኋላ ወዲያውኑ ተዘርቶ ማለቅ አለበት፡፡ መዋልም ሆነ ማደር የለበትም ዝናብም እንዲያቋርጥ አይፈለግም፡፡

[205] ከጓጉሻ ሽኩዳድ ወረዳ የኮሙኒኬሽን ቢሮ ለጥናቱ እንዲስማማ ሆኖ የተወሰደ (26 የውኃ መያዣ ፕላስቲኮች በሁለት ረድፍ ሆነው በአንዱ ረድፍ የጤፍ ዘር በሌላው ረድፍ ደግሞ ማዳበሪያ በማድረግ የሚዘሩበት ሲሆን ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ዘዴ ነው፡፡ ይህም ገበሬው ባህላዊ የግብርና ዕውቀትን ተጠቅሞ በአካባቢው በቀላሉ ከሚያገኘው የወዳደቀ የውኃ መያዣ ፕላስቲክ የተሰራ ነው፡፡

ሌላው ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር ለመዘመን ሲባል የመጡ ናቸው፡፡ እነዚህም ምርጥ ዘር፣ ጸረ-አረም፣ ጸረ- ተባይ... የመሳሰሉት በጊዜ ሂደት ከእድገት ጋር በተያያዘ የተፈጠሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ናቸው፡፡ ገበሬውም እነዚህን የተለያዩ የምርጥ ዘር አይነቶችን እየተጠቀመ ይገኛል፡፡ በዚህም ምክንያት ነባር ዝርያዎች እየጠፉና እየተለወጡ በአዳዲስ ዝርያዎች እየተተኩ ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ አቶ ይሁን ሲናገሩ

> ይኸ በግብርናው የሚመጣው ምርጥ ዘር በማዳበሪያ ሲዘራ ባንድ ጊዜ ነው የሚጓፍለው[206]፡፡ ተዚያ ኃይለኛ ዝናብና ንፋስ ሲመጣ ለጥ ይላል፡፡ ፍሬውም ረግፎ ይቀራል፡፡ የድሮው ዘር ብዙም ከፍ ስለማይል ብጭጭ አይልም፡፡ ውርጬም ብዙም አይጎዳውም ነበር፡፡ ይኼ ቶሎ ያድግና ቡክር ስለሚሆን ትንሽ ያስቸግራል፡፡ የኛን አካባቢ ውርጭና በረዶ ሊቋቋመው አልቻለም፡፡[207]

እንደ አቶ ይሁን ገለጻ እነዚህ አዳዲስ ዝርያዎች በሽታንና ሌሎች ነገሮችን ንፋስን፣ ወጀቦን መቋቋም የሚችሉ አይደሉም፡፡ ቶሎ ስለሚያድጉ በቀላሉ ለነፋስ የተጋለጡ ናቸው፡፡ በቀላሉም ይወድቃሉ/ ይተኛሉ፡፡ ፍሬው መሬት ረግፎ ይቀራል፡፡ ችግርን የሚቋቋም ዘር ማምጣት አልቻሉም፡፡ በማለት ይገልጻሉ፡፡ ቢሆንም ገበሬው ችግሮችን በተለያየ መንገድ ለማቃለል እየሞከረና ተቀብሎ እየተጠቀመ ይገኛል፡፡ ይህ ለውጥ በዘር እህሎች ላይም እየታየ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ በላይ በቡድን ውይይቱ ላይ የሚከተለውን ብለዋል፡፡ "በአሁኑ ጊዜ ዘር የሚሆን እህል መለየትና ማስቀመጥ የታለ፣ የለም እኮ አሁን እሱ ቀርቷል፡፡ ተግብርናው የሚመጣውን ምርጥ ዘር ነው የምንዘራው፡፡ አሁን ዘር ማዘጋጀትም አይጠበቅብንም፡፡ ይኸ የጠፉ እንደሁ ግን እንኛ፡፡"[208] እንደ አቶ በላይ ሃሳብ ከቴክኖሎጂው ጋር የመጡት በተለይም በምርጥ ዘር ምክንያት የተከሰቱ ለውጦች በባህላዊ ዘር አመራረጥና አያያዝ ላይ ለውጥን አስከትለዋል፡፡ ገበሬው ወደፊት ምርጥ ዘሩ ቢቋረጥስ የሚል ስጋት አለበት፡፡ ይህም

[206] የሚጓፍለው ፡- የሚያድገው

[207] አቶ ይሁን አድማስ፣ አግዛ ጋርዳ ኤሊያስ ቀበሌ፣ ሹምታ ደሽ፣ ቃለመጠይቅ፣ 15/11/2007፡፡

[208] የቡድን ሁለት ውይይት 19/11/ 2008፡፡

አብዛኛው ገበሬ ዘንድ ምርጥ ዘርን በመጠቀም ላይ በመሆኑ ነባር ዝርያዎችን የመምረጥና የመዝራቱ ሁኔታ እየተለወጠ ነው፡፡ ይህ ለውጥ ግን አሉታዊ ለውጥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተወሰኑ ገበሬዎች ባህላዊውን ዘር መጠቀምን ይመርጣሉ፡፡

ጠለተ በረድ በቀደመው ጊዜ በባህላዊ መድሃኒት አዋቂዎች (በደብተራ) የሚዘገጅን ድግምት ይጠቀሙ ነበር፡፡ አሁን ላይ ግን ይህ ቀርቷል፡፡ ቄስ ወርቁ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ድሮ ደብተራ ሲጫወትብን ነበር አሁን ግን እሱን ትተን ተቤክሲያን ወንጌል አውጥተን፣ ጥላ ይዘን፣ የሰኔ ሚካኤል በድንበሩ አዙረን ወንጌሉን ታስገባን በኋላ በእዚያው በግ አርደን (መስዋዕት) እሱን ተቀማምሰን እንለያያለን፡፡ አሁን የሚያስፈራራን የለም ተመጣም የራሱ ያምላክ ቁጣ እንጂ የሰው አይደለም፡፡ አምላክ ደሞ ብዙም አይጎዳም እኛን የጨረሱን ደብተራዎች እሰበሳቸው አየተፎካከሩ ነበር፡፡ አሁን እሱ የለም፡፡[209]

ከቄስ ወርቁ ገለጻ መረዳት የሚቻለው ለተለያዩ ደብተራዎች እህል ወይም ገንዘብ በማዋጣትና ለተለያዩ ደብተራዎች በመክፈል በደብተራዎች ድግምት ይጠቀሙ ነበር፡፡ አሁን ግን ይህንን በመተው በሃይመኖታዊ ስርዓት በሚፈቅደው መንገድ ለአምላካቸው መስዋዕት በማቅረብና ጸሎት በማድረስ ለመከላከል እየሞከሩ መሆኑን ነው፡፡

ሌላው ለውጥ የሆነው በተፈጥሮ ምክንያት የመጣው የዝናብ ወቅት ከተለመደው ዘግይቶ ወይም ቀድሞ መምጣት ነው፡፡ ይህም በደን መራቆት ምክንያት የመጣ የአየር መዛባት ለውጥ ነው፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያት በአካባቢው የነበሩት በርካታ የተፈጥሮ ደኖች እየተመነጠሩ ለእርሻ ተግባር በመዋላቸው ምክንያት የዝናቡ ዘግይቶ ወይም ቀድሞ መምጣት ሰብሎችን በትክክለኛው ወቅት እንዳይዘሩ ከማድረጉም በላይ

---

[209] አቶ አይቼው በላይ፣ በቡድን ወይይት ላይ ያነሱት ሃሳብ 29/7/2007

የተዘራውም ቢሆን በትክክለኛውን ጊዜ እንዳያፈራና ፍሬ እንዳይሰጥ ያደርገዋል፡፡ ይህን አስመልክቶ በቡድን ውይይት ላይ አቶ አይቼው የሚከተለውን ሃሳብ ገልጸዋል፡-

> … ድሮ ይህ አካባቢ ዱር ነበር፤ አውሬው መቼም ለብቻ ነው መሸት ካለ ማን ብቻውን ወጥቶ! ለጉድ ነበር አውሬው፡፡ አሳማ፣ ከርከሮ፣ ጃርት የምትባል ደሞ አለች ድንችና ማሽላ የምትበላ፣ ጦጣው ማቴ ነበር፡፡ ያን አዝመራ ሲደረስ አልጋችን ሰርተን አለጋ ላይ ሆነን አይናችንን ሳንነቀል በብር እንጉድ ነበር የምንጠብቀው፤ ድንጋዩን እንዲህ አነስ አነስ ያለውን እህሉን እንዳያረግፈው ጉሎውን ነበር የምንጠቀመው፡፡ አሁን ጫካም ዱርም የለም፣ አሳማውም፣ ጃርቱም፣ ጦጣውም፣ ጠፍቷል፡፡ አሁን አምሳያችንን ሰርተን ንፋስ ሲያወዛውዘው ይውላል፡፡

ከአቶ አይቼው ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው በአሁኑ ሰዓት አልጋ ሰርቶ ሰብል መጠበቅ ቀርቷል፡፡ በዚህ ሃሳብ ሁሉም የቡድን ተወያዮች የተስማሙበትና የተቀበሉት ነው፡፡ የምክንያቱም ሰብልን የሚያጠፉ አውሬዎች እንደ አሳማና ከርከሮ፣ ጦጣ ያሉት የእንስሳት መጠለያ የነበረው ዱር በመመንጠሩ ምክንያት ካካባቢው የሉም ጠፍተዋል፡፡ ስለዚህ እነሱን ለመጠበቅ ይጠፋ የነበረው ጊዜ ዛሬ ለሌላ ተግባር ይውላል፡፡

በዚህ የለውጥ ሂደት ውስጥ የሚያልፉት ትግበራዎች ብቻ ሳይሆኑ ልማዶች እምነቶች ቃላዊ ፈጠራዎችም ሁሉብጊዜና በሁኔታዎች አስገዳጅነት ተለውጠዋል ወይም ቀርተዋል፡፡ ነገር ግን ለውጥ ቢኖርም ሳይለወጡ የሚቀጥሉ ነገሮች አሉ፡፡

## 7.2. ቀጣይነት

ቀጣይነት፣ በጊዜ ሂደት ውስጥ የልምድን ሰንሰላታዊነትና (ተያያዥነትና) የማያቋርጥ ጉዞ የሚገልጽ ነው (sisms and stephens 2005)፡፡ ቀጣይነት በማንኛውም ባህል ውስጥ የሚከሰትና የቡድንን ማንነትንም የሚገነባው በረጅም ጊዜ ሂደት ውስጥ ነው፡፡ ይህም በረጅም የጊዜ ሂደት ውስጥ በማለፉ ልማድ ሆኖ ከትውልድ ትውልድ እየቀጠለ ያለ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡

የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ቀጣይነትን በተመለከተ ከትውልድ ትውልድ ሲወርድና ሲወራረስ በመጣው የዕውቀት ክፍል በምዕራፍ ሁለት በ2.2.5 ስር ስለ ማህበረሰብ ዕውቀት ለመግለጽ እንደተሞከረው የባህላዊ ግብርና ዕውቀት እስካሁን ድረስ በቅብብሎሽ የመጣው ቀጣይነት ያለው ዕውቀት በመሆኑና ልምድ ስለሆነ ነው፡፡

ገበሬው ከአያት ከቅድም አያቶቹ የተቀበለውና አሁንም እየተጠቀመበት ያለው የባህላዊ እርሻ መሳሪያ እረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ ነው፡፡ በእያንዳንዳቸው የበሬ እቃዎች ላይ ምንም አይነት ለውጥ ሳያደርግባቸው እስከሁን ድረስ ለረጅም ዘመናት እየተጠቀመባቸው ይገኛል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ እርሻ የሚጀምርበት ጊዜ፣ የአስተራረስ ዘዴው፣ የሚዘራበት ወቅትም ሆነ የሚሰበስብበት ወቅት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ዕውቀት እንጂ አሁን በአንዲት ጀምበር የተከሰተ አይደለም፡፡ ይህም እረጅም ዘመናትን ያስቆጠረው የአስተራረስ ዘዴና መሳሪያ የለመደውና ከራሱ ጋር የተዋሃደው ነው፡፡ ብላታ ዳኛው ስለ ቀጣይነት የሚከተለውን ብለዋል፡-

> የእርሻ መሳሪያው ያው መቼም ከአያት ቅድመ አያታችን የወረሥነው ልምድ ሆኖ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው፡፡ የበሬ እቃው፣ ማጭዱ፣ መንሹ፣ መኮትኮቻው ያው የድሮ ነው፡፡ የምንዘራውም ያው እነሱ ባቆዩን መንገድ ነው፡፡ ክረምቱን

> ጠብቀን እነሱ ባበጁትና ባቆዩን እናዘምራለን፤ በጋው ሲመጣ አዝመራችንን እንሰበስባለን፡፡ እኛ የለወጥነው ነገር የለም፡፡ ታለወቀቱና ታለጊዜው አንዘራም፡፡ እንዝራ ብንል እንኳን አዝመራው መና ሆኖ ይቀራል፡፡[210]

ግብርና ተጀመረበት ተብሎ ከሚጠቀሰው ጀምሮ እስካሁን ድረስ ግብርናውም ሆነ ገበሬው አለ፡፡ ገበሬው አሁንም ድረስ እየተጠቀመበት ያለው የግብርና መሳሪያም ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያለው ነው፤ ማረሻው፣ ማጭዱ፣ መንሹ፤ ቅርጫቱ፣ መኮትኮቻው፣ በሬው… ጥንትም የነበሩ አሁንም ያሉ ናቸው፡፡ የአስተራረስ ዘዴውን በተመለከተም እርሻ የሚጀምርበት ጊዜ፣ የሰብል ማሳን የማረሻ ጊዜ፣ የመዝሪያ ጊዜ፣ ያው የተለመደው ነው፡፡ የሚዘራበት ወቅትም ሆነ የሚሰበስብበት ወቅት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ዕውቀት እንጂ አሁን የመጣ አይደለም፡፡

ጥናቱ የተከናወነበት አካበቢ ማህበረሰብ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ በመሆኑ በአካባቢው ሃይማኖታዊ የሆኑ በዓላትን ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ ሙሉ ለሙሉ ስራ የማይሰራባቸውና በከፊል የሚሰራባቸው ጊዜዎች አሉ፡፡ ይህን በተመለከተ ቄስ ወርቁ እንዲህ ይላሉ፡-

> ቅድምም ታያት ተቅደመ አያታችን የወረሥነው የአባት አደሩ፣ በበአላት እንዲች ብለን በሬ አንጠምድም በአቦና በስላሴ፣ በሚካል፣ በገብሬል፣ በማሪያም፣ በመድሃኒያለምና በባለገዚሃር፣ ሰንበትን እሁድ ቅዳሜን፣ እርሻም ሆነ ሌላ ስራ አይሰራም፡፡ እንዲህ በሬ የማይጠመድባቸውና የእጅ ስራ የሚሰራባቸው ቀናት አሉ፡፡ ይህን ብናደርግ የ'ሰማዩን ቁጣ'[211] አንችለውም፡፡ ግብርኖች ስሩ ይሉናል እኛ ግን አንሰራም፡፡ አንዳመት ስሩ ብለው በግድ እንዲህ አልፎ

---

[210] ብላታ ዳኛው ሞገሴ አግዛ ጋርዳ ቀበሌ፣ ሹምታ ደሽ ፣ ቃለመጠይቁ የተደረገበት ቀን 21/07/2007
[211] የሰማይ ቁጣ፡- በረዶ፣ መብረቅ፣ ሀይለኛ ውሽንፍርና ዝናብ፣ ነፋስ የመሳሰሉት ከፈጣሪ ዘንድ የሚሰጥ ቅጣት ናቸው ተብለው ይታመናሉ፡፡

> አልፎ ቢያርሱት ድንቹን እንዳል አስቀረብን፤ በረድ መታን፡፡ በስራው ቀን የሰራነውን ተባረከልን ይበቃናል፡፡ እንኳን አሁን ይቺን የበሬ ግንባር የምታክል መሬት ቀርቶ ሞፈር ዘመትም[212] እናርስ የነበረው በዚሁ ባባት አደሩ ባህል ነው፡፡ ይህ የማይሻር ነው፡፡ ተፈጣሪ ያጣላል፤ ኧረረ! የማንስ ያለህ ይባላል፡፡[213]

አካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ በበአላት ማረስ ፈጣሪያቸው ዘንድ "የሰማይ ቁጣ"ን የመሰለ ቅጣት ያስቀጣል ብለው ያምናሉ፡፡ በዚህም መሰረት እስካሁን ድረስ እያከበሩት ይገኛል፡፡ ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላውና እስካሁን ያልተቀየረው ልማድና እምነት "ቁጥር" ነው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ "ሶስት" ቁጥር ትልቅ ቦታ አለው፤ ከብዙ ነገር ጋር ይገናኛል፤ ማህበረሰቡ የክርስትና እምነት ተከታይ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የስላሴን ሶስትነት፣ የክርስቶስን ሶስት ቀን በከርሰ ምድር መቆየት፣ ዮናስ በአሳ ነበሪ ሆድ ሶስት ቀን ማደር (ት.ዮ፡2÷1)፣ … ሲያያዝ፣ ምስክርነት በሶስት ይጸናል፣ ምርቃት በሶስት ሰው ያሳርጋል፡፡ ይህ አሁንም ድረስ ያለና የቀጠለ እምት ነው፡፡

ይህ ቀጣይነት ያለምንም ለውጥ ሳይነካካ ይቀጥላል ማለት አይደለም፡፡ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ ከጊዜው ሂደትና መርዘም የተነሳም የሚለወጡ ነገሮች መኖራቸው አይቀሬ ነው፡፡ ምክንያቱም ቀጣይነትና ለውጥ የማይነጣጠሉ የፎክሎር ገጽታዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ በተፈጥሮም ይሁን በሰው ሰራሽ ነገሮች ምክንያት ለለውጥ መጋለጡ አይቀሬ ነው፡፡

---

[212] ሞፈር ዘመት፡- ከአንድ ቀበሌ ወደ ሌላ ቀበሌ ወይም ወረዳ ሂዶ ማረስ
[213] ቄስ ወርቁ ወልደ ጊዮርጊስ፣ አግዛ ጋርዳ ቀበሌ፣ ወዳሽቲ ደሽ፤27/09/2007

# ምዕራፍ ስምንት

# ማጠቃለያና ይሁንታ

## 8.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ትኩረት "የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ትንተና በጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ" የሚል ነው፡፡ በዚህም መሰረትነት በጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ የሚገኙ ገበሬዎች የባህላዊ ግብርና እውቀታቸው ምንድን ነው? እንዴት ይገለጻል? እንዴትስ ይተላለፋል? ቀጣይነቱና ለውጡስ ምን ይመስላል? ከዚሁ ጋር የተያያዙት ስነቃሎች፣ ልማዶችና እምነቶች እንዴት ይተገበራሉ? የሚሉትን ማየት የዚህ ጥናት ዋና ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከዚህ ከጥናቱ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ቀደምት ስራዎች፣ ጥናቶች ተቃኝተው የሚያመሳስላቸው እና የሚያለያያቸው ጉዳይ ተብራርቶ ቀርቧል፡፡

የጥናቱ ዋና ትኩረት የሆነው ባህላዊ የግብርና ዕውቀት ትንተና ከማሳ ዝግጅት እስከ ሰብል ስብሰባ ድረስ ያለውን የተመለከተ ሆኖ በነዚህ ወቅቶች ገበሬው የሚያነሳቸው ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ስነቃሎች ልማዶችና እምነቶች ለምን እንደሚተገበሩ? እንዴት እንደሚተገበሩ እና የት እንደሚተገበሩ? ትርጓሜ ተሰጥቷል፡፡

ይህም የጥናቱን ንድፈ ሃሳብ፣ ጽንሰ ሃሳብና የጥናቱን ዘዴዎች መሰረት በማድረግ የተከናወነ ነው፡፡ ጥናቱ ፎክሎር የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ቃሉ በአንድ አካባቢ የሚኖሩና የጋራ የሆነ ዕውቀት ያስተሳሰራቸው ማህበረሰቦች የሚመለከት እንደሆነ በጥናቱ ተገልጿል፡፡ "ለፎክሎር አንድ ወጥ ብያኔ እንደሌለው ሁሉ አንድ ወጥ የሆነ የፎክሎር ጥናታዊ ዘዴም የለም..." (Goldstein, 1964፡2) Goldstein ገለጻ ፎክሎርን ለማጥናት አንድ ወጥ የሆነ የምርምር ዘዴ እንደሌለና የተለያዩ ዘዴዎች መጠቀም እንደሚቻል ያሳያል፡፡ የራሱ የሆነ የጥናት ዘዴም ሆነ ንድፈ ሀሳባዊ መሰረት

የሌለው መሆኑም በምእራፍ ሶስት ስር መጠቀሱ ይታወሳል፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ ግቡን ይመታ ዘንድ የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

በመረጃ ትንነተናውም በምእራፍ አምስት የባህላዊ የግብርና ዕውቀት ለመተንተን ማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብንና ሥነ-ፋይዳዊ ንድፈ ሃሳብን፣ መሰረት በማድረግ በአውዳዊና በተምሳሌታዊ የመተንተኛ ዘዴዎች ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በዚህም ገበሬው ስራውን በዘፈቀደ የሚያከናውን ሳይሆን የዓመቱን ወራቶች እኩል አራት ቦታ በወቅቶች በመከፋፈልና ለየወቅቶችም ከስራው ጋር ተዛማጅነት ያለው ስያሜ ማለትም ግቢ (ከክረምቱ በፊት ያለውን)፣ ክረምት (የዝናቡን ጊዜ)፣ ጥቢ (የክረምቱን መውጫ) እና መኸር (የሰብል መሰብሰቢያ ጊዜን) ብሎ በመከፋፈል ከጊዜው ዝንፍ ሳይል ተግባሩን በጊዜው ያከናውናል፡፡ በተለይም በግቢ ወቅት የዝናብ ቀድሞ ወይም ዘግይቶ መምጣት ለእርሻ ስራቸው ወሳኝ ስለሆነ በባህላዊ ግብርና እውቀታቸው ባዳበሩት ልምድ ባህላዊ በሆነ መንገድ ድንጋይ ፈንቅለው በሚያዩት ምልክት ማሳቸውን ያዘጋጃሉ፡፡

በዚህም የዝናቡ ሁኔታ የሰብሎችን መዘሪያ ወቅት ሳይለቅ ወደፊትና ወደኋላ በማድረግ እንደሚዘሩ በጥናቱ ታይቷል፡፡ የዝናቡ ሁኔታ ተጽእኖ ቢያሳድርበትም በጊዜ ሂደት በልምድ ያዳበረውን ዕውቀት ተጠቅሞ ችግሮችን በመቋቋም ይሰራል፣ ያመርታል፣ በዚህ መንገድም ኑሮውንም ሆነ ህይወቱን እንደሚገፋ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

ገበሬው ከመስክ ላይ ያለ ድንጋይን በመፈንቀል ከውስጡ የሚወጡ ነፍሳትን በመመልከት የዝናብን የአመጣጥ ሁኔታ መተንበይ ይችላል፡፡ ይህንም መሰረት አድርገው ማሳቸውን ያዘጋጃሉ፡፡ በትንበያቸው መሰረት ዝናቡ ቀድሞ የሚጀምር ከሆነ የመዝሪያ ጊዜውን ሳይለቅ በመዝሪያው ወቅት መጀመሪያ አካባቢ ይዘራሉ፡፡ የሚዘገይ ከሆነ ደግሞ በመዝሪያው መጨረሻ አካባቢ ይዘራሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉበት ምክንያትም ከጊዜው ቀድሞ የመጣ ዝናብ በእሸቱ ወራት መጠኑ ይቀንሳል፣ ዘግየት ብሎ የጀመረው ደግሞ በጥቢ ወቅት ዝናቡ ይከብድና በፍሬው ወራት ፍሬውን

ያረግፈዋል፤ ይህ እንዳይሆን ለመከላከል የዝናብ ትንበያውን እንደሚጠቀሙበት በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በሥራ ወቅቶችም የዓመቱ ወራት ስራዎችን ከፋፍሎ በሰዓቱና በጊዜው ይሰራል፡፡ በግቢ ወቅት እርሻ በማረስ መሬቱን አለስልሶ ለዘር ያዘጋጃል፡፡ በመጋቢት፣ በሚያዚያና በግንቦት የሚዘሩ የእህል አይነቶችን ይዘራል የሚታረመውን አረም ያርማል፤ የሚኮተኮተውን ይኮተኩታል፤ ለቀጣዩ ወቅት ማሳዎችን ለዘር ያዘጋጃል የጤፍና የዳጉሳ ማሳዎችን ያለሰልሳል፤ ይጎለጉላላ ያበራያል፣ ይዘራል፡፡ ቀደም ብለው የተዘሩትን ያርማል ይኮተኩታል፡፡ በክረምቱ ወቅት የሚዘሩ ያሉትን ያህል በነሐሴ የሚታጨድና ለምግብነት የሚደርስ ገብስም እንዳለ ጥናቱ አሳይቷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በጥቢና በመኸር የሚያከናውናቸው ተግባሮች አሉት፡፡ ጥቢ በክረምት የተዘሩት ሰብሎች አረም የሚታረምበት፣ ሰብልን ከወፍና ከእንስሳት የሚጠበቅበት ጊዜ ነው፤ "ልጅን በጡት እህልን በጥቅምት" እንደሚባለው፡፡ ዘር መዝራት፣ እርሻ ማረስ እና የደረሱ የደረሱ ሰብሎችን ማጨድ የዚህ ወቅት ስራዎች ናቸው፡፡ መኸር ሁሉም ሰብል የሚታጨድበት፣ የሚሰበሰብበት፣ የሚወቃበት እና ገበሬው የልፋቱን ውጤት የሚያይበት ጊዜ መሆኑ ለማየት ተችሏል፡፡

ከወቅቶቹ ጋር ቁርኝቱን ጥብቅ አድርጎ የሚሰራው ገበሬ በስራ ወቅቶቹ ተግባሮቹን ሲያከናውን የሚፈጽማቸውና የሚላቸው ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሆኑ ስነቃሎች፣ ልማዶች፣ እምነቶች አሉት፡፡ በስነቃሉ ሰነፉን ገበሬ ይነቅፍበታል፣ ጠንካራውን ያወድስበታል፣ የደረሰበትን ችግርም ሆነ በደል ይተነፍስበታል፤ ተቃውሞውን ይገልጽበታል፡፡ እየሰራ ያንጎራጉራል፣ ያቅራራል፤ ከብቶቹን ያሞጋግሳል፡፡ በልማዶቹና እምነቶቹ ለተትረፈረፈ ምርት፣ ለሰላም፣ ለፍቅር፣... አምላኩን ይማጸንበታል፡፡ ይደርስብኛል ብሎ ከሚያስበው መጥፎ ነገር ይከላከልበታል፡፡ በዚህም ገበሬው ባህሉንና ወጉን ልምዱንና እምነቱን ይጠብቃል፡፡

ባጠቃላይ ስነቃሉን፣ እምነቱንና ልማዱን እንደ መሳሪያ በመጠቀም ብሶቱን በመተንፈስ እራሱን ከድካም አላቆ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በምናቡ ድካምን፣ በደልን እንደሚረሳበትና፤ ውስጣዊ እርካታን እንደሚያገኝበት በጥናቱ የታዩ ፍሬ ሀሳቦች መካከል ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በምርት ሂደት ወቅትም ባህሉን ጠብቆ ከዘመናዊው ጋር አቻችሎ ለመሄድ ጥረት ሲያደርግ ይስተዋላል፡፡ ከሕይወት ተሞክሮው ካገኘው ልምድና ዕውቀት በመነሳትም ባህላዊ የማዳበሪያ አጠቃቀሙን ተከትሎ ሳይንሳዊው ማዳበሪያ ለአንድ ዓመት ጥሩ ምርት ቢሰጥም ለቀጣይ ዓመት መሬቱን ስለሚጎዳውና ባህላዊው ደግሞ ምርቱ ዝቅ ያለ ቢሆንም ቢያንስ ለሁለትና ለሶስት ዓመት የመሬቱን ለምነት ስለሚጠብቅለት በማሳው ላይ ሁለቱንም የማዳበሪያ አይነቶች በማቻቻል ሲጠቀም ይስተዋላል፡፡ ማዳበሪያዎቹን ሲጠቀምም በእርሻው ጊዜ ባህላዊውን በዘር ጊዜ ደግሞ ሳይንሳዊውን ሲጠቀሙ በጥናቱ የተስተዋለ ሲሆን ለፍሬው ሳይንሳዊውን ለመሬቱ ለምነት ደግሞ ባህላዊውን እንደሚጠቀም በጥናቱ ለማየት ተችሏል፡፡

የባህላዊ ግብርና ዕውቀት አይነትና ተስተላልፎ የሚለው ክፍል በማህበራዊ ሥነ-ዕውቀት እና በሥነ-ፋይዳ ንድፈ ሀሳቦች መሰረትነት እና በተምሳሌታዊና በአውዳዊ የመተንተኛ ዘዴዎች አማካኝነት ከአውዱ የተሰበሰበው መረጃ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ በሚካሄድበት አካባቢ የሚኖረው ማህበረሰብ ሶስት የዕውቀት አይነቶች ያሉት ሲሆን የግለሰብ፣ የቡድንና የማህበረሰብ ዕውቀት ናቸው፡፡ የማህበረሰቡ ዕውቀት ሁሉም የሚያውቀውና ከአያት ከቅድመ አያቶቹ፣ ከእናት ከአባቱ እንደወረሰው፣ እንደለመደው የሚናገረው ዕውቀት ሲሆን ሌላው የቡድንና የግለሰብ ዕውቀት ነው፡፡ የቡድንና የግለሰብ ዕውቀት በተሞክሮ በምልከታ እና በተለያየ መንገድ የሚገኝና የሚዳብር ነው፡፡ ይህም ዕውቀት ከግለሰብ ተነስቶ እስከ ማህበረሰብ፣ ከማህበረሰብ ተነስቶ እስከ ግለሰብ ድረስ የሚደርስ ነው፡፡ የግለሰብንም ሆነ የቡድንን ዕውቀት ማህበረሰቡ ተቀብሎ እውነትነቱንና ተግባራዊነቱን ፈትሾ ካላረጋገጠና ካላጸደቀው በስተቀር ተግባራዊ ሊሆን

እንደማይችል በጥናቱ ታይቷል፡፡ ማህበረሰቡ፣ ግለሰቡ ወይም ቡድኑ ለፈጠረው ስራ የባለቤትነቱን መብት አክብሮ የሚጠብቅለት መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

ዕውቀት ከተጎራባች አካባቢዎች፣ ከግብርና ሰራተኞች... ወደ ማህበረሰቡ ይገባል፡፡ ከማህበረሰብም ወደ ሌሎች (ወደ አካባቢው) ይተላለፋል፡፡ ተስተላልፎው ግን መጀመሪያ በተቀበሉበት መንገድ ሳይሆን በራሳቸው መንገድ አሻሽለውና ጨምረውበት ያስተላልፉታል፡፡ መተላለፊያ መንገዱም ቃላዊ፣ ተግባራዊና አውዳዊ እንደሆነ በዚህ ጥናት የታየ ሲሆን የሚተላለፍበት የተለያዩ ማህበራዊ አውዶች እንዳሉ ጥናቱ ያመላከታቸው ናቸው፡፡

የአካባቢውን ማህበረሰብ አንድ ያደረገውና ያስተሳሰረው ክር እንዳለ በጥናቱ ያሳየ ሲሆን ይህም ከባቢያዊ ሁኔታው አውዱ እና የባህላዊ ግብርና ዕውቀት እንደሆነ ለማየት ተችሏል፡፡

ለውጥና ቀጣይነት የፎክሎር አንዱ ባህሪ ነው፡፡ በዚህም የባህላዊ ግብርና ዕውቀቱ፣ ስነቃሉ፣ ልማዱና እምነቱ በለውጥ ሂደት ውስጥ እያለፈ ያለውን ያህል ቀጣይ ሆኖ እየዘለቀ ነው፡፡ ለውጡ ያረፈባቸው ሰብሎች፣ ከባቢያዊ ሁኔታው፣ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ምክንያት የተከሰቱ ናቸው፡፡ ለዚህም ዋና ምክንያት ሆኖ የሚጠቀሰው የስው ቁጥር መብዛት ነው፡፡


ባጠቃላይ በዚህ ጥናት በመረጃ ትንተናው ወቅት የታዩት ገናን ነጥቦች፡-

1. ገበሬው በአካባቢው ያያቸውን ወይም ያገኛቸውን ነገሮች ከራሱ፣ ከባህሉ፣ ከእምነቱና ልማዱ ጋር አስማምቶ፣ ፈትሾና አረጋግጦ ካልሆነ በስተቀር አይቀበልም፡፡ አስገዳጅ ነገር እንኳን ቢኖር ለራሱ አማረጮችን ይወስዳል፡፡
2. በአሁኑ ሰዓት ለሁሉም አካባቢ የሚሰጠውን ዩሪያና ዳፕ ለማንኛውም የእህል አይነት እንደሚጠቀሙበት ባህላዊ ማዳበሪያውን አይጠቀሙም፡፡ እንደ ተክሉ

እንደ መሬቱ አይተውና ለይተው ይጠቀማሉ፡፡ እርጥበት ላለው መሬት አመድን፣ ለድንች መሬት የፈረስ ፋንድያና የበጎችን በጠጥ፣ ከድንች ውጪ ላሉት ደግሞ የከብቶችን ፍግ ይጨምራሉ፡፡ ይህም ተክሉን ከተባይ ለመከላከል ይጠቅማል፡፡ ይህ በልምድ ያዳበረው ዕውቀት ነው፡፡

3. ገበሬው የባህላዊ ግበርና ዕውቀት በተግባር ድርጊቱ በሚከናወንበት አውድ፣ ለልጆቹ፣ ለጓደኞቹ፣ በማህበራዊ ግንኙነት ቦታዎች፣ ለቡድኑ ወይም ለማህበረሰቡ ያስተላልፋል፡፡
4. በባህሉ የማይነኩ የተከለከሉ ነገሮችን መንካት፣ የማይደረጉ ነገሮችን ማድረግ በጥቅምትና በሚያዚያ የሥንዴና የጤፍ ማሳን ማረስ፣ በበአላት ቀን ማረስ ዋጋ ያስከፍላል ብለው ያምናሉ፡፡
5. ገበሬው በራሱ ከከፋፈላቸው ወቅቶች ጋር የሕይወት ምህዋሩ በጥብቅ የተሳሰረ/ የተቆራኘ ነው፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ የገበሬው ባህላዊ የግብርና ዕውቀት ተደጋጋሚና ዑደታዊ ነው፡፡ ዑደቱ ከቀን ከወቅትና ከሕይወት ጋር በእጅጉ የተሳሰረ ነው፡፡ ዕውቀትም፣ የሕይወት ተሞክሮውም ሆነ ልምዱ የሚመነጨው በዚህ ሂደት ውስጥ ነው፡፡ ኡደቱ ቋሚ አይደለም የማያቋርጥ እንጂ፣ በዚህም በማጠቃለያው ላይ ያለው ምስል የሚያመላክተውም ይህንኑ ነው፡፡ ምስሉ የሚከተለውን ይመስላል፡፡




ምስል 2፦ ማጠቃለያ ምስል[214]

[214] በአጥኚዋ የተዘጋጀ

በመጀመሪያ በምስሉ ዙሪያ ያሉት የተለያየ ቀለም ያላቸው ቀስቶች የማህበረሰቡን እይታ መሰረት በማድረግ የየራሳቸው የሆነ ውክልና የተሰጣቸው ናቸው፡፡

**ብርቱካናማው ቀለም፡-** የአካባቢው ማህበረሰብ ጥዋት ፀሐይ ገና ልትወጣ ስትል ከሚኖራት ቀለም ጋር ያያዩዝታል፡፡ ብርቱካናማ ቀለም ከጊዜ፤ ንጋትን/ጥዋት የወክለ ሲሆን ንጋት የጨለማውን መገፈፍና በብርሃን መተካት የምናውቀበት የሁሉ ነገር መጀመሪያችን (ለሥራ፣ ለጸሎት፣ ለትምህርት…) የአዲስ ነገር መነሻ ነው፡፡ ይህ ቀለም በወቅት፡- ጥቢን ይወክላል፡፡ ጥቢ የክረምቱ ማብቃት የሚታወቅበት፣ አዝመራው የሚያሽትበት፣ ክረምቱ/ የጨለማው ጊዜ የሚያበቃበት፣ ልጆች በመስክ ጠግበው የሚገቡበት፣ እንስሳት የሚቦርቁበትን ጊዜ ነው፡፡ ቀለሙ ባጠቃላይ የተስፋ ምልክት ነው፡፡ ይህ ተስፋ ደግሞ ወደ ውጤት፣ ወደ ፍሬ ይሸጋገራል፡፡

**ቡኒ ቀለም፡-** በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ለፍሬ መድረስን፣ መጎምራትን መብሰልን፣ የሚያመላክት ነው፤ ይህም የምኞትና የተሰፋ ወጤት እውን የሚሆንበት ነው፡፡ ይህ ቀለም ከጊዜ፡- እኩለ ቀንን ቀትርን ይወክላል፤ ይህም ጥዋት የተጀመረ ስራ የሚገባደድበት ሙቀቱ ጠንከር የሚልበት ነው፡፡ እንቅስቃሴው እየፈጠነ የሚሄድበትና እረፍት የሚወሰድበት ጊዜ ነው፡፡ ቡኒ ቀለም ከወቅት፡- መኸርን ይወክላል፤ በመኸር ወቅት ዓመቱን ሙሉ የተለፋበት ሰብል ሁሉ አፍርቶና ጎምርቶ ለፍሬ የሚበቃበት እና የሚሰበሰብበት ነው፤ ገበሬው መጠነኛ እረፍት የሚያገኝበት ነው፡፡ ባጠቃላይ ቡኒ ቀለም መብሰልን ለፍሬ መድረስን የሚያመላክት ነው፡፡

**ግራጫ ቀለም፡-** በማህበረሰቡ ዘንድ የደበዘዘና ቀዝቃዛ ነው፡፡ ይህ ቀለም ከጊዜ ምሽትን ይወክላል፡፡ ምሽት ወደጨለማው መንድርደሪያ እና ቀዝቃዛ ነው፡፡ ሰውም ሆነ ከብቱ ቀጣዩን የጨለማ ጊዜ ለማሳለፍ ወደ ቤት የሚሰበሰብበት ነው፡፡ ከወቅት ግቢን /በልግን ይወክላል፡፡ ግቢ ወደ ክረምቱ መቃረቢያ ጊዜ ነው፡፡ ማሰብን ማሰላሰልን ማስተዋልን የሚጠይቅ ጊዜ ነው፡፡ ልክ በምሽት ሰውና እንስሳት ወደ ቤት እንደሚገቡ ሁሉ ለክረምቱ ማሳለፊያ የሚሆነው ማገዶ የሚሰበሰብበትና ወደ ደረቁ ቦታ ወደ ቤት የሚገባበት ነው፡፡ የስጋት ጊዜ ነው ቀጣዩን ወቅት በማሰብና በመፍራት፡፡ የቀኑን ማለቅ ምሽቱ እንደሚነግረን ሁሉ የክረምቱን መድረስም ግቢ/ በልግ ይነግረናል፡፡ ፍርሃት የሚረብበት ነው፤ መጪውን በመፍራት፡፡

**ጥቁር ቀለም**፡- ጥቁር ቀለም በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የሀዘን፣ የችግር፣ የመከራ፣ የመጥፎ ነገር ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በዚህም መሰረት ጥቁር ቀለም በጊዜ፤- ጨለማ/ሌሊትን ይወክላል፡፡ መከራን ጭንቀትን ይወክላል፡፡ ይህ ሰዓት ጨለማ ነው፡፡ ንጋቱ እስኪመጣ ድረስ ጨለማው አስፈሪና ከባድ ነው፡፡ የሚሆነውን ነገር ሁሉ በማሰብና በመፍራት ያልፋል፡፡ ይህ ቀለም በወቅት ደግሞ ክረምትን ይወክላል፡፡ ክረምት በገበሬው ዘንድ የጭንቀትና የመከራ፣ የችግር ጊዜ ነው፡፡ ያለው ሁሉ ተሟጦ የሚዘራበትና የሚበላ የሚያጥርበት ጊዜ ነው፡፡ ማገዶ የሚቸግርበት፣ ልክ እንደሌሊት ሁሉ አሰቸጋሪ ወቅት ነው፡፡ ገበሬው ዝናቡን ተስፋ አድርጎ የሚዘራበት፣ የሚያርምበትና የሚነከባከብበት ጊዜ ነው፡፡ የዘራውን ጎርፍ ጠራርጎ እንዳይወስድበት ተከብክቦ የሚሰራበት፣ የጎርፍ መውረጃ ቦዮችን የሚያዘጋጅበት ነው፡፡ በግቢ ከጨመረው ባህላዊ ማዳበሪያ ጋር ሳይንሳዊውን የሚያቀላቅልበትና የሚዘራበት ጊዜ ነው፡፡ የተዘራው ሰብል ለፍሬ ይደርስ ይሆን ብሎ የሚያስብበት፣ ከብቶቹንና ቤተሰቡን ደረሽ ጎርፍ እንዳይወስድበት፣ ከብቶቹን ዋኽማ እንዳይገድልብት የሚፈራበት ጊዜ ነው፡፡ ባጠቃላይ የስጋትና የፍርሃት ጊዜ ነው፡፡

እነዚህ ካላይ ያየናቸው ኡደቶች **ወቅትና ጊዜ** ከገበሬው ጋር በጥብቅ የተቆራኙ ናቸው፡፡ ገበሬው በግቢ/በልግ ላይ የዘራው እህል ሞቶ በጥቢ አብቦ ተስፋ ሆኖ ይታያል፡፡ በመኸር አፍርቶ አዲስ ዘር ይሰጣል፡፡ ጊዜም እንዲሁ ጥዋት፣ ቀን ምሽትና ማታ/ ሌሊት ከዚሁ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ዕውቀት የሚፈጥረውም ሆነ ስራውን የሚተገብረው በዚሁ ኡደት ነው፡፡ ኡደቱ ግን በቀስቶቹ እንደምንመለከተው ወጣ ገባ ነው፡፡ ይህም የገበሬው ህይወት አልጋ ባልጋ አይደለም፡፡ ህይወቱ መሰናክል የበዛበትና ለችግሮቹ መፍትሄ እየፈለገ በማያቋርጥ ሂደት ውስጥ አሁንም ያለ ወደፊትም የሚቀጥል ነው፡፡ በውስጥ ያሉት ቀስቶች የዕርስ በዕርስ ትስስሩን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ገበሬው በህይወት ለመኖርም ሆነ ለመለወጥ የኑሮው ዘይቤ የተመሰረተው በግብርናው ላይ በመሆኑ ሁልጊዜ ያለ መሰልቸት ትኩረቱን ግብርናው ላይ ያደረገ ነው፡፡ በዚህ ወቅትም በርካታ የህይወት መሰናክሎች ቢያጋጥሙትም በህይወት ተሞክሮው በዳበረው የኑሮ ዘይቤ መሰረትነት ከባህሉ ጋር እያዋኻደ ችግሮችን እየፈታ የሚቀጥልበት መንገድ አለው፡፡

## 8.2. ይሁንታ

1. የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ እስካሁን ድረስ የዘለቀ እንደሆነ በጥናቱ ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ይሁንና የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ሲጠና በብዛት አይስተዋልም፡፡ ስለዚህ ዕውቀት ለቀጣይ ትውልድ በሰነድነት የሚቆይበት መንገድ ቢመቻች፤
2. ይህን የባህላዊ ግብርና ዕውቀት የሚጠቀሙ ገበሬዎች እውቀታቸውን ከረጅም ጊዜ ልምድ ያካበቱት በመሆኑ ይህ ዕውቀት ከዘመናዊው ጋር ተሳስሮ የሚሄድበት መንገድ ቢፈጠር፣
3. ለአካባቢው የአየር ንብረት የሚስማማውን የሰብል አይነት/ ዝርያ ገበሬው ለይቶ የሚያውቀው በመሆኑ በየቀበሌው የሚገኙ ግብርና ሰራተኞቹም ከማስገደድ ይልቅ የገበሬውን ሃሳብ ተቀብለው ቢያጤኑት፣
4. ፖሊሲና መመሪያ አውጭዎችም ከታች የመነሳትና ማህበረሰቡን ዕውቀት መሰረቱን የመመርመርና ተነጋግረው የመስራት ልምድን ቢያዳብሩና አብረው ቢሰሩ፡፡
5. ይህ ጥናት ብዙ ቀርነቶች ይኖሩታልና ሌሎች የመሰኩ ተመራማሪዎች ክፍተቱን ቢሞሉት፤
6. ለዘመናዊው ግብርና መሰረት የሚሆነው ባህላዊው ስለሆነ ለባህላዊ ግብርና ዕውቀት ተኩረት ተሰጥቶት ተቀናጅቶ የሚሄድበት መንገድ ቢመቻች፡፡
7. ማህበረሰቡም በረጅም ጊዜ ልምድ ያዳበረውን ባህላዊ የግብርና እውቀቱን ለተተኪው ትውልድ የሚያስተላልፍበት፣ ልምዱንና ተሞክሮውን የሚያካፍልበት ተለያዩ መድረኮች ቢፈጠሩለት፡፡

# ዋቢ መጻህፍት[215]

## አማርኛ

መጽሐፍ ቅዱስ:: *የብሉይ እና የሀዲስ ኪዳን መጻህፍት*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1980::

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም *መዝገበ ቃላት*:: አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1978::

ሰዋገኝ አስራት:: "ፈረስና የፈረስ ማህበር ማህበረሰባዊ ፋይዳ በባንጃና በጓጉሳሽኩዳድ ወረዳ::" አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ 2002::

ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር:: *የአዊ፣ የሲዳማና የጉርጂ ኦሮሞ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓቶች*:: አዲስ አበባ፣ በአፕል ማተሚያ ቤት *ታተመ*፣ 2006::

ብርሃኑ አሳዬ:: "በባንጃና በአንከሻ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች በአዊ የሚያዜሟቸው የስራ ላይ ዘፈኖች ጭብጥ ገለፃና ትንተና::" አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ 1999::

አሉላ ፓንክረስትና ገብሬ ይንቲሶ:: "ሀገራዊ ዕውቀትና ተዛማጅ ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ::" ሽፈራው በቀለ (አርታኢ):: *ባህልና ልማት በኢትዮጵያ*:: ገጽ 77-96 ፎረም ፎር ሶሻል ሰተዲስ፣ አዲስ አበባ፣ 2004::

አያሌው ሲሳይ:: *የአገው ህዝቦችና የዛጉዌ ሥርወ መንግስት ታሪክ*:: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1997::

ኪዳነወልድ ክፍሌ:: *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፣ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948::

የአዊ ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ:: "የ2004 *አመታዊ ሪፖርት*::" እንጅባራ፣ 2004::

____________:: "2007 *አመታዊ ሪፖርት*::" እንጅባራ፣ 2007::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል:: *አማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993::

[215] የ "MLA" የዋቢ መጽሃፍት አጠቃቀስን መሰረት ደረገ ነው::

የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት፡፡ *አመታዊ መጽሄት*፣ ቲለሊ፣ 2007፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር*፡፡ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2004፡፡

ደስታ ተክለወለድ፡፡ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*፤ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ *የስነቃል መምሪያ*፤ አዲስ አበባ፣ ኢተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም፣ 1991፡፡

__________፡፡ "የመስክ ስራ የስነቃል አሰባሰብ፣ አከለሳሰፍ፣ አተናተን እና አሰናነድ፤" ለ"ባህልና የባህል አመራር ልማት፣ ሀገር- አቀፍ ኮንፈረንስ"፣ ዝግጅት ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ አዲስ አበባ፣ 1999፡፡

__________፡፡ "ቁዘማ: ፎክሎር /ባህል/ እና ልማት በኢትዮጵያ፤" ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፤ ፎረም ፎርሶሻል ስተዲስ፤ አዲስ አበባ፣ ኢሲሊፕስ ማተሚያ ቤት፣ 2004፡፡

ዣን ክሎድ ኮርመይ፡፡ *ስዕላዊ መዝገበ ቃላት*፡፡ አዲስ አበባ፣ አሳታሚ የትምህርት መሳሪያዎችና ማከፋፈያ ድርጅት፣ በ1984 በመጀመሪያ በአማርኛ ተተርጉሞ ታተመ፡፡

## English

Abera Ogata. "Indigenous common grazing Land Management in Chencha Woreda, South Ethiopia." MA Thesis in Regional and Local Development, Addis Ababa University, Addis Ababa, 2006.

Agrawal, A. "Dismantling the divide between Indigenous and Scientific Knowledge." *Development and Change.* Vol. 26, No 3, (1995). 413-439.

Akullo, D. and Knzikwera, R. Indigenous Knowledge in Agriculture: A Case Study of the Challenge in Sharing Knowledge of Past Generation in Globalization in A Globalized Context in Uganda. Worled Liberary and Information Congress: *73rd IFLA General Conference and Council.* Durban, South Africa, 2007.

Alemayehu Moges. "Traditional Ethiopian Medicine." *The Eighth International Conference of Ethiopian Studies.* Addis Ababa, 1984. pp. 109-144.

Alemu Alene. "The Use of Indigenous Knowledge for the Management of Crop Production Constraints: The Case of Awi Community in Ankesha Guogusa Woreda." M.A. Thesis, Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa University, Addis Ababa, 2008.

Anan, P. "Indigenous Agricultural Knowledge- A Sample Practice in Northeast Thailand." *International Journal of Environmental and Rural Development.* Department of Plant Science and Agricultural Resources, KhonKaen University, Thailand, 2010. pp. 68-73.

Atteh, D. *Indigenous Local Knowledge as Key to Local Level Development: Possibilities, Constraints and Planning issues in the context of African Studies in Technology and Social Change.* Ames: Towa State. USA. Towa University, No. 20, 1992.

Bahru Zewude. *A History of Modern Ethiopia 1855-1974.* Addis Ababa: Addis Ababa University Press. 1991.

Bascom, W. *Four Functions of Folklore.* Journal of American Folklore. Vol. 67. No. 266. (1954). pp. 333-349.

Bauman, R. "The Field Study of Folklore in Context." *In: Hand Book of American Folklore*, edited by Richared M. Dorson with Inta Gale Carpenter, Bloomington. Indian University Press, 1983. pp, 362- 368.

________. *Story Performance and Event.* Cambridge University Press, 1986.

________. (ed.) *Folklore, Cultural Performance, and Popular Entertainments: A Communication-Centered Hand book.* New York: Oxford University Press, 1992.

Bayleyegn Tasew. *Metaphors of Peace and Violence in the Folklore Discourse of South Western Ethiopia: A Comparative Study.* Amsterdam: VU University Press, 2009.

Bekalu Molla. "Traditional Agricultural Practice and Resource Management among the Agew of Gojjam." MA Thesis, Deparetment of Social Anthropology, Addis Ababa, Addis Ababa University, 1994.

Ben-Amos, D. "Toward a Definition of Folklore in Context." *Journal of American Folklore.* 1971.

________. "Context in Context" Western Folklore," *Theorizing Folklore: Toward New Perspectives on the Politics of Culture.* Vol. 52, 1993. No 2/4, p 209-226.

________. *Theorizing Folklore: Towards New Perspective on the Politics of Culture,* 1993.

________. "Folklore in Context." *Journal of African Studies,* 15 (3): 2006. pp. 24-255.

Berger, P. & Luck Mann, T. *The social construction of reality: A treatise in the sociology of knowledge.* New York: Doubleday, 1966.

Bernard, R. *Research Methods in Anthropology: Qualitative and Quantitative Approach's* 4th ed. Lanhum: Altamira Press, 2006.

Brousile P. et al. "Ethno ecology: An Approach to Understanding Traditional Agricultural Knowledge:" *Traditional Agriculture in Southeast Asia*: A Human Ecology perspective, Westview Press (Boulder, Colorado), 1986.

Bulmer, R. 1974. *Folk biology in the New Guinea highlands. Social Sciences Information 13: pp.9-28.*

Catherina, B. *Ritual: Perspective and Dimensions.* Oxford: Oxford University, 1997.

Catherine, D. *A practical Guide to Research Methods* A Frined *Manual for Mastering Research Techniques and Projects.* British Liberary Cataloguing in Publication, Oxford United Kingdom, 2007.

Central Statistical Agency (CSA). The 2007 Population and Housing Census of Ethiopia. Addis Ababa: Branna Printing Enterprise, 2010.

Creswell, W. *Qualitative Inquiry, and Research Design*: Chosing Among Five approaches. London: Saga Publication, 2002.

______. *Qualitative Inquiry Research Design: Choosing Among Five Approaches.* (2nded.) Thousand Oaks, London, New Delhi: Sage Publications, Inc., 2007.

Crotty, M. *The Foundations of Social Research: Meaning and Perspective in the Research Process.* London SAGE Publications, 1998.

Cliford, J. The Predicament of Culture: Twentieth-Century Ethnography, Literature and Art. Cambridge, mass., Harvard University Press. 1988.

Denscomde, M. *The Good Research Guide for Small-Scale Social Research Project 3rd Ed.* England: Open University Press, 2007.

Denzin N. and Lincoln Y. (eds.) *Hand book of Qualitative Research.* London SAGE Publications, 2000.

Desalegn Abera. "The Role of indigenous knowledge and water harvesting in sustainable agricultural system in Tigray, Ethiopia." PhD Dissertation, Saskatoon, University of Saskatchewan, 2006.

Desalegn Amsalu. "Traditional Association in Rural Ethiopia." M.A. Thesis, School of Graduate studies, Addis Ababa University, 2007.

Dorson, R. *Folklore and Folk life: An Introduction.* Chicago, the University of Chicago Press, 1972.

Dundes, A. *The Study of Folklore*. Englewood: N.J. prentice Hall Inc., 1965.

_______. "Who are the Folk? *In interpreting Folklore* pp1-19: Indiana University Press, Bloomington, 1980.

_______. *Folklore Matters: The Psychoanalytic Study of the Grimm's tales.* USA Knoxville: The University of Tennessee Press, 1989.

Ellen, R. Parkes, P. and Bicker, A. (eds.) *Introduction in Indigenous Environmental Knowledge and its Transformations.* Amsterdam, the Netherlands: Harwood Academic Publishers, 2000. pp.1-34.

Emery, R. "The Participation of Indigenous People & Their Knowledge," *in: Environmental Assessment & Development Planning Center for Traditional Knowledge.* Ottowa, Canada, 1996. pp. 16-25.

Fetterman, D. *Ethnography: Step by Step Applied Social Research Methods* Series; Sage Publication, Inc. 2010.

Ferraro, G. *Cultural anthropology an applied perspective*. U.S.A; an international Thomson publishing company,1998.

Finnegan, R. *Oral Literature in Africa*. Nairobi: Oxford University press, 1970.

_________. *Oral Poetry its nature, Significance and social context.* Cambridge: Cambridge University Press, 1977.

_________. *Oral Traditions and The Verbal Art.* Routledage, Inc. New York, 1992.

Firew Mekbib. "Folksong based appraisal of Bio cultural Heritage of Sorghum (*Sorghum bicolor r*(L.) Moench): A new approach in ethno-biology." *Journal of Ethno biology and Ethno medicine*. Vol. 3, 2009. pp.1-18.

_________. "Infra-specific Folk Taxonomy in Sorghum (*Sorghum bicolor* (L.) Moench) in Ethiopia: folk nomenclature, classification, and criteria." *Journal of Ethno biology and Ethno medicine.* Vol. 5, 2007. pp.1-38.

Gamast, F. *The Qemant Agew of Ethiopia: A study in cultural Change of a Pagan-Hebraic Michigan:* University Microfilms Inc. 1968.

Gecall, R. Kenya Folk Tales. Nairobi, East African Literature Bureau, 1970.

___________. *Folkloristic: An Introduction*. USA, Indiana University Press, 1995.

Gibald, Joseph. *MLA Handbook for Writers of Research Papers.* 6th ed. New York: 2003.

Given, L. *The Saga Encyclopedia of Qualitative Research Methods*. London, Saga Publication, Inc. 2008.

Glassi, H. "Tradition" *The Journal of American Folklore*, vol. 108, No 430, Common Ground: key words for the Study of Expressive Culture, American Folklore Society. 1995. pp345-412.

Goldstein, K. *A Guide for Field Workers in Folklore*. London: Folklore Associates, Inc. 1964.

Gorges R. and Michael J. *People Studying People*. University of California Press, 1964.

Green, T. *Folklore*: *An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art.* Santa Barbara California, Denorer Colorado, England, 1997.

Grenier, L. Working with Indigenous Knowledge: *A Guide for Researchers.* IDRC, Ottawa, 1998.

Gusfield, J. and Jerzy, M. "Secular Symbolism Studies of Ritual, Ceremony and, Symbolic Order in Modern Life." *Annual Review of Sociology,* Vol.10, 1984. pp.417-335.

Habtamu Tekelay. "Farmers' Indigenous Agricultural Knowledge Practice in South East Zone of Tigray." M.A. Thesis, Institute of Ethiopian Studies, Indigenous Cultural Studies, Addis Ababa University. 2011.

Haimanot Reta. "An Ethno-botancal Study of Useful Plants of the Farming Site in Gozamne Woreda, East Gojjam Zone of Amhara Region, Ethiopia." MSC in Biology (Botanical Science), Addis Ababa University, 2010.

Hymes, D. "The Contribution of Folklore to Sociolinguistics Research." Toward New Perspectives in Folklore. Eds. Americo Paredes and Richard Bauman. Austin: University Press of Texas Press, 1972. pp.35-71.

Hamlyn D. Epistemology, history of In Honderich T. (ed.) *The Oxford Companion to Philosophy* Oxford, Oxford University Press. (no year)

Hammersley, M. and Atkinson, P. *Ethnography Principles in Practice.* New York, published in the USA and Canada by Routledge, Third edition, 2007.

Henry, B. "The Use and Role of Indigenous Knowledge in Small-Scale Agricultural Systems in Africa: the Case of Farmers? in Northern Malawi." PhD Dissertation, Department of Geographical and Earth Science, University of Glasegawe, 2010.

Houston, D. *Wonderful Ethiopians of the Ancient Cushitic Empire Book I. Nations of the Cushite Empire. Marvelous Facts From Authentic*

*Records*. The Universal Publishing Company Oklahoma City, OKLA, U.S.A. 1926.

Jackson, B. *Fieldwork*. Urbana and Chicago: University of Illinois Press, 1987.

Jaccord J. and Jacob J. *Construction and Model- Building skills A Practical Guide for Social Scientists*. New York: The Gilford Press, 2010.

Julina, F. *Ethnography Research*. Lapan, 2008.

Johnson, A. Individuality and experimentation in traditional agriculture. *Human Ecology*. 1972. *1:149-59.*

Kruger, S. *Ethnography in the Performing Arts: A Student Guide*. Liver Pol: The higher Palatine Education Dance, Derma Academy and Music, 2008.

Kothari, C. *Research Methodology: Methods and Techniques*. india: new age international limited publisher, 1985.

Leslau, W. *English Amharic Context Dictionary*. Belgium; Otto Harrassowitiz - Wiesbaden Printing Press, 1973.

Lioyd-Evans, `S. Focus Group Doing Development Researched. Van Dana. Desai, and Robert B, Potter. London: Saga Publication (no year). pp.153-162.

Mac Donald, A Field Work Collection oral Literature. in Richard Dorson, (ed.) *Folklore and Folk life*: An Introduction. Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Matthews, B. and Ross, L. (*Research Methods: A Practical guide for the Social Sciences.* University of Birmingham, 2010.

Maykut, P. and More, R. *Beginning Qualitative Research A philosophic and Practical Guide.* The Flamer Press, London. Washington. D.C. 1994.

McCann, J. *An Agricultural History of Ethiopia, 1800-1990.* The United States of America, The University of Wisconsin Press, 1995.

Michael Shiferaw. "Liking Indigenous With the 'Conventional' Measures for Sustainable Land Management in the Highlands of Ethiopia: A Case Study of Digil Watershed, East Gojjam." MA, Department of Geography, Addis Ababa, Addis Ababa University, 2002.

Melakneh Mengistu. The Major Themes and Motifs of Southern Agew Folktales. M.A. thesis, School of Graduate Studies, Addis Ababa University, 1990.

Michael. O. (ed.) *Putting Folklore to Use. Kentucky*: University Press of Kentucky, 1994.

Mohapatra, P. "Tribal Pest Control Practices of Tami Nadu for Sustainable Agriculture." *Indian Journal of traditional Knowledge*. Vol. 8 (2), 2009. pp.218-224.

Mullen, P. *Listening to Old Voices*. Urbana and Chicago, University of Illinois Press, 1992.

Murchison, M. Ethnography Essentials: Designing, Conducting and presenting Your Research, SanFrancisco: Jossey-Bass, 2010.

Negash Demssie et.al. "Indigenous Technical Knowledge of Farmers in North Shewa: Soil and Water Conservation and Pest control." In Dejene Aredo (ed.) IKS in Ethiopia: Proceeding of the First National Workshop of the Ethiopian Chapter OSSREA. Addis Ababa. 2005. pp.106-119.

Normala, Othman, and et al. "Indigenous Knowledge and Biodiversity Conservation in Sabah, Malaysia." *International Journal of Social Science and Humanity.* Vol. 2, No. 2, 2012. pp.159-163.

Okpewho, I. *African Oral Literature.* Background Character. Indianapolis: Indianapolis University Press, 2004.

Oring, E. (ed.) Folk Groups and Folk Genres: An Introduction. Logan: Utah State University Press, 1986.

O'Reilly, K. *Ethnographic Methods*. London. Routledge, 2005.

Owuor, A. "Integrating African indigenous knowledge in Kenya's formal education system: The potential for sustainable development." *Journal of Contemporary Issues in Education*, 2(2), 2007. pp. 21-37.

Polthanee, "Indigenous Agricultural Knowledge - A Sample Practice in Northeast Thailand". 2010.

Radcliff-Brown, A. "On the Concepts of Function in Social Science," in American Anthropologist. No. 37. 1935.

Robson, C. *Real World Research, 2nd edition* Oxford Blackwell, 2002.

Rajasekaran, B. and Martin, A. "A Framework for incorporating IKSs into agricultural extension organization for sustainable agricultural development in India." *Paper presented at 9th Annual Conference of the Association for International Agricultural and Extension Education,* Arlington, Virginia USA. 1992.

__________. "A Framework for Incorporating Indigenous Knowledge System into Agricultural Research and Extension Organizations for Sustainable Agricultural Development in India." PhD Dissertation. Ames, Iowa, Iowa State University, 1993.

Robert, A. and Michael J. *Folkloristic: An Introduction.* USA, Indiana University Press, 1995.

Russell, H. *Research Methods in Cultural Anthropology.* London፡ Sage Publication (4th ed.) 1990.

Savage, J. "Ethnographic Evidences the Value of Applied Ethnography in health care". Journal of Research in Nursing: 2006. 383-389. 21 March 2015, <http:// jrn.sagepub.com/content/11/5/383>

Schoemaker, G. (ed.) *The Emergence of Folklore Everyday Life: Field Guide and Source Book.* Bloomington, Indiana: Trickster press, 1990.

Shoko, "Indigenous Weather Forecasting System: A Case Study of the Biotic Weather forecasting Indicators for Wards 12 and 13 in Meringa District, Zimbabwe" 2012.

Sims, M. and Stephens M. *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and Their Traditions.* Utah State University Press / Logan, Utah: 2005.

Spradeley, P. *Participant Observation.* Printed in United States of America, 1980.

Sundamari, M. and Ranganathan, T. *Indigenous agricultural practices for sustainable farming.* Agro bios (India). Jodhpur, India, 2003.

Tadsse Tamerat. Church and State in Ethiopia1270-1527 London, Oxford at the Clearendon Press, 1972.

Toelkon, B. *The Dynamic of Folklore.* Utah State University of Oslo, Institution for Educational Research. 1996.

Warren, D. Using IK for agricultural development. *World Bank Discussion Papers 127. Washington DC: World Bank*, 1991.

_______. "Indigenous Knowledge, Biodiversity Conservation and Development." *International Conference on Conservation of Biodiversity in Africa: Local Initiatives and Institutional Role.* In Nairobi, Kenya, From Aug 30-Sept. 3, 1992.

_______. "Putting Local Knowledge to Good Use." *International Agricultural Development.* Vol. 13 No. 4, 1993. 8-10.

Wolcott, H. *Ethnography: A Way of Seeing.* America: A Division of Rowan & Littlefield Publishers, Inc.1999.

Woldeselassie Abute. "Indigenous Knowledge of Shifting Cultivators and Strategies of Natural Resource Management: The Case of Gumuze in

Metekel North Western Ethiopia." Proceeding of *The Ethiopia Chapter of OSSREA*, 2005. pp.70-105.

Workenehe Abebe. "Identification and Documentation of Indigenous Knowledge of Beekeeping Practices in Selected Districts of Ethiopia." *Journal of Agricultural Extension and Rural Development*. Vol. 3(5), 2011. pp. 82-87.

Workman, M. "Folklore and Literature: From Text to Context." Introduction: Children and Folklore. (ed.) Blatt, Gloria T. New York and London: Columbia University Press, 1993. 131-139.

# አባሪ አንድ፡- የመስክ ጥናት ጥያቄዎች

**አጠቃላይ መግቢያ፡-** የጥያቄው መመሪያ የተዘጋጀው በፎክሎር የትምህርት ዘርፍ ለ3ኛ ዲግሪ (PhD) መርሃ ግብር ለመመረቂያ ጥናት ትምህርታዊ አላማ ነው፡፡

## 1.1. ለቃለ -መጠይቅ መረጃ አቀባይ የቀረቡ የመነሻ ጥያቄዎች

የዚህ ቃለ-መጠይቅ አላማ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ላይ ለ3ኛ ዲግሪ (PhD) ማሟያ ለሚሰራው ጥናት ግብአት የሚሆን መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ለውይይት መነሻ እንዲሆኑ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ከጥያቄዎች እና ከሚሰጡ መልሶች እየተመዘዙ የሚነሱ ጥያቄዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ መረጃዎቹ የሚሰበሰቡት ለትምህርታዊ አላማ ብቻ ነው፡፡ የምትሰጡኝ መረጃም ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ስለዚህ ለዚህ ቃለ መጠይቅ በቀናነት ትክክለኛ የሆኑ መረጃዎችን እንድትሰጡኝ በትህትና እየጠየቅሁ መረጃዎችንም በወረቀት ለመያዝ አስቸጋሪ መሆኑን ተገንዝባችሁ በመቅረጸ ድምጽና በምስል ወድምጽ እንዲሁም በፎቶግራፍ እንድይዝ ቀና ትብብራችሁን እየጠየቅሁ ለምታደርጉልኝ ቀና ትብብርም ከወዲሁ አመሰግናለሁ፡፡

### ሀ. የቃለ-መጠይቅ መረጃ አቀባዮች ግላዊ መረጃ

1. ስም______________________________
2. ዕድሜ ______________________________
3. ጾታ ______________________________
4. ሃይማኖት ______________________________
5. የጋብቻ ሁኔታ______________________________
6. ስራ ______________________________
7. የት/ደረጃ ______________________________
8. ቀበሌ _______________ ጎጥ _______________

9. በአካባቢው የቆይታ ጊዜ ______________________________
10. የገቢ ምንጭ ______________________________
11. የቃለ መጠይቅ ቦታ______________________________
12. የጠያቂው ስም______________________
13. ቃለ መጠይቁ የተካሄደበት ቀን_________

## ለ. ቃለ-መጠይቆች

1. እናንተ በአካባቢያችሁ መሰረትነት ምን ተብላችሁ ትጠራላችሁ?
2. አካባቢያችሁ ምን አይነት የአየር ንብረት አለው?
3. የስንት ዓመት ልጅ ሆነው እርሻ ጀመሩ?
4. የእርሻ ሙያን ከማን እና እንዴት ተማሩት? በምን ታርሳላችሁ? (በበሬ ወይስ በፈረስ) በፈረስ ማረስ መቼ ተጀመረ? ለምን? እንዴት?
5. በዚህ አካባቢ ስንት አይነት ማሳ አለ?
6. አዝመራ ከተሰበሰበ በኋላ እርሻ መቼ ትጀምራላችሁ? ማሳን ለዘር እንዴት ታዘጋጃላችሁ? በዓመት ስንት ጊዜ ታመርታላችሁ? የምርት ወቅቶቹ መቼ መቼ ናቸው? አይነት የማሳ ዝግጅት ታደርጋላችሁ?
7. በዚህ አካባቢ የሚበቅለው የእህል አይነት ምን ምን ነው? ስያሜውን እንዴት አገኘ?
8. አዝመራን ከእንስሳት፣ ከአእዋፋት፣ ከአይጥና ከተባይ እንዴት ትጠብቁታላችሁ? ዘር የሚሆኑ የሰብል አይነቶችንስ እንዴት ትለዩታላችሁ?
9. በግብርና ስራው ላይ የሴቶች፣ የልጆችና የሌሎች የቤተሰብዎ ድርሻ ምንድን ነው?
10. ይህን ከላይ የወረሱትን ዕውቀት ለልጆችዎ በምን መንገድ ያስተምሯቸዋል?
11. አሁን አዳዲስ የአስተራረስና የአመራረት ዘዴ አለ? ከየት መጣ? ከቆየው የአመራረት ዘዴ ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት ምን ይመስላል? (በፊት የነበሩ ሀገር በቀል የእህል ዝርያዎች፣ ምርጥ ዘር፣ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ማዳበሪ፣ የአፈር አጠባበቅ...)

12. ከግብርናው ጋር ተያይዞ የሚባል አባባል፣ ተረት፣ ዘፈን፣ ...ካለ እስኪ ይንገሩኝ
13. ሴቶች በግብርና ሙያ ላይ ይሳተፋሉ? ከተሳተፉስ በምን በምን ስራ ላይ? የማይሳተፉበትስ የስራ አይነት አለ? ካለ ለምን ?

ውድ ጊዜያችሁን መስዋዕት አድርጋችሁ ይህን መረጃ ስለጣችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ!

## 1.2. ተተኳሪ የቡድን ውይይት ጥያቄዎች

የዚህ የተተኳሪ ቡድን ውይይት አላማ በጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ የባህላዊ ግብርና ዕውቀት ላይ ለ3ኛ ዲግሪ (PhD) ማሟያ ለሚሰራው ጥናት ግብአት የሚሆን መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ የምትሰጡኝ መረጃም ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት ስኬትም የእናንተ የቡድን ውይይት ተሳትፎ ወሳኝነት አለው፡፡ ስለዚህ በቀናነት ትክክለኛ የሆኑ መረጃዎችን እንድትሰጡኝ በትህትና እየጠየቅሁ መረጃዎችንም በወረቀት ለመያዝ አስቸጋሪ መሆኑን ተገንዝባችሁ በመቅረጸ ድምጽ፣ በምስልና ድምጽ መቅረጫ እንዲሁም በፎቶግራፍ እንድይዝ ቀና ትብብራችሁን እየጠየቅሁ ለምታደርጉልኝ ቀና ትብብርም ከወዲሁ አመሰግናለሁ፡፡

ሀ. የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊዎች ግላዊ መረጃ

1. ስም____________________________________
2. ዕድሜ __________________________________
3. ጾታ ___________________________________
4. ሃይማኖት ______________________________
5. የጋብቻ ሁኔታ ______________________________
6. ስራ ___________________________________
7. የት/ደረጃ ________________________________
8. ቀበሌ _________________ ጎጥ ________________
9. በአካባቢው የቆይታ ጊዜ ________________________

10. የገበሬ ምንጭ ______________________
11. የቡድን ውይይቱ የተካሄደበት ቦታ______________________
12. የጠያቂው ስም______________________
13. የቡድን ውይይቱ የተካሄደበት ቀን__________

**ለ. የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊ መነሻ ጥያቄዎች**

1) አካባቢያቸሁ ምን አይነት የአየር ንብረት አለው?
2) ዝናብ ቀድሞ ሲመጣ ወይም ሲዘገይ ምን ታደርጋላችሁ?
3) የእርሻ ሙያን ከማን እና እንዴት ተማራችሁት?
4) በምን ታርሳላችሁ? __________ ማረስ መቼ ተጀመረ? እንዴት?
5) አዝመራ ከተሰበሰበ በኋላ እርሻ መቼ ትጀምራላችሁ?
6) ማሳ ዝግጅታችሁ እንዴት ነው?
7) የአፈርን ለምነት እንዴት ትጠብቃላችሁ
8) በዚህ አካባቢ የሚበቅለው የእህል አይነት ምን ምን ነው? ስያሜውን እንዴት አገኘ? ሰብለ መቼ እና እንዴት ይዘራል?
9) አሁን አዳዲስ የአስተራረስና የአመራረት ዘዴ አለ? ከየት መጣ? ከቆየው የአመራረት ዘዴ ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት ምን ይመስላል? (በፊት የነበሩ ሀገር በቀል የእህል ዝርያዎች፣ ምርጥ ዘር፣ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ማዳበሪ፣ የአፈር አጠባበቅ…)

ውድ ጊዜያችሁን መስዋዕት አድርጋችሁ ይህን መረጃ ስለጣችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ!

# አባሪ ሁለት፡- የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጾታ | ዕድሜ | ቀበሌ | ጎጥ | መረጃው የተሰበሰበበት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ሀብታሙ ጌታነህ | ወ | 25 | አደጋ ውባጅ | መሀልአምባ | 29/6/07፣3/7/07፣21/7/2007 |
| 2 | አቶ ልመን ዳኛው | ወ | 57 | አግዛ ጋርዳ | ሹምታ | 29/11/2007 |
| 2 | አቶ ሞላ እንዳላማው | ወ | 54 | አደጋ ውባጅ | | 24/6/2007፣ |
| 1 | አቶ ሞላ ፈቃዱ | ወ | 63 | አደጋ ውባጅ | መሰቀለኛ | 19/11/2007 |
| 1፣2 | ወ/ሮ ሰገዴ ሞላ | ሴ | 28 | አብስላ ዋርዳ | ባኳ | 3/7/07፣27/7/07፣19/11/2007 |
| 1 | አቶ ሽመካ ገዳሙ | ወ | 60 | አደጋ ውባጅ | መሰቀለኛ | 24/6/2007፣ |
| 2 | አቶ በላይ አለማየሁ | ወ | 52 | ›› ›› | ላይ ዘረገማ | 19/11/2007 |
| 3 | አቶ በየነ ኃይሉ | ወ | 38 | ጉሻ | | 17/07/2007 |
| 1 | ቄስ ታየ ታፈረ | ወ | 56 | አብስላ ዋርዳ | ዋህሳ | 24/6/07፣ 3/7/07 |
| 2 | አቶ ታደሰ ዳምጤ | ወ | 60 | ›› ›› ›› | ዳምቢሲ | 21/11/2007 |
| 2 | አቶ ታዴ ደስታ | ወ | 60 | ›› ›› ›› | ›› ›› | 21/07/2007 |
| 1፣2 | ወ/ሮ አለሚቱ ታዬ | ሴ | 40 | አደጋ ውባጅ | መሰቀለኛ | 27/6/07፣21/7/07 |
| 1 | አቶ አለማየሁ ምትክ | ወ | 57 | አብስላ ዋርዳ | ዳምቢሲ | 24/06/07፣22/11/0 |
| 2 | አቶ አሰጋ አየነው | ወ | 85 | አግዛ ጋርዳ | ስሚዞ | 21/11/2007 |
| 1፣2 | ወ/ሮ አስቻል ይሁን | ሴ | 33 | ›› ›› ›› ›› | ሹምታ | 4/9/06፣ 8/7/2007 |
| 3 | አቶ አበራ መኩሪያ | ወ | 60 | ጉደር | | 18/09/2006 |
| 1 | ቄስ አወቀ ተፈራ | ወ | 83 | አብስላ ዋርዳ | ሳሙኤል | 03/7/2007፣ |
| 2 | አቶ አወቀ ታየ | ወ | 57 | ›› ›› | ባኳ መስቀላ | 21/11/2007 |
| 1፣2 | አቶ አየለ አንተነህ | ወ | 83 | አደጋ ውባጅ | ሰባት ዓይና | 22/6/07፣2/7/07፣27/7/2007 |
| 3 | አቶ አያና አለማየሁ | ወ | 60 | አስኩና | | 29/07/2007 |
| 2 | አቶ አይቸው በላይ | ወ | 45 | አደጋ ውባጅ | ላይ ዘረገማ | 29/11/2007 |
| 2 | ወ/ሮ አዳኔ ተክሌ | ሴ | 56 | አብስላ ዋርደ | ሳሙኤል | 29/11/2007 |
| 2 | ወጣት አንዷለም ይሁን | ወ | 23 | አግዛ ጋርዳ | ሹምታ | 21/11/2007 |
| 2 | ወ/ሮ እናት አዛገ | ሴ | 55 | አደጋ ውባጅ | ላይ ጮኸኛ | 21/11/2007 |
| 1 | ቄስ ወርቁ ወልደ ጊዮርጊስ | ወ | 68 | አግዛ ጋርዳ | ወዳሽቲ | 21/9/06፣9/7/07፣ 29/7/2007 |
| 1 | ወ/ሮ ውዴ ተካ | ሴ | 60 | አብስላ ዋርዳ | ሳሙኤል | 3/7/07 |
| 1 | አቶ የትዋለ ከበደ | ወ | 75 | ቲሊሊ | | ከመስከ መልስ በየዕለቱ |
| 3 | አቶ የኔት ፈንታሁን | ወ | 67 | ጀምብር | | 7/07/2007 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ይሁን አድማስ | ወ | 62 | አግዛ ጋርዳ | ሹምታ | 4/9/06፣7/9/06፣15/11/2007 |
| 1 | ብላታ ዳኛው ሞገሴ | ወ | 90 | አግዛ ጋርዳ | ሹምታ | 9/7/2007 |
| 1 | ወ/ሮ ገነቴ ደምለው | ሴ | 63 | ቲሊሊ | | ከመስከ መልስ በየዕለቱ |
| 1 | ወ/ሮ ገነቴ ጌቴ | ሴ | 55 | አግዛ ጋርዳ | ሹምታ | 7/9/06፣ |
| 3 | አቶ ገደፋዬ አለሙ | ወ | 76 | ዳንጊያ | | 29/07/2007 |
| 2 | አቶ ጌትነት አድማስ | ወ | 48 | አደጋ ውባጅ | ውባጅ | 19/11/2007 |
| 1 | አቶ ጌታሁን ብሩ | ወ | 78 | አግዛ ጋርዳ | ሹምታ | 4/9/06፣7/9/06፣10/7/2007 |
| 2 | ወ/ሮ ጥሩ ጌታሁን | ሴ | 60 | አደጋ ውባጅ | ሰባት አይና | 21/11/2007 |
| 2 | አቶ ጥሩነህ ቢተው | ወ | 66 | አብስላ ዋርዳ | ምትሃ | 19/11/2007 |
| 2 | አቶ ጥበቡ ጉዳይ | ወ | 49 | አደጋ ውባጅ | መስቀለኛ | 29/11/2007 |
| 3 | አቶ ፈንቴ ወርቁ | ወ | 75 | አግዛ ጋርዳ | ሹምታ | 25/11/2007 |
| 2 | አቶ ፈንታሁን በየነ | ወ | 75 | አብስላ ዋርዳ | ቻዌ | 19/11/2007 |

በሰንጠረዡ ውስጥ፡- በተራ ቁጥር 1 የሚገኙት ቁልፍ መረጃ አቀባዮች፣

በተራ ቁጥር 2 የሚገኙት ተተኳሪ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች እና

በተራ ቁጥር 3 የሚገኙት ሌሎች መረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡


# አባሪ ሶስት፡- ልዩ ልዩ ፎቶግራፎች



አቶ ሽመካ ገዳሙ ቃለ መጠይቅ ሲደረግላቸው፣ ጓሽታ 24/6/2007 ፎቶ በዳኜ ይሁን




የተጎለጎለ የጤፍ እርሻ፣ ሹምታ፣ 20/11/2007 ፎቶ በአጥኚዋ



ብላታ ዳኛው ሞገሴ ጋር ቃለ-መጠይቅ ሲደረግ 09/7/2007 ፎቶ በዳኜ ይሁን፡፡



በምልከታ መረጃ ሲሰበሰብ፣24/11/2007 ፎቶ በዳኜ ይሁን፡፡




ለዘር የተዘጋጀ ድንች



አጥኚዋ በመስክ ጥናት ላይ




እርጥብ ቅጠል የተጣለበት የአውድማ ዳስ፣ 4/6/2007፣ ፎቶ በአጥኚዋ



የተደገረ ድንች ቅጠሉን እያቃኑ አፈር ሲያሳቅፉ፣7/9/2006፣ ፎቶ በአጥኚዋ



የጤፍን መሬት ጭቃ በራይ ሲያበራዩ፣



ሊዘራ የቀረበ ድንች፣



የአውድማ ላይ መሳሪያዎች ላፋት መጥረጊያና መንሽ፣ 09/7/2007 ፎቶ በአጥኚዋ

# አባሪ አራት፡- ናሙና ቃለ-መጠይቆች

## ሀ. የቃለ-መጠይቅ መረጃ አቀባዮች ግላዊ መረጃ

1. ስም፡- አቶ አየለ አንተነህ
2. ዕድሜ፡- 83
3. ጾታ፡- ወንድ
4. ሃይማኖት፡- ክርስቲያን (ኦርቶዶክስ)
5. የጋብቻ ሁኔታ፡- ባለትዳር
6. ስራ፡- እርሻ
7. የት/ደረጃ፡- አልተማርሁም
8. ቀበሌ፡- አደጋ ውባጅ ጎጥ፡- ሰባት አይና
9. በአካባቢው የቆይታ ጊዜ፡- በ23 ዓመቴ ነው የመጣሁት
10. የገቢ ምንጭ፡- ግብርና፣ እርሻ
11. የጠያቂው ስም፡- ሰዋገኝ አስራት
12. ቃለ መጠይቁ የተካሄደበት ቀን፡- መጋቢት 27/2007

ወደቦታው የመጡበትን ጊዜ ሲናገሩ (በትዝታ ወደ ኋላ ሄደው እና ትክዝ ብለው) የሚከተለውን አሉኝ፡፡

አሁን ውእእእ... ብዙ ነው ብዙ ነው ይሄ ያለንበት ዱር ነበር እልም ያለ ሰማዩ አይታይም ያን ሸቅብ ነበረ ኧኧኧ... ትልቁ ታቦታችን እዚያ ነው (በእጃቸው በሩቁ ቦታውን እያመለከቱ)ተዚህ ሄደን በዚያን ጊዜ ምን ነበር ጉልት ገዢ የሚባል ነበር ጉልት ገዢን ወክላ ሴት ናት ዘውዴ ትባላለች ያባቷ ስም ተዘነጋኝ እንጂ ተወክላ ነበር፡፡ ክስም ሲሆን ላይ ማሪታ የሚባለው አለ የዚህ ቁራጭ ማሪታ አቦ ኸዚያ ነበር የምንሄድ፡፡ ይህን (ዱር የነበረበትን ቦታ እያመላከቱ) ቀደን ስንሄድ ወፊቱ ስታንኮሻኩሽ እንኳን ሴት ወንዱ ይሰጋል፡፡ጫካ ነው፡፡ ያን ተራራውን እስተምንሄድ መቼም(በቁጭት አንገታቸውን እየነቀነቁ) ከሰው የሚያመልጥ የለም ያሁሉ ካንቻ ተመታ፡፡ዝም ብለን ያን ትልልቁን ትተን ትንሽ ትንሹን ካንቻ መተን መተን

ስንተወው አንዱን ትልቁን መተን የጣልን እንደሆነ አንድ ገዝም ሚሆነውን ይዞት ይወድቃል፡፡ሌላውንም ዠምረን ዠምረን ስናበቃ አንጨርሰውም ፡፡ አንዱን ትልቁን ስንጥል ያንን ሁሉ ይዞት ይወርዳል፡፡ ተዚያ ወዲያ ያነ የወደቀውን በእሳት እንልና እንጨቱን እንደቤት መዝጊያ ጨፉን አሹለን ያን እንደዚህ (በዱላቸው መሬቱን እየወጉ) እየተከልን የተውነው እንደሁ ዘቀዝቆ ነው የሚበቅል ማሽላው፤ ማሽላ ነው የምንተክል፡፡ በጋራ ቁጭ እያልን በዚያ ገጥ አንዱ፤ በዚህ ገጥ አንዱ፣ (በእጃቸው ቦታውን እያመላከቱ) እንዲያ በዚያ ደሞ አንዱ ነው፡፡ ጥበቃውም ዛሬ የኔ ቢሆን ነገ ደግሞ የሱ ነው፤ በወንፊል ነው የምንጠብቀው ጦጣው መከራ ነበር (ራሳቸውን በእጃቸው ይዘው) ማሽላው ጦጣ ቢሰቀል ዘመም አይልም፡፡ ክንድ ሙሉ (እጃቸውን ከክርን እስከ መሃል ጣታቸው ጫፍ ድረስ ያለውን እያሳዩ) ነው ማሽላው አናርሰውም ባመዱ ባቃጠልነው ነው የምንተክለው እርሻ የለም መሬቱ ዝም ብሎ ነበር፡፡አንዲት ፍጠረት ፈጥሬ ነው ወደዚህ የገባሁ ያቺን በቅፍ ይጄ ተዘህ ተዱሩ ገባሁ፡፡

አካባቢያቸሁ ምን አይነት የአየር ንብረት አለው?

አይ እኛ በውልም ባይሆን ወደ ቆላው ነን፡፡

የስንት ዓመት ልጅ ሆነው እርሻ ጀመሩ?

ገና ኮመቻ ነኝ ለናቴ ብርቅ፤ ከብት ጠብቅ፣ በግ ጠብቅ ሲሉኝ እንጃ እንግዲህ አስርም አይሞላኝ፡፡

የእርሻ ሙያን ከማን እና እንዴት ተማሩት?

ከብቶችን በጎችን ስጠብቅ ሂጄ የአንዱን እርፉን ለቀም፣ አቁሞት ያለውን ያንንም ለቀም፤ ተዚያ ደሞ አባባ እስቲ ልረስ ልቀቀውማ! ታለቀቀው ደሞ ልብ አይሆነኝም እንዲያ እያልሁ ሰሂድ በፈሰሱ ስወድቅ ስነሳ እንዲያ ስል ለመድሁኝ፡፡ ኋላ እነሱ ተጥላው ሆነው ቀን እስተቀን ያሣርሱኛል፡፡ዝም ብዬ የማንንም ሳርስ ለመድሁ አሁንም ጌታ የተመኘሁትን ሰጥቶኝ ይኸው እስታሁን ድረስ አርሳለሁ፡፡ጌታ ፈጣሪን አሁንም ወዲያና ወዲህ ሳትል ታፈሩ ውሰደኝ ነው የምለው፡፡

በምን ያርሳሉ? (በበሬ ወይስ በፈረስ) በፈረስ ማረስ መቼ ተጀመረ? ለምን? እንዴት?

በበሬ ነው የማርሰው ልጅ ሆኜም በበሬ ነው የማርሰው፡ያን ጊዜ ብዙ ሀብት ነበረን፡፡ እንዴውም በፈረስ አንድ ዓመት ተዚች ማዶ ገብቼ (በእጃቸው እያመለከቱ) በፈረስ የሚያርሱትን ሄጄ አየሁና ተፌት ተኋላ ያለውን ቀንበሩን ምራኑን ሁሉን አየሁና ጠቤቴ ፈረሶች ነበሩኝ አጎቴ ነው ያባቴ ወንድም ፈረሲቱን ልጠምዳት ነው አልሁት፡፡ መሃን ናት ጠግባ ያለች ናት የዚያን አይቼ አሮጌውን ጀንዲ ቀድጄ በጫንቃ የሚሆነውን ሰፍቼ ገለባ ሞላሁና እንዲያ አድርጌ አንድ ዓመት ነው ሁለት ዓመት አረስሁ፡፡

በፈረስ ማረስ መቼ ነው የተጀመረው?

እንጃ እንግዲህ ብቻ በኃይለ ስላሴ ጊዜ ሁለት ጊዜ ነው ይሆነኝ ታዲስአባ ወደዚህ የሄዱት፣ የዚያን ጊዜ እኔ አርሳለሁ፡፡ ራሴን ችዬ አርሳለሁ፡፡ ያን ጊዜ ጅባይታ ላይ ተቲሊሊ ወዲዚያ አቡጀዲ እየጣሉ ይሄዳሉ ያን ዜ በፈረስ ሲያርስ አይተውት ምንድነው ብለው ቢጠይቁ በሬ የሚገዛበት ብር አጦ ነው ድሃ ሆኖ ሲሏቸው የበሬ መግዣ ብር ሰጥተውት ሂዱ ብለው እኔ አልሄድሁም የሄዱት ማታ ተመልሰው ሲያወሩ ሰማሁ፡፡ ላዩ በፈረስ ያርሳል እኛ ግን በበሬ ነው የምናርሰው፡፡

በዚህ አካባቢ ስንት አይነት ማሳ አለ?

ሁለት ነው ሌላ ምን አለ ብለሽ ነው የጓሮ መሬትና የገጠር መሬት ነው፡፡ እንደድሮው ሞፈር ዘመት አለ ብለሽ ነው፡፡

አዝመራ ከተሰበሰበ በኋላ እርሻ መቼ ትጀምራላችሁ?

እይው እንግዲህ መጋቢትን አንድ ብለን እናርሳለን ዛሬ ሚያዚያ ውኃ ገቡን ድንች፣ ጎመን፣ ማሽላ፣ እንዘራለን፡፡ አሁንም ጥንድ በሬ አለኝ ያን ይዤ አርሳለሁ፡፡

ማሳን ለዘር እንዴት ታዘጋጃላችሁ?

እንግዲህ እንደሚዘራው እህል ነው ብዙ እርሻ የሚል አለ፤ የማይታረስም አለ፡፡ ዳጉሳና ጤፍ ብዙ እርሻ ይላሉ እስተ ሰባትዜ ስምንዜ ይታረሳሉ፡፡ ገብስ ሆነ እንደሁ ሶስትዜ አራትዜ ይታረሳል፣ ስንዴ እስተ ስድስትዜ ይታረሳል፣ ወንድ አተርና ሴት አተር ሶትዜ ይተረሳል፡፡ እንደእህሉ ነው እርሻውም፤ አሁን አሁን ቀረ እንጂ ግብጦ አይታረሰም በትኖ መተው ነው፡፡ የጤፍና የስንዴ መሬት በጥቅምትና በሚያዚያ ላይ አይታረስም፡፡ በዚህ ተታረሰ በፍሬው ዋግ ይበላዋል፡፡ ዋግ ታውቂያለሽ? አላውቅም! አዝመራውን፣ ፍሬውን ስታይው እንዴት ያምራል መሰለሽ ያሳዝናል ውስጡ ግን ፍሬ የለውም ፈሬውን በእጅሽ ስትጫኚው ትንቡሽ ይልና ጥቁር ዱቄት ይወጣዋል፡፡ ዋግ እህሉን እንዲህ ነው የሚያደርገው፡፡ እና ልጄ ሁሉም አንድ አደለም እንግዲህ ያባት አደሩን ይዘን ነው ያለነው፡፡ ጤፍና ዳጉሳ በደንብ ታርሶ ተጎልጉሎ ነው የሚዘራ ጤፍ ጭቃ በራይም አለው ተዚያ ወዲያ ነው የሚዘራው፡፡ ድሮ ያበቅል የነበረውን ጤፍ አሁን ግን መሬቱ እምቢ ብሏል እምብዛም አይደፍርም፡፡

በዓመት ስንት ጊዜ ታመርታላችሁ?

ገብስ ሁለት ጊዜ በግንቦት ዘርተን በነሐሴ እናችድና መልሰን በመስከረም እንዘራለን፡፡ ድንች በመጋቢት የጣልነው ዝናብ ተሰጠ በሰኔ ያን አውጥተን የክረምቱን እንዘራልን ደሞ በንሐሴ እንጥላለን ውኃ ገብ ያለቸው ደግሞ እንዲያ በበጋው ያበቅላሉ፡፡ የው የቺኑ ዝናብ ጠብቀን ነው፡፡

የምርት ወቅቶቹ መቼ መቼ ናቸው?

ያው በግቢ እናርሳለን ክረምቱን ጠብቀን አንድዜ ነው የምናመርተው፡፡ ሰኔን ይዘን ሐምሌን እንዘራለን በጥቅምት በህዳር እናጭዳለን፡፡ በትሳስ በጥር እናስገባለን፡፡ ድንችእና ገብስ ነው ተደጋግሞ የሚዘራው ሌላው የው ይቺን ዝናብ አይንሳን እሷኑ ጠብቀን ነው፡፡ ጤፍ በሰኔ ተጎልጉላ ቡክሮች ሐምሌ ሊገባ ሳምንት ሲቀረው ይጀምራሉ፡፡ አፍል የምናደርገው በሰኔ ተበስሎ ሐምሌ ላይ አፍላ ዘር ነው፡፡ ስንዴ

አሁንም በነሐሴ ውስጥ ተጤፍ በኋላ ይዘራል፡፡ ዳጉሳ ተጤፍ ጋር ነው፤ ድሮ ይበቅል የነበረና አሁን መሬቱ እምቢ ያለው ጤፍ ብዙም አይደፍርም፡፡ አሁን ያመጡልንን ቁንጮ ጤፍ ግን አልፎ አልፎ ተቀብለናል ነባሩ ጤፍ ጠፋ አንድኛውን ዳቦ የምንለው ነበር፣ ነጭ የምንለው ነበር፣ ሰርገኛ የምንለው ነበር ይኼ ሁሉ ጠፋ፡፡ ፌሶ እንኳን እዚህ አልገባም አሁንም በደጋው አለ፡፡

በዚህ አካባቢ የሚበቅለው የእህል አይነት ምን ምን ነው?

ድሮማ ምን እማያበቅለው ነበር አሁን እንኳን መሬቱን ግጠን ጨርሰነዋል፡፡ ጤፍ፣ ወንድ አተር፣ ሴት አተር፤ ሰመሬታና መስኖ ገብስ፣ ስንዴ የድሮው ጠጉር ያለው ነበር ምርቅ ያለው የሚያበቅል አሁን ይሄ መንግስት አስገድዶ ምርቅ የሌለው ስንዴ አመጣልን እሱ ይበቅላል፣ ዳጉሳ፣ ማሽላ፣ ተልባ፣ ሱፍ፣ አጃው፣ ስንዴ መናው፣ ሳልድሚው፣ ጠመዥ ይበቅል ነበር ዛሬ ያለ መስኖና ሰመሬታ የሚበቅል ገብስ የለም፡፡ አጃን እንኳን እኛው ነን የተውነው፡፡ ልፋቱ መከራ የረባ ውጤት የለውም፡፡

ሰመሬታ፣ መስኖ፣ ስንዴ መና፤ ጠመዥ እነዚህ የገብስ ዘሮች ናቸው ሰማቸው ግን ይለያያል ለምነድን ነው? ሰመሬታ ሰመሬታ ነው፤ መስኖ ግን በግንቦት የተዘራው መስኖ በነሐሴ ይታጨድና ይወቃል፣ የመስኖው መሬት ታርሶና ለስልሶ ሰመሬታው ዘር ሆኖ በመስከረም ሰመሬታው መሬት ጋር ይዘራል መስከረም ላይ ዝናብ ታገኝ ጥሩ ይሆናል በመስከረም ስለሚዘራ ነው የክረምት አይደለም፡፡ ስንዴ መና በጣም ነጭ ገብስ ነው እንጀራውም ሴት ተያዘው ሌላ ነው፡፡ ዶቄቱ ነጭ ነው ስንዴን ያስንቃል፤ በዚያ ነው ስንዴ መና ቀረ ተብሎ ነው፡፡ ጤፉ ምንም ጥቁር የሌለበት ጤፍ ነጭ እንለዋለን፣ ምንም ነጭ የሌለውን ፈካ ያለውን ቀይ ጤፍ ደበስ ያለውን ጥቁር ጤፍ (ዳቦ) እንለዋለን፡፡ነጭና ቀይ ድብልቁን ሰርገኛ እንለዋለን፡፡ ሰርግ መሀል የሚገኝ ሰው ሁሉንም አይነት ነው፤ ትልቁ፣ ትንሹ፣ አጭሩ፣ እረጅሙ፣ ጥቁሩ ቀዩ ጠይሙ እንዴው ምን አታከተሽ ሁሉም ይገኛል፡፡ ፈጠኔ ማሽላ በሚያዚያ በግንቦት ተዘርታ በነሐሴ ትደርሳለች፡፡ ጤፍም አለች ቸኮለች የምትባል ቶሎ የምትደርስ አሁን እንኳን ጠፍታለች፡፡ እና እንዲህ ነው ልጄ!

የመሬቱን ለምነት እንዴት ትጠብቁታላችሁ?

ድሮ ምናምን ቀለብ የለውም ነበር፡፡ የመንግስት ቀለብ የለውም በባህላዊው በአባት አደሩ በቃ ደገሌ ደገሌ አስር አስራአምስት ሆነን እጣ ይማታል የእረኛ አባት አለ በሱ መሰረት ሳምንትም ሆነ ሁለት ሰንበት በተራዬ ወስጄ አሁርቼ ነው የምመልሰው፡፡ የድሮው እሁራ ነው በእሁራ ነው የምንጠቀመው ከብቱ እዚያው እርሻው ላይ ነው የሚያድረው፡፡ ተረኛው ሲቀራ ያድራል፡፡ ሲነጋም የሚታለቡ ካሉ ባለቤቶቻቸው ጥጃቸውን እዚያው አምጥተው አራክበው አልበው ጥጆቻቸውን ይዘው ይመለሳሉ፡፡ ከብቶቹም ወደሚሰማሩበት መስክ ይሄዳሉ፡፡

አዝመራን ከእንስሳት፣ ከአእዋፋት፣ ከአይጥና ከተባይ እንዴት ትጠብቁታላችሁ?

ድሮ ዱሩ ሳለ ጡጣው፣ አሳማው ጃርቱ፣ መከራ ነበር በተለይ በፍሬው ጊዜ ወፉ መከራ ነበር እሸቱን ወፊቱ ትጠጣውና ባዶ ነበር እምታስቀረው፣ ወንጭፍ ሰርተን ድንጋይ ይዘን በብር አንጉድ አናባርራለን፡፡ ሸቀ አድርገን እንተወዋልን በዚያ ነበር የምንጠብቀው፡፡

ያን ለፍ የደረሰውን እህል አጭደን በሜዳው ላይ አልፈን አልፈን ዘርግተን አንድ ሁለት ቀን እንተወዋለን፡፡ ያም ያልደረቀ ታለው እንዲደርቅ፣ ፍሬው እንዲጨምት ነው፡፡ ተዚያ ወዲያ በነዶ በነዶ አስረን አምስት አስር ነዶ አስረን አንድ ላይ ቆምጨን እንተወዋለን ያ በደንብ ሲደርቅ ወደሚከመርበት ቦታ አውድማ እምንሰራበት ላይ ወስደን እንከምረዋለን፡፡ ያን መቼም አባሽታልሆነ በስተቀር ተጥምቀት ወዲህ አበራይቶ የሚያስገባ የለም፡፡ ባህሩ ሳይባረክ እና ጥምቀት ሳይውል እህሉ ስለማይበረክት አይበራይም፡፡

እይው እንግዲህ እህል ስናበራይ መጀመሪያ አውድማ የሚሆነው መሬት በደንብ ተፈቅፍቆ ውኃ እየተረበረበ እየተጠረገ ይተመተማል በበት ይለቀለቃል፡፡ ቴፍ የሆነ እንደሁ መጀመሪያ ጥራጥሬ ይበራያል፡፡ በድጋሚ ተለቅልቆ ጤፉ ይበራያል፡፡

እንግዲህ አውድማ ስንጥል በቂ ከብት ተሌለን ተጎረቤት፣ ተወዳጅ ከብት ይለመናል አግዙን ተብሎም ጉልበት ይጠየቃል፡፡ በደሮ ጩኸት ተነስተን ከብቶችን ይዘን ታውድማው እንሽድና አባቶች ሽማግሎች ተመረቁ በኋላ ተሽማግሎች አንዱ ተክምሩ መዞ ማንዘርዘር ይጀምራል፡፡

ተዚወዲያ ክምሩ ብዙ ተሆነ ሁለት፣ ሶስት ሆነው ክምሩን እየናዱ አውድማው ላይ ይነሰንሳሉ፡፡ እንዲያ ደሞ ሁለት ሶስት ሆነው ከብቶቹን ለጉመው በአውድማው ያዞራሉ፡፡ ፈረሶች ታሉ ተፊት ሆኖ ባንድ ገመድ አድረጎ ይስባቸዋል ከብቶች ብቻ ተሆኑ ተኋላ ሆኖ ማዞር ነው፡፡ ክምሩ ብዙ ተሆነ ዶሮ ሲጮህ ተጀመረው እስተረፋዱ ድረስ ተነስንሶ አያለቅም፡፡ እንደ ነግ ተሆነ ደሞ እንዲያ ረፈድፈድ ሲል ያልቃል፡፡ ድሮ መቼም አውድማ ሲጣል ድግሱ ለጉድ ነበር፡፡ አሁን አቅሙ አነሰ ሰውም ፍቅር አጣ (በሃሳብ ወደ ኋላ ተመልሰው ያለፈውን ሁኔታ እያስታወሱ)፡፡ ረፋዱ ላይ ቆሎ፣ ጠላ፣ አብዚው ይመጣል፡፡ ይበላል ይጠጣል፡፡ እኩለ ቀን ሲሆን ከብቶቹ ለውኃ ይለቀቁና ውቻሬው ይሳባል፡፡ ውቻሬው ታውድማው ዳር ይሆናል እንጂ ታውድማው አይወጣም፡፡ ተመልሶ ይገባል፡፡ ተስር ያለው በደንብ ተበርብሮ ተወጣ በኋላ ውቻሬው በትንሽ በትንሹ ይገባና ከብቶቹ በደንብ እንዲረግጡት ይሆናል፡፡

ዘር የሚሆኑ የሰብል አይነቶችንስ እንዴት ትለዩታላችሁ?

ዘር የሚሆነውን ለይተው የሚያስቀምጡት ሴቶች ናቸው፡፡ ያልደለበውን፣ ንጡሁን እነሱ ይለዩታል፡፡

በግብርና ስራው ላይ የሴቶች፣ የልጆችና የሌሎች የቤተሰብዎ ድርሻ ምንድን ነው?

ሴትዮዋ በግብርናው ስራ ያው እኛ ጉልጓሎ ስናበስል ሌት ቀደም ብላ ተነስታ ምሳ ታዘጋጃለች፣ ያው አብራኝ ጉልጓሎ ስለምትውል ያን አዘጋጅታ መከተል ነው ወደ ጉልጓሎ፡፡ ወደ እርሻ ስሄድ ቀደም ብላ ተነስታ ቁርሴን ታበስላለች እኔን ሸኝታ በጓሮ ማሽላ ትኮተኩታለች፣ ቅመሙን ትተክላለች፣ አረሞ ታለ አብረን እናርማለን ኩትኳቶ

ታለም እንኮተኩታለን፣ በዘር ጊዜም ዘሩን አጥርታ አዘጋጅታ ታቀርባለች፤ድነች ሲጣልም ታጣጥላለች፡፡ ሰው ተጠፋ ታጭዳለች፣ ነዶ ታስራለች፣ ነዶ ትሰበስባለች፣ አውድማ ትለቀልቃለች፤ በበራይ ጊዜ እህል ውኃ ተቀርባለች ሲያልቅም አህሉን ሰፍራ አስገብታ ይኸ ለዘር፣ ይኸ ለቀለብ ብላ ታስቀምጣለች፡፡ በእርሻው ጊዜ በሬ ታጣምዳለች፡፡ እርሻ ቦታ የኔንና የበሬዎችን ምሳ ይዛ ትመጣለች፡፡ ልጆቹም ወንዶቹ ወደ አባታቸው ስራ ይከታተላሉ፤ ከብት ይጠብቃሉ፡፡ ሴቶቹ ወደ እናታቸው ስራ ይሄዳሉ፤ ከብት ይጠብቃሉ፤ ያርማሉ ይኮተኩታሉ፡፡

ይህን ከላይ የወረሱትን ዕውቀት ለልጆችዎ በምን መንገድ ያስተምሯቸዋል?

ልጆቼን ባስተምርና እኔ ያላገኘሁትን ዕድል ቢያገኙ ጥሩ ነበር፡፡ አንዱ ቢወጣ ኖሮ ሁሉም እሱን እየተከተሉ ይወጡ ነበር፤ የትምህርት ስራ፣ የዕውቀት ስራ፣ የዕድገት ስራ ነው፡፡ የመጀመሪያው እምቢ ብሎኝ በኔ ሥራ ገባ ተዚያ ወዲያ እኔው እራሴ እንዲህ አድርግ እያልሁሞፈርም አስቀድጂ፣ ቀንበርም አስቀድጂ ቅንጭርትም፣ ሁሉንም ጅፍም አያያዝህ እንዴት ነው፡፡ በጭቃ እንኳ ጎትቶ በሬ ላይ መለጠፍ አላስተማርሁም፡፡ ሽብለል፣ ሽብለል ትክሻ ላይ በጭቃ ወስዶ እያላቆጡ በሬ ላይ ቢገርፉት ተጉሩ ይመለጣል፣ ጅፍ ጠገብ ይሆናል፡፡ እና እንዲህ አድርጌ ነው ያስተማርኳቸው፡፡ አያያዛቸው ያጠግባል ልጆቼ (ይህን ሲናገሩ በኩራት ነው)፤ በሬዎችም በድምጻቸው ይለዩዋቸዋል፡፡

የበሬ ዕቃ ማነው የሚያዘጋጅ?

የበሬን ዕቃ እራሴ ነው የማዘጋጀው፤ ለልጆቼ እንኳን ላገቡት አንዳንድ ዕቃ ላንድ ቀን ነው፡፡ ቢሰበር ቀጥ ነው፤ ሁለት ሁለት ነው አዘጋጅቼ የምሰጠው፡፡ እናቴ አሁን ይሄ ልጅ ሲሄድ በሬዎች ፈረጠሙና እምቢ አሉ አንድ ቀን እርሻ ብጠምድ እንጣጥ አሉና ማን ይቻላቸውጥጋብ ተሰመስቷቸው ሁለት ቀንበር በአንድ ቀን ሰበርሁ ሌላ ተካሁ እንዲችከሰው ደጅ አንጨትም አላነሳ (የግራ እጅ የሌባ ጣታቸውንና የአውራ ጣታቸውን

አንድ ላይ አገናኝተው በንቀት እጃቸውን ወደ ፊት እየዘረጉ)፡፡ እንጂማ ማንም ሰው አይሰራውም ባለሙያዎች አሉ ምፈር ቀንበር አራቂዎች አሉ እንጂ ያም በሳንቲም አደለም ተለምነው ነበር የሚሰሩት አሁን አሁን እንኳ አንጃ (በሀዘኔታ አንገታቸውን እየነቀነቁ) ሁሉም ነገር በሳንቲም ሆኗል፡፡ ጊዜው ተበላሽቷል፡፡

ለእርሻ መሳሪያ (ለሞፈር፣ ለቀንበርና ለእርፍ...) የሚመረጠው እንጨት ምን አይነት ነው?

ዛሬ ያው ያለው ባሕር ዛፍ ነው ዋናው ባህሕር ዛፍ ነው፡፡ ድሮ ግን ተዱሩ ውስጥ ስኒ የሚባላ የዱር እንጨት ነበር ጠንካራ እንጨት ዛሬም በድውሮው ጊዜ ያዘጋጀሁት ቀብር አለ ብጭጭም አላለ ይኸው ስንት አመቱ (ወደኋላ ሄደው ጊዜውን ለማስታወሰ እየሞከሩ) እንጨቱ ስኒ፣ ልምጭ ቅንጭር ልምጭ ነው የሚሆነው፡፡ ወይራም ዋናው ነው፡፡ አሁን ባህዛፍ ስለሆነ ተሱም ተመርጦ ቀጥ ያለው ነው የሚሆነው፡፡ ተዚያ ወዲያ ባለሙያው ያርቀዋል፡፡ ቀንበር የበሬ አንድ የፈረስ ሁለት ነው የሚሆነው ተፊቱ አንድ ተኋላው ደሞ አንድ ቀንበር ሁለት ምራንም አለው፤ እንደዚህ እንዳሁኑ ጋሪ ማለት ነው፡፡

አሁን አዳዲስ የአስተራረስና የአመራረት ዘዴ አለ? ከየት መጣ?

አሁን መንግስት ተድሮው የተለየ ለመሬት ቀለብ አምጥቶልናል፣ ዝም ብለን የምንደፋውን ፍጉን ምኑን በጉርጓድ እናደርገዋለን፣ ማዳበሪያ አምጥቶልናል፤ ምርጥ ዘር አምጥቶልናል፤ አንዳንድ ግዜ ዝምብላችሁ ዝሩ የሚሉት ነገር አለ፡፡ እኛ መቼ እና ምን እንደምንዘራና መቼ እንደምናርስ እናውቀዋለን፡፡ እነሱ ግን እሚሰማቸው የለም እንጂ ሊያስገድዱን ይሞክራሉ፡፡

ከቀየው የአመራረት ዘዴ ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት ምን ይመስላል?

አስተራረሳችን፣ የእርሻ መሳሪያዎች፣ የምንዘራበት ወቅት የተለወጠ ነገር የለውም ያው የድሮው ነው፡፡ አዲሱ ነገር የመንግስቱ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር፣ እርከን ነው፡፡ ሌላ አዲስ ነገር የለም፡፡

ከግብርናው ጋር ተያይዞ የሚባል አባባል፣ ተረት፣ ዘፈን፣ ...ካለ እስኪ ይንገሩኝ

በሬ ማሩ በሬ ማሩ
ንጭለት ከሳሩ ጠጣለት ከባህሩ
በሬ ላንተ ብዬ አያ ላንተ ብዬ
አምቦውን ከልክዬ፡፡
የበሬን ምስጋና ወሰደው ፈረሱ
አይበላ ስጋው አይለበስ ልብሱ
ከኋላ ተነስቶ ከፊት በመድረሱ

"ሐምሌ ችጋሩን ላይረሳኝ በጠላ አጠበኝ አለ" ክረምቱ የችግር ጊዜ በመሆኑ በእህሉ ሁሉ ይዘፈናል፡፡ ሰው እንዲህ ይላል፡-

እንግዲህ ጀመረ ሰኔ አቀለቀለ
በግማሽ እንጀራ ጎመን ተቀለለ፡፡

ጎመን እንዲህ በገብስ ብላ ዘፈነች ፡-

እኔ ባወጣሁት ነፍስ
እሪጥ አለች ገብስ
እፍታራሪ ጎመን ደጃች ሰመሬታ
ማሽላ ደረሰ ባለ ዘጠኝ ኩታ፡፡
ደጃች ሰመሬታ አንጠል አትናገር
አንገቴን ታርጄ ባቆየሁት አገር
እየተባለ ይዘፈናል፡፡

ጦጣዋም እንዲህ አለች እየተባለ እንዲህ ዝምብለው ወለም ዘለም በሚሉት ይዘፈን ነበር፡፡ በኔም ተዘፍኖብኛል፡፡

አ.ያ የገሌን ትክ ብዬ ባ.ያቸው
እኔን ይመስለኛል ፊት አወራርዳቸው፡፡
ያ ሞላ እንዳላማው ወላንሳ ወላንሳ

ጠግቤ እነሳለሁ እግሩን እስቲያነሳ፡፡ ይባል ነበር ዘሬ እንኳን ጦጣው ዱሩም እራሱ የለም፡፡

ሰነፉን ለመወቀስ ደሞ
አ.ያ በሬ ብለው ዘርተው ካላረሱ
ይሸታል ጨገዳው ስብ እንደጠበሱ፡፡

ውድ ጊዜያችሁን መስዋዕት አድርጋችሁ ይህን መረጃ ስለጣችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ!

## ሀ. የቃለ-መጠይቅ መረጃ አቀባዮች ግላዊ መረጃ

1. ስም፡- ቄስ አወቀ ተፈራ
2. ዕድሜ፡- 83
3. ጾታ፡- ወንድ
4. ሃይማኖት ክርስቲያን (ኦርቶዶክስ)
5. የጋብቻ ሁኔታ
6. ስራ፡- እርሻ
7. የት/ደረጃ፡- ቅስና
8. ቀበሌ፡- አብስላ ዋርዳ ሳሙኤል
9. ጎጥ፡- ባኪ
10. በአካባቢው የቆይታ ጊዜ 83 ዓመት
11. የገቢ ምንጭ፡- ግብርና/ እርሻ
12. የቃለ መጠይቅ ቦታ፡- አብስላ ሳሙኤል
13. የጠያቂው ስም፡- ሰዋገኝ አስራት
14. ቃለ መጠይቁ የተካሄደበት ቀን መጋቢት 3/2007

## ለ. ቃለ-መጠይቆች

አካባቢያችሁ ምን አይነት የአየር ንብረት አለው?

የአየር ንብረቱ ጥሩ ነው እምብዛም ሙቀት የለ፣ እምብዛም ቅዝቃዜ የለ መካከለኛ ነው::

የስንት ዓመት ልጅ ሆነው እርሻ ጀመሩ?

በ25 ዓመቴ ነው የጀመርሁት፤ የቤተ ክህነት ትምህርት እየተማርሁ ነው የዘገየሁት፡፡

የእርሻ ሙያን ከማን እና እንዴት ተማሩት?

እርሻውን ታባቴ! እርሱ የሚያድርገውን እያየሁ፣ አብሬ እያጣመድሁ ለመድሁ፡፡ የእርሻን ስራ ስጀምረው ወትሮ ያው ባህል ነውና እናት አባት ሲያሳየን እዩ ይኸን

እያሉ ሲጠመድም እንደዚህ ነው፣ ድግሩ እንደዚህ ነው፣ ሞፈሩም እንደዚህ ነው፣ መርገጫውም እንደዚህ ነው፣ ሞፈር ቀንበሩም እንደዚህ ነው፤ ቅንጭርቱም እንደዚህ ነው፣ ጅራፉም እንዲህ ነው የሚያዘው እያሉ ያሳዩናል ያን ተምረን እንፈጽማለን፡፡ የበሬ አጠማመድ ቅደም ተከተል አለው፡፡ በመጀመሪያ ሞፈር እንረግጣለን፣ ከዚያ በኋላ ሞፈር ቀንበሩን ተሸክመን እንሄዳለን ከዚያ ከማሳው ላይ እናስቀምጥና መጀመሪያ ያንን የተረገጠው እቃ ይቀመጣል፡፡

ከቤት ረግጣችሁት ነው ወደ እርሻ የምትሄዱት?

አዎ ምሳቸውን ገለባ አስቲበሉ ድረስ ቁርሴን ቀማምሼ እሱን እረግጣለሁ፡፡

ምን ምኑ ነው አንድ ላይ የሚረገጠው የእርሻ መሳሪያ?

የሚረገጠው? (... ሳቅ) አዎ!

የሚረገጠውማ ድግር እርፍ ይባላል ማረሻው ያን በውስጥ እናስገባና ደሞ አለ ወገል ብረት ነው እሱን ከድግሩ ጋር እናዋድድና መርገጫውን አድርገን ነው፡፡ ሞፈር ቀንበሩን እናስቀምጥና በቀንበሩ በሬዎችን እንጠምዳለን፡፡ ታለሁኝ አባቴ ቀንበሩን ይይዛል እኔ በሬዎችን እወስድለታለሁ፡፡ በዚያ በኩል (አቅጣጫውን በእጃቸው እያመላከቱ) እሱ በዚህ በኩል እኔ ሆነን ማነቂያውን ይዘን እናስራለን፡፡ በበሬው አንገት የሚያልፈው ቅንጭርት ማነቂያ ይባላል፡፡ ገመዷም ገመድ ናት አንዳንዴም ጠፍር ይደረጋል፤ የማነቂያ ገመድ ትባላለች፡፡ ተዚያ ይታነቅና ተዚያ በኋላ ሞፈሩን በምራኑ ውስጥ እናስገባና እንጨት አለች የምትገባ ሞፈር አፍንጫ አለች በዚያ እናስገባና እንደዚያ እናደርግና ተዚያ ወዲያ ጅራፋችንን አንስተን ተጓዝ ነው፡፡ ሀድ በል ማለት ነው፡፡ ቅንጭርቷ ልምጭ እንጨት ነው የምትበጀው፣ ምራኑ ተቆዳ ነው ቆዳ የሚሰሩት ፋቂዎች ናቸው የሚሰሩት፡፡ በጣም ጠንካራ እንዲሆንም ይፈተላል /ይገነገናል፡፡

ይህን ዕውቀት ለልጆችዎ እንዴት ያስተምሯቸዋል?

የተማሩት ተማሩ በኋላ ደሞ ያርሳሉ፡፡ እኔ እንዲህ ነው፡፡ አስተምሪያቸዋለሁ፤ ተትምርት ሲመለሱ ያርሳሉ፡፡ እንዲህ አድርጉ እያልሁ እየተከተልሁ ማረሻ ሲዘልቅ ብድግ እያደረግሁ እያሳየኋቸው ነው፡፡ የትምርት ሰዓቱ እስቲደርስ ያርሳሉ ሰዓቱ ሲደረስ ወደ ትምህርት ቤታቸው ይኸዳሉ፡፡ ባጨዳውም ማጭዱን እንዲህ ያዙ እህሉን ደሞ እንዲህ አድርጋጅችሁ በዚህ እጃችሁ ያዙ እያልሁ አሳያቸዋለሁ፡፡

በምን ታርሳላችሁ (በበሬ ወይስ በፈረስ)?

እዚህ እኛ አካባቢ በሁለቱም ነው፡፡ በበሬ ብቻ እሚያርስ አለ በበሬና በፈረስ የሚያረስ አለ፡፡ ሁሉም እንዳቅሙ ነው፡፡

በፈረስ ማረስ መቼ ተጀመረ?

እንጃ መቼም በንጉሱ ጊዜ ነው፡፡ በዚያ በደጋው የከብት በሽታ ገብቶ ነበር ተዚ ወዲህ ነው በፈስ ማረስ የተጀመረው፡፡

ለምንና እንዴት ነው በፈረስ ማረስ የተጀመረው?

ያው እንደነገርሁሽ በከብት በሽታ ምክንያት ነው፡፡ "ችግር ብልሃትን ትወልዳለች" ይባላል፡፡

በዚህ አካባቢ ስንት አይነት ማሳ አለ?

በዚህ በኛ ምን አለ ብለሽ ነው፡፡ የጓሮ መሬትና የገጠር መሬት ነው፡፡ ድሮ ባባቶቻችን ጊዜ ሞፈር ዘመት የሚባልም ነበር፡፡ በሬ ጠምድን ሽደን አድረን ስናርስ ውለን እንመለሳለን፡፡ አሁን ያ ሁሉ የለም እና ይኸው ነው ያለው፡፡

አዝመራ ከተሰበሰበ በኋላ እርሻ መቼ ትጀምራላችሁ?

ያው መጋቢት አንድ ሲል እርሻ ይጀመራል፡፡ በጥቅምት የተሰነጠቀው መሬት በመጋቢት አንድ ሲል ጀምሮ በደንብ ይታረሳል፡፡

ማሳን ለዘር እንዴት ታዘጋጃላችሁ?

ማሳን ለዘር ለማዘጋጀት እንደሚዘራው የእህል አይነት ይለያያል፡፡የጤፍ ሰባት ስምንት ጊዜ ይታረሳል ተዚያ ይጎለጎላል፤ ሲጎለጎል ፈሰስ እየተቀደደ ይተዋል ተዚያ ጎልጓዮቹ ጉሎውንና ሳሩን እያነሱ በፈሰሱ ውስጥ ስሩን ወደላይ አድርገው ያስቀምጣሉ፡፡ በተጎለጎለ በዘጠኝ ቀኑ ወገዝ እየተነዳ ጭቃ በራይ ይበራይል በደንብ እስቲደቅና መደብ እስቲመስል ይበራያል፡፡ ተዚያ ወዲያ ይዘራል፡፡ ዳጉሳም እንደዚያው ነው፡፡ ስንዴም እስተ ሰባት ስምንት ጊዜ ይታረሳል፡፡ ገብስ አራትዜ ይታረሳል፡፡ ሴት አተርና ወንድ አተር ሶስት ጊዜ ይታረሳል፡፡

በዓመት ስንት ጊዜ ታመርታላችሁ?

አንድ ጊዜ ነው፡፡ በዝናብ ብቻ ነው፡፡ ውኃ ያለበት አካባቢ በውኃ ገብ ያመርታሉ፡፡

የምርት ወቅቶቹ መቼ መቼ ናቸው?

ክረምቱ ብቻ ነው፡፡ አንድዜ ባመት እናመርታለን፡፡

በዚህ አካባቢ የሚበቅለው የእህል አይነት ምን ምን ነው? ሲያሜውን እንዴት አገኘ?

ጤፍ፣ ገብስ (ሰመሬታና መስኖ)፣ ሴትና ወንድ አተር፣ ማሽላ፣ ድንች፣ ግብጦ፣... ይበቅላል፡፡

አዝመራን ከእንስሳት፣ ከአእዋፋት፣ ከአይጥና ከተባይ እንዴት ትጠብቁታላችሁ?

ዣርት፣ወፍ እንዳይበላው እንትን የሚባል አለ ብር አንጉድ በገመድ እየፈተልን አጭንብላ ሰርተን በዚያ አርገን ድንጋይ አለ ይዘን ታልጋው ሆነን ስንወረውረው ዥውውው.. እያለ እየተምዘገዘገ ሲሄድ የዛፉን ቅጠል ያነቃንቀዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉም ትተው ይሄዳሉ፡፡ እንዲህ እያደረግን የእየተጋገዝን ስንጠብቅ እንውላለን፡፡ ሁለተኛም ደግሞ አዝመራን አሳማ እንዳይበላ መከላከል ነው፡፡ ሌሊት ደግሞ ዣርት የምትባል

አለች እሷ እንዳትበላ ደግሞ የሆነ ሽቶ የሚባል አለ እንጨት እንተክልና እሱን አስረን ስንተወው ንፋስ ሲነካው ኳኳ.. ስለሚል ሰው መጣ ብላ ትታ ትሄዳለች፡፡ ተዘራውን ወፎች እንዳይበሉት አፈር እናለብሰዋለን፡፡ አምሳያም እንሰራለን፡፡ እንጨት ተክለን ቡትቶው አልብሰን ሰው አስመስለን አልፈን አልፈን እናደርገዋለን፡፡ ያን ስታይ ወፏ ሰው ስለሚመስላት ወደ እርሻው አትመጣም፡፡ አይጧን ደሞ ስንከላከለው ያን ጉድጓድ እናይና ሁሉን ደፍነን ስናበቃ አንዱን እንተወውና የድንጋይ ወጥመድ አዘጋጅተን ተወጡ በኋላ በወጥመዱ እንደፍነዋለን፡፡ ተዚያ ዲያ መግቢያ በመሳጥ እንጨፈጭፋታለን፡፡ ሌላው ደግሞ በየጉድጓዱ አፍ ላይ ቁልቋል እናደርጋለን ያን ይበላና እዚያው ይሞታል፡፡

ዘር የሚሆኑ የሰብል አይነቶችንስ እንዴት ትለዩታላችሁ?

ለዘር የሚሆነውን እህል መርጠው አጥርተው የሚያዘጋጁት ሴቶች ናቸው፡፡ እኛ አምርተን ማስገባት ነው፡፡ ይኸ ለዘር፣ ይኸ ለቀለብ፣ ይኸ ለወር ጨው፣ ለሽመታ ብላ እምታስቀምጥ እሷ ናት፡፡

በግብርና ስራው ላይ የሴቶች፣ የልጆችና የሌሎች የቤተሰብዎ ድርሻ ምንድን ነው?

ባለቤቴ አንደኛ ጉልጓሎ ነው፤ ጉልጓሎ ማለት የጤፍ ማሳ ጤፍ ሲዘራ ሲታረስ ጉሎ ጉሎ የሆነ ነገር አለ አደል ያን እንዲለሰልስ እያነሳች ሽና ይሰጣታል በሽና በሽናው ታስቀምጣለች፤ ሲቀመጥ ስሩ ወደላይ እየሆነ እየተደፋ ይቀመጣል፣ አረሞ ታርማለች ፣ ድንቹን፣ ማሽላውን ትኮተኩታለች፡፡ በአጨዳው ጊዜ ሰው ተጠፋ ታጭዳለች፣ ነዶ ታስራለች፤ አውድማ ለቅልቃ ታዘጋጃለች፤ ተተጋኑ ቅመሟን ትዘራለች ትንከባከባለች፣ ምሳ አብስላ ታዘጋጃለች፡፡ ዘር አበጥራ ታቀርባለች፣ በሬ ጠምዳ አትረስ እንጂ ታጣምዳለች ጠምዶ ማረሱ ብቻ ነው እንጂ ተቤት እስተዳሬ ድረስ የሚቀራት ስራ የለም፡፡ልጆችም ከብት ይጠብቃሉ፣ አረሞ ያርማሉ፣ ይጎለጉላሉ፤ ሴቶች ልጆች ደግሞ እናታቸውን በቤት ስራ ያግዛሉ፡፡

የማይሳተፉበትስ የስራ አይነት አለ?

አዎ! በአባት አደሩ! በባህሉ! ሴት እርሻ አታርስም፣ ተበራይቶ እስቲያልቅ አውድማ ውስጥ አትገባም፡፡ ለምን ? አውድማ ንጡህ መሆንን ይፈልጋል ተጥላ አይታደርም፣ ተብዙ ነገር መጠበቅ አለበት፡፡

አሁን አዳዲስ የአስተራረስና የአመራረት ዘዴ አለ?

ድሮ በነበረውና አሁን ባለው የተለወጠ ነገር አለ፡፡ እኛ የዛን ጊዜ እንጠቀም የነበረው እንደነገርሁሽ በዚያ በሁራ በኮምፖስት በምናምን ነው ዛሬ ግን እንትን .... ማዳበሪያ ስለመጣ በማደበሪያ ነው የምንዘራው፡፡ ግን ቶሎ ይጋሽብና ይተኛል፡፡ ፍሬውም ይረግፋል ግንዱ ጠንካራ አይደለም፡፡ ጉልበት ያንሰዋል፡፡ መሬቱ እየደረቀ ስለሄደ ታለ ማዳበሪያ እሽ አይልም፡፡ ኮምፖስቱን ቀድመን እናደርግና ስንዘራው ደግሞ መንግስቱን ማዳበሪያ እንጨምራለን፡፡ አሁን መሬታችንን ትንሽ ቢወስደውም እርከኑ ጥሩ ነው፡፡ መሬቱን ተመበላት አድኖታል፡፡ በመስመር ዝሩ ይላሉ፡፡ ግን ሁሉም አልተቀበለውም፡፡ ጊዜ ይፈጃል ብዙ ሰው ይላል፡፡ ሳያልቅም ዝናብ ሊያቋርጠው ይችላል፡፡ እሱ ጥሩ አደለም፡፡ አንዳንድዜ መንግስት ሊያስገድደን ይሞክራል፡፡ ለመሬቱ የማይሆነውን ዝሩ ይለናል፡፡ ያም ሳይበቅል ይቀራል፡፡ ምርጥ ዘርም ይሠጡናል ግን በሽታን የሚቋቋም ማምጣት አልቻሉም፡፡

ድሮ ጥሩ ምርት ለማምረት እሁራ ነበር የምንጠቀመው፡፡ ቅራት እየተቀራ በክረምት እርሻ ላይ ከብቶች ያድራሉ፡፡ ይህም ወዲያው ወዲያው ይታረሳል የከብቶች እበታቸውም ሆነ ሽንታቸው በጣም እሁራ ይሆናል፡፡በዚያ አርሰን ስንዘራው እንደ ዛሬ ማዳበሪያ ያለ ከፍ ያለ ምርት ይሰጠናል፡፡ ሌላው ዘዴ ፋንድያው የፈረሱ ማሳው ላይ ይደረጋል፡፡ በተጋኑ መሬት ድንች የሚዘራ ተሆነ የፈረስ ፋንድያ፣ የበጎች ኮረኮር የደረግበታል፡፡ ሌላ የሚዘራ ተሆነ ደግሞ የከብቶች እበት፣ አዛባ ይደረጋል፡፡ ደንቹን ትል እንዳይበላው ለማድረግ ነው፡፡ ሌላው ዘዴ እሁራ እናሆራና ለከብቶች ግጦሽ እናደርገዋለን፡፡ መሬተ ታለ እንዲሁ እንተወዋለን፡፡ ተሌለ ደግሞ እናርሰዋለን ተሽይ ምርት እናገኝ ነበር፡፡

ከቆየው የአመራረት ዘዴ ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት ምን ይመስላል? አስተራረሱ ያው ያባት አደሩ ነው ሌላ የተለየ የለውም፡፡ የምንዘራበት የምናርስበት ያው ነው፡፡ አሁን አሁን በጥቅምትና በሚያዚያ የማናርሰውን የጤፍና የስንዴ መሬትም እረሱ ይሉናል፡፡ ማን ይሰማቸዋል፡፡ በዚህ ተታረሰ ዋግ በፍሬው ይበላዋል፡፡ እነሱ ትናንት ተወልደው የኖረውን ተውት ይሉናል፡፡ እስታሁን የኖርነው ይህን አክብረን ባህላችንን ጠብቀን ነው፡፡ ይህንን ተው ነው የሚሉት፡፡

ከግብርናው ጋር ተያይዞ የሚባል አባባል፣ ተረት፣ ዘፈን፣ …ካለ እስኪ ይንገሩኝ አሁን አረጀሁና ሊረሳኝ ነው መሰል እእእእ…..

ሆ በሬ ሆ በሬ
ክፉ አይናገሬ
አያንገራግሬ፡፡

ምነው በቅዳሜ ምነው በእሁድ ቢያርሱ
አበዳሪው ሲገኝ ይቸግራለ ዋሱ፡፡

ሲነግዱ አትነግድ ሲያርሱ አትረስና
አሟረቱብኝ በል ተጥላው ዋልና፡፡

ያረሰማ ጎበዝ እርፍ የነቀነቀ
እንደተደሰተ መስከረም ዘለቀ፡፡

በርዬ እሹሩሩ በርዬ እሹሩሩ
ጠጣልኝ ከውኃው ብላልኝ ከሳሩ
ባንተ ጫንቃ አይደለም ወይ የቀናው ሀገሩ፡፡

በሬ ያላንተማ ክንዴ ያላንተማ

አይኔም አያይልኝ ጆሮዬም አይሰማ፡፡

ብዙዎች ነበሩ ተዘነጋኝ፡፡

ውድ ጊዜያችሁን መስዋዕት አድርጋችሁ ይህን መረጃ ስለጣችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ!